

t.me/OLDBOOKSPDF

# ብ ቀ ላ

## የማሪኮሪሊ ቬንዴታ

ታደለ ገብረ ሕይወት
እንደ ተረጐመው

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

Kuraz Publishing Agency
1983

t.me/OLDBOOKSPDF

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ፖስታ ሣ. ቁ.
30933
P. O. Box

አዲስ አበባ
Addis Ababa

የውጭ ሽፋን ጥበበ ተርፋ

የመጀመሪያ እግርኛ እትም 1975 (ሚያዝያ)
የሁለተኛ እግርኛ እትም 1975 (ሐምሌ)
ሦስተኛ እግርኛ እትም 1976 (ጥቅምት)

ለንግድ ማተሚያ ቤት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አንድ

ይህን ታሪክ የምጽፍ ሰው የሞትኩና የተረሳሁ ነኝ ። የሞትኩ በውልና በምስክር በሕግና በተረጋገጠ ማስረጃ የተቀበርኩ ነኝ ። ስሜን ጠርታችሁ ማንኛውንም የትውልድ ሀገሬን ሰው ብትጠይቁ በ1884 በኔፕልስ ተነስቶ በነበረው የኮሌራ በሽታ ከተቀሰፉት ሰዎች አንዱ ነው ፣ አስከሬኑም በአባቶቹ መቃብር ቤት በመበስበስ ላይ ነው ይሉዋችኋል ። እኔ ግን አሁን በሕይወት እገኛለሁ ። የሰላሳ ዓመት ዕድሜዬ ሕይወት አፋፊ ደሜ በደም ስሮቼ ሲቅበዘበዝ ይሰማኛል ። ዓይኖቼ ሰርጸው ያያሉ ፣ እጆቼ ምጭጨው ይይዛሉ ፣ ብብቶቼ የጎረምሳ ጡረን ያመነጫሉ ፣ የሸገገ ቁመናዬ የመኸር ዘመን እፍላ እድሜውን ገና ወጥቶ አልታከተም ። አዎን!......ሞቷል ተብዬ ቢወራብኝም እኔ ገና በሕይወት እገኛለሁ ። ይህም ብቻ አይደለሁም ። በአባወራነት እድሜዬ ማግስት ትካዜዬ የጠበሰው ከፉ ምልክትም ይገሃለሁ ። ጥቁር ሀር ይመስል የነበረ ፀጉሬ ዛሬ እሜ በረዶ መስሎ ነጥቷል ። ብዛቱና ዘንፋላነቱ ግን ያው ነው ።

ሀኪሞች በፀጉሬ ንጣት የተከራከሩት ትዝ ይለኛል ። በረዶ የመሰለ ፀጉሬን ምስት ሆነው እያዩ እያንዳዱ በየተራ ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

"ከዘር፡ ሐረግ ተያይዞ የተወረሰ ሽበት ነው ?"
አለ ፤

ሌላው "ከድንገተኛ ከባድ ድንጋጤ የመጣ ነው።"

"አንድ የሆነ ንዳድ አቃጥሎት ነው ።"

ምስቱም ላደረጉት መላ ምት እኔ አንድም መልስ አልነበ ረኝም ። ካለአንዱ በስተቀር ለአንድም ሰው የሕይወቴን ታሪክ አላዋየሁም ። በሕክምና ሙያውና በደግነቱ የታ ወቀ አንድ ደግኛ ሰው አንድ ጊዜ ታሪኬን ድንገት አጫወትኩትና ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በመደነቅና በጥሞና አድምጦ ሲጨርስ «በታሪክህ ውስጥ የእብደት ምልክቶች ይታዩኛል» አለኝ ። ከዚያ ወዲያ ታሪኬን ለማ ንም ሰው ተናግሬ አላውቅም ።

አሁን ግን ተደብቆ የኖረውን ታሪኬን በእውነትና ያለናርሀት ጽፌ ለሕዝብ ማሳወቅ አለብኝ ብዬ ቆርጫ ለሁ ። ድንግል የተፈጥሮ ዛፍና ቅጠል ፣ ከሰው ልጆች ሥልጣኔ የራቀ የተፈጥሮ ልምላሜ ፣ የእአዋፍ ዝማሬና ፣ የዱር አራዊት ድምጽ ከቦኛል ። እዚህ በደቡብ አሜሪካ ጫካ ከንፋስ ሹክሹክታ በስተቀር ከእረፍቴ የሚቀሰቅ ሰኝ የለም ። ስለዚህ በዚህ የፀጥታ እፍታ ታሪኬን ለዓለም ማሰማት አለብኝ ። በእንዲህ ያለ ሰላማዊ አጋጣሚ ምሬት ያስጨነቀውን ልቤን ከፍቼ ከጭንቀቴ መገላገል አለ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብኝ ። ዓለም ታሪኬን ማወቅ አለበት ።

ሞቷል ግን አሁንም ይኖራል! ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ትሉኝ ይሆናል ። ስሙኝ ወዳጆቼ! ሙታን ዘመዶቻችሁ በእርግጥ የሞቱና የማይነሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እስከሬናቸውን አቃጥላችሁ ማጥፋት አለባችሁ ። ያለዚያ ግን ምን እንደሚፈጠር ማወቅ አይቻልም ። ሞተ የተባለው ሰው ሕይወት ዘርቶ ትንፋሽ አበጅቶ በነፍስ አውጪኝ ጉልበቱ ሳጥኑን በረቃቅሶ ቢወጣስ? ሞቷል ብለን አልቅሰን የቀበርነው እንደአላዛር የመቃብር ቤት ከፍቶ ብቅ ቢልስ? ሞቷል ብለን አልቅሰን የሀዘን ልማድ የሚጠይቀውን ሁሉ ፈጽመን የቀበርነው ሙት ታማኝ ወዳጅነታችንን ለመፈተን የመቃብር ቤት ሰብሮ ቢመጣስ? በተለይ ሀብቱን የምንወርስ ዘመዶቹ ሰውየውን ሳይሆን የምንወደው ሀብቱን ስለሆነ ከሙታን የተነሳውን ወገናችንን ብናምን እንኳን እንቀበለውም ። እንዲህ ያሉ ያለጊዜያቸው መቃብር ቤት ገብተው የሚመለሱ ለምስኪንነታቸው ምን ዓይነት ሀዘኔታ ይገባቸው እንደሁ እግዜር ይወቅ!

ወደራሴ ታሪክ ልመለስ ፣ እኔ ፋቢዩ ሮማኒ በቅርቡ ሞተ የተባል!ሁ ስለአንድዋ ዓመት የሕይወት ጣብዬ ላስፍር ። በቁጥር አንዲት ዓመት ነገር ግን በሕይወት ዘመን የሚያጋጥመውን መከራ ሁሉ አምቃ ፣ በመርፌዋ ሕሊናዬን ወግታ ፣ ልቤን በሾተልዋ ሰንጥቃ ፣ ደሙ የማይነጥፍ ፣ የቁስሉ ስፋት የማይገጥም መከራ ስለሰጠችኝ ጅራፋም



t.me/OLDBOOKSPDF

ዓመት ላውጋ ። ከባለፀጋ ቤት ስለተወለድኩ ድህነትን አላውቅም ። አባቴ ጌታ ፊሊጶ ሮማኒ ያለ ሀብቱን በሙሉ አውርሶኝ ሲሞት የአሥራ ሰባት ዓመት ልጅ ነበርሁ ። ሳላስበው በድንገት የዚያ ሁሉ ሀብት አዛዥ ናዛዥ ሆንኩ ። ብዙ ዓይነት ጓደኞች ነበሩኝ ። መጪ ሕይወቴን የሚገ ብዩም ነበሩኝ ። እንደነሱ አባባል የኔ ሕይወት መጨረሻው የማያምር ፣ ቁማርተኛ ፣ አባካኝ ፣ ሰካራምና የመጥፎ ጠባይ መጠራቀሚያ መሆን ነበር ። የሚያስገርመው ግን ተቃራ ኒውን ጠባይ ይዤ ወጣሁ ። ቁማርተኝነት የሚያስከት ለውን የቁምቅዠት ጅልነት ፣ መጠጥ የሚያስከትለውን የጤንነትና የእምነት ጠንቅነት እየተገነዘብኩ ሄድኩ ። ቁማርና መጠጥ በደህንነት ላይ የሚያንዣብቡ ወጥመዶች ናቸው የምል ሆንኩ ። ስለዚህ ለራሴ የሚጠቅመኝን የሕይወት መስመር መረጥኩ ። ንፉግ ወይም አባካኝ ሳልሆን የመሀሉን መስመር ይዤ ተጓዝሁ ። አእምሮን ወይም አካልን ከሚያደክም ነገር ሁሉ ተቆጥቤ የሰላም ሕይወት መምራት ጀመርኩ ።

በነጭ እብነበረድ ከተሠራው የአባቴ ቪላ የኔፕልስን ወደብ ወደታች እያየሁ የደስታ ጊዜዬን በብርቱካን ዛፎች ጥላ ስር እያሳለፍኩ አበባ አይቼና አሽትቼ ፣ በአእዋፍ ዝማሬ ረክቼ መኖር ጀመርኩ ። እርጋታ እንጂ ውካታ በሌ ለበት የአባቴ ግቢ ጠቢባን ተጨንቀው ከቀረጹት የምንጭ መፍለቂያ እየዘለለ በሚንሻሻው ፏፏቴ የበጋውን ንዳድ እያቀዘቀዘልኝ ፣ በተድላ ደስታ ለጥቂት ዓመታት ያለሀሳብ ኖርኩ ። በመጻሕፍትና ባማሩ ሥዕሎች ተከብቤ ፍላጎታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቻው ከሞላ ጎደል ከፍላጐቴ ጋር በሚጣጣም ጓደኞቼ እየተጎበኘሁ እቻ በሆኑ የማድነት ችሎታ ታዋቂ የጽሑፍ ሥራዎችን ወይም የኖረ ወይንጠጅ ጣዕም እያወጣደርን ደስ ብሎኝ ለመኖር ታደልኩ ።

ሴቶችን አልቀርብም ነበር ። እውነቱን ለመናገር ሆን ብዬ እርቃቸው ነበር ። ቢያጋጥሙኝና ብቀርብም እንዳጋጣሚ አልፎ አልፎ ነው ። ሲጋብቻ የደረሱ ሴቶች ልጆች ያሉዋቸው ወላጆች በየጊዜው ሲጋብዙኝ የተለያየ ምክንያት እየፈጠርኩ ከግብዣቸው እቀር ነበር ። በጣም የማያምንባቸው መጽሐፎቼ ከሴቶች እንድርቅ መከረውኛልና ። ከሴት ፍቅር ይልቅ በእውነተኛ ጓደኝነት እምነት ስለነበረኝ ጥሩ ጓደኛም አፈራሁ ። መጽሐፎቼ እንደመከሩኝ እርባ ክንድ ከሴት ራቅሁ ። ይህ ዝንባሌዬ እንደድኩም እየተቆጠረብኝ በጓደኞቼ ዘንድ መዘበቻ አደረገኝ ። ቢሳለቁብኝም ስሜቴን አላስፋጡትም ። በጓደኝነት ስለማምን በዚያን ጊዜ ጓደኝነት ከሕይወት ጋ በላይ የሚከብድብኝ የማምነውና የሚያምነኝ የሕይወት መስዋእትነት እንኳ ቢያስፈልግ ለመሰዋት የማላመነታለት ጉዶ ፈራሪ የሚባል ጓደኛ ነበረኝ ። ታዲያ ጉዶ ፈራሪም ለሴቶች ግዴለሽነቴን እያነሳ እንደሌሎቹ ሁሉ ይቀልድብኛል ። ሌሎች የሚሉኝን ሁሉ ይለኛል ።

«ከሴት ልጅ መንታ ከንፈር ወለላ ማር መጠህ እስክ ልቀመስክ ድረስ ሕይወትን ቀመስኩ ማለት አይቻልም ። የከዋክብትን ሚስጢር መገንዘብ የሚቻለው የጥልቅነቱ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስጢር፡ ወሰን የሌለውን የቤትን ልጅ የውስጥ ዓይነ
ትክ ብለው ሲመለከቱት ብቻ ነው ። በጉጉት የተዘረጉ
ክንዶችን በቤት ልጅ ቀጭን ወገብ ላይ ሳይጠመጠሙ
በፍላጎት የሚንዘረውን ልብ ከራስ ልብ ንዝረት ጋር ሳያ
ዳምጡ ሕይወትን ኖርኩ ማለት አይቻልም ። እነኝህ የመ
ጥን ያልካቸውን የጥንት መጻሕፍት የጻፉ ደስታ አልባ
ፈላስፎች በውስጣቸው የወንድነት መንፈስ አልነበራቸ
ውም ። ደማቸው ደም ሳይሆን ውሀ ነበር ። በሴቶችም
ላይ ያጕረፉት ውርጅብኝ የሚያንጸባርቀው ድክመታቸ
ውንና በሕይወት ላይ ያላቸውን ቅሬታ ነው ። የሕይወት
ዋናው ገጸበረከት ሳይደርሳቸው የሚያመልጣቸው ሁሉ
ሌሎችም እንዳይደርሳቸው ተሟጋች ሆነው ይቀራሉ ።
አንተ ግን ጎረምሳ ነህ! አፍላ ፍላጎትህ ያልረካ ፣ ዓይንህ
ከሩቅ የሚጠቅስ ፣ ልብህ ለቤት የሚደነግጥ ፣ የጥርስህ
ፈገግታ ሴቶችን የሚያስደነግጥ መልከ መልካም ጎበዝ
ነህ ፣ እንዲህ ያለ ቁመና ይዘህ የፍቅርን አረቄ የማትቀም
ስበት ምክንያት አይታየኝም።»

ጓደኛዬ ይህን ሲነግረኝ ያስቀኝ እንጂ ክርክሩ ሲያባ
ምንኝ ስላልቻለ ምንም መልስ አልሰጠሁትም ። አነጋገሩ
ግን ደስ ይላል ። ድምጹ ለዘብ ያለ ሲሆን ዓይኖቹ ግን
ከንግግር የበለጠ የመግለጽ ችሎታ አላቸው ። ፈጣሪ በሚ
ያውቀው ይህን ሰው ከአንጀቴ ፣ ከምቀኝነት ሁሉ በጠራ
ወንድምነት እወደዋለሁ ።

ብዙውን ጊዜያችንን አንድ ላይ እናሳልፍ ነበር።እርሱም
እንደኔው በልጅነት ወላጆቹን በሞት ስለተነጠቀ የወደፊት



t.me/OLDBOOKSPDF

ሕይወቷን ለራሱ በሚጥመው ዓይነት የመቀየስ ግዴታ ነበረበት ። የስዕልን ጥበብ እንደሙያ ዘርፉ መርጦ በሰዓሊነቱ መጠነኛ ዝናን አትርፏል ። በሀብት ግን እርሱ ድሀ እኔ ባለፀጋ ነበርን ። የገንዘብ ችግሩን እንዲወጣ እያልኩ ክብረ ሕሊናውን ሳልነካ በየምክንያቱ ስዕሎቹን እንዲስልልኝ አደርግ ነበር ። የዝቅተኝነት መንፈስ እንዳያድርበት እየ ተጠነቀቅሁ በየምክንያቱ ስለምረዳው የኔ ነገር አይሆን ለትም ነበር ። አመለካከታችንና ፍላጎታችን ሁሉ ከመደ ጋገፉ የተነሳ እንዳችን ያለአንዳችን መኖል አይሆንል ንም ነበር ። በአጠቃላይ እኔ የእርሱን ጓደኝነት የምፈል ገውን ያህል እርሱም የኔን ጓደኝነት አጥብቆ ይፈልግ ነበር።

በዚህ ዓለም ግን አንድ ሰው ምንም ያህል ንጹህ በመሆን ሌላውን ሳይጎዳ በጥንቃቄ ለመኖር ቢሻም ከፍ ላጎቱ ውጪ እንቅፋት መፈጠሩ አይቀርም ። እድል የሚ ሉዋት እጣፈንታችን ረጋ ያለ ሰላማዊ ኑሮን በርጋታና ለዘለቄታ እንድንኖር አትወድም ። ሳናስበው እንደቀልድ በየቀኑ በሚያጋጥሙ ተራ ነገሮች ይጀምርና ለዘመናት የገነባነው እለኝታችን ነው የምንለው የኑሮ ገመድ ተበ ጥሶ የኮራንበት ሰላም ድንገት እንዳልሆነ ሆኖ እናገኘዋ ለን ። የዚህ ዓይነት ለውጥ እንደማንኛውም ሰው በኔም ላይ በአንድ ተራ ቀን ፣ ድንገት ባጋጠመኝ ቅርኢት ምክንያት ደርሶ ኑሮዬ ደፈረሰ።

በ1881 አንድ ቀኑን በትክክል የማስታውሰው የሚያ ዝያ መባቻ ለት ኔፕልስ በጀልባ ላይ ብቻየን ነበርኩ።ከእኩለ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀን እንበቶ ጀንበርዋ ዘቅዘቅ እስክትል ጀልባዬ ላይ ሆኜ
አየር እቀበል ነበር ። ጓደኛዬ ለጥቂት ሳምንታት ዘመድ
ጥየቃ ሮም ሄዶ ስለነበር የልቤን የማጫውተው በማጣት
ብቸኝነት ተሰምቶኝ ነበር ። ጀልባዬ ከወደብ እንደደረሰች
ቀዛፊዎችዋ እየተቻኮሉ ወደየመደብቻቸው ሲያመሩ እኔ
ግን ኃሳቤ ባክና ለማድረግ የምፈልገውን መለየት አቅቶኝ
ፈዝዤ ነበር ። በኔፕልስ ብዙ የማውቀው ሰው ነበረኝ ፤
ነገር ግን ግብዣቸውም ሆነ ወሬያቸው እምብዛም አይጥ
መኝም ። ስለዚህ ከእነሱ ጋር ከመዋል ብዙውን ጊዜ
ብቻዬን መሆን እመርጣለሁ ። ከጀልባዋ እንደወረድኩ
የግድየለሽ መንገዴን አዘግም ጀመር ። የከተማውን ሰፈ
ጎዳና ይዤ የቪላዬን ዳገት አሻቅቤ እያየሁ ፤ በእግረ ልግባ
አልግባ እያልኩ ሳመነታ ድንገት ደስ የሚል ዝማሬ ሰማሁ።
ከሩቅ ነጫጭ ቀሚስ ያጠለቁ ቆነጃጅት ታዩኝ ። ወቅቱ
የድንግል ማርያም መከበሪያ ስለሆነ ዝማሪያኑ በዓሉን
ለማክበር የወጡ ደናግል ናቸው የሚል ግምት አደረብኝ ።
የሚያጣድፍ ነገር ስላልነበረኝ የልጃገረዶቹን መምጣት
በጉጉት ቆሜ እጠባበቅ ጀመር ። ጥዑመ ዜማቸው እየቀ
ረበኝ መጀመሪያ ቀሳውስቱ ፤ ለጥቆ ዲያቆናቱ ከዚያም
ፅናጽልና ግጠኛ የያዙ ካህናት አደባባዩን በመዓዛ እያወዱ
አለፉ ። የጧፍ መብራት የያዙ ወጣት ሴቶች መሀል ድን
ገት ዓይኔ አንድ ቦታ ላይ ተተክሎ ቀረ ። ስዕል የመሰለ
ብርቅና ድንቅ ውበት በዓይኔ ላይ ግጥም ብሎ የማየውን
ባለማመን የቆምኩበትን እስከስት ፈዝዤ ቀረሁ ። ዓይኔን
እንዲህ አፍዞ ልቤን የማረከው የአንዲት ውብ ልጃገረድ


t.me/OLDBOOKSPDF

ፊት ነበር ። በጨለመ ደመና ውስጥ ፈክቶ እንደሚታይ ቀስተደመና የደመቀውን የዚያችን ልጅ ፊት የውበት መስመር እንዳለቅ ተጠንቅቄ ዓይኔ እስኪቦዝ አተኮርኩ ። ፊትዋ እንደ ሕጻን ውብ ፊት ታይቶ አይጠገብም ። ፍጹም በሆነ ውበትዋ ላይ ሳተኩር ለቁንጅንዋ ፍጹምነት ተወዳዳሪ ስፈልግ ፊትዋ መሀል ጉብጉብ ያሉት ዓይኖችዋ እንደ ፍላጻ ስሜቴን ወጉት ። ከዋክብት ዓይኖችዋ ስሜቴን አተኮሱት ። ዓይኔን ከነዚያ ያፍዝ ያደንግዝ ዓይኖችዋ በግድ ለማላቀቅ ስታገል ከዓይኖችዋ ወረድ ብሎ በማማሽ ፈገግታ የተቀዳጁ ከናፍሮችዋን አየሁ ። ዋ! ማስደሰታቸው! በማየት ሰከሬ አፌን ከፍቼ ምስጥ ብዬ አየኋት ። ውበት ሰውን የሚያነሆልል ትንግርት መሆኑን ያን ዕለት ነው የተረዳሁት ። ይህች ሴት ሕይወቴን ሙሉ የፈራኋትና ልርቃት የሞከርኩዋት ሄዋን ናት ። ሴት የሚሉትን ጾታ በመጠርጠርና በውበትዋም ላለመጠመድ የተከላከልኩዋትን ያህል በአንድ ቀን ጀንበር ተብረከረኩላት ። ዕድሜዋ ግፋ ቢል ከአሥራ አምስት ወይም ከአስራ ስድስት አይበልጥም ። ዓይነርግብዋ ሆን ብላውም ይሁን በአጋጣሚ ወደኋላዋ ተጥሎ ስለነበር በዚያች አፍታ ገጸውበትዋን እንደጠዋች ጀንበር በሠራ አካላቴ እስኪዳረስ ድረስ ተማማቅኋት ። ዓይኔ ከዓይንዋ ጋር ተጋጨ ። እናያ ምትሃታዊ ፈገግታዋ በሰውነቴ ሁሉ ተሰራጨ ። የክብረ በዓል ዘማሪያን ሰልፍ አለፈ......ያየሁት ራዕይ ከዓይኔ ላይ እየጠፋ ሄደ ። ......ነገር ግን በዚያችን አፍታ የሕይወቴ አንደኛው የታሪክ ምዕራፍ ለመጨረሻው ጊዜ ተዘግቶ አዲስ የሕይወት ታሪኬ ተጀመረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያስ ምን ሆነ? አገባሁት ወይ ትሉኝ ይሆናል ። ማገባት ነው? ሳትውል ሳታድር ነዋ ። እንደሀገሬ ሰዎች እኔም እንደ ካፈቀርኩ ለፍቅር ጊዜ አልሰጥም ። ማፍቀር ፣ በፍላጐት መስከር ፣ ከዚያ ወዲያ ማጥመድ ነው የሚከተለው ። የድሪያ ጊዜያችን አጭር ነበር ። በጥንቃቄ ተጠንቶ እጥር ምጥን ብሎ እንደ ተዘመረ ጣዕመ ዜማ የድሪያ ጊዜያችን ጥፍጥ ያለች አጭር ነበረች ። ያፈቀርኳት ልጅ በጥብቅነቱ በታወቀ የገዳም ትምህርት ቤት ያደገች ፣ የማታ እንጀራው ያላማረ የፍሎሬንስ መስፍን የልጅ ልጅ ነበረች ።

አባትዋ በዓይናቸው እንባ እያቆረዘዘ «ስለዓለም የምታውቀው የላትም፣ የዓለም ጣጣ ያልገረፋት የዋህና እንደ መስከረም አደይ አበባ ንጹህ ናት» አሉኝ ። አመንኳቸው ። ይህችን ድምጿ ለጋ በእምቡጥ ዕድሜ ያለች የበልግ አበባ እየተቻኮልኩ ተላበስኳት ። አባትዋም የሚወድዋትን ልጃቸውን አሰማምረው አጎናጸፉኝ ፣ ከልባቸውም ሰጡኝ ። መንምና የነበረውን ሀብታቸውንና ጠውልጐ የነበረውን ስማቸውን እንዲታደስ የምታደርግላቸው መስላ ሳትታያቸው አትቀርም ። ስለዚህ ከአንጀታቸው መርቀው ሰጡኝ ።

ክረምቱ ሳይገባ ተጋባን ። ውድ ጓደኛዬ ጉዱ ፈራራ በዚያ ትሁትና ቀልጣፋ የአስተናጋጅነት ችሎታው የሠርግ ጊዜያችንን አደመቀው ። ሁሉ ነገር ከተፈጸመ በኋላ «በምክሬ የተጠቀመ አንድ ሰው ቢኖር አንተን አየሁ፣ የመጨረሻዋን ውድ አልማዝ ነው እጅህ ያስገባኸው» አለኝ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

እጁን ሜን ብዬ እስተያየቱን ስቀበል በሙሽራይቱ መምጣት በሁለታችን ማሀል የነበረው በጣም የተቀራረበ ጓደኝነት ራቅ ማለቱ ተሰማኝ ። ያለፈውን ሕይወቴን ጠቅለል አድርጌ እንዳለፈ ነገር አይቼ ስሜቱ ወደሚሽቱ ወዲያው አዘነበለ ። ውበትዋ ገዛኝ ። እንደንጋት ኮከብ የደመቁት አይኖችዋ የፍቅር ስሜቴን ሁሉ እንደሰም አቀለጡት ። ፍቅርን በሰራ አካላቴ ሁሉ አዳረሰች ። ከእርስዋ በስተቀር ሁሉን ነገር ረሳሁ ። የፍጥረት ሁሉ መክፈቻና መዝጊያ ፍቅር መሆኑን ተገነዘብኩ ። ልቤ በፍቅር ፈነጠዘ ። ሴት ከቀን አፈቀርኩ ። ለአፍታ ድካምና መሰልቸትን ሳላውቅ አፍቅሬ እንደማላውቅ ዓይነት አፈቀርኩ ። የሚሽቴም ውበት እየበረታ የኔም ስሜት ከመሸነፍ ሳይቦዝን የፍቅር ጥልቀቴን ሁሉ ተመላለሰችበት ። በፈገግታዋ ሳበችኝ ፣ ደካማነቴንና ብርታቴን ሁሉ ለይታ እመቀች ። ወንድ ልጅ ሃያኛ ዓመቱን ካለፈ በኋላ የሴቶችን ጥበብ ይማራል ። ጠንካራውን ጎበዝ የሚያለሰልስ ኃይል ያላቸው ሴቶች የባሮች ጌቶች ናቸው ። አፈቀረችኝ ፤ ከአንድ ሺህ ሴቶች ዘጠኝ መቶዎቹ ባሎቻቸውን ለሁብቱ ሲሉ እንደሚያፈቅሩ የኔዋም ሚሽት ያፈቀረችኝ መስሎ ነው የሚታየኝ ። የያዝኩት ቂም ግን የለም ። ከሴትነት ደረጃ አውጥቼ የመላእክትነት ስፍራ ከሰጠኋት ግን ጥፋቱ የኔ እንጂ የእርስዋ አይደለም ።

ቤታችን ለወዳጆቻችን ሁሉ ምንጊዜም ለመስተንግዶ ክፍት ነበር ። ቪላችንም የኅብረተሰቡ ታዋቂ አባላት መገናኛ ሆነ ። ባለቤቴ በውበትዋ ፣ በእንግዳ አቀባበልዋ


t.me/OLDBOOKSPDF

በቤት እያያዘዋ ዝናዋ በቅርብና በሩቅ ይሰማ ጀመር ። ከሚያደንቋት ሰዎች የኔው ጓደኛ ጉዱ ፈራሪ አንዱ ነበር ። ዝናዋን ሞቅ አድርጎ ነው የሚያወጋው ። የአበባ ስጦታ ያመጣላታል ። በትህትናና ደግነት ሲያሞግሷት በአክብሮቱ ይበልጥ ባለውለታዬ እየሆነ ሄደ ። እኔም በፍቅር ፣ በሀብትና በጓደኝነት ያለኝን መታደል እያደነቅሁ በደስታ ፣ በፍጹም ደስታ መኖር ጀመርኩ ። ከዚህ ሁሉ በረከት በላይ ለሰው ልጅ የሚያስፈልግ ምን አለ?

በደስታዬ ላይ ሌላ ደስታ ተጨመረልኝ ። በመሸር ወራት መባቻ የመጀመሪያ ልጃችን ተወለደች ። አንድ ቀን ምሽት አበቦች ጥላ ሥር ሻይ እየጠጣን ከጉዱ ጋር ስንጫዋወት ሞግዚትዋ አንድ በካሽሚር ሀር የተጠቀለለ ሕጻን አምጥታ አስታቀፈችኝ ። ሕጻንዋ አይንዋን ስትከፍት እንደንጋት ኮከብ እያበራ ትንሽዬ ፊትዋን ሳምኳት ፣ ጉዱም ሳማት ። ጽጥታ የሰፈነበት የሚታዘብ አይነት አስተያየት ከሕጻንዋ አይን አነበብኩ ። ንፋሱም የጽጌረዳ አበባ እግራችን ላይ እስኪረገፍ ድረስ እየፈነደቀ ከኔው ጋር ደስ አለው ። ሕጻንዋን ለሞግዚትዋ አቀብዬ «የመሸር ስጦታሽን በታላቅ ክብር ተቀብያለሁ በያትን» ብዬ ሞግዚትዋን ሸኘኋት ።

ሞግዚትዋ ከሄደች በኋላ ጉዱ እንደቆመ ትከሻዬን ያዝ አደረገኝ ። ፊቱ ያለ ወትሮው እየገረጣ ፣ «ፋቢዮ አንተ እኮ ግሩም ሰው ነህ» አለኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«እንዴት ፣ ምን ማለትህ ነው ፣ ከሌሎች በምን እኛ ላለሁ?»

«ከብዙዎቹ አንተ ጥርጣሬህ መጠነኛ ነው» አለኝ ።

በአድናቆት እያተኩርኩት «ምን ማለትህ ነው ጉዶ? ማንን ነው የምጠራጠረው ፣ የምጠረጥርበትስ ምክንያት ምንድንነው?» አልኩት ።

እየሳቀ መቀመጫው ላይ ቁጭ አለ ።

«የለም እንዲህ ማለቴ አይደለም ። የከተማችን አየር የተሞላው በጥርጣሬና በቅናት ነው ሕጋዊ በሆነም ሆነ በሕገወጥ መንገድ ሕጻናት በምቀኝነት መረገም እንደተጠመዱ ናቸው ። ንስሀ የሚገቡትም ከነርሱ ለባሱ ሀጥያተኛ ካህናት እየተናዘዙ ነው ፣ ታዲያ እንዲህ ባለው ዓለም እየኖርን ከዚሁ ሁሉ ሀጥያት የራቀ እንዳንተ ያለ ንጹህ ሰው ማግኘት ያስደስታል» አለኝ ። ጥቂት ቆየት ብሎ አሰላስሎ ደግሞ «በትዳሩ የሞቀ ፍቅር ተማምኖ የቅንጣት ያህል ጥርጣሬ ሳይኖረው ተደስቶ የሚኖር ከየት ይገኛል በዚህ ሰዓት» አለኝ ።

«ማንንም ላለማመን ምክንያት የለኝም ፤ የኔ ባለቤት ኒና እንደሆነች ዛሬ ከወለደችው አራስ ያልተለየ ሕጻን ንጽህና ነው ያላት ።»

«ትክክል ነው» አለ ጉዶ ። «በፍጹም ትክክል ነው» ፈገግ ብሎ ዓይኖቹን ከዓይኖቼ ሳይነቅል» እንደበረዶ የጸዳች ፣ እንደ አልማዝ የነጠረች ፣ ከሀጥያት ሁሉ የራቀች ናት ።» አለ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

አነጋገሩ ግን የወትሮው አይነት ስላልነበረ ሁኔታው ግራ አጋባኝ ። የንግግራችን ርእስ ወዲያው ተለወጠ ። ዳግመኛ ጉዶ ስላነሳልኝ ነገር አላሰብኩም ። ሁኔታዎችን አንድ በአንድ እያገጣጠምኩ የማሰላበት መራራ ጊዜ ግን ወዲው ደረሰ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሁለት

በ1884 የኔፕልስ ነዋሪዎች ምን ዓይነት የበጋ ወቅት እንዳሳለፍን ለማንም የታወቀ ነው ። በወቅቱ የየሀገሩ ጋዜጦች አሰቃቂውን መከራ በየገጾቻቸው አስፍረው ነበር ። ኮሌራው እንደአንጋፋ ጋኔን በአገሩ ላይ እንደልቡ ጋለበ ። በአጠውላጊው ዓይኖቹ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሽማግሌና ወጣት በየአደባባዩ እየተዝለፈለፉ እንደቅጠል ረገፈው ቀሩ ። የዚህ ሁሉ ጥፋት ምክንያት የሆነው የጽዳት ጉድለት በሽታውን ወልዶ በዓለም ሙሉ እስኪያንቀጠቀጥ ድረስ አደነደነው ። ሞት አደባባዩን ከጓሮ ሳይለይ ፣ ሽማግሌ ከወጣት ሳይመርጥ፣ጡት ያልጣሉ ሕጻናትን ሳይዘነጋ ሰውን በቁም አረገፈው ። ይህ ከጽዳት ጉድለት ምክንያት የተነሳው በሽታ ከእለት ወደ እለት እያደገ ሄዶ ከተማይቱን አጥለቀለቃት ። ከኮሌራው ይልቅ ሕዝቡን ይበልጥ የጎዳው ደግሞ ከመደናገጡ የተነሳ በትክክል ለማሰብና ራስን ለመቆጣጠር ባለመቻሉ ያስከተለው ችግር ነው ። በፍርሀት ፍጥረት ስለራደ መድሀኒቱ ከጠፋ ሞት ለማምለጥ በሩን ለጥንቆላና ከንቱ እምነት ከፈተ ። የሞት ፍርሀት ሕዝቡን በምቀኝነትና ራስ ወዳድነት እርስበርስ አናከሰው ። ከመከረኛ ታሪኩ አንዱ ብቻ ቢወጋ ብዙውን ሊገልጽ ይችላል ። ታዋቂ የሆነ መልከ መልካም እሣ አጥማጅ በጀልባው ላይ ሲሰራ በኮሌራው ተጠመደና በቃሬዛ ሰዎች



t.me/OLDBOOKSPDF

የወሳንሳ ተሸካሚው ወደ እናቱ ቤት አንዙት። አሮጊቷ እናቱ የበሽተኛውን አጀብ ገና ከሩቅ ወደ እርስዋ መምጣቱን ስታይ የቤትዋን በር ከውስጥ ቀርቅራ ገርበብ ብሎ በተከፈተው መስኮት «ስለኪዳነ ምህረት ብላችሁ ይህን እግዜር የተጣላውና በገዛ እናቱ ላይ መቅሰፍት ተሸክሞ የመጣውን ምስኪን አገኛችሁበት ጣሉት!» አሮጊትዋ ምላስዋን እንደ እባብ አሹላ ድምጽዋ እስኪሰል እየጮኸች «አጥብታ ያሳደገች ፣ ውሀ ሽጣ በጥረትዋ የምታድር እናት እስቲ ምን በወጣት ነው ኮሌራ የሚላከባት! በቅዱስ ዮሴፍ ብላችሁ! ከእንግዲህ ምንልጅ መውለድ! ማሳደግ ያስፈልጋል! እኔ ይህን ምስኪን አገኛችሁበት ጥላችሁ ሂዱ ብያችኋለሁ ።»

ወፍ ከልክል ማስፈራሪያ የመሰለችውን አሮጊት ማግባባት አስቸጋሪ ነበር ። ደግነቱ እሣ አጥማጁ ወጣት በበሽታው ራሱን ስቶ ስለነበር የእናቱን ክፋት ሳያውቅ በራፍዋ ላይ እንደወደቀ ወዲያው ተንፈራግጦ ሞተ ። እስከ ሬንም እንደማንኛውም ጉድፍ በሬሳ ሰብሳቢዎች ተነሳ ።

የኔፕልስ የፀሐይ ንዳድ አይነሳ ። ሰማይ ምድሩ ይፋጃል ። የፀሐዩ ሙቀት አልበቃ ብሎ በከተማው አቅራቢያ የሚገኘው ቨሲቪየስ እሳተ ጎሞራ ሳይቀር እሳት ይረጫል ። ከሙቀት የተነሣ የወፍ ድምፅ የሚባል ነገር ቀን መስማቱ ተረሳ ። የኛ ቤት ግን ጉብታው ላይ በደን ተከቦ የተሰራ ስለነበር ሙቀቱ ከሌሎች ጋር ሲተያይ ነፋሻ ነው ። የበሽታው መዛመቻ የሚሆነውን ሁሉ ከግቢያችን ለማጥፋት



t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ ራሴ ጥንቃቄ ወሰድኩ ። መንደሩን ለቅቄም ለመሄድ አስቤ ነበር ፤ ግን አባስ አጋጣሚ ብንወድቅስ የሚለው ፍርሀት መለሰኝ ። ባለቤቴ ግን ይህን ያህልም አልተረበሸ ችም ። የመልከዋ ውበት የውስጥ ስሜትዋን ይደብቅላት ለንደሆነም አላውቅ እንዲያው ሲፈጥራት ለእደጋ መርበ ትበት አታውቅም ። የሁለት ዓመትዋ ልጃችን ወፍራም አሻንጉሊት መስላ ትድበለበላለች ። ጤናዋ እናትዋን ወይም እኔን ለአንድ ቀን እንኳ አሳስቦን አያውቅም ።

በችግሩ ምክንያት ፤ ኮሌራው አስከፊ ደረጃ በደረሰ በት ወቅት ጉዶ ፈራሪ ከበሽታው ለመሸሽ ሲል እኛው ቤት ገብቶ መኖር ጀመረ ። ቆሻሻ ወዳድ የሆነውን የኔፕ ልስ ነዋሪ ኮሌራው በስለታም ጥርሱ በብዙ መቶ በሚቆ ጠር እያጨደው ሄደ ። ሶስታችን ከጥቂት የቤት ሠራተኞች ጋር በጥንቃቄ መኖር ጀመርን ። ቤተሰቡ በሙሉ በደንብ የበሰለ ትኩስ ምግብ እየበላ ፤ የተፈላ ውሃ እየጠጣ ፣ ገላ ውን በየእለቱ እየታጠበ በጠዋት ነቅቶ በጊዜ እየተኛ መኖር ጀመረ ። በቤታችን ልጅ አዋቂው ጤንነቱ ለአንድ ቀን አላጠራጠረውም ።

ባለቤቴ ካልዋት ውብ ለዛዎች አንዱ እንደግር የሚ ጣፍጥና የሰለጠነ ድምጽዋ ነው ። መንፈስን የሚያድስ ጣዕመ ዜማ ሁልጊዜ ታሰማናለች ። ጀንበር ከጠለቀች በኋላ ጉዶና እኔ አትክልት ውስጥ እያጨስን ስንዝናና ፤ና ልጅዋን እያስተኛች ምንው ባላለቀባት የሚያሰኙ ዜማዎ ችን ታሰማናለች ። ከአንድ ዘፈን ወደ ሌላው ፣ ከአንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዜማ ወደሌላው እየተሸጋገረች ስታንቆረቁረው ግጥሙም ዜማውም አለመዛነፉ ይገርመናል ። አንዳንድ ጊዜ የቅብ ብል ሲሆን ጉዶ ከደጅ ባለቤቱ ከቤት ሆነው እየተቀባበሉ ያዜማሉ ። የርሱ ድምጽ እንደፈረሰኛ ወሃ ሲንጎደጎድ የኒና ድምጽ ደግሞ እንደ አእዋፍ ዜማ ለስልሶ በጆሮአችን ይሰርጋል ። አንዳንዴ ብርዱ አባርሮን እቤት ስንገባ ዜማው ይቀጥልና ጓደኛዬና ባለቤቱ ራስ በራስ እየገጠሙ ተቀባብ ለው ያዜማሉ ። ክፍሉ በባለቤቱ ሽቶ ይታወዳል ። እኔ እንደ ንጉሥ በመቀመጫዬ ላይ ተደላድዬ በባለቤቴና በጓ ደኛዬ ችሎታ መታደሌን እያደነቅሁ እደሰታለሁ ። የኅብ ረት ድምጻቸው ዛሬም በጆሮዬ ሲደውል ባለፈው ጅልነቴ እቆጫለሁ ። ሰው ሙሉ በሙሉ የሚታለልባቸው ወቅቶች ሁሉ በደስታ ያንሆልላሉና እኔም ከራሴ ሕይወት አስበልጬ እወዳቸው በነበሩ በባለቤቴና በጓደኛዬ ጂልኩ ፤ ነሆለ ልኩ ።

በኔፕልስ የነሐሴ ወር ከወራት ሁሉ የከፋ በመሆኑ ሕዝቡ በመረደው መዓት ሞት ተስፋ ቆረጠ ። ኮሌራውም ሬሳ በሬሳ ላይ እያነባበረ ሕዝቡን ፈጀው ። በየአደባባዩ የሚወድቀውን ሬሳ ማንሳት ታከተ ። ከከተማ ወጣ ብሎ የወደቀ ሬሳ ላይ የቀንና ሌሊት አራዊት ተፈራረቁበት ። የኮሌራው ልዩ ልዩ መርዶ በሰፈው አስገመገመ ። ስምንቱ ጐረምሶች ስምንት ምርጥ ቆነጃጅት ይዘው ሆቴል ሄዱ አሉ ሰዎች ሲያወሩ ። ዋንጫቸውን ሲያነሱ ከመሀከላቸው ልቡ የደነደነው «ለኮሌራው መልካም እድል ዋንጫችንን እናንሳው» ብሎ እየተንከተከቱ አነሱ አሉ ። እስራ ስድስቱም



t.me/OLDBOOKSPDF

ያቺን ጀንበር ሳያዩ ሴሊቱን ተረፍርፈው አደሩና በማግስቱ በወልማጣ ሳጥን እናት ባናት ተቀበሩ ። የዚህ ዓይነት የጉድ ወሬ በሰፈው ይዛመታል ። እኛ ግን በልጃችን ጣፋጭ የሕጻን ጫዋታ ጊዜያችን ሁሉ ተይዞ እምብዛም ውጭ ስለማን ወጣ ከምንሰማው የማንሰማው ይበልጣል ።

በእንዲህ ያለው ደረቅ በጋ አንድ ቀን ያለወትሮዬ ማልጄ ተነሳሁ ። ባለቤቴ ድብት ያለ እንቅልፍ ወስዷታል ። እንዳትቀሰቀስ ተጠንቅቄ ለባብሼ ስጨርስ አስተኛኘትዋ ስሜቱን ኅበውና አየት አደረግኋት ፤ ፊትዋ ላይ ያለው ፈገግታና የውበትዋ ለዛ ልቤን አተራመሰው ። ለሦስት ዓመት ሚሽቴ ሆናለች ። የኔ ብቻ......የኔ የብቻዬ ሆናለች ። ጊዜው ባደገ መጠን የፍቅራችንም መጠን በዚያው ልክ እያደገ ሄዶአል ። ከጊዜው በላይ ለርስዋ ያለኝ ፍቅር ግን ለረጅም ዓመታት የተጠራቀመ ሆኖ ይሰማኛል ። ትኩረቴ እንደገና ገጽዋ ላይ አረፈ ። የፀጉርዋን አወጻደቅ በዓይኔ ተሳልሜ የተደገሰልኝን የእድል ጽዋ ባለማወቅ ለመቅመስ እንደቀልድ ከመኝታ ክፍላችን ወጣ አልሁ ።

ግቢያችን አፀድ ውስጥ የእየሩ መቀዝቀዝ ስለሳበኝ እያዘገምኩ የትናንትናውን ቃጠሎ ለማብረድ ሌሊቱን የተፈጠረውን ነፋሻ አየር እየተቀበልኩ እግሬን እፍታታ ጀመር ። በዚያችን እፍታ አእምሮዬ ፕሌቶ ባስተማራቸው ትላልቅ ርእሰ ትምህርቶች ተይዞ በጥልቀት እያሰብኩ ሳይታወቀኝ የግቢያችንን አፀድ አልፌ ቅጽር ግቢውን ትቼ ወጣሁ ። ከከባድ የፍልስፍና ርዕሶች ጋር እእምሮዬ


t.me/OLDBOOKSPDF

መጫዋወቱን እየተደሰተና የማስታወስ ኃይሌን እየፈተንኩ እግሮቼ የወደቡን መውረጃ መንገድ ይዘው እቆለቆሉ ። ወደቡ አካባቢ ለሰለስ ብሎ ይነፍሳል ፣ ትላልቅ ዛፎች ጥላዎቻቸውን በረጅሙ ጥለው በሩቁ በነጫጭ ሸራ ስር ጀልባዎች በንፋስ ኃይል ሲንሳፈፉ ከሩቅ ይታያሉ ። የመጣሁበትን መንገድ ተከትዬ ለመመለስ ሳመነታ አንድ የሆነ ድምጽ ጆሮዬ ጥልቅ አለና ደነገጥሁ ። በፍላጻ እንደ ተወጋ የእንስሳ ድምጽ ዓይነት እየከረረና እየጐረረ ጆሮዬን አልፎ ጭንቅላቴን አናወጠው ። ድምጹን ተከትዬ በዓይኔ ስፈልግ እድሜው ከአስራ አንድ የማይበልጥ ብላቴና የሚሸጠውን ፍሬ በትሪ አፍንጫውን መሬት ተክሎ ሲሰቃይ አየሁ ። በወይን በሩማን በሙዝና ዘይቱን ፍራፍሬ ተሞልቶ የነበረው ቅርጫቱ ከንብል ብሎ የሚያስጐመጀው ፍራፍሬው ተበትኖአል ። የዘመኑ ኮሌራ ፍሬ ሲያዩት ያምራል ቢበሉት አደገኛ ነው ። ልጁን ትከሻው ላይ ነካ አደረግሁት ።

«ምን ሆንክ ልጄ» አልኩት ። እንደሳንባ የተጠበሰ ውብ ፊቱን ወደኔ አዞር

«በሽታው ነው ጌታዬ ፣ በሽታው...... ስለእግዚአብሔር ከኔ ይራቁ ፣ እኔ እንደሁ መሞቴ ነው» አለኝ ።

አመነታሁ ። ለግል ሕይወቴ እንኳን አልፈራሁም ። ሚስቴና ልጄ......ለነርሱ ስል መጠንቀቅ ፈለግሁ ። የልጁን ስቃይ ግን እያየሁ ሳልረዳው መሄድም አልቻልኩም ። ስለ ዚህ ወደ ወደብ ወርጄ የሕክምና እርዳታ ልፈልግ ተነሳሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«በርታ» አልኩት "ተስፋ አትቁረጥ" ሕመም ሁሉ ተስቦ አይደለም ፣ ሀኪም ጠርቼልህ እስክመጣ እረፍ ብለህ ቆየኝ» ብየው ቁልቁለቱን ሊያያዘው ስል ወጣቱ በሽተኛ ቀና ብሎ ፈገግ እንደማለትም እንደመናገርም አለና ወደኔ እ ያተኮረ ጉሮሮውን ያነቀውን ነገር በእጁ ለመጠቆም ሞከረ። አልቻለም ። አዳኞች እንደ ተፈራረቁበት አውሬ ተዝለፍ ልፎ ሳር ውስጥ ዝርግፍ አለ ። ትቼው እርምጃዬን እያፋጠ ንኩ ቁልቁለቱን ተንደርድሬ ወደብ ደረስኩ ። ፍርሀት ፊታቸውን ያጠወለገው ጥቂት ሰዎች አግኝቼ የልጁን ሁኔታ እያስተዛዘንኩ እርዳታ ብጠይቅ ለአንዳቸውም ስሜት አልሰጣቸውም ። የወርቅ መሀለቅ አውጥቼ ባባ ብል እንኳ አንድም ለእርዳታ የሚደነግጥ አጣሁ ። በልበ ድንጋይነታቸው እየተናደድኩ ሀኪም ወዳለበት ፍለጋ ሄድኩ ። በመጨረሻው አንድ የፈረንሳይ ሀኪም አግኝቼ እርዳታ እንዲሰጠው ብለምነው ፣

«ልጁ ስለሞተ ቁጠረው ፤ ይልቅስ ሬሳውን እን ዲያነሱ ለሠራተኞች ንገር ። እኔ የኮሌራ ሬሳ ነክቼ ሞቴን አላፋጥናትም ፣ ደህና ዋል» ብሎ በሩን ፊቴ ላይ ዘጋብኝ ።

በተስፋ መቁረጥ ጉልበት አጠረኝ ። የፀሐዩ ንዳድ ተልካሻ ሽታ እያነሳ ወደ ልጁ ስመለስ ድካም ተስፋ መቁ ረጥም ተሰማኝ ። እንደ ማቅለሽለሽ ፣ እፈንም እንደ መም ረር ፣ እንደድካምና መዛል አለኝ ። በኮሌራ የተወረረው ከተማ በኔ ጤንነት ላይ የሚያመጣውን ጠንቅ ረስቼ ለልጁ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላደርግ የምችለውን በተስፋ መቁረጥ ሳሰላስል ድንገት በደግነት የለሰለሰ ድምጽ ሰላምታ ሰጠኝ ።

«እርዳታ ነው የሚሹት»

ሳላስባቸው ሕይወታቸውን በበሽታው ለሚሰቃዩ የኮሌራ በሽተኞች የመደቡ የክርስቶስ መነኩሴ አጋጠሙኝ ። የልጁን ሁኔታ ሳልዘረዝርላቸው ችግሬን አውቀው ልጁን ለመርዳት ተከተሉኝ ። በሰውነቴ ውስጥ የሚጓዘውን ድካም ባለማመን ፤

«እንኳን ሰው ውሻ እርዳታ ለማግኘት እየጮኸ ዝም ተብሎ አይታይም» አልኳቸው ። የት እንደምኖር ጠየቁኝ ። ስሜን ነገርኳቸውና ከመቅጽበት አውቀው የጊቢያችንን አቅጣጫ አመለከቱኝ ።

«ምን ዓይነት ፍርሀትና መርበትበት ይኸ ኮሌራ እንዳመጣ አይገባኝም» ስላቸው ፤

«ምን ማድረግ ይቻላል ። እዚህ ያለው ሕዝብ ምኞቱን ብቻ ነው የሚያሳድደው ። ለመኖር ብቻ ስለሚጓጓ ሞትን የመሰለ ተራ ነገር ሲመጣበት እንደ ሕጻን የሚገባበት ይጠፋበታል ። ይኸንን ሕዝብ አጠንክሮ የሚያቆመው አንድም ነገር የለም»።

«እርስዎን እንዲህ ሊያጠነክሮትና ሞትን ሊንቁ ያስቻልዎት ምንድነው?» አልኳቸው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«እኔ ሕይወቴን ለክርስቶስ እንደ ሰለሰጠሁ ተስቦ እኔን አያስፈራራኝም ። የመጣውን ሞት ሁሉ ለመቋቋም ለጌታዬ ስል ቆርጬ ተነስቻለሁ» አሉኝ ።

እየገረመኝ ትኩር ብዬ ተመለከትኳቸውና አድናቆቴን ልገልጽ ስል ከእግር እስከራሴ የሆነ ነገር ውርር ሲያደርገኝ ልናገር የፈለግሁትን መለስኩት ። መንገዱም ዛፉም እንደመገላበጥ አለብኝና እንዳልወድቅ የመነኩሴውን እጅ ሙጭጭ አድርጌ ያዝኩ ። ምድሩ ጃዊ የተነጠፈበት መስሎ አጥወለወለኝ ። መነኩሴው ተጨንቀው ምን እንደነካኝ ቢጠይቁኝ ጥቂት መለስ ስላለልኝ የግዴን ፈገግታ በፊቴ ላይ አሳየሁ ።

«ምንም አይደለ የፀሐዩ ግለት ነው ፤ ብቻ እኔን እዚህ ትተው ልጁን ይርዱት......እምላኬ!»

ይህን ስናገር በትክክል ነፍሴን አላውቃትም ። ጉልበቴ ሁሉ ስለከዳኝ በሰውነቴ ሁሉ የበረዶ ውሃ የፈሰሰበት መስሎ ራሴን ስቼ መንገዱ ላይ ተዘረርኩ ። መነኩሴው ግማሽ በሸክም ግማሽ በመጐተት በአቅራቢያው በሚገኝ አንድ የድሆች ሻይ ቤት አስጠጉኝ ። የቤቱን ባለቤት ጠርተው ፤ «ተጠንቅቀህ እኔ እስክመለስ ድረስ እርዳታ አድርግለት ፤ ይህ ከበርቴው ጌታ ፋቢዩ ሮማኒ ነው ፤ እኔ ፈጥኜ እመለሳለሁ!» እያሉ አስተካክለው ሲያስተኙኝ ሁሉ አስታውሳለሁ ። የቤቱ ባለቤት ስሜን ሲሰማ ፤ «ወላዲት አምላክ! ጌታ ሮማኒንም ኮሌራ ያዘው!» ብሎ ድንጋጤ እያብረከረከው ትራስ አምጥቶ ራሴ ስር



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲገፋልኝ መነኩሲው እንደ፡ የተበጠበጠ መድኃኒት በብርጭቆ ወደእፌ አስጠጉልኝና የግደዬን ሳላጣጥም ገርገጭ አደረገኝ ጥቂኩት ።

«እዚህ እረፍ ፤ እኔ ልጄን አየቼ በእኩል ሰዓት ውስጥ እመለሳለሁ» ብለውኝ ሊሄዱ ሲሉ ያዝ አደረግ ኋቸውና ድምጼ እየከዳኝ ፤

«ቁርጡን ልወቅ እባክዎ ተስቦው ነው ያየዘኝ ወይስ ሌላ?» አልኳቸው ።

«ምናልባት የፀሐዩ ሀሩር ይሆናል ፤ ቢሆንስ አንተ ገና ወጣት ነህ ፤ በሽታውን አሸንፈህ መነሳት አያቅትህም» አሉኝ ።

«አልፈራም» አልኳቸው ። «ብቻ አባቴ ቃል እንዲገቡልኝ የምፈልገው አለ ። ስለመቃመሜ አንድም መልእክት ለባለቤቴ እንዳያልኩ ። ኀሲናዬን ብስት ወይም ብሞት እንኳን ሬሳዬ ጊቢዬ እንዳይገባ ቃል ይግቡልኝ» ብዬ ተማጸንኳቸው ።

«ባለኝ የቅዱስ ኃይል ሁሉ ፍላጐትህን እጠብቃለሁ» አሉኝ ። ትልቁ ሸክም ቀለለኝ ። የምወዳቸውን የምሽቴንና የልጄን ሕይወት ማትረፌ ተሰማኝና በተመስጦ ደስ አለኝ ። ከዚህ ወዲያ መናገር ተሳነኝ ። መነኩሲው ከአጠገቤ ውልብ ሲሉ አእምሮዬ መዋዠቅ ጀመረ ። ባዶ ክፍል ፍራሽ ላይ ወድቄአለሁ ። የሻይ ቤቱ ባለቤት ከእሩቅ በፍርሀት እየተናጠ ይመለከተኛል ። ከወይውጪ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሻይ ለመጠጣት የሚገቡ ሰዎች አስተኛኘቱን ሲያዩ በሩ ደርሰው ይመለሳሉ ። የት እንደተኛሁ በትክክል አውቃለሁ ። ነገር ግን ቀጥ ያለውን ያልፐሰን ተራራ የምወጣ ይመስለኛል ። ቀጥካለው ዳገት ባሻገር ከምንጭ የሚወጣ የተዳፋት ውሀ ሲንሻሻ ይሰማኛል ። በሞት ቀለም የገረጣ ዳመና አይሉት ጉም ፣ እየተንከባለለ ይታየኛል ። ድንገት ደግሞ ከጉሙ ውስጥ የሚሽቴ ፊት ወደኔ ሲመጣ ይታየኛል ። «ኗና ባለቤቴ» እያልኩ መሮጥ ቮመርኩ ። «ፍቅሬ ፣ የጠዋት እድሜ አበባዬ ፣ ኗና! የፍቅር እመቤቴ!» እጆቼን ለእቅፍ ዘርግቼ ሳቅፋት ተንጠራርቼ ሳቅፋት...... ኢዲያ ያ ቀጥቃጣ የሻይ ቤት ጠባቂ ነው እስጨንቆ የያዘኝ ። እግርናና እጄን እያወራጨሁ ከእርሱ ጋር ብዙ ታገልኩ ።

«ልቀቀኝ አንተ ጅል! ሚሽቴ ልትስመኝ ከንፈርዋ ይንቀጠቀጣል ፣ ልቀቀኝ አልኩህ!»

ሌላም የሻይ ቤቱን ሰው ረድቶ ለሁለት ታገሉኝ ። ለሁለት አዳክመው ትራሱ ላይ አጋደሙኝ ። እንደሰማይ የከበደ ድካም ሁለመናዬን አዛለው ። ከዚያማ ወዲያ የቀን ቅዠቱ ነገር ምን ይወራል ። የሻይ ቤቱ ባለቤት ስለት ይዞ ሲመጣ ይታየኛል ። እኔን አልፎ ወንዙ ዳርና ዳር የተኮለኮሉትን አዞዎች መጀመሪያ ሊወጋ የወጣ ይመስለኛል ፣ ነገር ግን ምንም ሳያደርግ ቀጥታ ወደ እኔ ይመለስና ያን የተሳለ ሾተል ልቤ ላይ መላልሶ ይተክላል ። ጽልመት መጋረጃ ይውጠኛል ። ድምጽ ይሰማኛል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«እያዞህ ልጇ ፣ በርታ በልልኝ ፣ በርታ በል ፣ ነፍስህን ለክርስቶስ እያራ ተዋት» የሚል ድምጽ ይሰማኛል ።

መነኩሲው ናቸው ። ስላወቅኋቸው ደስ አለኝ ። መናገር ባልችልም ስለ ልጁ የጠየቅኋቸው ይመስለኛል ። እጆቻቸውን ደረታቸው ላይ አመሳቅለው «ነፍሱን ለሰላም እረፍት ያብቃት ፣ እኔ ስደርስ ሞቶ አገኘሁት» አሉኝ ።

«ሞተ? እንዲዚህ በቅጽበት!» የሞት ቅጽበታዊ ፍጥነቱ አናደደኝ ። ሳላስበው እንደገና ወደዚያው መውጫ የሌለው ትግሮት ሰመመን ውስጥ ገባሁ ። የሆነውን ሁሉ ዛሬ ለማስታወስ ብሞክር ምን እንደሆነ በትክክል አላውቀውም ። የማይቻል ሕመም እንደነበረብኝ ትዝ ይለኛል ። ከሕመም በላይ ሕመም ከስቃይ በላይ የመጨረሻው ስቃይ ይዞ የተራተረኝ አይዘነጋኝም ። እኔ ስሰቃይ የጸሎተኞች ድምጽ ሲተም እንደ ሰመመን ይሰማኛል ። ጸሎቱ መሀል ያወል ሲያንቃጭል እሰማለሁ ። በስቃዩ መጨረሻ ስወራጭ ከዚያ በኋላ የድካም ሰመመን ይዞ ሲገረስሰኝ ትውስ ይለኛል ። በስቃዩ መሀል ሬሳዩን ጊቢዩ እንዳትወስዱብዩ የለፈለፍኩ ይመስለኛል ። ከዚያ በኋላ የመነኩሴውን መስቀል እያየሁ ወደ አንድ የጭለማ አዘቅት ገባሁ ። እኔነቴ እዚያ ላይ አበቃ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሶስት

ከዚህ በኋላ በረጅም የዝምታ ጥላስር ድብት ያደረገው ጭለማ ውስጥ የተረሳ ሕይወት አሳለፍኩ ። ሕልም አይሉት ቅዠት ሁለመናዬን ትርጉም በማላገኝለት ፀጥታ ውስጥ ተዘፍቆ ከቆየ በኋላ እግርና እጅ የሌለው ትይንት ያብለጨልጭብኝ ጀመር ። እንደሰመመን ያሉ ነገሮች ቅርጽ አውጥተው ይመጡብኛል ። አይቼ የማላውቀው ዓይነት ቢራቢሮ ሁሉ ይዞረኛል ። ከጨለመው ማእዘን ብቸኛ አይኖች ወደኔ አጉርጠው ሲያስተውሉኝ አየሁ ። ከዚያ በኋላ በቀሰስተኛ ቆይታ ረጅም በስጋ ያልተሸፈን የአጽም እጅ ወደኔ እየጠቆመ ዛተብኝ ። ከዚያ ደም እንዳ ረገዘ ደመና የማታዋ ፀሐይ ምድር ሰማዩን ጃዊ እንዳስ መሰለች አይነት ሆኖ አንድ አስፈሪ እጅ ወደኔ ሲጓዝ አየሁ ። ደረቴ ላይ በብረት ክብደት ተወርውሮ ከተጫነኝ በኋላ ማንቁርቴን አንቆ አፈራገጠኝ ። ነፍሴን ለማዳን ወደ ግራና ወደ ቀኝ ተወራጨሁ ። ለመጮህም ሞከርኩ ። ግን የያዘኝ እጅ ሊያፈናፍነኝ አልቻለም ። ተስፋ ባለመቁረጥ ተፈራገጥኩ ። ጥቂት በጥቂት በመጨረሻው የሞት ሽረቱን ተጣጥሬ አንገቴን ነጻ አወጣሁና ነቃሁ ። «በስመ አብ» የትነው ያለሁት ብዬ ራሴን ጠየቅሁ ። በምን ዓይነት አስፈሪ ሁኔታ እንዳለሁ ለመገንዘብ ስሞክር ቀስ እያለ መንፈሴ እየተመለሰልኝ መጣ ። የመጨረሻውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሕመሜን አስታወስኩ ፤ መነኩሴውና የሻይ ቤቱ ትዝ አሉኝ ።

በጀርባዬ ዧ ብዬ ተኝቻለሁ ። ትራሱን ግን ለምን እንደወሰዱብኝ አልገባኝም ። እጄን ስዳብስ ይሞ ቃል ። የደም ስሬ ይንዝራል ። ግን የምተነፍሰው አየር ይከብዳል ፤ ይተነፍጋል ። «አየር ትኩስ አየር ያስፈል ገኛል» ብዬ ተናገርኩ ። ከመቅጽበት እጄ ዙሪያየን ሲቃኝ እጄን እንዳልዘረጋ የሚያግደኝ ጠጣር ግርዶሽ ገጠመኝ ። አንድ ሀቅ አእምሮዬን እንደጦር ወጋው ። «ተቀብሬአለሁ ለካ! ከነሕይወቴ ተቀብሬአለሁ!» ተርበተበትኩ ። እጄን እንዳልዘረጋ የሚያግደኝ ጠጣር ግርዶሽ የሬሳ ሳጥን መሆኑ ገባኝ ። ከጭንቀቴ ብዛት የሰይጣን ጉልበት አወጣሁ ። በጥፍሬም በጥርሴም ያፈነኝን የሬሳ ሳጥን ታገልኩት ። ሳጥኑ ፍንክች አላለም እንጂ የኔ ጥፍር ይደማል ። የግን ባሬ ላብ ዓይኔን ዘጋው ፤ ጭንቀት አንቀጠቀጠኝ ። ሌላም የሚያስፈራ ኃሳብ ኅሊናዬን አስጨነቀው ። የተቀበርኩት አፈር ውስጥ ፤አፈር ተጭኖኝ ቢሆንስ? ሳጥኑን ብከፍተው የባሰ አፈሩ በአፍና በአፍንጫዬ ገብቶ ወዲያው ቢገድ ለኝስ? አልኩ ። በተስፋ መቁረጥ ከት ብዬ ስስቅ የራሴ ድምጽ በጨለማ ውስጥ ሰቀጠጠኝ ያበድኩም መሰለኝ ። መተንፈስ መቻሌ ግን ገረመኝና ትኩስ አየር መለዋወጡን አረጋገጥኩ ። ቀስ ብዬ ብዳብስ በመጀመሪያው ትግሌ የሰነጠቅሁትን ቀዳዳ ዳበስኩ ። የነፍስ አድን እልህ እየተናነቀኝ ሳጥኑን ለመክፈት ቻልኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቦታው ከፍት ነው ። እንጨቱን ከላዩ በወረውር የሆነ ነገር እሳዩ ላይ ዘፍ እለብኝና የሞት ሽረቱን እግሬን እስ ራምቼ ቀና ብዬ ለመቀመጥ ቻልኩ ። ነፍሴን ለማዳን ያደረብኝ እብደት ዓይነት ጭንቀት ለቀቀኝ ። ዝግ ብዬ ሁኔታውን ማጤን ጀመርኩ ። ከንሕይወቴ መቀበሬን ፣ ረጅሙ ሕመሜ የሕይወት ስሜቱን ሁሉ ደብቆ የሞትኩ አስመስሎ ለመቃብር እንዳበቃኝ ገባኝ ። የተሰቦ ሞት ባራደው ከተማ የሻይ ቤት ሰዎች የኔን ሁኔታ እስከ መጨረሻው ለመከታተል ትእግስቱም ድፍረቱም ሊኖራቸው እንደማይችል ገባኝ ። በተሰቦ ሰሞን ተወናግሮ በተሠራ የሬሳ ሳጥን ተከትቼ መቃብር ቤት መግባቴ ገባኝ ። መናኛ የሬሳ ሳጥን አሠራራቸውን ግን አመሰገንኩ ። ከምርጥ እንጨት በጥንቃቄ የተሠራ ቢሆንና ሳቤን ሁሉ ጨርሼ በት ባይከፈትልኝስ ምን ይውጠኝ ነበር? ኃሳቡ ራሱ ዘገንነኝ ። ግን የትነው ያለሁት? የሚለውን ጥያቄ በዋዛ አልፈታሁትም ። ስሜን ለመንኩሴው መንገሬ ትውስ አለኝ ። የሮማኒ ቤተሰብ የመጨረሻው ወራሽ መሆኔን ያውቃሉ ። ስለዚህ ደግ መነኩሴ ያለፉት አባቶቼ ማረፊያ የሆነውን መቃብር ከፍተው አሳርፈውኛል ። የታላቁ ሮማኒ ቤተሰብ የመቃብር ቤት ለመጨረሻ ጊዜ የተከፈተው አባቴ በክብር ባረፈ ዓመት ነበር ። የአባቴን አስከሬን ተከትዬ ስገባ ያየሁት የመቃብር ቤት እስፈሪ ገጽታ ትዝ አለኝ ።

በመቃብር ቤቱ ግድግዳ ውስጥ የእናቴን አጽም ይዞ የተቀመጠውን ከዝግባ ተሠርቶና ከእርጅና ብዛት



t.me/OLDBOOKSPDF

የተብጫጨቀ ከፋይ የለበሰውን የሬሳ ሳጥን እንድመ
ለከት ጠይቀውኝ ከመቃብር ቤቱ ከብደት የተነሳ
ሕመም ተሰምቶኝ እምቢ ብዬ ተንገሽግሼ የወጣሁት
የወጣትነት ጊዜዬ ትውስ አለኝ ። ከሳጥኔ ስወጣ የሚጠ
ብቀኝን የብረት ዙሪያ ጥብቅ ግንብ ድድር የብረት መዝ
ጊያ ትውስ ቢለኝ ፍርሀት ለቀቀብኝ ። ያለሁበት መቃብር
ቤት ከመሬት ውስጥ ነው ። አዘቅቱን አልፌ በሩ እንኳ
ብደርስ በምን ቁልፍ በሩን እንደምከፍት ጨነቀኝ ። በአ
ባቶቼ መቃብር ቤት በረሀብ ተጠብሼ ዳግማዊ ሞቴን
የምጠብቅ መሆኔ እያንቀጠቀጠኝ ተነስቼ ከሳጥኑ ወጥቼ
በእግሬ ቆምኩ ። ባዶ እግሬን ስለነበርኩ የድንጋዩ ንጣፍ
ትዝቃዜ ጉልበቴ ድረስ ተሰማኝ ። በኮሌራ በሽታ
መሞቴን ወደድኩ ። እንደእድልም ቆጠርኩት ። ምክን
ያቱም በተሰቦው ፍራቻ ከነልብሴ ቀብረውኛል ። ስለዚህ ወ
ፍራም ሸሚዜንና ሱሪዬን እንደለበስኩ ነኝ ። አንገቴን ስዳ
ብስ የፍቅርና የሀዘን ጸጺት ወረረኝ ። የሚሸቴና የልጇ ገጽታ
ያለበት የአንገት ስዕል በወርቅ ሰንሰለት አንገቴ ላይ እንዳለ
ነበር ። በእንባ ትኩሳት ሳምኩት የኒና ፈገግታ ባልተሰናከለበ
ት ዓለም ለመኖር ሕይወት ስለጣመኝ ምንም ዓይነት
ፈተና ቢጠብቀኝም ሕይወቴን ይገድ ለመውጣት ወሰንኩ ።
ኒና ፍቅሬ ፤ ዓይኖችዋ በእንባ ታጅለው ፣ ሰውነትዋ
በሀዘን ተቆራምዶ ያ ውበትዋ በሀዘን ማቅ ተኮራምቶ በጭ
ለማ ታሰበኝ ። ልጇን ማታ ማታ ከማጫውትበት የብርቱ
ካን ዛፍ ስር ለጅዋጅዌ ለምን እንዳልወሰድኳት ሲጨንቃት
ተሰማኝ ። የኔው ፣ ጓዴ ጉዶ ደፋር ሀቀኛ ጓዴ በድንገተኛ
ሞቴ ተንሰቅስቆ ሲኮራመት ታየኝና ለዘላቂ ፍቅራቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

እኔም በሰቀቀን የታፈነ እንባዬን አፈሰስኩ ። የእነርሱን ደስታ ለመመለስ የያዘኝን የመቃብር ቤት እንደምንም ብዬ ገንጥዬ ለመውጣት ቆረጥኩ ። ውድ አለኝታዎቼ እንዴት እንደሚቀበሉኝ ታየኝ ። ሚሽቴ በላዬ ስትጠመጠም ፡ ልጄ ላዬ ላይ ስትንጠለጠል ፡ ጓደኛዬ ክንዴን ጨብጦ ሲዳብሰኝ ትኩሳታቸው ተሰማኝ ። ሀቀኛ ፍቅር በጊቢያችን እንደገና ሕይወት ሲዘራ በዓይኔ ላይ ስዕሉ ተሳለ ።

የድምጹ ምንገድ በወፍራሙ የሚተም ደወል ድንገት ጆሮዬ ጥልቅ ብሎ ከተሜነኝ ብቸኝነት ገላገለኝ ። ደወሉን ተከትዬ መቁጠር ጀመርኩ ። አንድ—ሁለት—ሶስት—ዘጠኝ ድረስ ቆጠርኩ ። ሰዓቱን ለምዕመናኑ የሚያሳውቅ የሆነ የቤተክርስቲያን ደወል መሆን አለበት ። ወዲያው ድንጋጤዬም መጣብኝ ። ዘጠኝ ሰዓት ሆኖአል ፤ ከቀኑ ነው ከሌሊቱ? ማወቅ አልቻልኩም ። ማሰላት ጀመርኩ ። ሲያመኝ ገና ረፋድ ነበር ። መነኩሴውን አግኝቼ ያን ምስኪን ፍራፍሬ ሻጭ ልጅ እንዲረዱ ስነግራቸው ሰዓቱ ገና ሁለት ሰዓት ገደማ ነበር ። ምቼ ተቀብሬ እስኪደመደ ምብኝ ድረስ ዘጠኝ ሰዓት ሆና ይሆናል ። ስለዚህ አሁን የተደወለው የዘጠኝ ሰዓት ደወል መሆን አለበት አልኩ ። አፈር የቀመስኩበት የመጀመሪያው ሌሊት ከእግር ጥፍሬ እስከራስ ጠጉሬ የሆነ ፍርሀት ሆዴ ውስጥ ገብቶ አንቀጠቀጠኝ ። ከተፈጥሮዬ በጉልበት ብርቱ ብሆንም በትምህርቴ ምክንያት የልዩ ልዩ እምነት ተገዥ ስለሆንኩ በደረቅ ሌሊት አጽማቸው ከፈራረሰ ሙታን መሀል ቆሜ ደወ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሉን ስሰማ ነፍሴን ጭንቀት አሳት ። ራሴን ለመግዛት ሞከ ርኩ ። ሆሞቴን ኮስተር አድርጌ የመውጫዬን ቀዳዳ ለማ በጀት በእጅና እግሬ እየዳበስኩ መንገድ ፍለጋ ቀጠልኩ ። በዚህ መሀል ምጥ አይነት ያዘነ ድምጽ ሰማሁ ። የመቃ ብር ቤቱ የገደል ማሚቶ እስኪያስተጋባ ደግሞ ጮኸ ። ቀዝቃዛ ላብ ጀርባዬን አቋርጦ ወረደ ። የራሴ ልብ ታምቡር ጆሮዬ እስኪደርስ ድረስ ጎድኔን እየወጠረ አስተ ጋባ ። አስፈሪው ድምጽ እያዘነ ደጋግሞ ጆሮዬ ገባ ። በመጨረሻው ጩኸቱ በሚርገፈገፍ ክንፉ ታግዞ አስተ ጋባና ነቃሁበት ። ጉጉት ነው ። በፍርሀቴ ራሴን ታዘብ ኩት ።

በጭለማ ሳፈጥ ሁለት እንደ እሳት የሚያበሩ ዓይኖች ከፊት ለፊቴ አየሁ።የሙታን ጠባቂ ጉጉቷ ትእግስቱና የሥራው ፈንታ ድልድሉ ገረመኝ።ከእየር አየር፡ከብርሀን ጥሩ ብርሀን በሌለው የሙታን ሰፈር ተደብቆ መኖሩ ከነከ ነኝ ። «ብቻዬን አይደለሁም ለካ» አልሁ ። ድምጼን ሲሰማ ሁለቱ ዓይኖቹ ወደኔ ሲገሰግሱ ታየኝ ። በክንፉ ትፍ፡ አድ ርጎ ፊቴን በጥፊ መታኝ ። የማላየው ግን ሲነካኝ የሚሰ ማኝ ክንፉ ይዞረኝ ጀመር ። ጥፊው እንዳይደግመኝ በሁ ሉም አቅጣጫ እኔም ክንዴን አወናጨፍኩ ። በዚያ ኩን ቢው ዓይኔን ጠርምሶ ሊያሳርፈኝ ሲንደረደር በእጄ ተከ ላከልኩ ። ጦርነቱ ለአንድ አፍታ ቀጠለ ። መታኝ እኔም መታሁት ። አላስተረፍኩትም ። መሬት ነክቶ ከተንደፋ ደፈ በኋላ ወደ አንድ አቅጣጫ በሮ ወጣ ። እግረ መንገዴን አቅጣጫውን እየዳበስኩ ተከተልኩት ። መውጫ ደረጃ



t.me/OLDBOOKSPDF

አግኝቼ በእግሬም በእጄም እየዳበስኩ ደረጃውን ወጣሁና ጣሪያውን በእጄ ነካሁ ። የጣሪያውን ጠርዝ ይገር ስከተል አንድ ሳጥን ዳበስኩ ። የእሬሳ ሳጥን መሰሎኝ ደነገጥሁ ። በሌላ ጠርዝ ደግሞ የሬሳ ሳጥን መሆኑ አጠራጠረኝ ። በሀር ጨርቅ ተለብዶአል ። ቁመቱን ልደርስበት ስላልቻልኩ ጠርዙን ተከትዬ በጣቴ የከፈፉን ጌጥ ዳበስኩ ። በሬሳ ሳጥን ቅርጽ የተቀመጠው ግዙፍ ሳጥን ጉብጉብ በሚሉ ጌጦች ተሸላልሞአል ። ከተጌጠው ሳጥን ውስጥ የማን እሬሳ ተኝቶ ይሆን ፣ የሚል ጥያቄ መጣብኝ ። የአባቴ ወይስ የእናቴ? ፍርሀት አንቀጠቀጠኝ ። ሳጥኑን ሸሽቼ በግንባሬ መሬት ተደፍቼ ለአምላኬ ኤሎሄየን ሳሰማ የውሀ ጥም ጉሮሮዬን ሰነጠቀው ። «ምህረት የማይሳንህ አምላክ ምህረትህን አውርድልኝ» ብዬ አለቀስኩ ። ማበዴ መሰለኝና መንፈሴን ሰበሰብኩ ። ጭንቀቴን ቀዝቀዝ ለማድረግ ሞከርኩ ። የንጋት ወፍ ስትጮህ ተሰማኝና ተስፋ የቆረጠ ልቤ እንደገና ጮቤ ረገጠ ። የንጋት ወፍዋን ድምጽ አቅጣጫ ተከትዬ የከበበኝን ድድቅ ጭለማ በዳበሳ ለመወጣት በእጅና በእግሬ መዳህ ጀመርኩ ። እየተደነቃቀፍኩ ደረጃውን ወጥቼ በሩን ለመያዝ ሙከራዬን ቀጠልኩ ። የንጋት ወፍ ድምጽ በሰማሁ ቁጥር የእናቱን ድምጽ እንደሰማ ሕጻን አቅጣጫውን ይገር ተሳብኩ ። የጨረቃ ብርሀን ለመጀመሪያ ጊዜ አየሁ ። የጨረቃዋን ብርሀን እያየሁ የንጋት ወፍዋን ድምጽ እየሰማሁ እመጣቢያው ንጣፍ ላይ ተዘርግቼ ጋደም አልኩ ። በድካም እጅ እግሬን ብቻ ሳይሆን ራሴን ጭምር ቀና ማድረግ እስኪያቅተኝ ነፍሴ ራስዋ ዛለች ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቂት ያንቀላፋሁ ይመስለኛል ። እንደመዛል እን
ደ ማቅለሽለሽ አለኝና አንገቴ ላይ የሆነ ስለት ወግቶ
ቀሰቀሰኝ ። ከስቃዩ ብዛት የመቃብር ቤቱ እስኪያስተጋባ
ጮኹኩ ። የጨረቃ ብርሀን በንጋት ብርሀን እየተዋጠ
ጠቅላላው የመቃብር ቤቱ ግንብ ቤት ወለል ብሎ መታየት
ጀመረ ። የታሰርኩበትን ድንጋይ ቤት እየተዘዋወርኩ ፈተ
ሽኩ ። ጥብቅነቱን ባረጋገጥኩ ቁጥር ብርክ ያዘኝ ። መዝጊ
ያውን ዳበስኩ የተድበለበለ ብረት ነው ። እርዳታ ለመጠ
የቅ ጉሮሮዩ የቻለውን ያህል ጮኹኩ ። የውጪው ዓለም
ናፈቀኝ ። ዛፉ ቅጠሉ ፤ ንጹው አየር ለአእምሮዩ ወለል ብሎ
እየታየ አንገኝ ። በሽቦው መሀል አስታከኬ ግንቡን
ተንጠልጥሎ የለመለመውን የወይን ቅጠል አግኝቼ ሸመጠ
ጥኩና ወደአፌ ስከት በሕይወቴ ቀምሼ የማላውቀውን
ጣፋጭ ምግብ ያገኘሁ ያህል አንድ ሁለቴ ቅጠሉን እያኘ
መደመድኩ ዋጥኩ ። የቅጠሉ ውሀ የተሰነጣጠቀውን ጉሮ
ሮዬን ፈወሰው ። መቃብር ቤቱ ሙሉ ለሙሉ ወገግ ሲል
ወለሉ መሀል የፍትሀት ማድረሻ ተዘዋዋሪ የሻማ መቅረዝ
አየሁ ። ከመቅጽበት እጄ ወደሱሪዬ ኪስ ዘው አለ ። ከብር
የተሰራ የሲጋራ መያዣዬ ፤ ሰዓቴ ከነሰንሰለቱ ኪሴ ውስጥ
ባይኖርም ከብሪትና ቁልፎች ቀባሪዎቼ በጥድፊያው የቀ
ደጉ የተቀበርኩበትን ሳጥን ለማየት ደረጃውን ወረድኩ ።

የቅድምአያቶቼን አጽም በየመደርደሪያው ተሰትሮ
በሻማ ብርሀን ጉበኘሁ ። የሚበሩና የሚሽሎከለኩ ነፍሳት
ብርሀኑን ሲያዩ መሸሽ ጀመሩ ። የራሴንም ሳጥን



t.me/OLDBOOKSPDF

አየሁ ። ስሜ የተወለድኩበትና የሞትኩበት ቀን ፣ በ
ኮሌራ መቅሰፍት መሞቴ ሁሉ ተጽፎበታል ። የነ
ፍስ አድን ቡጥሜ ትግሌ ሳጥኑን በረቃቅሶታል ።
ነጸነቴን ከተጐናጸፍኩበት ሳጥን ጐን አንድ ነጭ መስ
ቀል አገኘሁ ። የከፈኑኝ መነኩሴ ደረቴ ላይ የጣሉልኝ
መሰለኝ ። ከመቃብር ቤት እስሬ ከተላቀቅሁ ታሪኬን ለመ
ነኩሴው ስነግር እንዲያምኑኝ መስቀልዋን ለምስክርነት
ኪሴ ከትቼ ወደእናቴ ሳጥን አመራሁ ። ውበትዋ ፣ ደግነት
ዋ ትዝ አለኝ ። ሳጥንዋ ንክችም አላለ ፡ ሌላው ቀርቶ
ቀለሙ አልፈዘዘም ። ለአባቴ እና ለእናቴ ተንበርክኬ
ጸሎት አደረስኩ ። ተንበርክኬ ጸሎት ከማደርስበት አይ
ኔን ገለጥ ሳደርግ የሻማው ብርሀን የሆነ ብርቅዬ እንክብል
ላይ አረፈ ። አንስቼ ሳየው ሎሚ የሚያህል እንቁ ሆኖ አገ
ኘሁት ። ቀይ አበባ በመሰለ ጌጥ የታቀፈ እንቁ እጄ ውስጥ
ሲንቦገቦግ ባገኘሁት ተደንቄ የመጣበትን አቅጣጫ ለማ
ወቅ የመቃብር ቤቱን መቃኘት ጀመርኩ ። መሬት ላይ
ከወደጥግ አንድ ትልቅ የሬሳ ሳጥን ከሆነ ከፍታ ላ
ይ ተገፍትሮ ወድቆ በውስጡ የያዘው ውድ እቃ ተበታት
ኖአል ። ምን አይነት ቁመትና ግዝፈት ያለው ሰው ያንን
ትልቅ ሳጥን ሞላው እያልኩ ራሴን ስጠይቅ ይህ የተበታ
ተነው ብርቅና ድንቅ ጌጥ የሚወጣው ከምኑ ነው? የሚል
ጥያቄ መጣብኝ ። ቀረብ ብዬ ሳጥኑን ሙሉ ለሙሉ ከፍቼ
ዓይኔን አጕረጥኩ ። ሳጥኑ በሰው አጽም ሳይሆን በወርቅና
በአልማዝ የተሞላ ሆኖ አገኘሁት ። እያቶቼ ለምን ይህን
ያህል ሀብት አብሮአቸው እንዲቀበር እንዳደረጉ አልገባኝ
አለ ። ትላልቅና ትናንሽ ፣ የሚያበሩ ፣ ቅርጽ ያላቸውና



t.me/OLDBOOKSPDF

ቅርጽ ያልወጣላቸው የወርቅ ጭብጦች አገኘሁ ። ሰባት ጫማ ርዝመት ያለው ሳጥን በውድ የብርቅ ዕቃ ተሞልቷል ። የወርቅ ሳህን ሳይቀር ተደራርቦ ሳጥኑ ውስጥ ቦታ ቦታውን ይዞ ሳይ በአድናቆት አፌን ከፍቼ ቀረሁ ። ያገኘሁት ሀብት የኔ መሆኑ ለልቤ ኩራት ሰጠው ። ሞትን ድል ነስቼ ያገኘሁት ሀብቴ ነው እልኩ ። ግን ያለእኔ እውቀት ይኸ ሁሉ ሀብት እንዴት ሊቀመጥ እንደቻለ አልተከሰተልኝም ።

የሳጥኑን ዙሪያ ደግሜ በሻማው ብርሀን ለማየት ሞከርኩ ። በቀይ ቀለም የተቀባ ሳንጃ ላይ ካርሜሉ ኔሪ የሚል ፊርማ አነበብኩ ። ጭንቅላቴን መታኝ ። ካርሜሉ ኔሪ የታወቀው ሽፍታ! የሰረቀውን ሀብቱን ለመደበቂያ ያመነውና ሰው የማይደርስበት የመቃብር ቤት መሆኑ ብልጠቱ አስደነቀኝ ። በዘረፋና ግድያ የተጠራቀመው ሀብት ለኔ ቢዛወር ክፋቱን ይዞ እንደማይዛወር ተማመንኩ ። አረመኔው ካርሜሉ ዝነኛ ከነበረበት የፓሌርሞ ከተማ ይህን የሀብት ሳጥን ሬሳ አስመስሎ ማምጣቱ ቀስ እያለ ታወቀኝ ። እንዴት የእኔን አያቶች መቃብር ቤት እንደመረጠ ፣ በምንስ ቁልፍ ከፍቶ እንደገባ ግን ሊከሰትልኝ አልቻለም ። የሻማው ብርሀን ድንገት ውድም ብሎ ጠፋ ። ክብሪት ስላለኝ አልደነገጥኩም ። ግን በድንገት ምን ሊያጠፋው እንደቻለ ማወቅ ፈለግሁ ። ግድግዳውን ለመዳበስ እጄን ሰደድ ሳደርግ የነፋስ መግቢያ ሽንቁር ተሰማኝ ። ሻማዬን አያይዤ ስፈትሽ ሶስት ጥርብ ድንጋይ ተነቅሎ በቦታው እንጨት ገርበብ ብሎ ተስተካክሎ ተገጥሞበት አገኘሁ ። እንጨቱን ሳነሳሳ


t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ሰው ሊያስገባና ሊያስወጣ የሚችል መስኮት ተከፈተልኝ ። ሻማዬን ጥዬ ሳላመነታ ወደውጪው ዓለም ተወርውሬ ዱብ አልኩ ። ሳር ረገጥኩ ፤ የዛፍ ቅጠል ቀነጠስኩ ። ነጻ መውጣቴን አረጋገጥኩ ። የሕይወት አየር ደግሜ ደጋግሜ ተነፈስኩ ። ውቢቱ ባለቤቴ ኒናን ለመሳም ሕይወቴ ነጻ በመውጣትዋ ከደስታዬ ብዛት ፈነደቅሁ ። ሕይወትና ሀብት አግኝቼ ግቢዬ ለመመለስ ተዘጋጀሁ ። የሽፍታው ውለታ ግን ከበደኝ ። ሀብት የሚሰጥ ፤ ከወህኒ መውጫ በር የሚከፍት ጓደኛ የት ይገኛል።ይኼ ነፍሰ ገዳይ ሽፍታ ያደረገልኝን ያህል የምወደው ጓደኛዬ ጉዶ ምን አደረገልኝ እያልኩ የመቃብር ቤቱን ትቼ ወደዓለም መንገድ አዘገምኩ ። በዛሬው ምሽት ሀዘን ሁሉ ከቤቴ እንደሚሰረዝ ፤ ሚሽቴን ደረቴ ላይ ለጥፌ ፤ ልጄን እየኮረኮርኩ አሳስቄ ፤ የጓደኛዬን ትከሻ እየጨበጥኩ ሞትን ድል ስላደረግሁ ዋንጫችንን እናንሳ እያልኩ በኃሳብ የሙታንን መንደር አቋርጬ ዋናውን መንገድ አልፌ ወደብ ደረስኩ ። ሕያው ሆኜ የጀልባ ቀዛፊዎች ዝማሬ ስለሰማሁ ለጆሮዬ ጣእም ሰጠው ። ባዶ እግሬን መሆኔንና ግማሽ ልብስ መልበሴ ሲታወሰኝ በፍጥነት መቃብር ቤቴ ተመለስኩ ።

# ምዕራፍ አራት

ከመቃብር ቤቴ ሾልኬ እንደወጣሁ ሾልኬ ገባሁና
ወለሉ ላይ የተዝረከረከውን አልማዝና ወርቅ ለቅሜ ሳጥን
መለስኩ ። ሁለት ከረጢት ወርቅ ለራሴ አዘጋጅቼ ያዝኩ ።
ለሚሸቴ ስጦታ የሚሆን የአልማዝ ጌጥ በአንገቴ ላይ አጠ
ለቅሁ ። ሁሉን ነገር በማያጠራጥር እንደነበር አድርጌ መስ
ኮቱን ከፍቼ ከወጣሁ በኋላ እንደነበር አድርጌ እንጨቱን
ገጣጠምኩ ። ለራሴ ያዘጋጀሁትን ሁለት ከረጢት ኪሴ
ስከት ኮሌራውን ከፈሩ ችኩል ከፋኞቼ የቀረ ጥቂት ፍራ
ንኮች ከቁልፍ ጋር አገኘሁ ። በዚህ ገንዘብ ቤቴ ድረስ
ሰው አስመስሎ ሊሸኘኝ የሚችል አሮጌ ልብስ ለመግዛት
የምችል መሆኔን ብገነዘብም አሮጌ ልብስ የሚሸጥበ
ትን ስለማላውቅ ግራ ገባኝ ። አለባበሴ የኔፕልስን ከተማ
የወረርዋትን ለማኞች መስዬ ከተማውን ማቋረጥ ፍጹም
ቢያስጠላኝም የሚመጣውን ሁሉ ለመቋቋም የሙታኑን
ሰፈር ለቅቄ መሄድ የሚያስፈልገኝ መሆኑ ገባኝ ።

መንገዱ በየት ቢሆን ወደቤቴ እንደሚያቋርጠኝ ለማ
ሰብ ጉብታው ላይ ቆሜ ምርጫዬን ወሰድኩ ። የአባቶቼ
መቃብር ቤት የሚገኘው ከኔፕልስ ከተማ በራቀ ክልል ስለ
ነበር ትክክለኛውን አቋራጭ ለማግኘት ቢያጠራጥረኝም
የከተማውን ክልል ስለቅ ግራዬን ይዤ ጉዞ ጀመርኩ ። ፀሐ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይዋእስከትጠመርር ተንዝኩ። እንደበረሀ ረምጫ እግሬ እሸ ዋው ውስጥ እየጠለቀ ውብጥ እግሬ እንደ እሳት ነደደ ። ከላይ የሚወርደው የፀሐይ ንዳድ ግንባር ግንባሬን ቆጋኝ ። ረሀብ ጥማቴ ፣ ድካም ሀመሜ ግን ቤቴ የሚጠብቀኝን እቀ ባበል በማሰብ አልተሰማኝም ። እልፎ እልፎ ግን የነከሰ ኩትን ጥርሴን እያላቀቀ በሰውነቴ ድካም ሁለመናዬን ቢያ ንቀጠቅጠኝ የኮሌራው ሕመም ያገረሸብኝ እየመሰለኝ ልቤን ፍርሀት ፍርሀት ይለኝ ጀመር። ቤቴ ደርሼ በባለቤቴ ርብርቦሽ እስታማሚነት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሁሉም ነገር ይለቀኛል እያልኩ ራሴን በራሴ እያጽናናሁ መንገዴን ቀስ እያልኩ ተሻማሁት ። ዋናውን መንገድ እን ደጨረስኩ የወይን ፍሬ በአህያ ጋሪ ጭኖ እያንቀላፋ የሚነዳ ሰው ገጠመኝ ። ስለራበኝና ስለጠማኝ የወይን ፍሬው አስ ጐመጀኝ ። ቀስ ብዬ ማጅራቱን ነካ ሳደርገው አተኩሮ እንደ እውሬ ተመለከተኝና ከአህያዋ ጀርባ ወርዶ ሕይወ ቱን ብቻ እንዳተርፍ በመላእክት ስም ተማጸነኝ ።

«ሰውዬ ገለል በልልኝ ይልቅ ፤ እኔ ካንተ የምፈልገው የወይን ዘለላ ብቻ ነው ለርሱም የምከፍልህ አለኝ» ብዬ ፍራንክ አወጣሁ ። እጁ የዘገነውን አንዝርርጎ ሰጠኝና እ የተጠራጠረ ተፈተለከ ። በሁኔታው ግራ ተጋባሁ ። ጻረሞት ወይስ ሽፍታ መስየው ይሆን እያልኩ እየተጠራጠርኩ መን ገዴን ቀጠልኩ ።

ያገኘሁትን የወይን ዘለላ ምግብና መጠጥ አድርጌ እያ ንዳንድዋን ፍሬ በስስት እየመጠጥኩ መንገዴን ቀጠልኩ ። ሙሉ ለሙሉ ከተማ ውስጥ ከመግባቴ በፊት ልብስ መለ


t.me/OLDBOOKSPDF

ወጥ ስላለብኝ ዋናውን መንገድ ጥዬ መደብሮች ወዳሉዋት አነስተኛ መንደር ጐራ ስል ብዙ ሰዎች እያዩኝ ሲያልፉ እንደመጀመሪያው ጋሪ ነጂ አልተርበተበቱም ። እርጌ ልብስ በመስኮት ላይ የተደረደረበት ሱቅ አይቼ ገባ ብዬ የሚሆነኝን ልብስ መምረጥ ስጀምር የሱቁ ባለቤት የሆኑ ሽማግሌ ከእግር እስከራሴ ያዩኝ ጀመር ። አስተያየታቸውን ለማቀዝቀዝ «በጀልባ ስንዝ ግማሹን ልብሴን በማዕበል ስለተነጠቅሁ አንድ ሙሉ ልብስ ሊሸጡልኝ ይችላሉ? ማን ኛውም ሊሆን ይችላል» አልኳቸው ። ሽማግሌው ፒፓቸ ውን ከአፋቸው አውጥተው

«ተስቦውን ትፈራለህ?» ብለው ጠየቁኝ ።

«ተስቦውስ ይዞ ለቆኛል ፤ ግን ገና ገገምተኛ ነኝ ። ሽማግሌው የደስታ ዓይነት ሳቅ ካስካኩ በኋላ »

«አንተ የኔው ዓይነት ነህ ። እኛ ተስቦ አንፈራም ። ተስቦ ጥሩ ነው ። እንዲያውም ተስቦ እወዳለሁ ። ተስቦው የሚልክልኝን ልብስ ሁሉ እገዛለሁ ። ሳላጥብ ሳልተኩስ ሳይውል ሳያድር ይሸጥልኛል ። እግልክት ለሕዝቡ የሚል ኩትን ተስቦ የመሰለ በረከት የለም ። ሕዝቡ ሞት ያስፈ ልገዋል ። ሳይጠንዛ ከነለዛው ቢሞት ይሻለዋል ።

የሽማግሌው መንቀዥቀዥ የነበረኝን አክብሮት አቀ ዘቀዘው።አስገርሞኝ እስኪያቅለሸልሸኝ ትኩር ብዬ አየሁት ። መቃብር ቤት አንገቴ ላይ ተጣብቆ ምንጭቅ አድርጌ ከገ ደልኩት የሰባ አይጥ ያልተሻለ መስሎ ታየኝ ። በአንድ ጊዜ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠላሁት ። «ይልቅ እንድ እርጌ ልብስ ሊሸጡልኝ መቻል ያለመቻልዎን ይንገሩኝ» አልኩ፣መሰላቸትን ባዘለ ስሜት ፣ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ወደጉን ከተደራረበው አ ሮጌ ልብስ እንድመርጥ ጠቀመኝ ። ሽማግሌው ሲቆም ከሸምግልናው ብዛት እናቱን ወደመሬት የደፋ ቅርንጫ ፎቹ የመነመኑ አርጌ ዛፍ ይመስላል ።

«የራስህን ምርጫ ውሰድ» አለኝ ። ከተደረደረው ውስጥ የሚስማማኝ ጠፋ። መሳቢያ ከፍቶ ልብስ ይፈልግ ልኝ ጀመር ። ብቻውን ያነበንባል ።

«ለእንዳንተ ያለ እጥንተ ብርቱ ሽማግሌ የሚሆን ልብስ ነበረኝ ። የተስቦውን ነገርስ አለማንሣት ነው ከእን ግዲህ ። ተስቦው ትናንት ብቻ ደደብ ሥራ ሠራ። የከተማ ችንን ሀብታም ወጣትና ደፋር ጀግና ወሰደብን ። ትናንት ናውኑ ማለዳ ለክፎት ማምሻውን አባቅቶት መቃብር ቤት ከተተው ። ማርያምንም እግዚአብሔርንም ስረግምና ስሰ ድብ ዋልኩ ። እነርሱም እንደኛው ካልሰደቡዋቸው ሥራ ቸውን አያስተካክሉም ። ጌታ ፋቢዩ ሮማኒን በመውሰዳ ቸው አግልክት ተሳስተዋል» አለ ።

በዜናው ተደናገጥኩ ። እንዳይታወቅብኝ ራሴን ለመ ቆጣጠር እየሞከርኩ ፣...... ሀብታም መሞት የለበትም እንዴ፣ አልኩት ። ዐይኔን ትክ ብሎ ተመለከተ ።

«የኔፕልስ ነዋሪ አትመስለኝም ። ጌታ ፋቢዩ ሮማኒ ደግ ነበር ። የደግ መጨረሻ ቸር ለጋስ ነበር ። ደፋር ጀግ



t.me/OLDBOOKSPDF

ናም ነበር ። እኔ በደንብ አውቀዋለሁ ፤ ብዙ ጊዜ ተከትየ ዋለሁ ። ሰርጉም ላይ ተገኝቻለሁ ። ሚሽቱን ግን አልወዳ ትም ። ነጭ እባብ ናት ። እርሱና ሚሽቱ ተያይዘው በሰ ረገላ ሲሄዱ አያቸውና ማን ድል ያደርግ ይሆን እላለሁ ። ምን ይሆናል እርሱ ሞተ ፡ ሁሉን ጠቅላ እርሷ ባለድል ሆነች ። እግዜር መሳሳቱን ተረዳህ ታዲያ?....» አለኝ ።

በጥሞና አዳመጥኩትና አውቀዋለሁ ካለ አንዴት እራቱ ቆሜ አላወቀኝም የሚል ጥያቄ መጣብኝ ።

«ይኸ ጌታ ሮማኒ ምን ዓይነት ቁመና ነበረው» አልኩት ።

«ሸጋ ሰው ነበር ። የተሟላ ቁመና ፤ የሰውነቱ ቀጥታ እንዲህ እንዳተ ቁመቱም እንዳንተው ነበር ። ትከሻውና የደረቱም ስፋት ካንተ አይበልጥም ። ግን ያንተ ዐይን ጉድ ጓዱ ገብቷል ። ፊቱ የሞላ ፀጉሩም ድፍን ጥቁር ነበር ። የፀ ጉሩ ጥቁረት ካንተ ጋር ይቃረናል የርሱ ድፍን ጥቁር ያንተ በረዶ ነጭ ነው» አለኝ ።

ድንጋጤ ሁለመናዬን ወረረው ። ፈራሁ ። የአንድ ሌሊት መከራ ይህን ያህል ለውጥ አመጣብኝ እንዴ ብዬ ራሴን ተጠራጠርኩ ። ፀጉሬን ዳበስኩና ባለቤቴ ኒናስ እን ዲሁ ታጠፋኝ ይሆን የሚል ፍርሐት ወረረኝ ። ጓደኛዬ ጉዶ ዲሁ ታጠፋኝ ይሆን ... ባለቤቴ ምልክቶቼን እንዲሁ ይጠራጠር ይሆን አልኩ ። ባለቤቴ ኒና አይታኝ በመደሰት ፈንታ በሁኔታዬ ተሸብራ ትደነግጥ ይሆን? የሚል የፍርሀት ስጋት አለቀኝ አለ ። እኔ በሀሳብ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደተዋጥሁ ሽማግሌውም ጨርቁን እያገላበጠ መለፍ ለፉን ቀጠለ ።

«ዘላቂ ጥንካሬ ያለው ይመስለኝ ነበር ጌታ ሮማኒ ። ያቺ እባብ መሳይ ሚሽቱ ስትዋሸውና የመታመንን ክብር ስትነፍገው የመጨረሻ ቅጣትዋን ይሰጣታል ብዬ አስብ ነበር ።»

ስለ ኒና ምን የሚያውቀው ነገር አለና ነው እንዲህ የሚቀዣብረው ይኸ ሞት የጠላው ሽማግሌ ብዬ ሰውነቴ በንዴት ረመጥ ተቃጠለ ። ራሴን እንደ ምንም ተቆጣጠር ኩና ትንፋሼ እየጋመ ፤

«ለምንድነው የሰውየውን ባለቤት እንዲህ የጠሉዋት ፥ የበደለችዎት ነገር አለ እንዴ?»

«በትክክል ለምን እንደጠላኋት እነግርሀለሁ። አንድ ቀን በሰረገላዋ ብቻዋን ስትሄድ ፈረሶቹ ገፍትረው ረግጠው ከመሬት ደባለቁኝ ። እንደማዘን በሁኔታዬ ተንከትክታ ሳቀች ። እርሱ አብሯት ቢኖር ያዝንልኝ ነበር ። እኔ ታዲያ ሚሽት ትመስላለች ። ለዚህ ነው ነጭ እባብ ያልኋት ። የኔዋ ሚሽት እኔ ከከተማ ወጥቼ እስክመለስ ታማኝነትዋን እየዞረ ያጐረሱትን እያሞካሸ የሚኖር ጠብደል መልከ መ ልካም ጉረምሳ አቅፋ ያዝኋት ። የሚሽቴ ሴባ ሲያዮኝ ዘሎ ጉሮሮዬን አነቀኝ ። እኔ ወንድምህ አጥመለመልኩና ደረቱ ላይ ጉልበቴን አሳረፍኩ ። እርስዋ ተነስታ ስታዩኝ ዐይንዋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ፈጠ ጥርስዋ ገጠ የምትናገረውን አጥታ አቀብ አቀብ ስት
ተነፍስ ዱላ እንደሚጠብቀው ሕጻን አልፎ አልፎ ምጥ ዓይ
ነት ድምጽ ታሰማ ነበር ። የውሽማዋን ዐይን እየጠበቅሁ
«እኔ ጉዳዩ ካንተ አይደለም ፣ ጥርስዋን ባትገለፍጥልህ አት
ደፍረኝም ። ካንተ የምፈልገው እዚህ ጥቂት ቆይተህ እን
ድትታዘብ ብቻ ነው» ብዬ እጅና እግሩን ጥፍር አድርጌ እን
ዳይነቃነቅ አሰርኩት ። ከዚያ ጩቤዬን አውጥቼ የባቄላ
አበባ የሚመስለው ዐይንዋ ወደ እሳትነት እስኪለወጥ
ድረስ፣የስቃይ ጩኸትዋ እስኪዘገንነኝ ድረስ፣የሚብለጨ
ለጨውን ስለት በሰውነትዋ ውስጥ እያመላለስኩ የሕይወ
ትዋን ፍጻሜ አቃረብኩት ። ውሽማዋ በደም የተነከረ ሬ
ሳዋን እያየ ተንገፍግፎ አጓራ ። የእርስዋን ሕይወት በፈጸ
ምኩበት ጩቤ እርሱ የታሰረበትን ገመድ ቆርጨ ነጻ ለቀ
ቅሁት ።

«እሬሳዋን ውሰድ ሸልሜሀለሁ ፣ በወር ውስጥ አንተ
ንም እንዲሁ ትከዳህ ነበር» አልኩት ። እንደአበደ ሰው የሚ
ያደርገውን አጥቶ እያማጠ ሄዶ ሕግ አስከባሪዎችን ጠርቶ
ተያዝኩ ። እንዴታ፣እንደነፍሰ ገዳይ ተወንጅዬ ለፍርድ
ቀረብኩ ። ግን እኔ የፈጸምኩት ፍርድ እንጂ ወንጀል ስላ
ይደለ ደግሞም ዳኛው እንደኔው ሚሽት ስላለው በጥቂት
ቀኖች ነጻ ተለቀቅሁ ። ስለዚህ ያቺን በቪላ ሮማን የምትኖ
ረዋን ወይዘሮ የምጠላው ለዚሁ ነው።ከኔዋ ሚሽት ጋር ብዙ
ነገራቸው ይመሳሰላል ። የባልዋ መሞት እኔን ለምን እን
ደሁ አላውቅም ግን እንደእግር እሳት ይፈጀኛል ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

የሸማግሌውን ታሪክ እየዘገነነኝ ሰማሁ ። ልቤን እልር እጥንቴ ድረስ ጤነኛ ያልሆነ ስሜት ተሰማኝ ። ባለቤቴም ይሆን ምስኪን ደሀ ሰው በማስቀየምዋ ቅር አለኝ ። እርሱ ብዙ ተናግሮ እኔ ምንም ስላልተናገርኩ «ምን ታስባለህ ስለትጣቴ እምላከም ቢሆን ከዚህ የተሻለ ቅጣት አይሰጠኝም ነበር ።» አለኝ።

«ባለቤትህን መቅጣቱ ባልከፋም ነበር ፣ ነገር ግን አንተ ራስህ ወንጀል መፈጸም አልነበረብህም» አልኩት ።

«ኸኸ!!» ብሎ አንባርቆብኝ «ወንጀለኛ አልከኝ፣ እንዴት ወንጀለኛ ትለኛለህ?» አለኝ ። «ወንጀለኛዋስ እርስዋ ናት ። አስቀድማ እኔን ገደለችኝ ። እራሳዬ ውስጥ ሰይጣን ገብቶ ወንጀል አስፈጸመኝ ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ሰይጣኑ አብሮኝ ይኖራል ። ሞት እማልፈራው ተስቦ የማል ሸሸው ለዚህ ነው ። ግን በቅርብ ሰይጣኑ ትቶኝ ይሄድና አንድ ባዶ ቦታ እወሸቃለሁ፡እስከዚያ ግን በየማታው እንዳየኋት የስቃይ ድምጽዋን እንደሰማሁ እኖራለሁ» አለና እየተቻኮለ ልብሱን ይመርጥልኝ ጀመር ። ሁኔታው እየገባኝ ሄደ ። ሴቶችን ሁሉ የጠላ እድሜውን ሙሉ የተበሳጨ ሰው በመሆኑ አሳዘነኝ ።

«ልክ ለአንተ የሚገባ የዓሣ አጥማጅ ልብስ አገኘሁልህ» አለና አመጣልኝ ።

«ዓሣ አጥማጁስ ሚስቱን ገድሏል» ብዬ ጠየቅሁት ።

«የለም እርሱ ፍርድን በእጁ መውሰድ የማይፈልግ ስለነበር ራሱን ገድሎ ሚሽቱን ለዳኞች ትቶ ሞተ ››



t.me/OLDBOOKSPDF

«ልብሱን ተቀብዬ ዋጋውን አራት ፍራንክ ከፈልኩ። የመልበሻ ክፍል አሳየኝና በሩን ከውስጥ ቆልፌ መልበስ ከመጀመሬ በፊት ፊቴን በመስታወቱ ውስጥ ለማየት አን ገቴን ብቅ ከማድረጌ የገዛ ፊቴ አንጀጦር ወጋኝ ። ሽማግ ሌው እንዳለው እኔም በሰላሣ ዓመቴ ሽማግሌ ሆኛለሁ ። የሃያ ዓመት ስቃይ እንኳ እንዲህ ሊያደርግ አይችልም ፤ ሕመሙ ፊቴን መጦታል ። ዐይኖቼ ጉድጓዳቸው ውስጥ ሸሽተው ገብተዋል ። ፀጉሬ በሙሉ ሸብቷል ። የወይን ሻጩ የደነገጠበት ምክንያት ገባኝ ። ለእኔው ራሴ እንኳን እኔ ራሴ መሆኔ አጠራጠረኝ ። ባለቤቴና ጓደኛዬ እንዴት ሊያውቁኝ እንደሚችሉ ግራ ገባኝ ። ራሴን በራሴ ሚስኪን አልኩና እንባ ከዐይኔ ሳላስበው ዠርግፍ አለ ።

ራሴን በራሴ ማጽናናት ጀመርኩ ። አይዞህ ፋቢዩ አል ኩት ራሴን ። ሚስትህ ለጊዜው በሁኔታህ መለዋወጥ ብት ደነግጥም የደረሰብህን ስቃይ በማገናዘብ ትረዳዋለች ። ወዲያው ፍቅርዋን ደጋግማ ስትሰጥህ የአንድ ቀን መከራ እየተከፈለ ፀጉርህንም ዐይንህንና ፊትህንም እንደጥንቱ መል ሶ ያስተካክለዋል አልኩ ። ተጣጥቤ የአሣ አጥማጁን ልብስ ለበስኩ ። ከመቃብር ቤት ያመጣሁትን የወርቅ መሀለቅ አዲሱ ልብሴ ኪስ ከተትኩ ። ሽበቴን በዓሣ አጥማጁ ቆብ ደብቄ ክፍሉን ከፍቼ ለሽማግሌው ታየሁት ። ከድንጋጤው ብዛት የያዘውን እቃ ጥሎ ፤ «እረ በእመቤቴ ማርያም! በወ ጣትነት ዘመንህ እንዴት ጉበዝና ያማረብህ ሰው ነበርክ?» ብሎ ፍጥጥ ብሎ አየኝ ። «የለም አንተ ሰው ጠንካራ ነህ ፤ አሁንም ተፈለግህ ጠላትህን መግደል ትችላለህ» አለኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ኪሴ የተረፉ ሶስት ፍራንኮች አውጥቼ እግር ሹራብ ይፈልጉልኝ ፣ ብዬ ያወለቅሁትን ልብስ በነጻ ወረወርኩለ ትና እየመረቀኝ እግር ሹራቡን አውጥቶ ሰጥቶኝ ተላበ በስኩ ።

በኔፕልስ ከተማ ያልታየ አዲስ አለባበስና አዲስ ሰው መስዬ ቆምኩ ። ለመውጣት ከተዘጋጀሁ በኋላ አንድ ሀሳብ መጣብኝ ። ሁኔታዬ እንዲህ ተለዋውጦ ድንገት ኒና ብታ የኝ አይጠና ሆድዋ ስለሆነች በድንጋጤ ጉዳት ያገኛታል ብዬ መሸትሸት ሲል መሄድን መረጥኩ ። ጊቢዩም ስደርስ በዋናው በር አልገባም ። በጀርባ ነብቼ ከአሽከሮቼ ለአንዱ አስረድቼ ኒናን ቀስ ብለው ነግረው ስለ ሁኔታዬ አለማም ደው ብንገናኝ ይሻላል ብዬ ከራሴ ጋር ተወያየሁ ። ስላምታ ሰጥቼ ልወጣ ስል ሽማግሌው መጥቶ ክንዴን ያዝ ሲያ ደርገኝ ሊናገር የፈለገው ነገር መኖሩ ገባኝ ።

«ራቅ ያለ መንገድ ነው የምትሂደው?» ብሎ ጠየቀኝ ። በአወንታ ራሴን አወዛወዝኩ ። «ለማንም አልነግር ፣ ሚስጢሩ አብሮኝ ይሞታል ፣ ሴትጋ ነው በሞቴ የ ምትሔደው?» ይህን ሲጠይቀኝ ጓጉንቸር የመሰለ ተን ኮል ፈላጊ ዐይኑ መልሴን ለመረዳት ይቅበዘበዝ ጀመር ።

«አወን ሴትጋ ነው የምሄደው ።»

እንደገና ክንዴን ጨበጥ ጨበጥ አደረገና «ክንድህ



t.me/OLDBOOKSPDF

ገና እንደብረት የጠነከረ ነው ። ሂድና ግደላት ፣ ታማኝነ ትን ከነፈገችህ ግደላት» አለኝ ። እየሸኘኝ በራፉ ላይ ቆሞ እንደሰይጣን ጥፍራም ጣቱን እየነቀነቀ «እንደ መከርኩህ አድርግ» አለኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አምስት

ቀኑ በጣም ረዘመብኝ ። ጊዜ ለመግደል በከተማው ስወጣና ስወርድ እምብዛም የማውቃቸውን አላየሁም ። በተለይ ከበርቴዎች ኮሌራውን ፈርተው ነው መሰል በመንገድ ላይ አላየኋቸውም ። በየሄድኩበት መአዘን ጥቂት ሰዎች አስከሬን ይዘው ቀብር ሲሄዱ ማየትን ተላመድኩ ። የሬሣ ሣጥንም ውድ ስለሆነ ትልቁን አስከሬን በትንሽ ሳጥን ለማብቃቃት ቀባሪዎች የሙታን አጥንት እየሰበሩ ጉልበት አጥፈው ሳጥን ሲከቱ ማየት ታከተኝ ። በሽተኛው ገና ሰልም ከማለቱ ለቀብር ሲያዘጋጁት ደግሞ አይቼ የኔ ጉድ እንዳይደርስ «መሞቱን አስቀድማችሁ አረጋግጡ ።» ብዬ ስጮህ የሟቹን ጭንቅላት እንደተድበለበለ ድንጋይ ከግራ ወደቀኝ እያጋጩ «ይኸ ህይወት ካለው እኔ አንገቴን እሰጣለሁ » ብለው ከፋኞች ዐይናቸውን አፈጠጡብኝ።ያን ቦታ ጥዬ ወረድ ስል እንዲት ወፍራም ሴት ሬሳ ከሚሰበሰቡት ጋር ትጣባለች ። «እንዲት ደቂቃ ስጡንና መሞት መኖርዋን እንለይ» ትላቸዋለች ። በርዋ ጠጋ ብዬ ስመለከት አልጋ ላይ እንዲት እንቅልፍ ያሸለባት የምትመስል እንቡጥ ሴት ልጅ ፀጉርዋን በትና ተኝታለች ። የፊትዋ ወዝገና አልተከተተም ። ከጉንዋ አንድ ሰው ደረትዋን ጥርቅም አድርጎ ፀጉርዋን ተላብሶ ሙቀት የማይሰጠውን ገላዋን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሞጭሎጮ ተኝቷል ። ነፍስዋ ከወጣ ጀምሮ ሙሉ ሌሊት ቀኑን ጨምሮ ላይዋ ደርቆ መዋሉንም ሴትዮዋ በሩን እየጠበቀች በጆሮዬ ነገረችኝ ። በሩን በርግጄ ራሴን ስቼ ጠባብዋ ክፍል ስገባ እንባ አንቆኛል የሞት እልህ ተናንቆኛል ። እንደምንም አለስልሼ ፣ «ሰውዬ ፣ በን ውነተኛ ፍቅር እኮ ሞት የለም» አልኩት ። ከሙታን መሀል የማይሞት ፍቅር አይቼ እንባዬ በዩን ስፉ በአራት መአዘን ፈሰሰ ። «ፍቅርህ እውነተኛ ከሆነ ዘለዓለማዊነትን ስጠው» ብዬ ስጮህ ምስኪኑ ፍቅረኛ እጁን ሰብስቦ በተስፋ መቁረጥ እያለቀሰ ቀና ብሎ አየኝ ። የቀዘቀዘ እጇን ደግፌ ከአልጋ ላይ ወረደ ። ሲትዮዋን ጠርቼ እሬሳዋን መከፈን ጀመረች ። ከዚህ ቤት እንደወጣሁ ትዝ ያለኝ የራሴ ሬሳ የወጣበትን ሻይ ቤት እንደገና መጎብኘት ስለነበር በብዙ ችግር ፈልጌ አገኘሁት ። የሻይ ቤቱ ባለቤት ብርጭቆውን እንደወትሮው እየወለወለ ፣ «እህ አቶ አሣ አጥማጅ ሥራው የተቃና ነበር?» ብሎ አናገረኝ ።

ለአፍታ ተምታታብኝ ። ወዲያው ሁሉን ነገር አስታወስኩና በፈገግታ አወንታዬን ከገለጽኩለት በኋላ «እርስዎስ እንደምን ነዎት ፣ ኮሌራውስ?» አልኩት ።

«የኮሌራው ነገር አይነሣ» አለኝ። ራሱን እየነቀነቀ «ሕዝቡ እንደዝንብ እየረገፈ ነው ። የትናንትናውንማ ቅዱስ ዮሴፍ አይመልሱት።»

«ምነው ምን ተፈጠረ ትናንት ? እኔ እኮ ገና መግባቴ ስለሆነ የከተማውን ዜና አልሰማሁም» ።


t.me/OLDBOOKSPDF

እየተጠራጠረና በሀሳቡ እየተጨነቀ ፣ «የትናንቱን ጉድ እንዴት አልሰማህም? የባለፀጋውን ጌታ ሮማኒን በኩ ሌራ አሟሟት አልሰማህም?»

አለማወቄን ጭንቅላቴን እወዛውዤ ገለጽኩለት ።

«ምን ያደርጋል ወንድሜ ፤ እንደ ንጉሥ ይከበር የነ በረው ባለፀጋ ጌታ ሮማኒ ዛሬ የለም ። ትናንትና የአጥቢያ ችን ትልቁ መነኩሴ ገጉትተው እዚሁ ቤት አምጥተው እግ ርህ አጠገብ ያለው ቦታ አስተኝተውት ነበር ። አንሱኝ መልሱኝ ሳይል ፣ ሀጥያቱንም ሀብቱንም ሳይናዘዝ በአንድ ቀን ጀምበር በተስቦው ተለክፎ ሞተ ። ጥቂት ከተከዘ በኋላ «ምን ይኸ ብቻ መሰልዎት ጉዱ ። እኒያ ቅዱስ መነ ኩሴ እስከመጨረሻው ሳይለዩ አስከሬኑን ሲከፍኑ በሽታው ያዛቸውና ዛሬ ጠዋት እርሳቸውም እንደሱው አፈር ቀመሱ»

በሀዘንና በድንጋጤ የቀረበልኝን ቡና እየመረረኝ ቀመ ስኩ ። ሀዘኔ ግን እንዳይታወቅ ተረጋግቼ ማድመጥ ጀመ ርኩ ።

«መነኩሴው የራሳቸውን የደረት መስቀል ደረቱ ላይ አድርገውለት አባቶቹ መቃብር አስተኙት ፣ ሰዓቱንና የሲ ጃራ መያዣውን ለባለቤቱ ሰጥተው መርዶውንም አርድ ተው በበሽታው በስለው ተመለሱ ።

ኒናዩ ትገዘ አለችኝና ጥያቄዬ ከአፌ አምልጦ ወጣ ። «የሟቹ ባለቤት ሀዘንዋን እንዴት ቻለችው፣መቼም አብዳ ይሆናል?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሴቶች እንኳ በሁሉ ነገር ያብዳሉ ፣ እንኳን ለባል
ሞት ለበግና ፍየል ሞት ያብዳሉ ፣ ብቻ ቂሉ ተይዘው ስለ
ነበር ይኸን ሁሉ አልተናገሩም ።»
ይሀን ስንነጋገር በበሩ አንድ ሰው በዝግታ እርምጃ
አለፈ ። ጓደኛዬ ጉዶ ፈራሪን መሰለኝ ። ዘልዬ ልጠመጠም
በት ከጀልኩ ። የሆነ ነገር መለሰኝና በዐይኔ ተከተልኩት ።
ፒፓውን ያጨሳል ፣ ከፊቱ ፈገግታ ይታያል ። እኔው ቅጽር
ግቢ የሚበቅል የጽጌረዳ አበባ ኮሌታው ላይ ሰክቷል ።
ስሜቴ ሁሉ በአንድ ጊዜ አመድ ትቢያ ነከሰ ። ያየሁትን
ማመን አቃተኝ ። የመጨረሻው ውድ ጓደኛው ገና ትናንት
ትና ሞቶ የእርሱ ገጽታ ግብዣ ቤት የሚሄድ ደስተኛ ይመ
ስላል ፣ እንዴት ሊሆን ይችላል? ከንዴቴ ብዛት ሳቄ መጣ ።
ሌላም ሀሳብ በተቃራኒው መጣብኝ ። እኔ ጓደኛው የሞት
ኩት ገና ትናንት ነው ። የሀዘን ሥርዓት የሚጠይቀውን
ገና ላያሰባስል ይችላል ። ጽጌረዳውም ቢሆን ልጁ ስቴላ
አድርጋለት እርስዋን ለማስደሰት ኮሊታው ላይ ትቶት
ይሆናል ። ብቻ ለሁሉም ማምሻዬን ቤቴ ስገባ እረዳለሁ
ብዬ ልከተለው የነበርኩትን ትቼ ሂሣቤን ከፍዬ በሌላ
አቅጣጫ መንገዴን ቀጠልኩ ።

ሞትን አሸንፎ ወደፍቅርና ደስታ የሚመለስ ድል አድ
ራጊ የሚሄደውን እርምጃ እየተራመድኩ ምሽትን እጠባበቅ
ጀመር።ትእግስቴ ሲያልቅ ጀንበርዋ ጠለቀች።በጣም የተጠበ
ቀው ምሽት መጣ።ንፋሱ ቀዝቀዝ ብርሀኑም ደብዘዝ አለ።ወደ
ቪላ ሮማኒ የሚወስደውን ዋና መንገድ ይዤ ሳዘግም ፀሐይዋ
ትታው ያለፈችውን አድማስ ጨረቃዋ ዝግ እያለች ተረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከበች ። የልቤ ትርታ እየጨመረ ጉልበቴ በደስታ ብዛት መደንቃቀፍ ጀመረ ። መንገዱ ግን ያለወትሮው ረዘመ ብኝ ። መድረስ አይቀር በመጨረሻው ዋና በር ደረስኩ ። የግቢዬ በር ግጥም ብሎ ተቸንክሮአል ። የቤቴ ጠረን አወ ደኝ። ፈገግታዬ ሁሉ ተመለሰ።የሁኔታዬ መለዋወጥ ዋናውን በር እስከፍቶ የሚያስገባ ስላልሆነ በብርቱካን አጸድ አድ ርጌ ለመግባት ወደ ጓሮ ዘወር አልኩ ። የጓሮውን በር ወት ሮውንም በልዩ ልዩ ዛፎች ቅጠል የተሸፈነ ስለሆነ እወደ ዋለሁ ። እንግዳም ሆነ የቤት ሰው ይህን በር ስለማይጠቀም በት አብዛኛውን ጊዜ ብቻዬን መሆን ስፈልግ የምዝናናው በዛፎቹ ስር ነው ። በሩን አልፌ ግቢዬ ውስጥ መሄድ ጀመ ርኩ ። የዋናው ቤት ጀርባ ስለሆነ እንጋፋዋ ምግዚት ታጋ ጥመኝ ይሆናል ብዬ ጠበቅሁ ። ናፍቆት ፣ በመላው ሰው ነቴ የናፍቆት ትኩሳት ነዘረኝ ። ኗናዬን አሁን አግኝቼ እቅፍ አድርጌ በሀዘን የነደደ ፊትዋን እፈውሳለሁ ። ጓደኛ ዬን እጨብጠዋለሁ ፣ ልጄ ግን በአሁኑ ሰዓት እንቅልፍ ወስዷታል ። የናፍቆት ስእል በዐይኔ ላይ ይኾጉደጉዳል ። እፀዱን አቋርጬ ወደ ዋናው ቤት ልጠጋ ስል ጆሮዬን የሆነ ድምጽ ድንገት ወጋው ። እእምሮዬን የወጋው የባለቤቴ ድምጽ መሰለኝና የቆምኩበትን ቦታ እስክስት ድረስ ደነ ገጥኩ ። ደስ ሲላት እንደሀጸን ስትፈነድቅ ሳቅዋን ተከትሎ የሚወጣውን የደስታ ድምጽዋን ሰማሁ ። ሁለንተናዬ ቀዝ ቃዛ ጉድጓድ ውስጥ የተዘፈቀ ቁርበት መሰለኝ ። ባለማመን እቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ ። ጭንቅላቴ የጥያቄዎች መፈል ፈያ ሆነ ። ይግባኝ በሌለው ሞት ተለይቻት እንዴት እንዲህ በደስታ ሳቀች? በዛፎቹ ውስጥ ዐይኔ ነጭ ሀር የለበሰች

t.me/OLDBOOKSPDF

የቤት ቅርጽ ያየ መሰለኝ ። ደስተኛው ሳቅ እንደገና ተንከ ትክቶ ድምጿ እንደ ሾተል ጆሮዬን እየነደለ አእምሮዬን ደምበደም አደረገው ። አለ ጥርጥር በመሞቴ ተደስታለች ። ሚሽቴ ያልጠበቅኋትን ሆናለች ። አፈር በቀመስኩ ማግስት ክፍልዋ ውስጥ ተዘግታ ፊትዋን በእንባ እያጠበች ማዘን ይገባት ነበር ። ተደነጋገረብኝ ። ያሰብኳትን አልሆነችም ።

እንደገና ሌላ ሀሳብ መጥቶ ልቤን አንሰፈሰፈው ። ባለ ቤቷ ከሀዘን ብዛት አእምሮዋን ስታ ይሆን ብዬ ራሴን ጠየ ቅሁ ። እንደሀምሌት እጮኛ በእብደት መንፈስ ቅጠል ለቅ ጠል መባከን ጀምራ ይሆን ? እንደ ጻረሞት በዛፍ ቅርንጫፍ ተከልዬ ሁኔታውን ለማረጋገጥ አጎበደድኩ ። ወንድና ሴት ናቸው ። ጓደኛዬ ጉዱና ባለቤቴ ናቸው ። ምን አለበት ታዲያ ጓደኛዬ ሀዘን የበዛበት ባለቤቴን ማጽናናት ይገባ ዋል ። ግን......ግን ይኸ ብቻ አይደለም ። ሚሽቴ ጓደኛዬ ላይ እንደመደገፍ ሳይሆን......ወይኔ ምነው እንደሞትኩ በቀ ረሁ ። ምነው መቃብሬን ባልከፈትኩት ። የመቃብር ውስጥ ስቃይ ከዚህ በምን ይብሳል ። የገደለኝን ለመግደል ፣ የከ ዳኝን በሞት ለመቅጣት እጆቼ ወደብረት ስለት ተለውጠው ቅጣት ለመስጠት ተዘጋጁ ፣ ራሴን ለመቆጣጠር ሰውነቴን ለማቅዝቀዝ የዝሆን ጉልበት አስፈለገኝ ። ራሴን ለማስ ታገስ የነከስኩት ጥርሴ ደም አግቶ እርጥብ ስጋ አፌን ሞላው ። እግሬን መቆጣጠር አቅቶኝ በኔና በነርሱ መሀል ባለው አምስት እርምጃ ርቀት ብቻ ተለያየን ። በእጁ ወገ ብዋን በአፉ ከንፈርዋን በእግሩ ዳሌዋን ተዋሰቦአል ። ነጭ በነጭ ለብሳለች ። በቀይ ጽጌረዳ ፀጉርዋን አስጊጣለች ።


t.me/OLDBOOKSPDF

በቀይ ጽጌረዳ ፋንታ ቀይ ደም በእናትዋ ማፍሰስ ይገባል ። ፊትዋ የሀዘን ምልክት ጨርሶ የለበትም ። ፍቅርን ብቻ ያመነጫል ። ያ ከገነት በራፍ እንደሚፈልቅ ምንጭ ይጣፍጠኝ የነበር ድምጽዋ በሰራ አካላቴ እንደመርዝ ተሰራጨ ። በስፊው ስታነበንብ ሰማኋት ። የሚባባሉት አንድ በአንድ አንጎሌን እያነደደ አዳመጥኩ ።

«አንተ ተላላ ጉዶ ፣ ለመሆኑ ፋቢዮ ባይሞት ምን ይውጥህ ነበር ፣ አንድ ቀን ነገሩ ቢታወቅስ?»

«በብልሐትሽ እንዳመሉ ትይዢዋለሽ ፣ እስከመቼም የሚታወቅ አይመስለኝም ።»

«ብቻ እንኳን ሞተ ! አረፍኩ ። ከእንግዲህ ግን እንደ ፈለግነው ልትጎበኘኝ አይገባም ። አሽከር ገረዱ ያወራል ። ቢያንስ ከድስት ወር አዝኜ መታየት አለብኝ ።»

«ግን እንዳትዘነጊ ። ፋቢዮ መሞቱ ጉዳትም አለው ። ለሁለታችንም የገንዘብ ምንጫችን ነበር ።» እንደቆመች በኔው ፊት ከደረዘን ጊዜ በላይ ሳማት ። በቀጠሮ ደሙን ለማፍሰስ ወደኋላ እንደሚሄድ ነብር ድምጼን አጥፍቼ ማፈግፈግ ጀመርኩ ።

የእግሬ ኮሽታ ይሁን ሌላ ኒናን ጥርጣሬ አሳደረባትና ፣

«እሽሽ ዝም በል ። እርሱ የሞተው ገና ትናንት ነው ። ጻረሞት የራሱን ግቢ ይጎበኛታል ይባላል እኮ፡፡እንዲያውም በሕይወት ዘመኑ ይህን ቦታ ይወደው ነበር ። እዚህ በመምጣታችን አጥፍተናል ።» እንደመጸጸት እያለች


t.me/OLDBOOKSPDF

«ምንም ቢሆን የልጄ አባት እኮ ነው ።»

«ባልሽ መሆኑን መቼ አጣሁት ፤ በሳመሽ ቁጥር ቅናት ያቃጥለኝ ነበር ።»

ከእናት ልጅ የምቀርበው ጓደኛዬ መቃብሩን በገዛ እጁ ሲቆፍር ቆሜ አደመጥኩ ። ባል ሚሽቱን ሲስም ውሽማ የሚቀናበት ጊዜ መጣ? ትከሻው ላይ በተበተነው ፀጉርዋ እየተጫወተ «ለምንድነው ለመሆኑ ፋቢዩን ያገባሽው?» አላት ።

«የገዳም ኑሮ አሰልችቶኝ ነው ። ከዚህም በላይ እርሱ ሀብታም ነበር ። ደሀ መሆንን እንደሞት እጠላለሁ ። በዚህ ላይ ደግሞ አፈቀረኝ ።» በኩራት ወደሰማይ አንጋጣ «አወን በፍቅሬ አብዶ ነበር ።»

«አንቺስ አላፈቀርሽውም እንዴ?»

«ለአንድ ሁለት ሳምንት አፍቅሬው ነበር መሰለኝ ። ከዚያም ወዲያ ጋብቻ ሆነ ። ሀብትም ክብርም እድልም ሰጠኝ ።»

«ጋብቻሽ ከኔ ጋር ቢሆን ኖሮ ግን ምንም የምታገኚው ነገር የለም ማለት ነው?»

«አንተን በፍቅረኝነት መያዙ በቂ ነው ። ከዚህ በላይ ሌላውን እርግጠኛ አይደለሁም ። አሁን ግን ነጻ ነኝ ። ነጻ ነቴን ማስከበር አለብኝ ። የፈለግሁትን ማድረግ እችላለሁ ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

ንግግርዋን አላስጨረሳትም ። የንዴትም የፍላጐትም ግፊት ይዞት ጎትቶ ደረቱ ስር ጨመቃት ።

«ኒና ልታምኚኝ አትሞክሪ ። የሰርግሽ እለት በፍቅርሽ ተንደፍኩ ። መልአክ እንዳልሆንሽ ስለማውቅ ጊዜዬን ጠበቅሁ ። ባገባሽ በሶስተኛ ወር የፍቅር ምኞቴን ነገርኩሽ ። ከዚያ በኋላ በነገርም በምልክትም ፈቃድሽን ገለጽሽልኝ ። ፋቢዮ ባልሽ የሆነውን ያህል እኔም የባልሽ ያህል ነበርኩ ። በሀጥያቴ አልጸጸትም ። ፋቢዮ አምኖኝ ከአንቺ ጋር ሲለቀኝ አይገባም ነበር ። በገዛ እጁ ለሀጥያት ዳረገኝ ። ስለዚህ በምንም ምክንያት ከእጄ ልትወጪ አትችይም ።»

ኒና በአነጋገሩ ተቆጥታ ከእቅፉ ለመውጣት ታገለች ። «ልቀቀኝ! ትዳፈራለህ ፣ በጣም አሳመምከኝ» ለቋት ለአፍታ ብቻዋን ፅጥ ብላ ቆም እንዳለች እንደገና ይዞ ጨመጨማት ።

«ይቅርታ አድርጊልኝ ላስቆጣሽ አልነበረም ። ውበትሽ ነው እንዲህ የሚያደርገኝ ። ፈጣሪ ወይም ሰይጣን ውበትሽን እንዲህ አስተካክሎ የፈጠረው ተሳስቷል ። የልቤ ልብ የነፍሴ ነፍስ ነሽ ።»

ካለብዙ ትግል ተጠጋችው ። ከንፈር ለከንፈር ተጋጠሙ ። እነርሱ በተሳሳሙ ቁጥር እኔንም አዲስ ሾተል አእምሮዬን ወጋው ። ሀሳቤንም እነርሱንም ማዳመጡ ግራእጋባኝና ፈዝዤ ሳለሁ «ስለዚህ ፍቅሬን አትጠራጠሪ ። ጊዜ እንዲህ በግላጭ እጋጥሞን የፍቅር በረከቴን ገሸሽ አታድርጊ። የጀመርንበትን ጊዜ ታስታውሻለሽ? ፋቢዮ የፕሌቶ መጽ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሐቶ ላይ ተደፍቶ እኛ ዜማ እየተለዋወጥን ስንዘፍን «ከሁሉ ፍቅር በላይ ያንቺ ፍቅር ይበልጥብኛል ያልኩሽ ትዝ ይል ሻል?» አላት ።

ተያይዘው መራመድ ሲጀምሩ ባካሄዳቸው ሕሊናቸው ንጹህ ይመስላል ። ከዐይኔ እስኪሰወሩ ተመለከትኳቸው ። ጨረቃዋ የደም ብርሀንዋን አለበሰችኝ ። መሬቱን በረገጥኩት ቁጥር የከዳኝ ይመስለኛል ። ምድርም ሰማይም የሰይጣን ሥራና መጫወቻ ሆኖ ታየኝ ። በዓለም ላይ የምወዳት ፣ ሕይወቴን የምሰጣት አንዲት ሴት ታማኝ ልትሆንልኝ የማትችልበት ምድር ምን ዓይነት የሰይጣን ሥራ ናት? ይህች አንድ ሕይወቴ ፣ የልጇ እናት ፣ በክብር ፈንታ ውርደት የመረጠች ምን መደረግ አለባት? ይኸስ ምንም ነገር ያልነፈገሁት የእንጀት ጓደኛዬ ምን ቅጣት ይገባዋል?

«ሂድና ግደላት» ያለኝ የሽማግሌው ድምጽ በጆሮዬ አስተጋባ ።

«ሽማግሌው ወንድ ነው።ከመቅጽበት ተበቀለ ። ግን ስለታም ብቀል ምንድነው አልኩ ። ረጅም ስቃይ የሚሰጥ በቀል መምረጥ አለብኝ ። በደም ፍላት ገድዬ ወንጀለኛ ተብዬ መጠቆም የለብኝም ።» ጊቢዬ ውስጥ አረፍ አልኩ ። አፌ ደም እንደጐረሰ ነው ። ከንፈሬ ከትኩሳቴ ብዛት ተሰነጣጥቋል ። መመለስ የማይገባኝ ግቢዬ ተመልሻለሁ ። ጸረሞቴ ግን አይደለሁም ። ለበቀል የተላኩ መሆኔ ገባኝ ። የነበረኝ ሀብት አብሮኝ ባይኖርም በመቃብር ቤቴ ያለው የሸፍታው ሀብት ከበርቴ ሊያደርገኝ ይችላል ። ገንዘብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደግሞ ሊሰራ የማይችለው ስለሌለ የበቀል ዓላማዬን አሳ
ካበታለሁ ። ፍጹም ተወዳዳሪ የሌለው በቀል መጠንሰስ
አለብኝ።ክርስቶስ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ያለው በሴት ፍቅር
ባለመጠመዱ ነው ። እኔ ግን ሬትና ማር ቀምሻለሁ ። በቀ
ሌን ለኔ እንደሚጥመኝ እደግሳለሁ ። በቃ ወሰንኩ ። ትን
ፋሹ ቀለል አለኝ ። የሶስት ዓመት ተበዳይ ቂሜን የምወ
ጣው ረዘም ብሎ በተሰካ ሳንጃ ነው ። መነኩሴው እሬሳዬ
ላይ ትተውልኝ ያገኘሁትን መስቀል አውጥቼ ፡ ስሜ ቃል
ገባሁ ። የቂም በቀል እርምጃዬን እስከፈጽም ባልተኛ
በአምላክ ስም ቃል ገባሁ ። ጨረቃና ከዋክብት ለቃል
ኪዳኔ ምስክሬ ሆነው ከተቀመጥኩበት ተነሰቼ በገባሁበት
የጓሮ በር ወጣሁና ዋናውን መንገድ ተያያዝኩ ። ኔፕልስ
ያደግሁበት ከተማ ገብቼ እንደባይተዋር በሆቴል የመኝታ
ክፍል ይዤ አደርኩ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ስድስት

ሰማይና ምድር ወገግ ሲል ማልጄ ተነሳሁ ። ሌሊቱን ያውጠነጠንኩት የበቀል እቅዴ ተስተካክሎ በአእምሮዬ ቅርጽ አውጥቷል ። አሁን የቀረኝ በሥራ መተርጐም ብቻ ስለሆነ ድብቅ ዓላማዬን አንድ ብዬ ለመጀመር ባትሪ ፣ መዶሻና ሚስማር ይዤ ከተመልካች ሁሉ ተደብቄ ወደመቃብር ቤቴ ጉዞ ጀመርኩ ። እንደደረስኩ መቃብር ቤቱ አካባቢ ብቻዬን መሆኔን እየተገላመጥኩ አረጋግጬ በዚያው የሚስጢር መግቢያ ገብቼ የሀብቱን ሳጥን ከፈትኩ ። ሳላምታታ የወረቀቱን ገንዘብ በመልክ በመልኩ እየለያየሁ በኪሴ ከተትኩ ። ከብርቅ ሀብቱ በያዝኩት ከረጢት አጭቄ ባለ ብዙ ሺ ፍራንክ ሆኜ የሀብቱን ሳጥን በያዝኩት መሣሪያ ዘግቼ በገባሁበት ቀዳዳ ተመልሼ ወጣሁ ።

ተቻኩዬ ስለነበር አንዲት ደቂቃም በዋዛ ሳላሳልፍ ከኔፕልስ የሚያወጣኝ ጀልባ ፍለጋ ያን ዕለቱን ወደብ ወረድኩ ። ጥቂት ሰዎችን ስጠያይቅ አንዲት ወደ ፓሌርሞ የምታመራ ጀልባ መኖርዋን ሰምቼ የጀልባዋን ካፒቴን አስፈልጌ አናገርኩ ። ከብዙ ማጠያየቅ በኋላ የፊቱ ቆዳ በፀሐይ ንዳድ የጠየመ ዐይኖቹ ለማሳሳቅ የሚንቀዠቀዡ ካፒቴን አገኘሁ ። ካፒቴኑ የጠየቀኝን ዋጋ ከፍዬ በጀልባ ውስጥ ቦታዬን ያዝኩ ። ያስከፈለኝን ገንዘብ በኋላ ሳሰላ ከመደበኛው



t.me/OLDBOOKSPDF

እጥፍ ድርብ ሆኖ አገኘሁት ። ወደ ፓሌርሞ መሄዱ ግን ለጉዳዩ ተስማሚ ስለነበር አልተቃወምሁም ።

ጉዞው እንደዋዛ ተጀመረ ። ጀልባዋ የሜዲተራኒያንን ባሕር ቀዳ ስታልፍ ከባህሩ ጋር በሚስጢር የምታንሾካሹክ ትመስላለች ። ብቻዬን ከበስተኋላ በኩል የጀልባዋን ጠርዝ ተደግፌ ስንዝ በውሀ ውስጥ የሚሽቱ ፀጉር እየሰረገ ጀልባዋ እየከፈለች ከምታዋኸቀው ባህር ውስጥ የሕይወቴ ደሊላ እጆችዋን ቀልፋ በሞት ፈገግታ እየሳቀች ታየችኝ ። ያለፈው ሌሊት ከውሽማዋ እቅፍ ውስጥ ሆና እየሳቀች ካየሁት ተወዳዳሪ የሌለው ውበትዋ ባሕሩ የሳላት ለስሜቴ ተስማሚ ሆኖ አገኘሁት ። ትናንት ማምሻውን ያየሁት ውበትዋ በሕይወቴ ዘመን ከኔ ጋር ከነበረው ውበትዋ በልጦ አነደደኝ ፤ ሳላስበው አንድ ሰው ትከሻዬን ነክቶ ከቀትር ሕልሜ አነቃኝና ዞር ስል የጀልባዋ ካፒቴን ነው ።

«ጌታዬ ሲጃራ ያጨሳሉ?» ብሎ ጋበዘኝና አመስግኜ ተቀበልኩ፤

«ለምን ጌታዬ ይሉኛል፣እኔ የጥቃቅን ቃርሚያ ዓሣ አጥማጅ ነኝ ።» አልኩት ።

«እንዳሉ» ብሎ ሲጃራውን እየለኮሰ ጥርጣሬውን መደበቅ አልቻለም

«ምነው ተጠራጠሩ» አልኩት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«የእጅዎ ልስላሴና ልብስዎ የሚናገሩት ለየቅሉ ነው።»

«እና ታዲያስ?»

«ለማለት ያህል ነው ። ከኔ ጋር እስካሉ ድረስ ከማን ኛውም ነገር ነጻነትዎ የተጠበቀ ነው ። ሁኔታዎ ይነበበ ኛል ። ሕይወት የሚያመጣው ብዙ ሀዘን አለ ፤ የፍቅር ሀዘን አለ ፤ ጥል አለ ፡ በቀል ፤ የገንዘብ ጥፋት ብዙ ችግሮች ሰውን ከቦታ ቦታ ያሳድዱታል ። አሁን ግን ከኔ ጋር ሆነው አይጠራጠሩ ።»

አይጠራጠሩ ባለኝ ቁጥር እጠረጥረው ጀመር ። ቀረብ ካለ ፖሊስ ጣቢያ ነግሮ ዓላማዬን ሳልፈጽም ቢያስናክለ ኝስ የሚል ሀሳብ መጣብኝ ። ሲጃራውን እያጣጣምን ማጨስ ጀመርን ።

«ግሩም ሲጃራ ነው ፤ አይደል?» አለ ።

«በጣም ግሩም ነው» አልኩት ።

«ምርጥ ሲጃራ የሚያጨስ ሰው ነው የሰጠኝ ። ካር ሜሎ ኔሪ እውነተኛ ጌታ ነው ።»

ካርሜሎ ኔሪ ሲል ድንጋጤዬን መከላከል አልቻል ኩም ። ሀብቱን አባቶቼ መቃብር ቤት ደብቆ አሁን ደግሞ የርሱን ሲጃራ እያጨስኩ እንድጓዝ የሚያደርገኝን አጋ ጣሚ ተጠራጠርኩ ።

«ካርሜሎ ኔሪን ያውቁታል» አልኩት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«ማወቅ ብቻ ነው ፣ ራሴን ከማውቀው በላይ አውቀ ዋለሁ ። ችግር ሲገጥመው ፣ ፖሊስ ሲከታተለው ነፍሱን ከነሀብቱ የማድንለት እኔ ነኝ ። አንድ ቀን ቴሬማን ይዞ ሕይ ወቴን ሙሉ አይቼው የማላውቀውን ወርቅ አስታቅፎኝ የምፈልገው ቦታ ታደርሰኛለህ ወይም ጉሮሮህን እሰነጥቅ ሀለሁ ብሎ አስፈራራኝ ፣ ጉሮሮዬም አይሰነጠቅ እናን ተም ከመንገዳችሁ አትቀሩ አልኩት ። ቴሬሣ ትከሻዬን እየመታታች ብልህ ሰው ነህ አለችኝና ወሰድኳቸው ።»

‹‹ ቴሬሣ ደግሞ ማናት፣ አልኩት ።

«ቴሬሣ የቆንጆዎች ቆንጆ ናት ። ካርሜሎ ከሌላ ሴባ የቀማት ሚሽቱ ናት ።»

«ታማኝነትዋን በምን ተማምኖ ነው ታዲያ ይዟት የሚዞረው፣»

«መታመን የማትችል ሴት ሞት ይገባታል» አለኝ ።

ብዙም ሳንጫዋወት ተጠርቶ ጀልባዋ ምድር ቤት ወረደ ።

ብቻዬን መቀመጡን እየወደድኩት ነው። አእምሮዬ ግን ዞር ዞሮ በቀል ከማውጠንጠን አይቦዝንም ። «ሂድና ግደላት» ባለኝ ምክር ላይ ይኸ ለገንዘብ ነፍሱን የሚሸጥ መርከበኛ እንኳ መታመን የሌላት ሴት ሞት ይገባታል ያለኝ ጆሮዬ ውስጥ ወዲያው ይደውል ጀመር ። ነፍሰ ገዳይ ሽፍታ አምና ፍቅርዋን ለመስጠት በአደጋ ውስጥ የምትኀዝ ቴሬ ሣንና የፀዳ የጋብቻ ኑሮ የሰጠኋትን የኔዋን ሚሽትኒናን ማወ ዳደር አስቸገረኝ ። ቴሬሣ ሽፍታው ነፍሰ ገዳይ ባልዋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊሞት የወንጀሉ ተባባሪ ተብላ መወንጀልዋን ታውቃ ለች ። የኔዋ ግን ብትታመን ንጹህ ክብረን ብቻ ነበር የም ትወርሰው ።

በዚህ ዙሪያ የተጠማጠመ ሀሳብ መሀል የልጄ ትንሽ ራቷ መጥቶ ተደቀነና ፅንባዬ ሳላስበው መከራ የጠበሰውን ፊቴን እጭርጦ ወረደ ። ንፁህ ዐይንዋ ትንሽ አፍዋ ትዝታዬን አሸበሩት እርስዋን ምን ሳድርጋት? ሳላስበው ቃሉ አፌን አምልጦ ወጣ የበቀል እቅዴ ከተፈፀመ በኋላ ወደ አንድ የኑሮ ሁኔታ የሌለው ቦታ ወስጃት ሕይወቴን በሙሉ እርስዋን ሰው ለማድረግ ሕይወቴን በሙሉ እሰጥ ይሆን ?

አዝናለሁ እርስዋም ሴት ናት ፣ ያውም ቆንጆ ሴት ። ከተመረዘ ዛፍ የተገኘች አበባ ናት ። ማን ያውቃል አብሯት አድጐ ለዐቅመ ሄዋን ስትደርስ የሚወጣ መርዛም ትል ከውብ ትዋ ጋር ብቅ ይል ይሆናል ።

ቀኑን ሙሉ ብቸኛ ሆኜ ተጓዝኩ ። ንፋሱም ባህሩም በሳማዊ ሆኖ ተቀባበለን ። እልፎ እልፎ ካፒቴኑ ብቅ እያለ ያነጋግረኛል ። የቀን ብርሀን ለጨረቃና ከዋክብት ቦታውን ትቶ ሲያልፍ የኔም የደስታ ቀን እልፎ የጭለማ ሕይወቴ መቀጠሉ ታወሰኝ ። ጥርጣሬ ያከሳውን ፊቴን ጭለማ ውስጥ መደበቅ ወደድኩ ።

ከእንግዲህ የምውለውም የማድረውም የተቀደደውን የክብሬን ሰንደቅ ለመስፋት ሆነ ። ለዚህ ሥራዬ ምንም አይነት ምድራዊ ሕግ እንደማያግደኝ ልበሙሉ ሆንኩ ። ለተበደልኩት በደል አንጀቴን የሚያረካ በቀል ለማዘጋጀት ሕግም ፍርድም ራሴ ነኝ አልኩ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ሴቱን ስንቀዝፍ አድረን በነገታው ፖሴርሞ ገብተን አደርን ። ጀልባው መሬት ሲወጋ ፖሊሶች ወረቀት አሳይ ተው ካርሜሎ ኔራ ጀልባ ውስጥ ተደብቆ እንደሁ ለመፈተሽ ገቡ ። ጨሉሌው ካፒቴን በቃላት አጣጥቦአቸው ባዶ እጃ ቸውን ተመለሱ ። ካሰብኩት ደርሼ አመስግኜ ከመለየቴ በፊት ፣ «ውለታህ ብዙ ነው ፣ አመሰግናለሁ ድንገት እር ዳታዬን ከፈለግህ ኔፕልስ እንፈላለግ» አልኩት ።

«ስምዎን ታዲያ ለምን ነፈጉኝ?» አለኝ። አዲስ ስም የማውጣቱን አስፈላጊነት አስቤበት ስለነበር በውሀ ዋና የሞት የልጅነት ጓደኛዬን ስም ለመስጠት ወሰንኩ ።
«ጌታ ሲዛር አሊቫ» ብለህ ጠይቀኝ አልኩት ።

«እኔም አውቄአለሁ ። እጆ የጌታ እጅ እንጂ የዓሣ አጥ ማጅ እጅ አይመስልም ።» ብሎ በአዋቂነቱ የነቢይ ስሜት ተሰማው ።

ጊዜ ሳላጠፋ ከጀልባዋ ወርጄ ፖሴርሞ መሀል ከተማ ገባሁ ። ጥሩ ጥሩ ልብስ ከሚሰፋበት ትልቅ መደብር ጥልቅ ብዬ ባለቤቱን በርከት ያለ ልዩ ልዩ ዘመናዊ ልብስ እንዲ ሰፋልኝ ጠየቅሁት ። ዓሣ አጥማጆችን ለማስደሰት እንር ሱኑ መስዩ በግብገሮቸው ላይ ተገኝቼ መመለሴ ነው አል ኩት ። ጌታ ሲዛር አሊቫ እባላለሁ ስለው ትእዛዙን ሁሉ አምኖ ተቀበለ ። በከተማው ውስጥ ትልቅ የሚባለውን ሆቴል ስምና አድራሻ ጠየቅሁት ። ለጊዜው ለኔ የሚመጥን ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ዘመናዊ ልብስ ጓዳው ገብቼ እንድ ለውጥ አመጣልኝ ። ምርጥ የሆቴል ክፍል ይዤ የበቀል


t.me/OLDBOOKSPDF

እቅዴን ባሰባሰል ስምንት ቀን ተቀመጥኩ ። ይገዜ የምዞ ረውን ከባድ ገንዘብ በአዲሱ ስሜ ለባንክ ባስረከብ እኔን ቴን ማረጋገጫ ሰነድ የባንኩ ባለቤት እንዳይጠይቀኝ አንድ ትልቅ የአልማዝ ስጦታ ሰጥቼ አፉን አዘጋሁት ። ከዚህ ቀጥሎ ያደረግሁት ጥንቃቄ በድምጽ ፣ በመልክ ሆነ በቁመት ከጌታ ሮማኒ ጋር ሰዎች እንዳያመሳስሉኝ አዲስ ያለባበስ ያነጋገርና ያካሄድ ፈሊጥ መልመድ ነው ። እኔን ቴን በተቻለ መጠን ለመደበቅ ሪዝ ማሳደግ ጀመርኩ ። ሰፊ የፀሐይ መነጽር አደረግሁ ። ዐይኖቼ በሳምንት ምቾ ትና በቂ እንቅልፍ በማግኘቴ ከጉድጓዳቸው መውጣት ስለጀመሩ ማንነቴን የሚያሳጣው ጥቁር መነጽር በደንብ ሸፈነልኝ ። ድምጼን ለመለወጥ ግን አስቸገረኝ ። ስናገር ካለመጠን የሚንቀሳቀሰውን እጄን ረጋ አድርጌ አዲሱን ስሜን ለመምሰል ልምምድ አደረግሁ ። ከኔው ጋር ከሚ ኖር የእንግሊዝ ዜጋ ፎርም መቅዳት ጀመርኩ ።

ቀጥዬ ያደረግሁት ራሴን በጌታ አሊቫ ስም ከኔፕልስ ከተማ ሕዝብ ጋር ማስተዋወቅ ነው ። ስሜ ጌታ ሲዛር አሊቫ መሆኑን ፣ ወደ ትውልድ ሀገሬም ከብዙ ዓመት ስደት በኋላ ባለ ብዙ ሀብት ሆኜ መመለሴንና የተቀረውን ሕይ ወቴን በኔፕልስ ለማሳለፍ መወሰኔን በደብዳቤ ዓምድ እንዲያ ወጣልኝ ከሃምሣ ፍራንክ ጋር ለአንድ የኔፕልስ ከተማ ጋዜጣ አዘጋጅ ላኩኝ ። የላኩት ደብዳቤ በጋዜጣ ወጥቶ ስለነበር በሳምንቱ ከጋዜጣው ተቆርጦ ከብዙ ምሥጋና ጋር ተላከ ልኝ ። የኢጣሊያ ጋዜጠኞች በትንሽ ጉቦ ንጉሥ በሉኝ


t.me/OLDBOOKSPDF

እንኳ ቢሉዋቸው ከማለት የማይመለሱ መሆናቸውን አረጋገጥኩ ።

በዚሁ ከተማ ውስጥ ጥቂት ቀናት እንደቆየሁ ካርሜሎ ኔሪ የተባለው ሽፍታና ነፍሰ ገዳይ ተይዞ በአደባባይ ታየ ። ፍቅረኛው ቴሬዛ ሌላ ሰው አይነካኝም ብላ በገዛ እጅዋ ሕይወትዋን ማሳለፍዋን ሌባው ራሱ ሲናገር ተሰማ ። ከተከታዮቹ ሶስቱ ተይዘው የተቀሩት በየጐረቤት ሀገሩ ተበትነዋል ። ስለ ካርሜሎ ኔሪ መጨረሻ ማወቅ ለኔ በቀል ዘለቄታ ማረጋገጫ ስለነበር የጠባቂዎቹን መሪ ሄጂ ጠየቅሁ ።

«የካርሜሎ መጨረሻ ስቅላት ነው» አለኝ ጠባቂው ።

አመስግኘው ተመለስኩ ። አያቶቼ መቃብር ቤት የደበቀው ሀብቱ ካለ ጥርጥር የኔ መሆኑን አረጋገጥኩ ። የማንኛውም የካርሜሎ ተከታይ ኔፕልስ ሙታን ሰፈር ሄዶ ሀብቱን የማይነካ መሆኑ እርግጠኛ ሆኖ ታየኝ ። ችግር ሁሉ ቀሎ ታየኝ ። መንገዴ ያለ እንቅፋት ወለል ብሎ ቀረበልኝ ። እግዜር እንኳ ከኔ ጋር የቆመ መሰለኝ ። ከሁሉ በላይ ያስደነቀኝ ይህን ትልቅ በወንጀል የተሰበሰበ ሀብት እኔ ደግሞ ለወንጀል መቅጫ ለማድረግ መዘጋጀቴ ገረመኝ ። የሀብቱ ሰብሳቢ ካርሜሎ ኔሪ የተፈጸመብኝን በደል ሰምቶ ገንዘቡን ለዚህ ቂም መበቀያ ማዋሌን ቢሰማ ምን ያህል ይደሰት እንደነበር ታየኝ ። የካርሜሎን ሞት ስሰማ አያቶቼ መቃብር ቤት የደበቀው ሀብቱ የራሴ የግሌ ሀብቴ መሆኑን አረጋገጥኩ ። ለበቀል እቅዴ የሚያስፈልገኝ ገንዘብ ነጻ በመውጣቱ እንቅፋት ሁሉ ተወገደልኝ ። ስለ ቴሬዛ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውብት በመርከበኛው የተነገረኝ ሁሉ እንደሥዕል እየታ የኝ በገዛ እጅዋ በሰነዘረችው ስለት እየደማች እንደአሞራ ከሚናጠቅዋት ፍቅረኞችዋ ሁሉ ነጻ መውጣትዋ ገረመኝ ። ከውርደት ሞት የሚመርጡ ለዓላማቸው መስዋእት ለመ ሆን የተዘጋጁ መኖራቸው ከመጠን በላይ አስደነቀኝ ። በተለይ ምርጥ ምግብ በጉሮሮአቸው ካልወረደ ፣ ነጭ ሀር ለመልበስ እድል ካላጋጠማቸው ቤቶች መሀል እንዲህ ያለችው መገኘትዋ ገረመኝ ። የእንጀራ ጠርዝ ቆረጠኝ የምትለዋ ደልቃቃዋማ የተሰበረ ፍቅርዋንና ቃልኪዳንዋን የምትጠግነው በስለት ሳይሆን በሌሎች አዳዲስ ፍቅረኞች ነው ።

ከቤቴ በወጣሁ በሦሩ ኔፕልስ ተመልሼ ገባሁ ። እየሩ ቀዝቀዝ ብሎአል ። የኮሌራው መቅሰፍት ቀንሶ ሕይወት እንደገና መለምለም ጀምሮአል ። ንግድ እንደወትሮው ማሯሯጡን ቀጥሎአል ። ታም የተነሳ እግዜርን ረሳ እንዲሉ የነዋሪው ህዝብ አሸሸ ገዳሜና አስረሽ ምቺው ታይቶ የማይ ታወቅ ይመስላል ። ከተማ ስገባ እኩለ ቀን ነበር ። የበቀል ግብሬን ለመወጣት እቅዴን በብልሀት መመስረት ስለነበ ረብኝ ይህንን እቅዴን ለማሳካት እንዲያመቸኝ እጅግ በጣም ምርጥ በሆነው ሆቴል ክፍል ያዝኩ ። ሀብት ከብረቴን በሰፊው የሚገልጽ ዝግጅት ማደራጀት ጀመርኩ ። በኔፕ ልስ የመጨረሻውን ጥሩ ሆቴል ተነጋግሬ ከያዝኩ በኋላ ሰረገላና ፈረሰኛ አስፈለገሁ ። ቀስ በቀስ በገንዘብ ችሮታዬ ቦዮች እኔን ብቻ ለማገልገል ይሽቀዳደሙ ጀመር ። በኔፕ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሎስ በመጀመሪያው ምሽቱ የመጀመሪያውን የበቀል ሥራዬን ለመጀመር እርምጃ ወሰድኩ ።

እጅግ በጣም ደስ የሚል ምሽት ነበር ። የባህሩ ንፋስ ጥሩ ትዝታ ያመጣል ። ሰማዩ ጠርቶ ከዋክብት ከቦታቸው ቀረብ ያሉ ይመስላል ። ራት ከበላሁ በኋላ ፋቢዮ ሮማኒ በነበርኩበት እድሜዬ ወደምሄድበት ታላቁ ቡና ቤት አመራሁ ። ጉዶ ፌራሪ ከዚህ ቡና ቤት እንደማይጠፋ ስለማውቅ ግራና ቀኙን በዐይኔ እያጠናሁ ከቡና ቤቱ በረንዳ ደረስኩ ። መቀመጫ በብዛት ወጥቶ ሰው የማታውን አየር ከመጠጥ ጋር ይጐነጫል ። አልተሳሳትኩም ፤ የምፈልገው የጥንት ጓደኛዬ የዛሬው ባላጋራዬ እግሩን አንፈራጦ የፓሪስን ጉረምሳ መስሎ ፒፓውን እያጨሰ ሲዝናና አየሁት ። ለማስመሰል ጉዶ ሙሉ ጥቁር ለብሶአል ። ጥቁር በዚያ መልኩ ላይ አሳምሮታል ። ፒፓውን ባንከላወሰ ቁጥር ጣቱ ላይ ያደረገው ዶሊች አልማዝ ይፍለቀለቃል ። ገና ከሩቅ ሆኜ ነው የእጅ አልማዜን በጣቱ ላይ ያወቅሁት ። አጠገቡ ካለው ባዶ መቀመጫ ሄጄ ተቀመጥኩ ። ጋዜጣውን ዘርግቶ አጥርቶ ካየኝ በኋላ ከሸበተ ሽማግሌ ጋር ጉዳይ ስለሌለው ፒፓውን እንደልቡ ማጨስ ቀጠለ ። እኔም እንደርሱው ሲጋራ አውጥቼ ቡና አዘዝኩ ። ለቦዩ የተለመደውን ቸርነቴን ከዘረጋሁ በኋላ ጠረጴዛዬ በጥንቃቄ ተወለወለ ። ጋዜጣው ተሰብስቦ ጥግ ተቀመጠ ።

ቦዩን ጠቀስኩና አዲስ በተለማመድኩት አነጋገር የጌታ ፋቢዮ ሮማኒን ጊቢ ያውቅ እንደሁ ጠየቅሁት ። ይህን ስጠይቅ ፌራሪ የቆነጠጡት ያህል ደነገጠ ። ቦዩ በፋ


t.me/OLDBOOKSPDF

ቢዮ ሞት ሐዘኑን አውጥቶ ሲነግረኝ እኔ ካለመጠን ደነገ ጥኩ ።

«አይደረግም በወጣቅነት እድሜ ተቀሰፈ!» ብዬ ተማ ረርኩ ። ጥቂት ከተከዝኩ በኋላ ፣

«አዝናለሁ ፣ የአባቱ ጓደኛ ነበርኩ ምን ያደርጋል አላገጣጠመንም ፣ ብዙ ዘግይቼ መጣሁ ። ገና ህጻን ሳለ ነበር ያየሁት ። ለመሆኑ ቤተሰብና ልጅ አለው ሀዘኔን የምገልጽ በት?»

«አዎን ባለቤቱ በሮማኒ ግቢ ይኖራሉ ። አሁን ግን በሀዘኑ ምክንያት ማንንም አይቀበሉም ይባላል ። አንዲት ሴት ልጅም አለቻቸው ። የጌታ ሮማኒ ባለቤት በውበታቸው በጣም የተደነቁ ቆንጆ ናቸው ።» ብሎ ቦዩ ሲቀጥል ሲል ፈራራ ወደእኔ ዘወር ብሎ ፣
«ይቅርታ ጌታዬ ስለጌታ ሮማኒ በኔፐልስ ካለው ሰው በላይ እኔ ስለማውቅ ጥያቄዎን በደንብ ልመልስልዎ እችላ ለሁ ።» ብሎ በአክብሮት አንገቱን ዝቅ አደረገ ።

አዲሱ ስሜ የታተመበትን ካርድ አውጥቼ ሰጠሁት ። በጋዜጣ ስሜንና ዝናዬን ማንበቡን ከገለጸ በኋላ በማንኛ ውም በኩል አገልግሎቱን ሊሰጥ ቃል ገብቶ የመታወቂያ ካርዱን አውጥቶ እጄን ለመጨበጥ እጁን ዘረጋልኝ ። ለዚያ ሁሉ ወሮታዬ ጥላቻ ከመለሰልኝ ከሀዲ ጋር መጨ ባበጡ የሲኦል ያህል ከበደኝ ። ግን በትንሽ ስህተት እቅዶ ሁሉ ከሚበላሽ የኢዮብን ትእግስት ልዋስ ብዬ ከነጓንቲዬ ጨበጥኩት ። ተደሰተ ። መጠጥ አዞ ጽዋውን አነሳልኝ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሠዓሊነቱ ፣ ስለደህንነቱ እየነገረኝ የወርቅ የሲጋራ መያዣዉን ከኪሱ አውጥቶ ጋበዘኝና የገዛ ፊርማዉን እያነበብኩ አንዲት ሲጋራ አውጥቼ አቀጣጠልኩ ።

ስለካውንት ሮማኒ ባለቤት ውበት ጠየቅሁትና «ሚን ደርሰዋ ያለች ውብ ሴት በኔፕልስ ታይታ አትታወቅም ፣ የምታስገኝ ቆንጆ ናት» አለኝ ።

«እንደውነቱ ከሆነ ለፋቢዮ ሮማኒ የምትገባ ሴት አይደለችም» አለና እንደገና የውስጥ እሳቱን ቀሰቀሰብኝ ።

«እኔ ልጅ ሆኖ ብቻ ስለማውቀው የቅርብ ሁኔታውን አላውቅም ። በልጅነቱ ግን አንባቢ ተመራማሪና ሰውን የሚያምን ነበር» አልኩት ።

«አዎን የሞራል ሰው ነው ፣ ሞራል በሌለው ሀገር የሞራል ሰው መሆን ጅልነት ነው» አለኝ ።

የሞራል ሰው ያለመውደዱን አድንቄ ዋንጫዬን እያነሳሁለት« ከአንተ ጋር ጓደኝነትን በእርግጥ እመርጣለሁ» አልኩት ።

ካውንት ሮማኒ እንዴት እንደ ሞተ ተረከልኝ ። ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የጂል አሟሟት እንደሞተ አድርጐ ተረከልኝ ።

የካውንቱን ልጅ ሁኔታ ጠየቅሁት ። እንደአባትዋ አይነት ጂል ናት አለኝ ። ልጂ በአንድ ወር ዕድሜ ከቤቱ እንድም የሚወዳት ሊገኝ ያለመቻሉን ከእነጋገሩ ተረድቼ የእልሀና የተበፋ መቁረጥ ላብ በጀርባዬ ከለል ብሎ ወረደ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

የቀብር ሥነሥርዓቱ እንዴት እንደነበር ጠየቅሁት ።

«እኔ ራሴ ቀብሩ ላይ ተገኝቼ ነበር»

«አንተም! አንተም በቀብሩ ላይ ተገኘህ?» ብዬ ጥን ቃቄዬ ሁሉ ከዳኝ ።

«እኔ እኮ ከወንድም የቀረብኩ ጓደኛው ነበርኩ ። እን ዴት ቀብሩ ላይ መገኘት የለብኝም?»

«ይቅርታ አድርግልኝ ፤ እኔ ተስቦ ስለምፈራ አንተም ይህንኑ አስበህ እንደሁ ብዬ ነው ።»

«የለም ተስቦ እንኳ እንደማያስጋኝ በልጅነቴ የማው ቀው ነገር አለ ።»

«ምን ዓይነት ነገር?»

«በተስቦ እንደማልሞት ተረጋግጦልኛል ። እኔን የሚ ያስጋኝ የቅርብ ወይም ከወንድም የቀረበ ጓደኛ ሕይወቱን እንደሚያጠፋ ነበር ። ከወንድም የቀረበው ጓደኛዬ አሁን ሞቶአል።ከእንግዲህ የሚያስጋኝ ነገር ያለ አይመስለኝም።»

ተደላድዬ ሲጃራውን እያጨስኩ ተቀመጥኩ ። እር ሱም እንዲሁ ተደላድሎ በመተማመን እግሩን አነባብሮ ተቀመጠ ።

አንድ ቦታ ብዙ ስለተቀመጥን በእግራችን እየተንሸ ራሸርን አየር እንድንቀበል ሀሳብ አቀረብኩና ቡና ቤቱን ትተን ወጣን ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«እና ጓደኛህን ታፈቅረው ነበር ማለት ነው?»

«ማፍቀር እንኳን አይደለም ስዕሎቼን ይገዛኝ ስለ ነበር እወደው ነበር ። መውደድም ቢሆን ከልቤ የነበረው ሚስት እስካገባ ድረስ ነበር ።»

«ሚስቲቱ በመሀላችሁ ገባች መሰለኝ ።»

ወጂያው እርእስቱን ለመለወጥ ተቻኮለ ። አካሂዴን እድሜ እንዳስቸገረው ሽማግሌ እግሬን ጐተት አደረግ ሁና« ብርሃን ሲበዛብኝ እንደምታየው የዐይኔ ሕመም ይነ ሳብኛል »ካልኩት በኋላ«አንድ ቀን እንግዲህ ስዕሎችህን ታስጐበኘኛለህ ።»

በጣም ተደስቶ እንድጐበኘው ጋበዘኝ ። ምናልባትም በስዕሎቹ ደስ የሚለኝ ቢኖር በስጦታ መልክ እንደሚያበ ረክትልኝ ገለጸልኝ ። በስድስት ወር ውስጥ ሙያውን እስከ ጭራሹ ለመተው እንዳቀደ ሲጠቅስልኝ ፣

«አሄ የሆነ ሀብት አገኘህ መሰል?»

«ሀብት እንኳን አይደለም ፣ ሀብት ያላትን ላገባ አቅ ጃለሁ ።»

ስድስት ወር የሀዘን መፈጸሚያ አጭሩ ጊዜ ነው ። ከስድስት ወር በኋላ ሚሹቴን ሊያገባ ነው ። ስድስት ወር ድረስ ስንት ነገር እንደሚፈጸም ሳይገባው መቅረቱ ገረ መኝ ። ጉሮሮውን አንቄ እዚያው ልጨርሰው ከጀልኩ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ጣቶቼ በእልህ ተቆለፉ ። ስሜቴን የሚያረሳሳ ጥያቄ አመ ጣብኝ ።

«ጌታዬ ብዙ ሀገር የመጐብኘት እድል አጋጥሞታል ፣ ለመሆኑ የመጨረሻዋን ቆንጆ ያገኙት በየትኛው ሀገር ነው?»አለኝ ።

«እኔ ሕይወቴን ያሳለፍኩት ቆንጆ ሴት በመምረጥ ሳይሆን ሀብት በማግበስበስ ነው ። ሀብት ቆንጆ ሴት ጭምር ይገዛል የሚል ፈሊጥ ስለነበረኝ ልቤ ወደሴት መስመሩን ሳይለውጥ እርጅናው መጣ» አልኩት ።

ከት ብሎ ከሳቀ በኋላ «ፋቢዮ ሮማኒም ከማግባቱ በፊት እንዲሁ የሚለው ነገር ነበረው » አለ ።

«ለመሆኑ የፋቢዮ ባለቤት ቆንጆ ናት?» ብዬ ጠየቅሁት ።

«ቆንጆ? የቆንጆ ቆንጆ ናት እንጂ ፣ ብቻ የሟች ባልዋ አባት ጓደኛ ስለሆኑ አንድ ቀን ሊጐበኝዋት ይገባል ። እኔ አስተዋውቃችኋለሁ ።»

«ለምን ? አሳፈላጊ አይደለም ፣ በሀዘን የተጨበጠች ሴት ለሌላ ሰው ደንታ የላትም ።»እነጋገሬ እንደተዋጣ ልኝ ገባኝ ። ቸልተኛ በሆንኩ መጠን ፌራሪ እኔን ለማስተ ዋወቅ ቋመጠ ። የገዛ ሚሽቴን ለማስተዋወቅ መነሳሳቱ ግን ውስጥ ውስጡን አንገበገበኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ያውም በአክብሮት ነው የምትቀበልዎት ። በሀዘን የምትጨበጥበት ምክንያት ደግሞ ምንም የለም ። በአፍላ ወጣት እድሜዋ ላይ ናት ፣ በዚህ ላይ ደግሞ ፋቢዮን የም ትወደው ሰው አልነበረም ። የመጽሐፍ ሰው እንጂ ፍቅርን የሚለግስ ሰው አልነበረም ። ከዚህ በላይ ደግሞ አባትዋ ለሀብት ሲሉ አጋብዋት እንጂ እርስዋ ወዳው አልተጋቡም።»

ሆቴል ደረስን ። ክፍሌ ውስጥ ምርጥ ቪኖ ጋበዝኩት ። ክፍሌ ውስጥ ባለው ዕቃ ፣ በጋበዝኩት ቪኖ ውድነት ተገ ረመ ።

ሀብቴን አይቶ «ቀናሁብዎት» አለኝ ። «ልትቀናብኝ አይገባም» አልኩት ። «አንተ ወጣት ነህ ፍቅር እጣ ፈን ታህ ናት ። እኔ ግን የድሎትና የቅንጦት እንስሳ ብቻ ነኝ » አልኩት ።

ትኩር ብሎ ከተመለከተኝ በኋላ «ጌታዬ በልጅነቶ በጣም መልከ ቀና እንደነበሩ ሁኔታዎ ይናገራል» አለኝ ።

አንገቴን ዝቅ አድርጌ ለአስተያየቱ ካመሰገንሁ በኋላ «ለወንድ እንኳ በመጀመሪያ ደረጃ አስፈላጊው ጉልበቱ ነው ፣ ከዚያ መልከ ቀናነቱ ሁለተኛ ደረጃ ነው ፤ ይመስገ ነው ጉልበት ዛሬም አለኝ» አልኩት ።

«አጋጣሚነቱ ይገርሞት ይሆናል ፤ አንዳንድ ሁኔታ ዎና ለዛዎ ያንን ሟች ጓደኛዬን ፋቢዮ ሮማኒን ይመስላል ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር ለማደናገር ወይን ጠጁን ሞላሁለት ። የመጨረሻውን ጠጥቶ ፣ «ይቅርታ ያድርጉልኝና አሁን ልሂድ ። እንግዲህ ለሮማኒ ባለቤት የሚልኩት ሰላምታ ካለ በዚህ ምሽት የማገኛት ስለሆነ ለመላክ ቸል እንዳይሉ ።»

«የምልከው ሰላምታ እንኳ የለኝም ። አየህ ቆንጆ ሴቶች የሀቅ ሚዛን ስለሚጎድላቸው ላናግራቸው አልወድም ። ብቻ እንግዲህ ልቸገር ካልክ ሟች ባለቤትዋ ባለውለታዬ ስለሆነ በዋጋ ለመተመን የሚያስቸግር የእንቁ ስጦታ አዘጋጅቻለሁ ። ፋቢዮ ሮማኒ በሕይወት ቢኖር ለእርሱ ነበር የምሰጠው ፣ ዞሮ ዞሮ የእርስዋው ስለሆነ ይህንኑ ብታስረዳልኝ እወዳለሁ ።»

«በደስታ እታዘዛለሁ ።» በአክብሮት ከመቀመጫው ተነስቶ ለመሄድም እየተዘጋጀ ፣ «እንዲያውም እንዲህ ላለው የታላቅ ሽልማት መልእክተኛ መሆን የሚመረጥ ነው ። ሴቶች ብርቅና ድንቅ ጌጥ ይወዳሉ ። ደግሞ አይፈረድባቸውም ። የሚያማምር ዓይንና የአልማዝ እንክብል ይፈሊጋል ። አሁን ሊሂድ ፣ ከእንግዲህ ብዙ ጊዜ እንገናኛለን» ብሎ ሊጨብጠኝ እጁን ዘረጋ ፣

«እንዴታ! መገናኘታችን አያጠራጥርም» ብዬ የተዘረጋ እጁን ጨበጥኩትና ከክፍሌ እየተቻኮለ ወጣ ። የሆቴሉን ደረጃ ወርዶ የአትክልቱን መስክ አልፎ ዋናውን መንገድ ሲያያዝ በመስኮት ይታየኛል ። ትኩር ብዬ ሳየው እስኪያቅለሸልሸኝ ድረስ ጠላሁት ። ትክልክል ብሎ



t.me/OLDBOOKSPDF

የተሰራው ቁመናውን ሁሉ አጥንቴ ድረስ እስኪነዝረኝ ረገ ምኩት ። አካሄዱ ግን አስገረመኝ ። ነገ ተነገወዲያ የሚጠብ ቀውን ባለማወቅ ፅድሉ የደስታ ፈረስ ያስጋለበችው ይመስል አካሄዱ የልቡን ደስታ ይገልጽ ነበር ። ባረማመዱ ከስድ ስቱ ወር የጓደኛ ሞት ሀዘን በኋላ መጪው ዘመን ለርሱ የዘንባባ አክሊሉን ይዞ የሚጠብቀው ይመስል ነበር ። እንደ ጊዜ ብቻ እንደመቆም አለና ወደክፍሉ ዞር በማለት እያመነታ ባርኔጣውን ብድግ ፊቱን እንደማራገብ አድርጎ መንገዱን ቀጠለ ። ጨረቃዋ የቁመናውን ግርማ ሙልጭ አድርጋ እስከታሳይ ድረስ ከጠራው ሰማይ ጋር የተዋጣለት ስዓሊ ሥራ ይመስል ነበር ። የአደን አውሬን በመነጽር እንደ ሚያይ አዳኝ እኔ ስለቱን እያደራጀሁ አየሁት ። አሁን ፍጹም ወጥመዴ ውስጥ ገብቷል ። ነፍሱን በማይምረው አጥፊው እጅ ገብቷል ። እንድምረው የሚያደርገኝ አን ድም የፀፀት ንስሀ የመግባት ፍንጭ ስላልሰጠኝ ቅጣቱን ያለ ይቅርታ ደገስኩለት ። በሁለቱም ከሀዲዎቼ መሀል የሚ ሽቴ ሀጥያት ማመዘኑን ግን አልተጠራጠርኩም ። ራስዋን ለማስከበር የቅንጣት ያህል ፍላጐት ቢኖራት ኖሮ ፣ የዓለም ፈተና ቢፈታተናት እንኳ ማለፍዋ አይቀርም ነበር ። ስለ ዚህ በሁለቱም ላይ የበቀል ስለቴ የሚያርፍ መሆኑን አረ ጋገጥኩ ። ይህን ሁሉ እያሰብኩ በመስኮት ከዐይኔ ርቆ እስ ኪሄድ ድረስ አየሁት ። ወዴት እንደሚሄድ አውቃለሁ ። የባል ሀዘን ያደቀቃት አልቃሽ ለማጽናናት ነዋ! የበቀል ጅምሬ በእንዲህ ዓይነት ተከናወነና መስኮቱን ጥዬ አረ ፍት ወሰድኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ በሆነ ማግስት ፌራሪ ከቁርስ ኀበታ ሳልነሳ ተመ ልሶ መጣ ። የሮማኒ ባለቤት ስጦታውን ከመቀበልዋ በፊት የባለቤትዋ እንግዳና ወዳጅ በመሆኔ በእስቸኳይ ተቀብላ ልታነጋግረኝ መፈለግዋን ነገረኝና እንዲቀመጥ ጋበ ዝኩት «እህ ትናንትና ማታ እንዳልከው አገኘሀትን» አልኩት ።

«አዎ ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው ። መልእክትዎን ሰጠኋት ። በጣም ተደስታለች ። ብቻ ስጦታውን ከመቀበ ልዋ በፊት እንዲያነጋግርዋት አበክራ ጠይቃለች ። በሀዘ ንዋ ምክንያት እንግዶችን እንደልብዋ ለመቀበል ባት ችልም የባለቤትዋን ወላጆች ወዳጅ ለመቀበል ትፈልጋ ለች ።»

በአክብሮት አንገቴን ዝቅ አድርጌ «በእውነት ከሚገ ባኝ በላይ ነው ወይዘሮዋ የምታከብረኝ ። እንዲህ የሚያንጓ ግብዣ እምብዛም ደርሶኝ አያውቅም ። ግን አዝናለሁ ግብ ዣውን ለመቀበል ያዳግተኛል ። በተለይ በቅርብ ጉብኝቱን ለመፈጸም አይመቸኝም ። እባክህ አስተዛዝነህ አለመቻ ሌን ንገርልኝ ።»

በጣም ተደንቆ ግራ የተጋባ መሰለ ። «እውነት ከእ ንጀትዎ ነው? ግብዣዋን አይቀበሉም?»

«በእውነት ነው የምልህ፤እኔ ምንም ያህል ቢዋቡ የቆ ንጆ ሴቶችን ፈቃድ የምከታተልበት ጊዜ የለኝም ። በኔፕ ልስ የሚያስቸኩሉኝ ብዙ ጉዳዮች አሉኝ ። ይህ ከተጠናቀቀ ከዚያ ወዲያ ምናልባት ለእንዲህ ያለው ጉዳይ ጊዜ ሊኖረኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይችላል ። ግን አትጠራጠረኝ ወዳጄ ፤ እመቤቲቱን እጅ የምነሳበት ጊዜ ወደፊት አላጣም ።» እኔ ለጊዜው ቤት ወይዘሮ ለማነጋገር እቅዱም ሆነ ጊዜው ስለሌለኝ ይቅርታ እንድታደርግልኝ በተገቢው ምርጥ ቃል እንዲገልጽልኝ ጠይቄ እንደገና አስደነቅሁት ።

ከት ብሎ ከሳቀ በኋላ «በእውነትም የሚያስደንቁ ሰው ነዎት ። የቤት ጥላቻዎ ከፍተኛ መሆን አለበት ።»

«ጥላቻ ማፍቀርን ተከትሎ የሚመጣ ነው ። እኔ ቤትን አፍቅሬም ጠልቼም አላውቅ ። በኔ አስተያየት የሚጠሉበት አይታየኝም ። ጥላቻ ከማፍቀር ይጠነክራል ። የኔ ስሜት ቤቶችን በሚመለከት ለፍቅሩም ሆነ ለጥላቻው ግድ የለሽነት ነው ።»

በሀሳቤ ያለመስማማቱ ግንባሩ ላይ እየተነበበ «ምንም ቢሆን በጊዜዎ ቤት አፍቅረዋል ። የቤት ፍቅር እንደ ፀሐይ ጨረር ነው ። በወቅቱ ለፍቅሩ ጨረር መጋለጥ በግድ ያስፈልጋል ።»

«አፍቅሬስ ነበር ።» አልኩት ። «ብቻ የኔ ፍቅረኛ ሳልጠግባት የቅድስናን ሕይወት መርጣ ምናኔ ገባች ።»

«በራስዎ ጥፋት ነው ። ሳይጠግብዎት እንዴት ለቀቅዎት?»

«ይልቅ ስላንተ ስዕል እንጫወት ዛሬ ልጐበኝልህ ብችል ከዘጠኝ እስከ አሥር ጊዜ ነበረኝ ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

ፊቱ በደስታ ፈክቶ «ዝግጁ ነኝ ። ብቻ ዛሬ ዛሬ ስዕሌ እጅግም የሚያመረቃ ስላልሆነ ክብርዎን የሚመጥን ላይ ሆን ይችላል ።»

«ግዴለም የወዳጄን የእጅ ሥራ ማየት ደስታ ይሰጠኛል ።» አልኩት ። ከገበታ ላይ ብድግ ብዬ «ለፋቢዮ ባለ ቤት የተዘጋጀውን የአልማዝ ስጦታ ማየት ትፈልግ እንደሁ...»

ጥግ የተቀመጠውን ሳጥን ከፍቼ ለእንቁ ማስቀመጫ ፓሌርሞ ያሠራሁትን የእንጨት ሙዳይ ከፍቼ የአንገት ፣ የጆሮርና የእጅ አልማዝ አውጥቼ አሳየሁት ። አፉን ከፍቶ ራሱን መቆጣጠር እስኪያቅተው አደነቀ ። እያንዳንዱ አልማዝ በመልክ በመልኩ ያስደረግሁት ፖሌርሞ ሆኜ ነው ። እጁ ላይ ካደረግሁለት በኋላ «ስለኔ ሆነህ ለማዳም ሮማኒ ስጥልኝ» አልኩት ።

ካመነታ በኋላ «ግን ሊጐበኘዎት ይገባል ። ምስጋናውን እንድትገልጽልዎ እድል ይስጥዎት ። ያለዚያ ይህን የሚያህል ስጦታ ተቀብላ ዝም ማለቱ ያሳፍራታል» አለ ።

እንጨት ሙዳይ ውስጥ አስገብቼ እንደገና ከረጢት ውስጥ ከከተትኩት በኋላ ከነቁልፉ ሰጠሁት ።

«በቅርብ ቀን ታስተዋውቀኝና እናግራታለሁ ። ዛሬ ግን ያንተን ስቱዲዮ አያለሁ ። ለጊዜው ብቻዬን መሆን ስላለብኝ ሳሰናብትህ ይቅርታህን እየለመንኩ ነው ።» ስለው ፈጥኖ ተነስቶ ተሰናብቶኝ ወጣ ። የን ሀብት ይዞ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሲወጣ ሰው ሳይሆን አጥንት ተሰጥቶት ይዞህ ውጣ የተባለ ውሻ መስሎ ታየኝ ። የበቀል ግርፋት እንዲህ በረጅሙ ሲደግስ በዓለም የመጀመሪያ ሰው እኔ ነኝ ለማለት በልቤ ውስጥ ቃጥቶኝ ኩራት ተሰማኝ ።

ቀኑን ብቻዬን በፀጥታ ውዬ በቀጠሮው ሰዓት ወደ ፌራሪ ቤት አዘገምኩ ። ቤቱ ደርሼ አንኳኳሁ ። ተንደርድሮ ከፈተልኝና እየተርበተበተ የፎቁን ደረጃ እንድወጣ ጋበዘኝ ። ወዲያው ስዕሎቹን ማድነቅ ጀመርኩ ። እንዳለውም እንድም አዲስ ሥራ የለውም ። ሁሉም የማውቀው ነው ። ዘና ብዬ ተቀምጬ ስዕሎቹን ካየሁ በኋላ በመሬት አቀማመጥ ውበት ሥራው ላይ አተኮርኩ ። ሥራው የባለሙያ ሳይሆን የተማሪ ነው ። ቢሆንም በጣም አድንቄ ያየሁትን በአምስት መቶ ፍራንክ እንደምገዛ ገለጽኩለት ። በዚህች ብቻ የሕጻን ዓይነት ደስታውን ለመቆጣጠር እስኪያቅተው እየገለፈጠ ሌሎች አራት ስዕሎች እንዳይ ጋበዘኝ ። እነኝ ያንም እርሱን ለማስደሰት ስል ገዛሁለትና እንደ ህጻን ፈነደቀ ።ቢኖ ጋብዞኝ የሚያስቁ ቀልዶች ሲያወራልኝ የሰረገላ ድምጽ ሰማሁ ። ቀጥሎም የበሩ ደወል አንቃጨለ ።

ማን እንደ መጣ ልቤ ነገረኝ ። መነጽሬን አስተካክዬ እንደተቀመጥኩ የምድር ቤቱ በር ተከፈተ ። ደረጃውን ክብደት የሌለው ፈጣን ጫማ ሲረግጠው ሰማሁ ። ክፍሉን የቤት ሽቶ ጠረን አወደው ። ባለቤቱን ፊት ለፊት ቆማ አየኋት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሰባት

ውበትዋ ለአንድ አፍታ አፈዘዘኝ ። መጀመሪያ ሳያት የማረከኝ ውበት እንደገና ስሜቴን ለመማረክ ቃጣው ። በጥንቃቄ የተሰፋው የሀዘን ልብስ ውበትዋን በይበልጥ አጉልቶ አውጥቶታል ። ለጥቂት ሴኮንዶች በማራኪ ፈገግታዋ ካየችኝ በኋላ በአክብሮት «ባልሳሳት ጌታ ሲዛር አሊ ኛ ይመስሉኛል» አለች ።

ሀዘኑም ፣ ድንጋጤና እልሁም በአንድ ጊዜ ስለተባበሩ ብኝ አፌን አሳውሼ የምናገርበት ልሳኔ ክው ብሎ ደረቀ ። እንዲያው ከአንገቴ ጐንበስ ብዬ አወንታዬን ገለጽኩ ።

ደርበብ ብላ ሁለት እጅዋን ለሰላምታ ዘረጋች ። «እመቤት ሮማኒ ነኝ ። የሲኞር ፌራሪን ስቱዲዮ የመጐብኘት እቅድ እንዳለዎ ሰምቼ ለላኩልኝ ከግምት በላይ ውድ ስጦታዎ ላመሰግንዎ መጣሁ።ልባዊ ምሥጋናዬን እባክዎ ይቀበሉኝ ።» ብላ ከአንገትዋ በአክብሮት ዝቅ አለች ።

እጅዋን ጥርቅም አድርጌ ጨበጥኳት ። ቀለበትዋ ስጋዋን ከፍሎ እንደሚገባና እንደሚያማት አድርጌ ጨበጥኳት ። ስሜትዋን ተቆጣጠረች እንጂ አፍ አውጥታ መጮህ ነበረባት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«ይልቅስ ምስጋናው ከእኔ ሊደርስሽ ይገባል» ብዬ በሻከረ ድምፅ ለምሥጋና ጉንበስ አልኩ ። «አልማዝ ዋጋ በማይሰጥሽ የሀዘን ወቅት የማይረባ ስጦታዬን በመቀበልሽ ባለ ማመስገን የሚገባኝ እኔ ነኝ ። ሀዘንሽ ግን የኔው ነው ። ባለ ቤትሽ በሕይወት ቢኖር በእጁ አልማዙን አንገትሽ ላይ ያጠልቅልሽ ነበር ። ከኔ እጅ በመቀበልሽ ምስጋናዩ ጥልቅ ነው ።»

እስተያየትዋ አስደነገጠኝ ። ድንግጣ ያስደነገጠችኝ ትክ ብላ በመነጽሬ ውስጥ ለማየት ስትሞክር ለማደናገር ፊጥኝ የመዝናኛውን ወንበር አቀረብኩላትና ሁሉን ትታ እንደ ንጉሥ ሚሽት ደልቀቅ ብላ ተቀመጠች ። ፊትዋ ግን በድንጋጤ ወዲያው ወየበ ። ካለማቋረጥ በሀሳብ ተውጣ ታስተውለኛለች ። ፈራሪ አዲስ የወይን ጠጅ እያዘገጃጀ የባጥ የቆጡን ይለፈልፋል ። «እህ ተነቃብዎት አይደል ጌታዬ?» አለ ወደ እኔ እያተኮረ ። «ይህን ሚስጢራዊ ቀጠሮ እኛ ሆን ብለን ነው ያዘጋጀነው ። ልናስደንቆትም ፈልገን ነው ። ወደ ሮማኒ ጊቢ የሚሄዱበት ቀኑ ሚስጢር ሲሆን ብን ማዳም ሮማኒ ደግሞ ለተላከላት ስጦታ ሁሉ ምስጋና ዋን እስከታቀርብ እንቅልፍ የሚወስዳት ስላልሆነ ይህን የሚስጢር ግንኙነት አዘጋጀን ። ታዲያስ በእመቤቲቱ ውበት ምን ያህል ነው የተደነቁት?»

«ማነው በእንዲህ ያለው ውበትና ልጅነት የማይደ ነቅ? በዚህ ላይ ደግሞ እመቤቲቱ በእኔ ላይ ያላትን ስሜት ስመለከት ልቤ በኩራት ተሞልቷል ። በተለይ ሀዘን ልብ


t.me/OLDBOOKSPDF

ዋን በሰበረበት በአሁኑ ወቅት እኔን ለማስተናገድ መነሳትዋ በጣሙን የተለየ ውለታ ነው ያደረብኝ ።»

ሀዘንዋን ስጠቅስ ስሜትዋ ጠውለግ ካለ በኋላ «ዋ ያፋቢዮ እዚች ቦታ አሁን ቢኖር ምንኛ ደስ ባለውና በሞገስ ባስተናገድዎ ። እኔ እኮ አሟሟቱ ድንገት ስለሆነ ላምን አልቻልኩም ። እስከ መቼም ሀዘኑ የሚወጣልኝ አይመስለኝም ።» ዐይንዋ በእንባ ሲሞላ ቀና ብዬ ፌራሪን አየት አደረግሁትና አፈር አለ ። ጓደኛዬ የባለቤቴን ያህል ማስመሰል አይችልም ።

«እባክሽን ለመጽናናት ሞክሪ ። ከሀዘን የሚገኝ ነገር የለም ! ልጅ ስለሆንሽ መጪው ዘመን ያንቺው ነው ። ባንቺ እድሜ ያለ ሰው ሀዘን ሊያበዛ አይገባም ።» ይህን እንዳልኳት እንባዋ ድርቅ ጥርስዋም ፍልቅቅ አለ ።

«ሀዘኔን ሊያጽናናኝ የሚችል ከእንግዲህ የእርስዎ ጉብኝት ነው ። መላው ቤቴ እርስዎን ለመቀበል ደስተኛ ነው።»

ግብዣውን መቀበሌን ከአንገቴ ዝቅ ብዬ ገለጽኩ ።

ጉዶ ፌራሪ የሚያሾፍ መሆኑ እየታወቀበት «ጌታዬ ሴቶችን እንደማይወዱ ማዳም ሮማኒ አታውቅም» አለ ።

እንዳላሳፍረው «ትክክል ብሎአል ሲኞር ፌራሪ ፤ ሴትን የሚቋቋም ጉልበት የለኝም ። መልአክ የምትመስል ሴት ፈገግ ስትል መድረሻ ይጠበኛል» አልኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሙኑ ከቀትር በኋላ ቤትዋ ልመጣ ፣ ጉዶ መጥቶ ሊወስደኝ ፣ በቀጠር ሳላሳፍራት እርስዋም ልጅዋን (ልጇን) ስቱላን ልታሳየኝ ቀጠሮ ተቆርጦ ተስማማን ። እንደ መላ እክት ጉብኝትዋ አጭርና ጥፍጥ ያለ ሆነብኝ ።

እጅዋን ለሰላምታ ዘረጋችልኝና ጎንበስ ብዬ በከንፈሬ ነካሁት ። መነጽሬን አተኩራ ካየች በኋላ ዐይንዎን ያምዎ ታልን?» አለችኝ ።

«ብርሀን አይደፍርልኝም ። ከእድሜዬ ጋር የተያያዘ ነው ።»

«እድሜዎ እንኳ ይህን ያህል የገፋ አለመሆኑ ግልጽ ነው ።»

«ፀጉሬ እንዲህ ጥጥ መስሎ ከዚያ ወዲያ ምን ይጠበቃል ።»

«ብዙ ወንዶች በወጣትነት በነጭ ፀጉር ይሸፈናሉ ፣ ሽበት እኮ የእርጅና ምልክት አይደለም ።»

ይህን እየተባባልን ሰረገላዋ ደረስን ። ጉዶ ፈራሪ እጇን ዘርግቶ እያለ የኔን እጅ ይዛ ሰረገላዋ ወጣች ። ልብስ ዋን አስተካክየላት ሰረገላው ትቶን ተሸከረከረ ። ዘወር ብዬ የጉዶን ፊት አየት ባደርግ ቅናት በልቡ መጠንሰሱ በጉልህ ይታያል ።

«ምነው ስሜትህም ጨዋታህም ድንገት እንደጨለመ ብርሀን ደብዘዝ አለብኝ ። ሴትየዋ እንዳልከው ተወዳዳሪ የሌለው ውበት ነው ያላት» አልኩት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«አላልኩዎትም......አላልኩዎትም በውበትዋ መሸነፍዎ ገባኝ ።»

ሲጃራዬን እያቦነንኩ በሀሳብ እንደሚሟገት ሰው ካመ ነታሁ በኋላ በውበትዋ እንኳ መሸነፍ አልተሸነፍኩም ፣ ብቻ እንደርስዋ ያለች ውብ ሴት አይቼ አላውቅም ።»

«እኔም አስቀድሜ ነግሬዎታለሁ ። ከእንግዲህ ግን አስጠነቅቆታለሁ ።»

«አስጠነቅቃለሁ?» ከመጠን በላይ ተደንቄ ፊቴን ቅጭም አደረግሁና ፣ «ከምን ፣ ከማንስ እንድርቅ ነው? መቸም ከእመቤቲቱ እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ ። ምክንያ ቱም ያስተዋወቅኸን አንተው ነህ ። መቸም ተላላፊ በሽታ ወይም ለሕይወት አስጊ የሆነ ነገር የለባትም ። በሽታ አለ ባት እንዴ?»

በሀሳቤ አመጣጥ ተደንቆ ሳቀ ። «የለም ሴትየዋ ስሜ ትዋ ስለሚለዋወጥ ዳግመኛ ሲያይዋት ቀዝቀዝ ትልቦት ይሆናል » አለ ።

ስቄ ትከሻውን መታ ካደረግሁት በኋላ «ለመሆኑ በየ ትኛው እድሜዬ ነው እርስዋን የመሰለ የተወደሰች ሴት መማረክ የምችለው?»

«እንዴ! ሽበትዎ የእድሜዎን ማርጀት አይገልጽም አላለችዎትም እንዴ? ብቻ ይቅርታ ያድርጉልኝ ወይዘሮዋ ለኔ እንደ እህት ናት ። ያለፈው ጓደኛዬ ፋቢዮ ከባለቤቱ ጋር የወንድምና የእህት ፍቅር እንድናጠናክር አድርጎ ነው


t.me/OLDBOOKSPDF

ያለፈው ። አሁንም ያው እየሳበኝ ልጠብቃት ሰሜቴ ይገፋፋኛል ።»

አካሄዱ ገባኝ ። እርሱ የመሬቱ ባለርስት ለመሆን ነው ሀሳቡ ። ምንም ዓይነት ተካፋይ እንዳይነሳበት ነው ጥረቱ ። በርሱ አስተሳሰብ ትክክል ነው ። ግን የመሬቱ ባለቤት እኔ ነኝ ። ስለዚህ የኔ አስተሳሰብ ደግሞ ከእርሱ ለየት ይላል ። ስለዚህ ጫወታችንን አውቄ አቀዘቀዝኩት ።

እርእሱቱ የሰለቸኝ አስመሰዬ ስሜቴን አስከፋሁኝ ። ፈራሪ በሁኔታዬ ተደስቶ ግብዣውንም ቀልዱንም እንደ ገና ሕይወት ዘራበት ። በሚከተለው ቀን ከቀትር በኋላ በጌታ ሮማኒ ግቢ እንደምንገናኝ አስታውሶኝ ስለ ኔፕልስ ሰው አለባበስ መወያየት ጀመርን ። ስለኔፕልስ ነዋሪዎች የሞራል መላሸቅ አስተያየት ሰነዘርኩ ። ሊሰጠኝ የሚች ለውን አስተያየት እያወቅሁ ጀሮዬን ሰጠሁትና መለፍለፉን ቀጠለ ።

«እባክዎ ይተውት የሞራል ነገር» አለ የያዘውን ሲጃራ እምዘግዝጎ ወረወረና ። «ሞራል እልባ ፤ ሞራለ ቢስ ፤ የሞራል ውድቀት ፤ ምንድነው ይኸ ሁሉ መያዣ መጨበጫ የሌለው ነገር አንድ ወንድ ሀያ የማፍቀር ችሎታ እያለው በአንዲት ሴት እንዲታሰር የሚደረገው ለምንድነው ። ሲያገብዋት ቆንጆ የነበረች ልጃገረድ ከሠርጉ በኋላ ቀፈታም ፤ ሻካራ ፤ ወይም እንደ ሲባጉ የመነመነች ነጭናጫ ትሆናለች ። በሕይወት እስካለች ድረስ እንግዲህ የሞራሉ ግዴታ


t.me/OLDBOOKSPDF

የወንድ ፍትወት በርስዋ ታስሮ እንዲኖር ነው ። ሕጉ ጤነኛ አይመስለኝም ፤ ደረቅ ነገር መጨረሻው መሰበር ነው ። ሕጉ ሲጣመም ደሞ ኅብረተሰቡ ጉድ ይላል ። ራስን ማታለል ነው ። አንዳንዱ ሀገር ይህን ሁሉ ድክመት ሸፋፍኖ መያዝ ይችላል ። የእንደኛ ያለው ደግሞ ፊት ለፊት ይጋጠመዋል ።»

«በዓለም የሚፈለገው ግን ይኸ ብቻ አይደለም» ብዬ ጀመርኩ ። «ሰው ማለት የአራዊት ባሕሪውን ያሸነፈ ማለት ነው ።»

«መጽሐፉ ምንድነው የሚለው?» ብሎ አቋረጠኝ «ብላ ፤ ጠጣ ፤ ተደሰት ነገ ትሞታለህ አይደለም እንዴ የሚለው?»

«የኔፕልስ መጽሐፍ ፤ አዎን ይላል አልኩት።» የሚያው ቀውን እንዲያነብ እንጂ ልከራከረው ስለማልፈልግ «የዘመናዊ ስልጣኔ ሞራል ጠንቃቃ መሆንን አይጠይቅም ፤ አስፈላጊው በሕዝብ ፊት ቀሎ ያለመገኘት ብቻ ነው ። ይኸ ደግሞ ቀላል ፤ የቀላል ቀላል ነው» አልኩት ።

በአስተያየቴ ተደስቶ ራሱን ነቀነቀ ። «ትክክል አስቀመጡት ። ይኸ ደግሞ የሚቻል ነው ። የሴትን ስም ወይም ክብር እንውሰድ ፤ ይህ ስምዋ ከማግባትዋ በፊት በቀላሉ ሲጠፋ የሚችል ነው ። ነገር ግን ፤ አግብታ ፤ ትዳር ከመሰረተች በኋላ ነጻ ነች ። አስራ ሁለት ውሽማ ልትይዝ ትችላለች ። አያያዙን ካወቀችበት ባሏም ላያውቅባት ይችላል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ባል በሚማግጥበት ሀገር ሚሽት የማትማግጥበት ምን አጥ ጋቢ ምክንያት አለ?»

የልቡን ሴሰኝነት ሁሉ አውጥቶ ሲዘበዝብ አተኩሬ አየሁት ። ያ ቅክልክል ብሎ የተሰራው ፊቱ ቢከፍቱት ብል ግና ብቻ ሆኖ ታየኝ ። የሚያስከብር ባሕል የሌለው ወፍ ዘራሽ ሻካራ አረም ነው ። ስሜቴ በሙሉ በአፈጣጠሩ ተቅ ለሸለሸ ። የሕመም ስሜት ተሰማኝ ። የፊት ገጽታዬ ተኮ ማተረ ። ትንፋሼ ከመጠን በላይ ከበደ ። ሁኔታዬ ፈራሪን አስደነገጠውና «ምነው አመሞት እንዴ ጌታዬን?» አለኝ ።

«አልፎ አልፎ እንደዚህ ያመኛል ። ሂጂ ልረፍ !»ብዬ ብድግ አልኩ ። ስሜቴን በሙሉ ብልግናው ስላስቆጣኝ እንዳይከተለኝ ተከላከልኩ ። ጥቂት ቃላት ከተለዋወጥን ማንቋርጡ ላይ መወርወሬ ስለማይቀር ስሜቴን በብቸኝነት ለማቀዝቀዝ ተጣደፍኩ ። በስዕሉ ባለቤትነት መበልጸጌን ባጭሩ ገልጬ ፣ ወዲያው ከፈልኩት ። አመስግኖ አዲዮስ ብዬ ተሊየየን ።

ቤቴ ስገባ ሌላ ሕመም ጠበቀኝ ። በጥንቃቄ ተመርጦ የተለቀመ ልዩ ልዩ ፍሬ በቅርጫት ተሞልቶ መሀል ጠረ ጴዛ ጠበቀኝ ። በግል እንዲያገለግለኝ የቀጠርኩት ሠራተኛ ዬን ቪንቼንዞን ፍሬው ከየት እንደመጣ ስጠይቀው «ክብ ርት ማዳም ሮማኒ» አለኝ ። ስምዋ የታተመበትን ካርድ አውጥቶ አሳየኝ ። አገላብጬ አየሁ ። የሚሽቴ የእጅ ጽሕ ፈት አርፎበታል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ጌቶች ቃል የገቡልኝን የነገውን ጉብኝት ለማስታ ወስ» ይላል ። ንዴት ሳይሆን ብሽቀት አደረብኝ ። ወረቀ ቱን ጨምድጄ ፍሬውን በንዴት በተንኩት ። ቪንቼንዞን «ይህን ፍሬ ቶሎ አውጣና ለሆቴል ጠባቂው ልጅ ስጥ» ስለው ሠራተኛዬ በትህትና ፍሬውን ሰብስቦ ወጣ ። ከራቤ ግቢ የተለቀመ የፍሬ ስጦታ ተላከልኝ ። ራሴን መቻል አቅቶኝ ሶፋው ላይ ተወረወርኩ ። በመገረምና በብሽቀት ልቤን እስኪያመኝ ከት ብዬ ሳቅሁ ።

ማዳም በቅጽበት ወጥመድዋ ገባች ። ሀብቱን እንጂ ምንነቱን ለማታውቀው ሰው ተሸነፈች።ይህ ወርቅ የሚሉት ቢጫ የመጠንቆያ ብረት ምን የማይሠራው አለ ። ኩሩውን ሰው ጫማ ያስልሳል ። የሴት ፍቅር ለወርቅ የሸቀጥ እቃ ነው ። ወርቁ በተለቀ ቁጥር የፍቅር ሸቀጡ በርከት ይላል ። ያዘጋጀሁት በቀል ብዙ የሚያደክም ውጣ ውረድ ያለው መስሎኝ ነበር ። ወጥመዱን ገና ከመዘርጋቴ የምፈልጋት ጅግራ ሰተት ብላ ገባች ። ወርቁ እንኝህን ውሽታሞች ፣ ራሳ ቸውን የሚያታልሉ ድልሎች ከንቱ ቁመናቸውን አራቆ ተልኝ ። ሚሽቴ እኔን ብቻ አይደለም የከዳችው ። ተፈጥ ሮዋ በሙሉ የጽናት ሳይሆን የክዳት ፣ የሴሰኝነትና የወረት ነው ። ፈራሪን ካሁኑ ሰልችታለች ። ጳውሜው ይቀጥ ላል።እንደጓደኛዬ ፈራሪ እና እንደ ሚሽቴኒና ያሉ ከአውሬ የባሱ አራዊቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ ቦታ ሊኖራቸው ይገ ባል? አውሬ ምን ጥፋት አለው ። አይዋሽም ከሞቱ በኋላ ቆዳቸው ያገለግላል ። የውሸታም ሰው ግን ምላሱ ሆነ አስ ከሬኑ አየሩን ከመበከል ሌላ የሚሠራው ፋይዳ የለም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የአንበሳ ሀቁ አባር የያዘውን ፊት ለፊት በመዳፉና በጥርሱ ማድቀቅ ነው ። ሰው ግን ተደብቆ በመሣሪያ ኃይል ፍርሀቱንና ጨካኝነቱን ያስመሰክራል ። ስለዚህ ለኔ ከሰው ይልቅ አራዊት ክብረት ይገባዋል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ስምንት

«ጌታ ሮማኒ ግቢ እንኳን ደህና ገቡ» ብላ ስትቀበለኝ፣ ለጆሮዬ ያልተለመደና ያልተጠበቀ አነጋገር ሆነብኝ። እኔው ራሴ እገዛ ግቢዬ መስክ ላይ መቆሜን ተጠራጠርኩ። በደመነፍሴ የራሴን ሚሽት እጅ ስነሳ፣ ፍልቅልቅ ብላ ተውባ ተቀበለችኝ። ለአንድ አፍታ አእምሮዬ ውሉን ሳተ። የግቢው አጸድ ዋዠቀብኝ። በክብረ ሞገስ የቆመው ዋና ቤት፣ የሕጻንነት ጊዜዬን ያሳለፍኩበት ቤቴ በአንድ አፍታ ክምብል የሚል ሆኖ በዓይኖቼ ስር ከመቅጽበት ተንኮታኩቶ የሚወድቅ መሰለኝ። ጉሮሮዬን ድርቅ አነቀው። የወንድ ልጅ እምባ በዋዛ አይመጣም። ያን አፍታ ግን እዬዬ ብዬ እንብቼ ማልቀስ ከጀለኝ። ዋ ውድ ቤቴ! ምነው እንደጊታው ተንኳኩቶ መቃብር በገባ የሚልም ምኞት መጣብኝ። ይኸ የማነው ቤት ዛሬ? የሚል ጥያቂ ተመላለሰብኝና ፈራራን እየት አደረግሁት። እርሱ የቤቴ ጌታ አይሆናትም አልኩ። ተወልጄ ያደግሁበትን ቤቴን በስስት በህዘን ስሜትና በፍቅር ዐይን ቃኘሁት። አንዳንድ ነገሮች ተለዋውጠዋል። ደስተኛ የነበረው መጠጥ አሳላፊዬ ከዚህ በፊት ያልታየበት የአካል ጉስቁልናና የውስጥ ስሜት ጉዳት ይታይበታል። ሰውነቱና ውስጣዊ ስሜቱ ተጎድቷል። ተጉሳቁሎአል። ከበረንዳ ተነስቶ የማያውቀው የግል የመዝናኛ ወንበሬ ከቦታው የለም። ያሳደግሁት ውሻዬን ወደጌት



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳደረሱት አላውቅም ። ስሜቱን በመቆጣጠር ረገድ ግን ብርቱ ጥንቃቄ አደረግሁ ።

የፊቱን ማዘን ካጤነች በኋላ ቀልድ በተቀላቀለው ስሜት «ግቢዬ ድረስ መጥተው ስለጐበኙኝ ሀዘን ተሰማዎት መሰለኝ» አለችኝ ።

«ይቅርታ እመቤቴ ። በእውነት ይህ ከታየብኝ ከወንዶች ሁሉ በደለኛ ነኝና እከሳለሁ ። ግን እኔም ጥያቄ ላቅርብልሽና ዳንቴ ገነትን እንዲጐበኝ ሲፈቀድለት ሀዘን ነው ደስታ የተሰማው?»

ፊትዋ እንደማፈር አለና ጠወለገ ። ፌራሪ የተስፋ መቁረጥ ዓይነት የቅናት ስሜት እንፀባረቀ ። እቤት ገብተን የቤቱን ውስጥ ድርጅት ታሳየኝ ጀመር ። የመዝናኛ ክፍሉ መስኮት በሰፊው ተከፍቷል ። ፒያኖው በቅርብ እንደተዘፈነበት ያስታውቃል ። አበባ በየባዙ ፈክቶ ተንተርኳል ። ሶፋው ላይ አረፍ ካልኩ በኋላ ፤

«ሁሉም ትዝ ይለኛል» አልኩ ። ፌራሪ ደንግጦ «ትዝ ይለኛል ነው ያሉት?» አለኝ ።

«አዎን ከፋቢዮ አባት ጋር ብዙ ጊዜ እዚህ እንጫወት ነበር ። የፋቢዮ እናት በልጅነትዋ ነው የሞተችው» ብዬ ቤተሰቡን በዝርዝር ማወቄን ገለጽኩ ።

«ቤተሰቡን እንዲህ የሚያውቁ ከሆነ ልጄን ስቴላን ቢያዩዋት ፤ ወይስ ልጅ ሰልችቶዎታል?» አለችኝ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«እኔ ለልጅ ያለኝ ፍቅር ከፍተኛ ነው» ብዬ ስሜቴን በቀላሉ አቀዝቅዤ የልጇን መምጣት እጠባበቅ ጀመር ። በሩ በቀስታ ተከፈተ ። ልጇ ብቅ ስትል ልቤ ሀዘኑን አልችለው አለ ።

«አይዞሽ ነይ አትፍሪ» ብላ እናቲቱ አበረታታቻት ። ልጇን በተለየኋት ጥቂት ቀናት ሁኔታዋ በብዙ ተለዋውጧል፤ተጫዋችነትዋ ተቀንሷል፤ተጠራጣሪና ዐይናፋር ሆናለች ። በዕድሜዋ ሊኖር የማይገባው ጠርጣሪነት ፊትዋ ላይ ይነበባል ። ጠቅላላ ሁኔታዋ ለኀሊናዬ ብዙ ነገር አዋየኝ ። ልጂ መዘንጋትዋን ነፍሴ ነገረችኝ ። ወደእኔ መምጣት ከጀመረች በኋላ መሀል መንገድ ቆማ ፈራራን አየት አደረገች ።

«ነይ እንጂ ስቴላ ። እኔ እኮ ባለጌ ካልሆንሽ አልቆጣሽም ። ጭራቅ መስዬ እኮነው የምታየት ። ነይና እኝህን የአባትሽን ወዳጅ ሰላም በያቸው።»

ልጇ የአባትዋ ስም ሲጠራ ዐይንዋ ፋኖስ መስሎ እርምጃዋ መተማመኛ አገኘ ። ሮጣ ትንሽ እጅዋን በአንገቴ አዙራ ጥምጥም አለችብኝ ። እንደሚስም ሆኜ ፀጉርዋ ሥር ቆየት ብዬ ፍልቅ ብሎ የመጣውን የወላጅ እንባዬን መለስኩት ። ጥቁር መነጽሬን የምትፈራው መስሎኝ ነበር ። እርስዋ ንቅንቅም አላለች ። በረካ መንፈስ ጉልበቴ ላይ ተደላድላ ተቀመጠች ። የትኩረት አመለካከትዋ ግን የውስጥ ስሜቴን የመቆጣጠር ኃይሌን እንደማናጋት አደረገው። ብዙ ካየችኝ በኋላ አንድ ለንባብ የሚያስቸግር ፈገግታ ፊትዋ


t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ተቀረጸ ። እንደገና ልትስመኝ ወደእሌ ስትጠጋ ነገሩ እንዳያስታውቅ ብዬ እቅፍ አደረግኋት ። የቻልኩትን ያህል ድምጼን ጉርንን አድርጌ «ስቴላ ፣ አንቺ በጣም ደስ የም ትይ ሕጻን ነሽ ፤ ስቴላ ማለት ትንሽ ኮከብ ማለት ነው » ብዬ ሳጫውታት ትከሻዋን ከንጼ ላይ አስደገፋ ።

«አባቱን አይተውታል ፣ በቶሎ ይመጣል?» አለ ችኝ ። ፈጥኜ መልስ ለመስጠት ስላልቻልኩ ፌራሪ መል ሱን ወዲያው ወረወረ ።

«ቅዠትሽን አታምጪ እንግዲህ ፣ አባትሽ ርቆ መሄ ዱን ታውቂ የለ ። በጣም ባለጌ ስለሆንሽ ነው ጥሎሽ የሄ ደው ። እረፍት የማይሰጡ ጨቅጫቃ ልጆች ወደሌሉበት አገር ነው የሄደው አባትሽ» አላት ።

በትዝብትና በፍርሀት ልጂ ፌራሪን በጥላቻ ስታስ ተውለው አየኋት ። እኔም ሰው ስታዘብ እንዲህ ያለ አስተ ያየት ስላለኝ ገረመኝ ። ምን እያሉ እንደሚያደድቡዋት ግን ገባኝ ። ሆን ተብሎ ልጅቱ ግራ እንድትጋባና ራስዋን እንድትጠላ የተደረገ ደባ ነው ።

ፌራሪ የልጅቱን ሁኔታ አስተውሎ ከት ብሎ ከሳቀ በኋላ እንደታቀፍኳት ፀጉርዋን ከግራና ቀኝ ጠምዞ ጢም ለማስመሰል አፍንጫዋ ሥር እየጉተተ «ጠቅላላውን እኮ የፋቢዬ ሮማኒ ፎቶ ናት» አለ ። ፀጉርዋን በጨመደደ ቁጥር ልጅቱ ደረቴ ውስጥ ሽሽትዋን ቀጠለች ፣ ሚሽቴ ምንም አስተያየት አትሰጥም ። እኔ ብዙ ከተከላከልኩ በኋላ ድም ጼን እንደመቀለድ፣ አገርሜ «ከሕፃን ጋር ገራገሩን መጫ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወት ነው የሚበጀው ፡ ያለዚያ እንደጭራቅ መታየትን ያስ ከትላል» አልኩት ።

«ይህች እንከን የለሽ ስታድግ እንግዲህ አንድ ወንድ ስላሾፈባት በወንዶች ሁሉ ላይ ለማሾፍ ምክንያት ታገኛለች ። አይመስልሽም እመቤቴ?» አልኩ ወደ ሚሽቴ ዞወር ብዬ ።

«አንድ ወንድ ስላሾፈባት ሌላው ወንድ ደግሞ ደግ ስለሆነላት ነገሩ ይማታባታል እንጂ በወንዶች ላይ አታሾፍም» አለች ።

ድንገት አሽከር የእልፍኙን በር ከፍቶ ራት መዘጋጀቱን ተናገረ ። ልጅቱን ከጭኔ ላይ አወረድኳትና ወደ ክፍልዋ ሄደች።ሶስታችንም ወደ ገበታ ቤት አመራን ። ስለ እንግድነቴ በክብር መቀመጫው ላይ እንድቀመጥ ተጋብዤ ተገቢ ቦታዬን ያዝኩ ። ከአባቴ ጊዜ ጀምሮ ቆሞ የሚያበላኝ ሠራተኛዬና ጓደኛዬ ከኋላዬ ቆሞ ዋንጫዬን በሞላ ልኝ ቁጥር በመነጽሬ ውስጥ እየፈራ ማንነቴን ለማጣራት አየት ያደርጋል ። ከተቀመጥኩበት ፊት ለፊት ግድግዳ ላይ የአባቴ ገጽታ ትክ ብሎ እኔን ልጁን በሀዘን እያየ ሚስኪን የሚለኝ መሰለኝና ትክ ብዬ ፎቶውን እያየሁት ከንፈሬ እየተንቀጠቀጠ ስሜቴ ከዳኝ ።

«ፎቶው በትክክል የፋብዮን አባት ይመስላል?» ብሎ ፌራሪ ጠየቀኝ ።

ከው ብዬ ከደነገጥኩ በኋላ ስሜቴን ዋጥ አድርጌ «እንዴታ ባል ሳሳት ጌታ ሮማኒን ቁርጥ ይመስላል ፤ ልቤ የተ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠራቀመውን ትዝታ ሁሉ ፈንቅሎ አወጣው እኮ ። አብረን ያሳለፍነውን ደጉንና ክፉውን ጊዜ ሁሉ በአንድ አፍታ ከፊቴ አምጥቶ አነጠፈው እኮ ። ዋ! ምንኛ የሚያኮራ ትልቅ ሰው እንደነበር ብነግራችሁ አታምኑኝም ።»

«ፋቢዮም የሚያስኮራ ግን በስሜቱ ቀዝቃዛ የሆነ ሰው ነበር » አለች ሚሽቴ ።

ውሸታምነትዋ እንደገና ሲያዋርዳት ነው ። ደፋር ውሸታም ናት ። ስሜቱ ለእርስዋም ሆነ ለሌላ ቀዝቃዛ አያውቅም ። ስሜትዋን በደስታ ለመሙላት የምከታተል ባሪያዋ እንጂ ስሜት የሌለኝ የበረዶ ቅርጽ አልነበርኩም ። ድምጼን ከፍ አድርጌ «ስለ ጓደኛዬ ስሜት በትክክል አውቃለሁ ።ባጠቃላይ የሮማኒ ቤተሰብ ስሜተ ቁጡ እንጂ ስሜተ ቀዝቃዛነት እንኳ የለባቸውም» አልኩ ።

እዚህ ላይ ከኋላዬ የቆመው መጋቢ በትህትና ለመናገር መፈለጉን ገልጾ ሲናገር ሲል ፈራራ ዋንጫውን እያስሞላ «ይልቅ የቤቱን አሮጌ ሊቅ እናድምጥ ፤ እርሱ ሁለቱንም ጌታ ሮማኒዎች ያውቃል» በማለት ተንከትክቶ ሳቀ ።

ዘወር ብዬ የመጠጥ አሳላፊውን ፊት አተኩሬ ካየሁ በኋላ «ፊትህ ትዝ አይለኝም ምናልባት እኔ ከሄድሁ በኋላ ይሆናል እዚህ መሥራት የጀመርከው አልኩት ።»

አወንታውን እጅ በመንሳት ገለጸልኝ ። «አዎን ጌታዬ፣ እኔ እዚህ ሥራ የጀመርኩት እሜቴ የጌታ ፋቢዮ ሮማኒ እናት ከመሞታቸው አንድ ዓመት አስቀድሞ ነው ።» ስሜቱ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉ ተሰባብሮአል ፤ አድማጭ አጥቶ ከንፈሩ ሲናገር፤እን ደእምነት አጉዳይ ይንቀጠቀጣል ።

ስሜቱን ለመደገፍ ፤ «እኔ አገር ጥዬ ከሄድኩ በኋላ ነው እዚህ የገባኸው ፤ ቢሆንም ጌታ ፋቢዮን ከሕጻንነት ታውቀዋለህ ማለት ነው?»

«አዎን ጌታዬ ።»

«ትወደው ነበር መሰለኝ?» ስለው ጥያቄዬ ፊቱ ላይ ብርሀን አፈካ ።

«እወደው ነበር ፤ ለሰው መልካም ነገር የሚመኝ ነበር ። ነፍሱ በመላእክት እጅ ናት ዛሬ መሞቱን ግን አሁ ንም አላምንም ። አሮጌ ልቤ መርዶውን ስትሰማ የተቃጠለች ይመስለኛል ። ከዚያ ወዲህ እኔም እኔ አይደለሁም ፤ እመቤ ቴም ብዙ ጊዜ በዚሁ ምክንያት አትደሰትብኝም ።»

«አዎን ልቤን እያደረቅህ አስቸግረኸኛል ።» ብላ ገረ መመችወና እጁ እየተንቀጠቀጠ ዋንጫችንን የመሙላት ሥራውን ቀጠለ ። ይንከተከት የነበረው ፈራሪ ይህን ስን ባባል ስሜቱ እየተዘጋ ሄደ ። ከሚሽቴ ጋር የተለየ ፈገግታ ስንለዋወጥ ፈራሪ በይፋ ማኩረፉን ጀመረ ። እስተያየት ከመስጠት የማትቦዝነው ሚሽቴ ፤ «ጉዶ አንተ እኮ በእው ነት ወላቢላ አመል ነው ያለህ» ብላ ዘለፈችው ። ቃሉ አፍ ዋን ካመለጠ በኋላ እየት አደረገችኝ ። መናናቃቸው እንዳ ያስታውቅ «ከሲኞር ፈራሪ ጋር ለብዙ ጊዜ እንደ ወንድ ምና እህት ስለኖርን አንዳንዴ ስሜታችንን እንደልብ እን



t.me/OLDBOOKSPDF

ትላለጸለን» አለች ። ጉዶ እየት ሲያደርጋት በዐይንዋ እኔን ጠብቃ በግልምጫ አቀለጠችው ።

ደርበብ ብላ በልሰልታት ግርማ ብድግ አለችና «ወይን ጠጃችሁን እስከትደግሙ ብቻችሁን ልተዋችሁ ። እንዳንዴ ወንዶች ቀልዳችሁ የቤቶችን አብሮ መቀመጥ ስለማይፈልግ ብቻችሁን ልተዋችሁ ፤ ጌታዬ እንደተመችዎት በረንዳ ቡና ተዘጋጅቶ ይጠብቃል» ብላ ልትወጣ ስትል ፈጥኜ በአክብሮት በሩን ከፈትኩላት ። ለሁለታችንም ወይን ጠጁን ቀድቼ ብሽቀቱን መደበቅ የማይችለውን የጥንት ጓደኛዬን እየት አደረግሁት ። የመጠጥ አሳላፊው ጂያኮሞ ቀደም ብሎ ወጥቶ ስለነበር ገበታው ቤት ብቻችንን ቀረን ። ብቻዬን ከጠላቴ ጋር መቀመጤ የግጥሚያው መጨረሻ እንዲሆን ሁኔታዎች ገፋፉኝ ።

ለአንድ ሁለት ደቂቃዎች ስለበቀል እቅዴ ማውጣት ማውረድ ጀመርኩ ። እንደገበጣ ጫወታ ግጥሚያው ልብን የሚሰብ ሆነልኝ ። እንደመሰረ ተጋጣሚ በቆራጥነት እር ምጃዬን ቀጠል አድርጌ ወጋሁ ።

«ምንኛ የምትፈቀር ቆንጆ ቤት ናት! በዚህ ላይ ብልህ ናት ፣ የውበት ምርጫህ ያስደንቀኛል ሲኞር» አልኩት ፣ የወይን ጠጁን እየተጎነጨሁ ።

እንደመደንገጥ ፣ እንደመቆጣትና እንደመደነቅ እያለ «ምን? ምን ማለትዎ ነው ጌታዬ?» አለ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«አይ ወጣትነት» አልኩ እራሴን እየነቀነቅሁ «የወጣትነት ትኩስ ደም እንደምንም የፈለገውን ያገኛል ። ሰማህ ወይ ወዳጄ ትኩስ ስሜትህ ሊያሳፍርህ አይገባም ። ላዝንልህ የሚገባኝ ሴትየዋም ያንተው ዓይነት የመውደድ ስሜት ባይኖራት ነበር ። እንዲህ ከሆነች ደግሞ ጂል ናት ። አጋጣሚው እንዲህ ተስተካክሎ ቀርቦላት እምቢኝ የምትል ከመቶ አንድ ሴት ናት ።»

«እና ፣ እርስዎ እኔ ይህችን ሴት......ይህችን ሴት...»

«እምን ታፈቅራታለህ እንጂ ለምን አታፈቅራትም ። የሟች ባለቤትዋ ምርጥ ጓደኛ ነህ ። አማልክት እንኳን የሚፈቅዱት ነው የሚመስለኝ ። መልካም የፍቅር እድል እንዲገጥምህ ዋንጫዬን እንዳነሳልህ ፍቀድልኝ ።» ዋንጫዬን ግልብጥ አድርጌ አጋባሁ ። አሁን ደግሞ ጭድ አይቶ ገደል የገባ በሬ ሆነብኝ ፣ እኔን የሚጠራጠርበት ልቡ ጭልጥ ብሎ ገደል ገባ ፣ ፊቱ ከቅናት ሁሉ ነጽቶ ቁልጭ አለ ። እጄን አንስቶ ጫኔን አለው ።

«ይቅርታ ያድርጉልኝ ጌታዬ ፤ ተሳስቼ ነበር ። ልጅቱን ራስዎ የፈለግዋት መስሎኝ ተሳስቼ ነበር ። በእውነት ዝቅ ብዬ ይቅርታ ልለምናት ይገባል ።» ግን እኔ የእሷን ውሽማ ሳይሆን ሕይወቱን መፈለጌን ሊጠረጥር አልቻለም ።

«ልትፀፀት አይገባም ። ፍቅረኞች ሁሉ ሊገጥማቸውና ሊያንፀባርቁት የሚገባውን ነው ያሳየኸው ። ብቻ ያለ ምክንያት ነው ራስህን የጐዳኸው ። በኔ እድሜ ደግሞ ስትደርስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሌት ፍቅርና ከንፈር ይልቅ የብርና የወርቅን ቅጭልጭ ልታ ትመርጣለህ ። እመነኝ ወዳጄ እኔን የፍቅር ሱስ አይማርከኝም ።»

ዋንጫውን ብድግ አድርጎ የሞላውን ጠጅ በአንድ ትንፋሽ ጠጣው ። «እንግዲያውስ የልቤን አውጥቼ ልንገርዎት ። ወይዘሮዋን አፍቅሬአታለሁ ። ፍቅር ስል የስሜትን ግለት ሁሉ አውጥቶ ሊገልጽልኝ ቃሉ ላይ ድክመት አለው ። ጣቶችዋ ሲያርፉብኝ አጥንቴ ድረስ ይሞቀኛል ። ድምጽዋ ነፍሴን ጭምር ያረካዋል ፤ ዐይኖችዋ በውስጤ ይቀልጣሉ ፤ ያለብኝን ሕመም ሁሉ እኔም ልገልጽልዎት አልችልም ። እርስዎም በትክክል ሊረዱልኝ አይችሉም ።»

«ራስህን ረጋ አድርግ» አልኩት ። በለስ እጄ ውስጥ የከተተውን ጠላቴን ራሱን በራሱ ሲያራቁት በደንብ ተመለከትኩት ። «ደምህ በስሜትህ ንዳድ ሞቅ ሲልብህ ራስህን ቀዝቀዝ ለማድረግ መሞከር አለብህ ። ለመሆኑ ወይዘሮዋ የምታፈቅርህ ይመስልሀል?»

«መምሰል? ፤ ለምን መምሰል ብቻ ።» አመነታ ። «የለም የለም ይህን ጥያቄ እኔ መንካት የለብኝም ። ብቻ ለባልዋ ግድ እንደሌላት አውቃለሁ ።»

«ይህንንም አውቃለሁ ፤ ዳተኛ ተመልካች እንኳን ይህን መመልከት አያቅተውም ።»

«ይኽ ሊያስደንቅ አይችልም ። ስሜቱን ገልጾ ሊወስድና ሊቀበል የሚገባውን ፍቅር መገመት አይችልም ነበር


t.me/OLDBOOKSPDF

ጓደኛዬ ። እንዲህ ያለው ሰው ይህችን፤የመሰለች አልማዝና እንቁ ለማግባት ምን ችግር ውስጥ ከተተው መጀመሪያ ውኑ?»

ንዴቴ በግዝፈት ሙጥቶ እቅዴን ሊያበላሽብኝ ታገለኝ ። ድምጼንም እንቅስቃሴዬንም ሰከን ካደረግሁ በኋላ «አሁን ሞቷል ። ነፍሱ በሰላም ትረፍ ። ጥፋቱ ምንም ቢተልቅ ባለቤቱ እስከ ሕይወቱ ማለፊያ ታማኝ ነበረች ፣ አይደለም እንዴ?»

«አፈር ብሎ አንገቱን ሰበር አድርጐ በፈራ ተባ ድምጽ» ትክክል ነው አለ ።

«አንተም ታማኝና የልብ ወዳጁ ነበርክ ። የዐይናማዋ ባለቤቱን ስበት ሁሉ አሸንፈህ የጓደኝነትን ወሰን ጠብቀህ ትኖር ነበር ።»

«አሁንም ትክክል ነው» ሲል ዛና ብሎ የተዘረጋው እጁ በጭንቀት እንደመንቀጥቀጥ አለ ።

«በኔ አስተያየት አሁን ከወይዘሮዋ ጋር ያለህ ፍቅር ይበል ይበል የሚያሰኝ እንጂ እንከን ያለበት አይመስለኝም ። እኔም ይቅናህ ከማለት ሌላ የምጨምረው የለኝም።»

እተቀመጠበት የሚጨብጠውን አጥቶ ተቁነጠነጠ ። ፀይኑን ወደግድግዳ ሲወረውር የፋቢዮ አባት አፈጠጠበት ፣ ወደእኔ ዞሮ «እርስዎ ግን የወይዘሮዋ ፍቅር እንደማይግርኮት እርግጠኛ ነዎት?» ብሎ እንደገና ጠየቀኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ይቅርታ አድርግልኝ ወይዘሮዋ መማረክ ትማርከ ኛለች ፣ ግን እንዳንተ ባለው ዓይነት አይደለም ። አንተን ደስ ካለህ ማረጋገጫ ልስጥህ ፣ ወይዘሮዋ እንተኛ ብላ ካላ ስገደደችኝ እኔ—»

«እህ እርስዎ —» መልሴን ለማግኘት አሾተለ ።

«እኔ እንተኛ ብዬ አልጠይቃትም ።»

«ይህማ ሊሆን አይችልም ።»

«ያውልህ እንግዲህ ልትተማመንብኝ ትችላለህ ። በል ቡናችንን እንጠጣ» ብዬ እጁን ይዤ አስነሳሁት ።

በረንዳ ወጥተን እኔ ከጋባዢ አጠገብ በተዘጋጀልኝ ወንበር ተቀመጥኩና ቡናው መቀዳት ተጀመረ ። ሰማዩ የሙሉ ጨረቃ ብርሀን ተጐናጽፏል ። የሌሊት ወፎች እያ ለፉ ይጮኸሉ ። አንድ የሆነ የሕመም ዓይነት ጩኸት እያ ረፈ ጆሮዬ ጥልቅ ይላል ።

ምሽቴ ሠራተኛ ጠርታ «ዊቪስን ፈተህ ልቀቀው» አለችው ።

ውሻዩ ከመቀጽበት ጩኸቱን አቁሞ እየፈነደቀ ሜዳ ውን አቋርጦ ወደ እኛ ሲገሰግስ አየሁት ። እመቤቲቱንና ፌራሪን አልፎ እኔን ይሳለም ጀመር ። ጭራው ተወራጨ ፣ ምራቁ ጫማዬ ላይ ተዝረበረበ ። በጭንቅላቱ ጉልበቴን እያሸ በእፎይታ ተነፈሰ ። ኒናና ፌራሪ እንዳይጠራጠሩ መላ መፍጠር ነበረብኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ይኸውላችኋ አልነገርኳችሁም መሰለኝ ውሾች ሲባሉ በደረስኩበት ሁሉ ፣ እንዲህ ሆነው ተጨንቀው ነው የሚ ቀበሉኝ ። እኔ ራሴ ይገርመኛል ።»

ማጅራቱን ይገፍ በትእዛዝ ዓይነት ወደ መሬት ጫን ሳደርገው ስልጡን ውሻዬ እግሬ ሥር ተኛ ። አልፎ አልፎ ብድግ እያለ ናፍቆቱን ይወጣል ። የደረሰብኝን የሰውነት ለውጥ ምን እንደፈጠረው የሚመረምር ይመስል ፊቴን ትክ ብሎ ያያል ።

ኒና በሁኔታው የተረበሸች መስላ ታየችኝ ።

«ውሻው ድንገት ችግር እንዳያመጣብኝ አሰብሽ እንዴ እመቤት» አልኳት ።

«የለም ፡ እንዲያው ገርሞኝ ነው ። ውሻዬ እንግዳ ይፈራ ነበር ። እንዲህ ያለ አቀባበል የሚያደርገው ለባለ ቤቱ ብቻ ነበር.....»።

ፌራሪ ከሀሳብዋ ጋር ተስማምቶ በነገሩ ግራ የገባው መስሎ ጉችር ብሎ ተቀመጠ ።

«እኔም በጣም ገርሞኛል» ብሎ ፌራሪ ሲናገር ውሻው ቀና ብሎ እምም በማለት ሲያጉመተምት ሲል በእግሬ ረገጥ አደረግሁትና ተመልሶ ተኛ ። ያሁኑ ሁኔታው ለኔም ገረመኝ ። ከመሞቴ በፊት ውሻዬ በፌራሪ ላይ እንዲህ ያለ የጥላቻ ምልክት አያሳይም ነበር ። ሁኔታቸውን ማረጋገት ስለነበረብኝ ፣ «እኔ በሕይወቴ ውስጥ ብዙ ውሾች አይቻ ለሁ ።'ብዙ ውሾች በእጄ አድገው ስላለፉ ውሾች ደግነትን



t.me/OLDBOOKSPDF

በእጇ ላይ የሚያሸቱ ይመስለኛል ። ስለዚህ የዚህም ውሻ ሁኔታ ይኸው ይመስለኛል ። ጌታው የሞተበትን ውሻ እንኳ እኔ ሄጇ ሳጽናና ውሻው የሀዘን ድምጹ ይቀንሳል ። ዛሬም ከመሄዴ በፊት ብትፈቅዱልኝ እኔው ባስረውና ብደ ባብሰው ከሀዘንተኛ ድምጹ እፎይታን ታገኛላችሁ» አልኩ ።

ለመሄድ ስነሳ ውሻውን አስሬ ተመለስኩ ። ሆቴሉ ድረስ አብሮኝ ለመሄድ የተነሳውን ፌራሪን ብቻዬን እንድ ሄድ ጠይቄ መለስኩት ። ራሴን ዝቅ አድርጌ እጅዋን ስሜ ተለያየን ። ፌራሪ በሩ ድረስ ሸኝኝና ዋናውን መንገድ እስ ኪይዝ ቆሞ አየኝ ። እንደሽማግሌ እግሬን እየጐተትኩ ቀስ ብዬ አዘገምኩ ። በሩ መዘጋቱን ስሰማ ዋናውን መንገድ ትቼ ወደጐን ሸውጄ በምሥራቅ በኩል ተክሉን እየከፋፈ ልኩ ግቢው ትይዩ ጉብታ ላይ ተደበቅሁ ። በረንዳው ፊት ለፊት ከመታየቱም በላይ የጊቢው ኮሽታ ሳይቀር ይሰማ ኛል ።

ኒና እና ፌራሪ ጉንለጉን ተቀምጠዋል ። እርስዋ ደረቱ ላይ ተደግፋ እርሱ እጇን በወገብዋ አዞሮ ተደላድለው ተቀ ምጠዋል ። በዚህ ዓይነት እቅፍ ለእቅፍ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ከተቀመጡ በኋላ ፣

«አንቺ ኒና በጣም ጨካኝ ነሽ ፣ ያንን ሽማግሌ የፈለ ግሽው መስሎኝ ነበር ።»

«ልክ ነውና አሁንም እፈልገዋለሁ ። ሽማግሌው ያንን አስቀያሚ መነጽር ባያደርግ እንከን የሌለው መልከመል



t.me/OLDBOOKSPDF

ካም ነው ። የሚሰጠኝ እልማዝ ደግሞ ሌላ ኃይሉ ነው ። ይልቅ ጨመርመር ቢያደርግልኝ እንዴት በወደድኩት።»

«ጨመርመር ቢያደርግልሽ የምታፈቅሪው ይመስል ሻል ኒናን?» እንደ ቀና በድምጿ ያስታውቃል ።« እኔ መቼም የምታደርጊው አይመስለኝም ። በዚህ ላይ በጣም በራሱ ይመካል ። ለምሳሌ ሴት አስቀድማ ካልጠየቀችኝ እኔ አል ጠይቃትም የሚለው አነጋገር አለው ።»

ከት ብላ የዘማዊት አሳሳቅ ከሳቀች በኋላ «ጥንታዊ አነጋገር ነው ። ድንቅ ሰው ነው ። ተነስ እንግባ ይልቅ ብርዱ መጣ ።» እቅፍ አድርጐ አነሳት ።

«ምንን ሽማግሌ አያትሽን በፍቅር ዓይን ስላየሽ አንድ መቶ ከንፈር ትቀጫለሽ፤ትንሽ ብልግና አለብሽ ፣ ከአያትሽ ጋር ትቀብጫለሽ ።»

«ስማ ይልቅ ጉዶ ሰውየው አንዳንድ ነገሩ ፋቢዮን አይመስልህም ። እኔ ብዙ ሁኔታው ፋቢዮን ቁርጥ ሆኖብ ኛል ።»

«እኔም እንዲህ ያለ ስሜት ከአንድ ሁለቴ መጥቶብኝ ነበር ። ግን ምን ሊሆን ይችላል ። አንዳንድ ሰዎች ራሳቸ ውን የሚመስል ጥላ ዓይነት ምስያ አላቸው ይባላል ። በኔ አስተሳሰብ ሰውየው የቅርብ ዝምድና ከሮማኒ ቤተሰብ ጋር ያለው ይመስለኛል ። የፋቢዮ አጐት ሊሆን ይችላል ። ደግሞ በጣም ሀብታም ነው ። ለኛ መቸም ጥሩ ጥገት ሊሆ ነን ይችላል ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

ተያይዘው ወደቤት ሲገቡ መስኮቱን ዘጉት ። ማንነቱን ባለመረዳታቸው ደስ አለኝ ። የወጥመዱ ቁልፍ አሁንም በእጄ መሆኑ አስደሰተኝ ። እስከአሁን ከእቅዴ አንድም የተበላሸብኝ ነገር ያለመኖሩ ልበሙሉ አደረገኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ዘጠኝ

ጊዜው ሳይታወቅ ከነፈ ። አንድ ወር ከዚያም ስድስት ሳምንት አለፈ ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ግን የሀብቴ ስፋት ፤ የአኗኗሬ ምላት ፤ የትልቅነት ዝናዬ በመላው ኔፕልስ ታወቀ ። ሀብታም ሆኜ መገኘቴ ብቻ በየትኛውም ከበርቴ ቤተሰብ ሁሉ ተቀባይነትን ሰጠኝ ። ከዚያ ሁሉ አድናቂዬ መሀል ብልህ ልሁን ሞሮን ፤ ሰይጣን ልሁን መልአክ ማንነቴን ለማጣራት የከጀለ አንድም ጠርጣሪ አልነበረም ። አስፈላጊው ብዙ ሀብት መያዝ በምርጥ ሰረገላ መንዝ ነው ፤ ምርጥ በልቼ ምርጥ ለብሼ በቲአትር ቤትና ስብሰባ የክብሩን ቦታ ይገኔ መቀመጤ በኔፕልስ ከተማ መታወቅ ያለበት ባለፀጋ አደረገኝ ። ጨረቃ በሰረቀ ቁጥር ለደስታዬ እየተጨነቁ ጣዕመ ዜማ የሚያሰሙ ሙዚቀኞችን ማዘዜ በአጭር ጊዜ በኔፕልስ መታወቅ ያለበትን ሁሉ በቅርብ እንዳውቅና እኔንም ማወቅ በሰዎች ዘንድ እንደብርቅ ነገር ተገመተ ። ስሜ የትም ተወራ ፤ ዕለታዊ ሥራዎቼ አለ በሚባለው ትልቅ ጋዜጣ በየጊዜው ይወጣ ጀመር ። የለጋስነት ዝናዬ እንዲህ በየአደባባዩ ፤ በየመጠጥ ቤቱና መገናኛው ሲዛመት ከኔ ጋር ለመተዋወቅ ብቻ ነጋዴዎች ለግል ሠራተኛዬ ለቬንቼንዞ ጉርሻ ሳይቀር ይሰጡት ጀመር ። እርሱም የተቀበለውን ጉርሻ ልክና የሰጠውን ሰው ጥልቀትና ቅሌት ዘርዝሮ ሳይደብቅ ይነግረኛል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሀብታምነቴ ካመጣልኝ ልዩ መስተንግዶ አንዱ አን ዳንድ ወጣቶች እየመጡ የጡት አባታቸው እንድሆን መጠ የቃቸው ነው ። ገና ሲጋ ቆንጆ ሴቶች በሰበብ አስባብ እየተ ዋወቁኝ ማዳም አሊቫ ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ በረቀቀ ጥበብ ይሞክሩ ጀመር ። የፈላጊዎቼን ሴቶች ጥረት መመር መሩ ብቻ ለኔ የጊዜ ማሳለፊያ ጊዜያዊ ሥራ ሰጠኝ ። ሽበ ቴን ሳይቀር ውብ ነው እያሉ የሚያወድሱኝ የልጃገረድ ዕድሜ ሴቶች ቋቅ እስኪሉኝ አጋጥመውኛል ። እንደ ኮከብ የሚያበራ የልጅነት ዐይናቸው ባገኘሁ አጋጣሚ ሁሉ ይጠ ቅሰኛል ። ከንዳቸው ያልተሸፈነ ቆንጆጆች ሴቶችን ዳበስ ሳደርግ «አድርግ» ከማለት የሚቆጠቡ አላጋጠሙ ኝም ። ሀብት የሚሰጠው እንዲህ እንዲህ ያለውን ድብቅ እድል ሁሉ መሆኑ ገባኝ ።

ለክብሬ ስል ብዙ ግብዣዎችን ደግሼ ስጠራ ቆንጆ ጆች ሴቶች ለሀብቴ ሲሉ በግብዣዬ ላይ ለመገኘት ጥረት አድርገው ይመጣሉ ። በአብዛኛው ግብዣ ላይ ኗና ኳና ጉዶ አይጠፉም ። ባለቤቴ በመጀመሪያዎቹ ግብዣዎቼ ላለ መገኘት ሞክራ ነበር ። ነገር ግን ይህን ልጅነት ይዘሽ በሀዘን መጨበጡ ዋጋ የለውም ስለምላት ፣ «እርስዎን በማ ክበር ብቻ ፣ የሮማኒ ቤተሰብ የቅርብ ወዳጅ በመሆንዎ ባለ ቤቴን በልጅነቴ ያውቁት ስለነበር ብቻ ነው የምመጣው» እያለች ትመጣለች ።

ጉዶን ግን በብዙ ዓይነት ስጦታ ልቡን ስለብኩት ። ከኔ ወዲያ የሚመካበት ሰው የሌለ እስኪመስለው ድረስ በየጊዜው ወለታዬን አከበድኩበት ። ሕይወቱን እንደም



t.me/OLDBOOKSPDF

ፈልግ እንዳይጠራጠር ዐይኑን በስጦታ ሸፈንኩት ። ሚስ ጢሩን ሁሉ አውጥቶ ይዘረግፍልኝ ጀመር ። በማን እጅ ውስጥ እንዳለ ለዘናጋሁት ። ሊኖረው የማይገባውን የረጅም ጊዜ እቅዱንና ውጥኑን ሲያወራልኝ እገረማለሁ ። ለጥፋት ቅጣት መኖሩን ፣ በሰፈሩት ቁና መሰፈርን መዘንጋቱ ያስገ ርመኛል ። እልፎ እልፎ ፍጹም ራሴን ዘንግቼ ሀጥያተኛ ነቱን ፣ ለቅጣት የቀረበ መሆኑን ፣ ቀኑ የተቆረጠች ጉድጓዱ የተማሰች መሆንዋን ንገረው ንገረው የሚል ግፊት ከው ስጤ ለመውጣት እንደ እሳተ ገሞራ ልፈትለክ ይልና እኔው እንደ ብልሀቴ ራሴን በራሴ እቀዘቅዘዋለሁ ። አንድ ቀን ግን ስሜቴ እንዳያጋልጠኝ እፈራ ነበር ። ብዙ ጊዜ ጉሮሮው ላይ ነክሼ ማንነቴን ለመንገር ቃጥቶኝ የመጨረሻዋን ሰዓት በመጠበቅ ብቻ ትእግስትን በግድ እገዛና ራሴን እቀ ዘቅዛለሁ ። ጉዶ ጥሩ ወይን ጠጅ መውደዱንም ስለማውቅ ክፍሌ በመጣ ቁጥር መስከሪያውን አስመርጠዋለሁ ። በእ ድሜ ከጓደኞቹ ፊት ሚስጢሩን በአደባባይ እንዲናገር እደ ርጋለሁ ። ሰክሮ ሲመለስ ኒና እንዴት አድርጋ እንደምታ ስተናግደው ሁሉ እውነቱን ከውሸት ሳይለይና ሳይደብቅ በመጠጥ አፍ እንዲለፈልፍ አደርገዋለሁ ። ኒና ከነገር ሁሉ ሶካራም ሰው እንደሚያንገሸግሻት ስለማውቅ አስከሬ እል ክላታለሁ ።

የሮማኒን ግቢ እንደልቤ በፈለግሁበት ሰዓት ገብቼ መውጣት ቻልኩ ። የፈለግሁትን ያህል ተጫውቼ መመ ለስ ለመድኩ ። እገዛ ንባብ ቤቴ የገዛ መጽሐፎቼን እን ብቤ ፣ ውሻዬን ፈትቼ በራሴው የአትክልት ቦታ እንደልቤ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንሸራሸረለሁ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን አንዲት ቀን እንኳን ሮማኒ ቤት አድሬ አላውቅም ። በእድሜ አንጋፋ ሰው ሊጠ ነቀቅበት የሚገባውን ሁሉ ሳላጓድል ተጠንቀቅሁ ። ጉዶን ከሚያስቀና ነገር ሁሉ ተወገድኩ ። በየማለዳው ሆቴል ክፍሌ ድረስ ጂና በሴት ሠራተኛዋ የምትልክልኝን ፍራፍሬና የእንደምን አደርክ ሰላምታ ለጉዶ ፈራሪ አልነግረውም ነበር ።

ባለቤቴ ሌሎች ቆንጆ ሴቶች እንደሚከታተሉኝና እን ደሚፈልጉኝ ማወቅ ስትጀምር ራስዋ በድብቅ ሆቴሌ ድረስ መምጣት ጀመረች ። ጉዶ እኔን በቀላሉ የሚደለልና የማ ይጠራጠር ምስኪን ነበር ባለው ዓይነት እኔም እርሱን ዓይኑ ሥር አታለልኩት ። እኔ እርሱን እንዳመንኩት እርሱም እኔን እንዲያምነኝ አደረግሁት ። አወዳደቁ ግን የተውተ በተበና ጥልቅ አዘቅት ውስጥ እንዲሆን ከወደቀ የሚንከ ታኮትበት እንጂ የሚተርፍበት እንዳይሆን ሸረብኩለት ።

ሮማኒ ግቢ በተመላለስኩ ቁጥር የልጇን የስቴላን ናፍቆት እስከረካ በድብቅ የአባትነት ፍቅሬን ሰጠኋት ። ሕጻንዋ በኔ መምጣት የተፈጥሮ ደስታዋ ሁሉ ተመለሰ ። በተፈጥሮ ማንነቴን ተረድታ ከሀዘንዋ ፍጹም ዳነች ። እን ዳንዴም ሞግዚትዋ ሕጻንዋን ሆቴሌ ድረስ እያመጣች አንድ ሁለት ሰዓት ከኔ ጋር እንድትጫወት ታደርጋት ጀመር ። ጉልበቴ ላይ አስቀምጬ የሕጻናት ታሪኮችን ሳወ ጋላት ልጇ በበለጠ ትደሰታለች ። የነሐሴ ወር መግቢያ ድረስ ደህና ታዳጊና ደስተኛ ሆነች ። ከዚያ በኋላ አንዳንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኔታዋ የሕመም ምልክት አመጣ ። እየከሳች መሄድ ጀመ
ረች ። ሰውነትዋ መገርጣት ያለወቅቱ ድካም ታየባት ።
ምግዚትዋ የሕጻንዋ ሁኔታ መለወጡን ለእመቤትዋ ብትነ
ግርም እመቤቲቱ ደንታም እንዳልሰጣት ሰምቼ እኔ ራሴ
አንድ ቀን ለኒና አነሳሁባት ።

በደግ አስተሳሰቤ አመስግና ልጅቱ ምንም የጠና እን
ከን እንደሌለባት ልትነግረኝ ስለሞከረች ጫን ብሎ መከ
ራከሩ ማንነቴን የሚያስጠረጥር ስለሆነብኝ ለጊዜው ጨክ
ኜ ዝም አልኩ ።

የነሐሴ ወር እንደተጋመሰ ሰው ከሸርሽሩ የመመለሺ
ያው ጊዜ ስለሆነ አንድ የዳንስ ግብዣ ለወዳጆቼ ለመስጠት
ስዘጋጅ አንድ ቀን ማለዳ ጉዶ ክፍሌን ለሚጠብቀው ቪንቼ
ንዞ መምጣቱን ሳይናገር አንኳኩቶ ማረፊያ ክፍሌ ጥልቅ
አለና ቀጥታ ሶፋው ላይ ውድቅ አለ ። በሁኔታው የደነገ
ጥኩ መስዬ ፡—

«ምንድነው ችግሩ» ብዬ የተጨነቀ ፊቱን ለማንበብ
እየሞከርኩ «የገንዘብ ችግር ከሆነ እንደራስህ ባንክ ልት
ተማመንብኝ ትችላለህ» አልኩት ። ውለታየ መብዛቱ እየ
ከበደው አስር አስሬ እጅ እየነሳ «የለም የገንዘብ ችግር አይ
ደለም ጌታዬ» ብሎ በዝምታ ዋጠው ። እንደገና ነገሩን ለማ
ወቅ ፤

«እንዴት ነው ወይዘሮዋ አላገባህም ብላ አስደነግ
ጠችህ እንዴ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እንዲህ እንዲህ እንኳን አይቃጣትም» አለኝ ።

«አይቃጣትም አልከን?»

«የለም እንዲህ እንኳ ማለቴ ሳይሆን ፡ ብዙ ምልክቶችን ካሳየችኝ በኋላ እምቢ አትለኝም ብዬ ነው ።» ሳያስበው ካፉ በወጣው ቃል እያፈረ አንገቱን ደፋው ።

«የፍቅር ወይም የገንዘብ ችግር ካልሆነ አንተን እንዲህ ያስጨነቀህ ታዲያ ምንድነው? ፊትህ ላይ ብርቱ ነገር ይታየኛል ።»

«ወያሮም መሄድ ግድ ሆኖብኛል ።» የደነገጥኩ መስዬ ፈዘዝኩ ። በለስ ስለቀናኝ ውስጥ ውስጡን ደስታ ሊገድለኝ ደረሰ ። ፍልሚያውን ትቶ እኔን ባለድል ለማድረግ መዘጋጀቱ አስገመኘኝ ።

«አጐቴ በጠና ታሞ እያጣጣረ ነው አሉ ። ባለፀጋ ስለሆነ ወራሹ ነኝ ። ነፍሱ ሲወጣ እዚያ መሆን እንዳለብኝ የሕግ አዋቂዎች አማክረውኛል ። ምናልባት ሁለት ሳምንት ቢፈጅ ነው ።» ይህን ካለ በኋላ በመጠራጠር ውስጥ ዐይኔን ትክ ብሎ ተመለከተ ።

«ታዲያ ምንድነው ጭንቀቱ እኔም የምታዘዝህ ካለ ከማዘዝ ወደኋላ አትበል ።» አልኩት ።

«የእርስዋ ነገር ብቻ ነው የሚያሳስበኝ ። መችም ልተማመንቦት እችላለሁ ። እርስዋን ይመልከቱልኝ ። ቆንጆ ናት፡ጥንቃቄም የጐደላት ናት ። እድሜዎ አንጋፋ በመሆኑ፣ አቋምዎ የሰከነ፡ለሮማኒ ቤተሰብም የቀረቡ በመሆንዎ ታከ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሮታለች ። ስለዚህ ሌላም ወንድ እንዳይደፍራት ፡ እር ስዋም፤አውቃም ሆነ ሳታውቅ በሌላ ወንድ እንዳትጠመድ ጌታዬን ማስቸገር ግድ ሆኖብኛል ።»

«እረ ምን ሲደረግ ይኸ ሁሉ ውስልትና ይፈጸማል» ብዬ የንዴት ተውኔት ተጫወትኩ ።

«ወዳጄ ጉዶ ልትተማመንብኝ ትችላለህ ። ወይዘሮዋን ጠብቄ አቆይሀለሁ ፡ እጅህን አምጣ» ብዬ በቃል ኪዳን ውስጥ እጁን ጣ አድርጌ መታሁት ። «ለጓደኛህ ለፋቢዮ ያደረግከውን ታማኝነት ሁሉ ከኔ ልታገኝ እንደምትችል አስተማምንልሀለሁ ።» አልኩት ።

ሳያስበው በመርዝ እንደተነደፈ ያህል ጉዶ የፋቢዬን ስም ሲሰማ ደነገጠ ። ፊቱ ገርጥቶ ፈዞ ቆመ ። ምንም ሊያ ደርግ ስለማይችል የቀፈፈውን ሁሉ በግድ አለባብሶ ።

«አመሰግናለሁ ፡ ታማኝነትዎን አልጠራጠርም» አለ ።

«እና መቼ ነው ጉዞህን ወደሮም የምትጀምረው ።»

«የግዴን ነገ በጠዋት ባቡር መጓዝ አለብኝ ።» ጽሕፈት ጠረጴዛዬ ላይ ያሉትን የግብዣ ካርዶች እያንሳሳሁ ፤

«የዳንስ ግብዣ ላደርግ ነበር ። እንግዲህ እስክትመጣ መቆየት አለበት ። ክብርት እመቤቲቱን ግን እስክትመጣ ብቸኝነቱ በጣም እንዳያጠቃት ከሌላው ዓለም ለይቼ አቆያታለሁ ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

ፊቱ እንደገና በደስታ ፈካ ። ሀሳቡ የተንጠለጠለባቸውን ጥርጣሬዎች ስላስወገድኩለት እየደጋገመ አመሰገነኝ ፣ እጇን ስሞ መረቀኝ ፣ ጠዋት ባቡር ጣቢያ ድረስ ሄጄ እንደምሸኘው ነግሬው እየፈነደቀ ወጣ ። ያን ዕለት ደግሜ አላየሁትም ። የት እንደነበር ለማወቅ ግን አያስቸግርም ። ሚሽቴን ሲሰናበት መሆኑ ይገባኛል ። እንዳትከዳው በጨረቃና ከዋክብት ሲያስምላት መሆን አለበት ። ተደብቆ የሚሰራውን ሁሉ በዐይነኅሊናዬ እያየሁ «ጉዶ ሆይ በርታና ዳግም እንዳያምርህ የመጨረሻውን የስርቆት ፍቅርህን ዘርፈህ ውጣ» አልኩት።«ይህ የመጨረሻህ ነው።ደግመህ እንዲህ ያለውን ሀጥያት እንዳትፈጽም ተንኮለኛው እጅና ልብህ ስለሚታሰር የመጨረሻው ንጥቂ!ህን ሰስን ። ሳም ፣ እቀፍ ፣ ቀንህ ግን ስላለቀ የመክዳት የመቀማትና የመዝረፍ እጣህ ተሟጧል ። የወይን ጠጅህን አሁን ከእጅህ ሳልደፋት ጨልጠህ ጠጣት ። ግን እንደማትደግማት አትጠራጠር ። በሩን በላይህ ላይ ዝጋ ፣ መብራቱን ለመጨረሻው ጊዜ አጥፋ ፣ የውሾችን ሙዚቃ ከፍተህ አድምጥ ። የመታመን ድምጽዋን በጆሮህ ታንቆርቁርልህ ። እመናት ። እንቡጥና ለግላጋ ገላዋን ለሌላ እንደማታሳይ ስትነግርህ እመናት ። ለስልስህ ተለሳልስህ ተለያት ። ደግመህ ግን አታያትም ። እስከመጨረሻውም አታያትም ።

በማግስቱ ልክ በባቡር መነሻ ሰዓት ባቡር ጣቢያ ተገኝቼ ጉዶን ሸኘሁት ። ዐይኖቹ ጉድጓዳቸው ውስጥ ገብተዋል ። ፊቱ በስጋት ነጥቷል ። እንደለማኝ አሮጊት በያዘው ቡቱቶ ምክንያት ከሚኞቹ ጋር ይናሚል ። አንባቢ ለመም


t.me/OLDBOOKSPDF

ሰል አንድ መጽሐፍ በቢጫ ወረቀት ሽፍኖ ይዟል ። በመጨረሻው ባቡር ውስጥ ቦታውን ይዞ ተቀመጠ ። ባቡሩ ሊነሳ ሲል አንገቱን ወጣ አድርጐ ፤

«አደራ እንግዲህ በደንብ ይጠብቁልኝ» ከማለቱ ባቡሩ ተንቀሳቀሰ ። ብቻዬን ቆምኩ ። እርምጃዬን ሁሉ ያለ ከልካይ ለመውሰድ ብቻዬን በመቆሜ ደስ አለኝ ። ሚሽቴን በፈለግሁበት ሰዓት ልገድላት እንኳ እንደምችል ተረጋገጠልኝ ፤ ያን ዕለቱን ማታ ውስልትነዋን ነግሬ ቅጣትዋን ለመወሰን እንደምችል ብረዳም የመጀመሪያውን እቅዴን መለወጥ እንደማያስፈልገኝ ተገነዘብኩ ። ሞት ይገባታል ፤ ግን እኔ ወንጀለኛ ተብዬ ለምን እንዴትስ ጣት ይጠቆምብኛል ። ይህን እያሰላሰልኩ ሳዘግም የከፍል ጠባቂዬ ቪንቼንዞ ትንፋሹ እየተቆረጠ ወደኔ ሲሮጥ አየሁት ። አስቸኳይ የሚል የጽሑፍ መልእክት ይዟል ። ተቀብዬ የሚሽቴን የእጅ ጽሑፍ ገልጬ ማንበብ ጀመርኩ ።

«ስቴላ በጣም ስለታመመች ቶሎ ይድረሱ ። ስምዎን እየጠራች ስለሆነ እባክዎ ቶሎ እንዲመጡ» ይላል ።

በጥድፊያ እየተራመድኩ ወረቀቱን ማን እንዳመጣ የልጅቱስ ሁኔታ እንዴት እንደሆነ ጠየቅሁት ።

ሴሊቱን ሕመም እንደጀመራት ፤ ትኩሳትዋ ከፍተኛ መሆኑን ፤ ያያትም ዶክተር ዘግይቶ በመጠራቱ የሕጸንዋ ጤንነት አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን ነገረኝና ልቤም ስሜቴም በአንድ ጊዜ ተሟሟተ ። ጉሮሮዬን የሚያንቅ እልህ ዐይኔን



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚጋርድ እንባ መጣብኝ ። ሠራተኛዩ ሰረገላ እንዲጠራ አዝዤው እኔ ጨርሶ መራመድ አቃተኝ ። ሰረገላው መጥቶ ወደቪላ ሮማኒ ዳገቱን ተያያዝነ ። ለቪንቼንዞ ቀኑን ሙሉ ሆቴል እንደማልመለስ ነግሬው ሄደ ። ቪላሮማኒ ስደርስ ትልቁ በር ተከፍቶ ጠበቀኝ ። የእንግሊዝ ተወላጅ ዶክተር ልጇን አይቶ ሊወጣ ሲል አገኘኝሁት እንዲመለስ ለመንኩ ትና ትንሽ ክፍል አስገብቶ በሩን ዘግቶ ስለሁኔታዋ ይነግ ረኝ ጀመር ።

«ይኸን ሁሉ ጣጣ ያመጣው ሕጻንዋ ሙሉ በሙሉ መዘንጋትዋ ነው ። በጥንቃቄ ጉድለት በሽታን የመከላከል ኃይልዋ ተዳክሞአል ። ሕጻንዋ በተፈጥሮ ጠንካራ በመሆ ንዋ ነው እስከአሁንም የቆየችው ። ትኩሳቱ እንኳ ገና ሲጀ ምራት ብጠራ ኖሮ ለማዳን አያስቸግርም ነበር ። ከእኩለ ሌሊቱ በኋላ ሞግዚትዋ እናቲቱ መኝታ ክፍል መግባት ስለፈራች ችግሩ ተባባሰ ። አሁን ሁሉ ነገር ከችሎታዬ ውጭ ሆኖአል ።» አለኝና ነገሩን ሁሉ እንደ ህልም አደመ ጥኩት ። ጉዶ ፈራሪ የመጨረሻ ፍትወቱን ሲሸራሞጥ የኔ ልጅ ሕመምዋን ያለ እናት እንድትሰቃይ መደረጉ አንገበ ገበኝ ። ፈዝዤ ነገሩን ሁሉ ስሰማ ዶክተሩ አይቶ «ልጅቱ ስምዎን ብዙ ጊዜ ስለጠራች እንዲጠሩ እናቲቱን እኔ ነኝ የገፋፋሁ ፤ እርስዎ እንኳን ሕመሙ ድንገት እንዳይጋባብ ዎት አመንትቶ ነበር ።» ሲል ፤

«እኔ ተስቦ የምፈራ ሰው አይደለሁም» ብዬ አቋረጥ ኩት ። እጇን ይዤ እንዲቆይ ስለምነው «ሕመሙን የሚከ ፍል መድሀኒት ለሞግዚትዋ ሰጥቻለሁ ። በእኩል ሰዓት


t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ሁሉን ነገር ማወቅ ስለምንችል ሰንት ሲደርስ እመ ለሳለሁ» ብሎኝ ሄደ ። እንዷት ቤት ልጇ የሕጻንዋን ክፍል ስትጠቁመኝ ደረጃውን መውጣት ጀመርኩ ።

ክፍሉ ስገባ ሞግዚትዋ ፊትዋ በሀዘን ተውጦ ከተቀ መጠችበት ተነስታ ተቀበለችኝ ። ምስኪንዋ ሞግዚት እን ደብርቅ በእንባ ዐይንዋ እያየችኝ ፡

«በእግዚአብሔር መንግሥት የማይፈለገው ብቻ ነው በዚህ ዓለም የሚኖረው፡መጀመሪያ ያን ደግ ጌታ ወሰደ ፡ ቀጥሎ ደግሞ ይህችን ሊወስድ ነው» አለች ።

ባጠገቤ አንድ የታመመ ድምጽ «አባዬ» አለኝ ። ስቴላ ቀና ብላ ዐይንዋን ቦልቀቅ አድርጋ ስትቀመጥ ጉን ጮችዋ በትኩሣት ፍም መስለዋል ። ከንፈሮችዋ ተሰንጣ ጥቀዋል፡ትንፋሽዋ አቀብ አቀብ ያቃትታል ። ሁኔታዋ እያ ንሰፈሰፈኝ በአባትንት ጭንቀት ልጇን ከእቅፌ ውስጥ አስ ገብቼ ሕመምዋን ለመካፈል ጥረት አደረግሁ ። የሚፋጀ ውን ፊትዋን ወደ ግንባሬ አስጠግቼ ፡

«ስቴላዬ ረጋ ብትይ ፡ ጥቂት አረፍ ብትይ ሕመምሽ በረድ ይላል ፡ አዎ! እንደዚህ ፡» መኝታዋ ውስጥ መልሼ ሳስተኛት ዐይንዋ ትክ ብሎ ከላዬ ላይ አልነቀል አለ ። እኔም ዐይን ዐይንዋን እያየሁ አልጋዋ አጠገብ ተንበርክኬ ሕመምዋ መቀነሱን አጠባበቅ ጀመር ። ስቃይዋ ግን አይ ቀንስም ። ሰዓቱ በደቂቃ በገፉ ቁጥር ትንፋሽዋ ችግርዋን ይናገራል ። ልብዋ በኃይል እየመታ ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

«አንተ አባቴ ነህ፤ አይደለህም?» አለችኝ ። በትኩሳት የነደደ እጅዋን እየሳምኩ ዝም አልኩ ። ሞግዚትዋ የሕጻንዋን ከንፈር በውሀ እያራሰች ታነባ ጀመር ።

«እባክሽ ሆዴ አትናገሪ ፣ አትወራጪ ፣ ያለዚያ የቆሰለው ጉሮሮሽ አይድንም» ብዬ አባበልኳት ።

«ዝም እንድል ከፈለግህ ሳመኝ» አለችኝ ።

የናፍቆቴንና የአባትነቴን ያህል ሳምኳት ። ዐይንዋን ሸፍና ከመወራጨት ረጋ አለች ። አሥር ደቂቃ ፣ ሀያ ደቂቃ፣ ሀያ አምስት ደቂቃዎች ፀጥ ብላ አረፍ አለች ። ዶክተሩ ባለው ሰዓት መጥቶ ገባ ። እንዴት ነች ብሎ ጠየቀኝ ።

ዐይንዋን ገልጣ በፈገግታ ሶስታችንንም አየች ። «ምን ሽን ነው አሁን የሚያምሽ » አልኳት ።

«አያመኝም ፣ ምንም አያመኝም»

«ባለጌ ልጅ ስለሆንኩብህ ነው ትተኸኝ የሄድከው? ነው እንዴ አባዬ?» አለችኝ ። ከአልጋዋ ላይ አንስቼ ፊቴን በፀጉርዋ ሸፍኜ «አይደለም ሆዴ» አልኳት ።

«ለምንድነው ይህን አስቀያሚ መነጽር ዐይንህ ላይ የምታደርገው?» አለችኝ ። ድምጽዋን ሌላ ሰው እንዳይሰማት ዝቅ አድርጋ «ዓይንህን ሰው መታህ እንዴ? መነጽርህን አውልቅና ዐይንህን አንዴ አሳየኝ ።» ብላ በሕጻን እንደበትዋ ለመነችኝ ። ሞግዚትዋም ዶክተሩም እንዳያዩኝ ተከልዬ መነጽሬን አውልቄ በዐይኔ ሙሉ አየት አደረኳት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የሰበው እንደተሚባለት ሰው ካለመጠን ፈንድቃ «አባዬ ፡ አባዬ ፣ አባዬ» ብላ ጮኸች ። ወዲያው ትንሽ ሰውነትዋን በሙሉ እንደወባ ሰበቃት ። አንቀጠቀጣት ። መነጽሬን ስመልስ ዶክተሩ ወደ ሕጻንዋ ተጉነበሰ ። ፊትዋ እንደነደደ ቅጠል ከመቅጽበት ተለዋወጠ ። ትከሻዬ ላይ እንዳለች ተዝለፈለፈች ። ጉሮሮዬን የእልህ እንባ ተናነቀኝ ። የልጇን ቀዝቃዛ ሰውነት እንደተሸከምኩ የጨው አምድ ሆኜ ቀረሁ ። እንባዬ ትኩሳቴን እየገመሰ በጉንጮቼ ወረደ ። ከፍሉን የሞት ዝምታ ጭጭ አደረገው ። ሙልእከ ሞት የልጇን ነፍስ ይዞ ሲወጣ ሞግዚትዋ እሪ ብላ ጮኸች ። ያቺን አንዲት እንቡጥ አበባዬን ከማይጠወልገው የገነት አበባ መሀል ለመትከል ሞት ይዟት ኮበለለ ።

ጥቂት የመከራ ጊዜ እንዳለፈ ዶክተሩ ድምጹ በሀዘን ኮስሶ ፣ «እባክዎን ከሕመምዋ ሁሉ የተገላገለችውን ሕጻን ያሳርፍዋት ፣ አባትዋ መስለው የመጨረሻ ሕይወትዋን ደስታ ሰጥተውት አልፋለች ። የእርስዎንም ጤንነት በጣም ያናጋችው ስለመሰለኝ ያሳርፍዋትና ይረፉ ።»

ሳስተኛት የትራስዋ ሙቀት ገና እንዳለ ነው ። ዐይኔን በዕንባ ጨፍኜ እንደ እሳት የሚንቦገቦገውን ዐይንዋን ከደንኩ ። እንደሰም የቀለጠ ጉንጭዋን ሳምኩ ። ከንፈርዋን በአፌ አማትቤ እጆችዋን እንደፀሎተኛ አመሳቀልኩ ። ፊትዋ ላይ ፈገግታ ነበር ። ፈገግታዋ ውስጥ ከሕይወት የጠለቀ ከማር የጣፈጠ እማይሞት መሳይ ግርማና እውነት ነበር ። ሞግዚትዋ የአንገትዋን መስቀል በጥሳ ህፃንዋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ደረት ላይ አስቀመጠች ። ፀፀትና እፍረት የደበቃትን እናት ዋን ሊታረዳ ሞግዚትዋ ደረጃውን ስትወርድ ሁሉም ነገር በመበላሸቱ ልዩና የማልጠብቀው ሀዘን ተሰማኝ።ቢቸግረኝ ልጇ እስከመጨረሻው የቁም ስቃይ ሙት ሆና የምድርን ሀጥያትና ጽድቀት ሳታይ ማረፍዋ ደስ አሰኘኝ ። አድጋ ሴት ሆና ሴት ልጅ የምትፈተነውን ፈተና ሁሉ ከመቀበል መዳ ንዋ አስደሰተኝ ። የወንድ ባሪያ ከመሆን ፣ የጉልበት እናሳ ከመሆን ፣ ወንድ ሲያዝንላት በደንብ የምትኖር ፣ ሲጨክን ባት በጉስቁልና የምትሰቃይ ከመሆን በመዳንዋ ልቤ ከጭ ንቀት አረፈ ።

እስከሬንዋ ከተስተካከለ በኋላ ዶክተሩን ተከትዬ ደረ ጃውን ወረድኩ ። እናቲቱ ከፍልዋ እንዳለች መጮህ ጀመ ረች ። ዶክተሩ እንኳ ታዝቦ «ማስመሰል የምትችለዋ እመ ቤት መጮህ ጀመረች እንግዲህ» አለ ።

ነገሩን ለማደናገር «መልከ ቀና ሴቶች ብዙ ጊዜ የሚ ደርስባቸውን መገመት አይችሉም» አልኩትና እመቤቲ ቱን ለማጽናናት ከፍልዋ ገባሁ።የቤቱን እቃ እየዞርኩ የማይ መስዬ እንባዬ እንደልቤ ወርዶ ሀዘኔን ስቃመስ ዶክተሩ ወዲያውኑ እየተጉመተመተ ወጣ ።

«አሁን ቢጮኹ ፣ ቢዘሉና ቢፈራገጡ ፣ ነፍስ አጥተው ቢፈሱ ቢቅለሰለሱ ምን ይጠቅማል ። እርስዎ ይልቅ ለጊ ዜው ሆቴልዎ ይግቡና ጠንከር ያለ ወይንጠጅ ይጠጡ ።» ብሎኝ እጄን ጨብጦ ወጣ ። ሚሽቴ አንጋፋውን የአባቴን ሠራተኛ ሳሎን እንደቆምኩ ላከችብኝና



t.me/OLDBOOKSPDF

«ብዙ አላቆይህም ፣ ሳላናግርህ እንዳትሄድ ብላህለች» አለኝ ። የእባቷ ሎሌና አማዳጊዋ ሮማኒ ግቢ መምጣት ከጀመርኩ አንስቶ ፋቢዮ መሆን ያለመሆኔን ሲመረምር ከኖረ በኋላ በመጨረሻ መወሰኑን አንተ ብሎ ሲያናግረኝ ገባኝ ። እቅዶ ሊበላሽ እስጊ አፋፍ ላይ መድረሱ ስላስፈራኝ የግድ መከላከል ነበረብኝ ።

አስተያዩቷን በንቀትና እብሪት የተሞላ በማስመሰል «ወደ ጂልነት ያመራህ ይመስለኛል ሰውዬ ። ይልቅ ሂድና እመቤትህን በምትፈልገኝ ጊዜ ሁሉ ልታዘዛት ዝግጁ መሆኔን ንገራት ። ገባህ ወይስ ልድገምልህ ።»

የታማኝ አሳዳጊዬ ፊት በአንድ ጊዜ በእፍረት ኩስምን ብሎ ጠወለገ ።

«አሁንስ መሳሳቴ በትክክል ገባኝ ። የኔ ጌታ እንዲህ እናግሮኝ በጭራሽ አያውቅም» ብሎ እየተበሳጨ ወጣ ።

እየተጉመተመተ ሲወጣ ልቤ እንደ አሎሎ ከበደኝ። በሀዘን ላይ ሀዘን ተሰማኝ ። የጥንት ወገኔን በንግግሬ አስከፋሁት ፣ ምርጫ አልነበረኝም ። ይህን ሁሉ የመከራ ቀንበር ይገፍ ብቻዬን መቆምን ወድጄ አልመረጥኩም ። ፎቅ የተኛችውን ልጄን በመንፈስ ተሰናብቼ ከቤት ወጣሁ ። መስኩ ላይ ልጄ ለውሻው እየወረወረች የምትጫወትበትን ኳስ እየተገላመጥኩ አንስቼ ኪሴ ከትቼ ወደ ሆቴሌ አመራሁ ። ሆቴሌ እንደደረስኩ ቪንቼንዞን ማንም ሰው ቢፈልገኝ የለሁም ብዬ በሬን ዘጋሁ ። የልጄ መሞት ያስደሰተኝ መሆኑን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰዎች ሲሰሙ ጨካኝ ይሉኝ ይሆናል ። ሊደርስባት የሚችለውን መከራ ግን ሳስብ መሞትዋን አሁንም እመርጣለሁ ።

ክፍሌ እንዳለሁ ጉዶ ፌራሪ የስቴላን ሞት እንዲረዳ ቴሌግራም ወደ ሮም አደረግሁ ። ባያዝን መደንገጡ እንደማይቀር ገመትኩ ። ወይዘር ኒናን ግን አጽናኝ እንደማያስፈልጋት በትክክል እንደሚረዳ አወቅሁ ። ሕጻንዋ በሁለቱ መሀል እየገባች አስቸግራቸው ስለነበር መሞትዋ ለሁለቱም ግልግል ሳይሆን አልቀረም ። የሕጻንዋን አሟሟት እንደ ኔው ሞት እንደበረከት ነው የሚቀበሉት ። ልጂ ግን አረፈች ። የባከኑ ወላጆችዋን ታሪክ እያውጠነጠነች አድጋ የጉድ ልጅ ከምትባል መሞትዋን መረጥኩ ።

የልጇ የስቴላ የቀብር ሥነ ሥርዓት መፈጸሚያው ደረሰ ። እናቲቱን ስላመማት ቀብሩን እኔው እንዳስፈጽም ጠየቀችኝ ። በሮማኒ ቤተሰብ መቃብር ቤት ውስጥ የሕጻንዋ አስከሬን እንዲያርፍ ለመከላከል እድሉ ስላጋጠመኝ ተደሰትኩ። ያቺ ሀጥያት ያልነካት እምቡጥ አበባ እዚያ ማስ ፈራሪያ ዝግ ቤት እንዳትገባ ከሚመለከተው ጋር የመቃብር ቦታ መረጥኩ ። እኔ ራሴ ከመቃብር ቤቱ ወጥቼ መጀመሪያ የቆምኩበት ዛፍ ሥር ጉድጓድ ተቆፈረ ። እዚያ ሞቃቱ እናት አፈር ውስጥ ውድ ልጂ አረፈች ። የተመረጠ ሙሽራ አበባ ችምችም ብሎ መቃብርዋ ዙሪያ ተተከለ ። በተራ የእ ብነበረድ መስቀል ላይ «የጠፋችው ኮከብ» ከሚለው ሥር የቤተሰብዋ ስም የትውልድና የሙት ቀንዋ እንዲጻፍ አደ ረግሁ ። በዚሁ ዓይነት የልጇ ቀብር ተፈጸመ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አሥር

ይህ ከተፈጸመ በኋላ እየተመላለስኩ ብዙ ጊዜ ሚሽቴን ጠየቅኋት ። ለሌላ ሰው ሲሆን በልጅ ሞት አመካኝታ የለሁም እያለች የማትገኘዋ ለእኔ ግን ብቻዋን ቤት ውስጥ ታነጋግረኛለች ። የሚገርመው ግን ሰውነትዋ በሀዘኑ ምክንያት ፀመጕሣቆል ፈንታ ይበልጥ እያማረባት መሄዱ ነው ። የውበትዋን ኃይል ስለምታውቅ ፣ እኔን ለማጥመድ ማታለያዎችዋን ሁሉ ዘረጋች ። እኔ ግን ፍንክችም አላልኩ ። አበከራ ካላስጠራችኝ መሄዱንም አቆምኩ ። ይባስ ብዬ እንክብካቤዬንና ጉብኝቴን ሆን ብዬ ቀነስኩ ። ብሄድም የእርስዋን ውበት ከማድነቅ ይልቅ የሚነበብ ነገር ፈልጌ እዚያ ላይ ማተኮር ጀመርኩ።አልፎ አልፎ ከጉዶ ዘንድ ደብዳቤ ይመጣላታል ። በልጅቱ ሞት ማዘኑን በቃልዋ ትነግረኛለች ። ለኔ በጻፈው ደብዳቤ ግን የልጅቱ መኖር ልረሳው የሚገባኝን ስለሚያስታውሰኝ መሞትዋን የምፈልገው ነው ብሎኛል ።

•

ስለ አጐቱ ጉዶ ፈራሪ ሲጽፍልኝ ፣ «አጐቴ ሞት በራፍ ላይ ተገትሮአል ፣ በራፉ ወለል ብሎ ተከፍቶለት ሳለ በሩን ለመግባት እስከአሁን አልወሰነም ። የእርሱ ማመንታት የትም እንደማያደርሰው ሀኪሞች ነግረውኛል ፣ ቢሆንም ባይሆንም ከእንግዲህ እዚህ ብዙ መቆየት አልችልም ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

የአጐቴ የውርስ ሀብት ይቅርብኝ እንጂ ከኒና ተለይቼ መቆየቱን አልወደድኩም ። ምንም እንኳ እርስዎ በታማኝነት ቢጠብቁልኝም ብዙ መዘግየቱ መዘዝ ስለሚያስከትል ፈጥኜ እመጣለሁ» ይላል ደብዳቤው ። ይህንኑ የደብዳቤውን ቃል በተለይ እንዳለ ለኒና ሳነብላት ደንግጣ አደመጠችው ። ቃሉን እያፍረጠረጥኩ ዝግ ብዬ ሳነብ ስሜትዋን ለማወቅ ፊትዋን እየሰረቅሁ ተመለከትኳት ። ከማነበው የደብዳቤ ቃል ይበልጥ በሰማች ቁጥር ጉንጮችዋ ሀፍረት በተቀላቀለበት ሁኔታ ቃሉ የአታላይነት ገጽታዋ ፊትዋ ላይ ወለል ብሎ ቅንድቦችዋ ለብዙ ጊዜ በማውቀው ዓይነት ተጠማዘዙ ። ከንፈሮችዋ በመጨረሻው ፈገግ ብለው ለመናገር ሲዘጋጁ ቅዝቃዜም ውብትም እየታየባቸው ፤ «በእውነት በጣም ነው የማመሰግንዎት ጌታዬ ። ይኽ የፈራሁን ብልግና በትክክል አረጋግጦልኛል ። ባለቤቴ ለእርሱ የነበረው ቅርበትና አሁን እርሱ በኔ ላይ የሚያሳየው ስልጣን ፍጹም ተቃራኒ ነው ። ታላቅ ወንድም በእህቱ ላይ ያለው ዓይነት የበላይነት ነው የሚያንፀባርቀው ፤ የማዝነው በሌላ ሳይሆን እስከአሁን ባላየሁት ትእግስት ነው ። በላዬ ላይ እንዲጨፍር ነው ያደረግሁት ።

«እውነትን?» ብዬ በመቆጨት አዳንቅሁላትና ማሰብ ጀመርኩ ። አሁን እሞቀው መራር ጫወታ ተዳርሰናል ። ከእንግዲህ ማመንታት እንደማያስፈልግና የገበጣው ውጣ መካሄድ እንዳለበት ገባኝ ። የጉዶን ደብዳቤ ወደ ኪሴ እየመለስኩ ፤ እኔ እንደገባኝ ሲኖር ፈራሪ እኮ የሚያስበው በቅርብ ቀን አንቺን ለማግባት ነው አልኳት ። እዚህ ላይ የቴአ



t.me/OLDBOOKSPDF

ትር ችሎታዋን ሁሉ አውጥታ በንዴት ፊትዋን ከሰከሰች ። ዐይንዋን አጉረጠረጠች ፣ ከንፈርዋን ነከሰች ያ ሁሉ መተሻሸት ፣ መሳሳምና ቃል መለዋወጥ እንደድንጋይ ላይ ውሃ ባከና የቀረ ይመስል «የጋብቻው ነገር እንኳ መልክ ያጣ ድፍረት ነው» አለች ። እኔን እንደከዳች ጉዶንም ከድታ እንደገና እኔኑ ከወጥመድዋ ለመክተት ሽንጥዋን ትስብቅ ጀመር ። ኮስተር ብዬ እርምጃዬን መውሰድ ጀመርኩ ።

«ማንም ወንድ ያለፈቃድሽ ሊደፍርሽ አይችልም...... ግን ለሲኖር ፌራሪ ምንም የመውደድ ስሜት የለሽም?»

«እረ ምንም ነገር ። እርሱ ደፋርና ባለጌ ነው ። በዚህ ላይ ለወይንጠጅ ያለው ፍቅር ይኸ ነው አይባልም ። እረ እንዲያውም ለሕይወቴ ያሰጋኛል ።»

«ይኸ ከሆነ ፌራሪን ሀዘን ይገጥመዋል ። ብቻ ምን ያደርጋል ፌራሪ ካልተሳካለት ፣ ደግሞ ሌሎች እድላቸውን ይሞክራሉዋ»። አልኳት ።

«እኔ ከዚህ ሁሉ እርሱ ከሮም ከመመለሱ በፊት እኮ ልስን ጥዬ ብሄድስ ?»

«እኮ ለምን ?»

«የለም እርሱ ብዙ ጣጣ ውስጥ ነው እስከአሁንም የከተተኝ ። በዚህ ላይ በሁኔታው ሁሉ እየፈራሁት ሄጃ ለሁ ። በእርስዎ ሥር እስካለሁ ድረስ ማንም አይደፍረኝም ። ግን ይኸ ደግሞ እርካታ አይሰጠኝም ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

ትጭም ብዬ ፣ «ለምን እርካታ አይሰጥሽም ?»

ደንግጣ ከመቀመጫዋ ብድግ አለች ። «ምን ማለትዎ ነው ጌታዬ እስተያየትዎ ሊገባኝ አልቻለም»።

«በኔ ሥር መጠበቁ አያረካሽም ብትይኝ እኔ ደግሞ ምኞቱ ከሆንሽ ልትረኪ ትችያለሽ ነው የምልሽ።»

«ጌታ ሲዛር!» ትን እንደማለት አላትና አረጋጋኋት ።

«በእርግጥ በመሀላችን የእድሜ ልዩነት መኖሩን አውቃለሁ ። በዚህ ላይ የጤና ፣ የገልምስና መልክና የወጣትነት ገጽታ በኔ ላይ የተዳከመ መሆኑን አውቃለሁ ። ሀዘንና ብስጭት ነው እንዲህ ያደረገኝ ። ግን ተዝቆ የማያልቅ ሀብት አለኝ ። በኅብረተሰቡ ዘንድ መከበርንና መታመንን አትርፌአለሁ ። በዚህ ላይ የምትፈልጊውን ሁሉ ማሟላት ለኔም ደስታ ይሰጠኛል ። ከኔ ጋር መኖር ደስታ የሚሰጥሽ ከሆነ ሳትሸሽጊ በይፋ ንገሪኝ ። ደሙ በርዶአል ፣ ፍላጐቱ ረግቷል ብለሽ እንዳትሳሳቺ እኔ ተግባሬን በደንብ እንደ ምፈጽም አረጋግጥልሻለሁ ።»

ይህን ካልኩ በኋላ ዝም ዝም ተባባልንና በሀሳብ ተውጣ ቁጭ አለች ። ጥቂት ቆይታ ፍቺ እንደተገኘለት ሀልም ከንፈርዋ በፈገግታ ተፈታ ። ዐይንዋ በላዩ ላይ ስቅል ብሎ በማፍቀር ዓይን አየችኝ ። ትሰራ የነበረውን የጥልፍ ሥራ አስቀምጣ ቀስ ብላ ጠጋ አለችና ጣፋጭ ትንፋሽዋ ጉንጬን አሞቀው ፣ አስተያየትዋ አስደነቀኝ ። ወዲያው የደም ስሮቼ ሁሉ በተመስጦ ተንቃቁብኝ ። በአንድ ጊዜ ከአንቱ ወደ አንተ ተሸጋገረች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«እኔን እኮ እንዴት ሳታፈቅረኝ ሊታገባኝ ትጠይቀ ኛለህ? አታፈቅረኝም አይደል?» አለችኝ ። በማግባባት ዓይነት እጅዋን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጋ እንደደከመው ሰው ላዩ ላይ ስልምልም አለች ። ፀዋታ ዋጠኝ ። በውስጤ ተራ ፍላጐት ተዛመተብኝ ። የሚያሳሳ ከንፈርዋን በአፌ ክድን የማድረግ ፍላጐት በውስጤ ጋለ ፣ ወፈፍ ያደረገኝን ፍላጐት እንደምንም አቀዝቅዤ ራሴን ለዝምታ አስረከ ብኩ ። ጣቶችዋን በፀጉሬ ውስጥ እያስኬደች ፣

«አንተ ግን አትወደኝም ፣ አይደል? እኔ ግን እውነቱን ልንገርህ አፈቅርሃለሁ»

ውሸትዋን ስትደረድር ፈገግ ብላ ስለሆነ የቅንጣት ያህል አልተጠራጠርኩም ። እንደ አባብ የተጥመለመለብኝ የመሰለኝን እጅዋን ወደታች አውርጄ ተጫንኩና «እው ነት ታፈቅረኛለሽ? በጭራሽ ፣ እኔ አላምንሽም ፣ ሊሆንም አይችልም።»

አለሳልሳ እንደገና ሳቀች ። «ግን እውነት ነው ። መጀ መሪያ ገና ሳይህ እንደማፈቅርህ አውቄው ነበር ። ባሌን እን ኳን አልወደድኩትም ። ምንም እንኳ በአንዳንድ ሁኔታህ እርሱን ብትመስል በሌሎች እርሱን ታስከነዳዋለህ ። ብታምንም ባታምንም በዓለም ካሉ ወንዶች ሁሉ ያንተን ያህል ያፈቀርኩት የለኝም ።»

አቤት ያላት የማስመሰል ችሎታ! ይህን ስትናገር ፊትዋ ላይ እፍረት እንኳ የላትም ። እንዲያውም የህሊና



t.me/OLDBOOKSPDF

ኩራት ያላት ይመስላል ። በማስመሰል ችሎታዋ እየተገረ
ምኩ ፤

«እንግዲያማ ሚሽቴ ትሆኛለሽ ማለት ነዋ?»

«እሆናለሁ ፤ ስምህ ሲዛር ነው አይደል ?»

«ነው ።»

«እንግዲህ ሲዛር ፣ መጀመሪያ በጣም እንድታፈቅረኝ አደርግሃለሁ ።»

በፍላጐት የፋመ ፊትዋን ከብለል አድርጋ «ሳመኝ» ብላ ጠየቀችኝ ። ማብቂያ እንደሌለው ሕልም ሳላመነታ ያን የውሸት ቋት ከንፈርዋን ሳምኩ ። ከእርስዋ ይልቅ ከን ፈሬን ለመርዛሙ እባብ ማቅረብ ምንኛ በቀለለኝ ነበር ። መሳሙን ከሳምኩ በኋላ ብዙ ሕመም በውስጤ ተቀሰቀሰ ። አለሳልሼ እጅዋን ከአንገቴ ዙሪያ አወረድኩ ።

በፍቅር መንፈስ ጐንለጐን እንደተቀመጥን ፣ «በእውነት ታፈቅሪኛለሽ?»

«አዎን»

«ለመጀመሪያ ጊዜ በእውነት የወደድሽው እኔን ነው አልሽ?»

«አንተ ነህ የመጀመሪያ እውነተኛ ፍቅሬ ።»

«ፈራሪን አትወጂውም ማለት ነው?»

«በፍጹም።»

«እንደኔ ስሞሽ ያውቃል?»

«እንዴም አልሳመኝ እንዳንተ»


t.me/OLDBOOKSPDF

አቤት ውሸቷ እንዴ ቂቤ ሲወርድ ያዝ እንኳ አላደረ ጋትም ። እጅዋን ስቤ ፣ የቀለበት ጣትዋን አቅንቼ መጀመ ሪያ ያጠለቅሁትን ቀለበት አውልቂ በቦታው በአልማዝ የነደደ ቀለበት ከተትኩላት ።

«ውይ ሲዛርዮ እንዴት ደስ ይላል!»

በደስታ ግጥም አድርጋ ሳመችኝ ። እጅዋን ወደላይ አንስታ አልማዙ ከጨረሩ ጋር ሲፈልቅ አየት አደረገች ።

«ግን አሁኑኑ ስለመጋባታችን ለጉዶ እንዳትነግር።»

«በእርግጥ አሁን አልነግረውም።ሲመለስ ነው የምነ ግረው ። አሁን ከነገርኩት ከሮም ሲገሰግስ ይመጣል ።»

ለጥቂት ደቂቃዎች ሁለታችንም ፀጥ ብለን ተቀመጥን ። ያቀፈችኝ የመጀመሪያ ባልዋ ፣ የከዳችኝ ባልዋ ፣ በመሞቴ ደስ ብሎኛል ያለችው ባልዋ ፣ ጅል ነው ብላ ያላገጠችብኝ ባልዋ እኔው መሆኔን ብታውቅ እንዲህ ፈገግ ብላ ትቀመጥ ነበር? እንዲህስ ትስመኝ ነበር? ብዙ ጥያቄ መጣብኝ ።

ለጥቂት ደቂቃዎች የሰጠኋትን ቀለበት ጣትዋ ላይ እየጠመዘዘች ደረቴ ላይ አረፍ አለች ። አልፎ አልፎ አየት ታደርገኛለች ።

«እባክህን እንዴት የምጠይቅህን ትፈጽምልኛለህ?» አምቢ በማያሰኝ ለዛ ጠየቀችኝ ። «ትንሽ ነገር ናት ። የምትሰጠኝ ደስታ ግን ትልቅ ነው ።»

133



t.me/OLDBOOKSPDF

«ምንድነው እርሱ ፣[እንቺ ለመጠየቅ እል ደግሞ ለመ ፈጸም ነው ያለሁት ።»

በአስተያየቴ መተማመንን ገለጽኩላት ።

፣እሺ እንግዲያስ ፡ ይህን የጨለመ የዐይን መነጽር ህን ፤ ልአንድ አፍታ አውልቅልኝ ።» ከሶፋው ላይ በርግጌ ተነልቼ በማዘን፡

«ምንም ነገር ጠይቂኝ ይኸ መነጽር ግን ከዐይኔ ላይ ከተነሳ ለሚቀጥሉት ረጅም ሰዓታት በነርቭ ሲስተሜ ላይ ሀውከት ይፈጥርብኛል ። እባክሽ ለጊዜው እንዲሁ አይተ ሽኝ ደስ ይበልሽ ። ወደፊት ግን ማውለቄ አይቀርም።»

«መቼ?»

መልሴን በጉጉት ስትጠብቅ እጅዋን ላም አድርጌ «የጋብቻችን ምሽት ነዋ!» አልኳት ።

እንደማፈር ብላ ፊትዋን ዞር አደረገች ።

«ያ በጣም ረጅም ጊዜ ይወስዳል»

«ብዙ ጊዜ የሚወስድ አይሆንም ። አሁን መስክረም ነን ። ሠርጋችን በኅዳር እንዲሆን ብትፈቅጂ ደስ ይለኛል ።

«ባል የምተብኝ ነኝ በዚህ ላይ ስ ቴላ» ስሜትዋ ተከዝ አለ ። የሽቶ መሀረብዋን አውጥታ ሽፋሽፍትዋ ሥር ጫን ጫን አደረገች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በኅዳር ባለቤትሽም ከሞተ መንፈቅ ይሆነዋል ። የመንፈቅ ሀዘን በእንቺ እድሜ ላለች ቆንጆ ሴት በቂ ነው ። የልጅሽ ሞት ብቸኝነቱን እንደሚያባብስብሽ የታወቀ ስለሆነ የግድ አንድ አጽናኝ እንደሚያስፈልግሽ ሁሉም ያውቃል ። በዚህ ላይ እኔ የሚመጣውን ጉምጉምታ ሁሉ ፀጥ የማድርግበት ዘዴ አለኝ ።»

መንፈስዋ ሁሉ ደስ መሰኘቱ ከፈገግታዋ ይነበባል ። «በኔፕልስ ካሉት ባለሙብት ወንዶች በሴቶች ላይ በመኩራት የታወቅከው ጉበዝ ዛሬ እንዲህ ለሠርግ ከተጣደፍክ ፡ የምትለኝን ሁሉ አልቃወምም ።»

አስተያየትዋ ለወጥ አለ ። የፍትወት ፍላጎቷ ቶሎ ገባኝ ። እንደገባኝም ገባት ፡ «እመቤቴ እኔ እኮ የምፈልግሽ እስከመጨረሻው እንዳትለይኝ ነው ። እኔ የፍቅር ጥበብ አላውቅም ።»

«ማወቅህን አታውቅም እንጂ ጥሩ ፍቅረኛ ይወጣሀል ። እኔ ምንም ዓይነት ልዩ ፀጋ አልፈልግም ። በአንተ ሥር መኖር ታላቅ ጥላ ማግኘት ነው ለኔ ።»

«ሁሉም ነገር እንዳልሽው ይሆናል ። አሁን ግን ልሂድ እየጨለመ ነው ። የጤንነቴን ሁኔታ ታውቂዋለሽ ።»

«እረፍትና መዝናናት ጤናህን ሊመልሰው ይችላል ። ይህን ደግሞ እውን ለማድረግ እታገላለሁ ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ያስቸግራል ፤ አዝናለሁ ፤ ለራስሽም እንድታጤኚው የምፈልገው እንደባል የመረጥሽው ሰው ብዙ ችግር ያለው ነው ። በወጣትነት ሕይወትሽ ላይ የወሰድሽውን ውሳኔ አስተውለሻል።»

«አውቃለሁ ፤ አፈቅርሀለሁ ። ይህን ያህልም በሽታ የሚያጠቃህ አይመስለኝም ፤ በዚህ ላይ ሰውነትህ ጠንካራ ነው፣ገና ያልተነካ ሰውነትህ ውስጥ ብርቱ ጉልበት አለህ ።»

«ጉልበትስ አለኝ ፡ ይመስገነው።» ሳላውቀው ሰውነቴን ቀጥ አድርጌ ቆምኩ ። ለጥቂት አፍታ ሁለንተናዋ በሙሉ ልውጥውጥ ሲል ታየኝና

«ምነው ምነው የኔ ቆንጆ አመመሽ እንዴ?» ብዬ ልትወድቅ የነበረችዋን እቅፍ አድርጌ እንደገና ነፍስ ዘራች ።

«በስመአብ» አለች፣«እ—ንገረኝ እባክህ ከሮማኒ ቤተሰብ ጋር የቀረበ ዝምድና አላችሁ? አሁን ከተቀመጥክበት ብድግ ስትል ልክ ፋቢዬን መሰልከኝ ።»

ሶፋ ላይ አስቀመጥኳት ። ዐየሩ ቢቀዘቅዝም መስኮቱን ከፈትኩላት ።

«ደክሞሽ ነው እመቤቴ ። በሀሳብሽ ስዕል እየሳልሽ ነው ። ከሮማኒ ቤተሰብ ጋር ለዛቸው እንጂ ደማቸውስ የለኝም ። አንዳንድ ሰው ይመሳሰላል ። ለሁሉም ጥቂት እረፊ እስቲ ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቂት ከቆየን በኋላ

«መስኮቱን ዝጋው ፤ አሁን ደህና ነኝ ። ለጥቂት እፍታ በጣም ፈርቼህ ነበር?»

«ፈርቼህ ነበር ? ይቅርታ ልትጠይቂኝ ይገባል ። እን ዴት ? እኔ የማስፈራ ነኝ እንዴ? አሁንም አልዘገየሽም ፤ ሕይወትሽ ከሚያስፈራራ ሰው ጋር ተቆራኝቶ ከመጨነቅ አሁኑኑ ንገሪኝና ቆርጨ በዕድሌ ልዘን ።»

ብድግ ብላ እጅዋን በአንገቴ ዙሪያ አቅፋ «እንዳል ተቀየምከኝ አውቃለሁ ። ዓለምን በአንተ ፍቅር ስለማለ ውጥ ፍቅርህን እፈልገዋለሁ ።»

«እንግዲያስ ደህና ፤ ብቻ ሴሊቱን በደንብ እረፊ ። የሰርጋችን ዜና ግን ለጊዜው ሚስጢር ይሁን አልሺ?»

«አዎን ሚስጢር ቢሆን ይሻላል ። ሊያገቡህ የሚሯ ሯጡ የኔፕልስ ሴቶችም ከአሁኑ እጃቸውን እንዳይቀስሩብኝ እፈራለሁ ። ደግሞ ከአፍ ከወጣ አፋፍ ስለሆነ ጉዶ ፈሪ ሪም ሊሰማ ይችላል ።»

«ደህና እደሪ» ብዬ ሳምኋት ።

ሸኘችኝ ። ዝናቡ ደጁን አርሶታል ። ቀዝቃዛ ጭቃ ውስጥ የተኛችው ልጇ ትዝ ብላኝ እምባዬ እያቋተ ወደቤቴ መንገዴን ቀጠልኩ ። የታጨሁ ሰው ፤ ከዱሮዋ ሚሽቴ ጋር የተሚጨሁ ሰው መሆኔ እቤቴ በራፍ ስደርስ ትዝ ብሎኝ ከልቤ አሳቀኝ ። የበቀል መዝጊያው ጊዜ መድረሱ በትክ ክል ታወቀኝ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራአንድ

የሜዲተራኒያኑ የብርድ ወራት መጣ ። እየኑ እየቀዘቀዘ ከተማውም እርጥብ ጭጋግ አዟውትሮ መልበስ ጀመረ ። ይህ ቀዝቃዛ ጭጋግ አየር የየሰውን መንፈስ ቢጫነውም ግዴለሽና ደስተኛው የኔፕልስ ሕዝብ ከወትሮው ይበልጥ ትኩስ ቡና በመጠጣትና ልጅ አዋቂው ከምሽት እስከ ጉሀ በመደነስ ሰውነቱን ሲያሟሙቅ ያድራል ። ኮሌራውማ ያለፈ ታሪክ የተረት ጉዳይ ሆኖአል ። ከተማውን የማጽዳቱ ግዴታ ፣ የጤና አጠባበቅ ሥነ ሥርዓት ሁሉ ተወርቶና ታቅዶ በቃለ ጉባኤ ቀርቷል ። ለመጪዎቹ ዓመታት የኮሌራው መምጣት አሳሳቢነት የምናልባት ሳይሆን የልምድ ጉዳይ ነው ተባለ ። በዋዛ ፈዛዛ የሚስቀው ሕዝብ በኮሌራ የተቀጠፉትን ሙታን መቃብር እንደ አበባ ተክል መዛለል ጀምሮአል ።

«ባለፈ ሀሳብ አንለቅ ፡ ስለዛሬው ብቻ እንጨነቅ ፡» እያለ ሕዝቡ የጥንቃቄን ነገር እርግፍ አድርጎ ትቷል ። «ነገን እመብርሃን ታዘጋጃለች»እያለ በዋል ፈሰስ እሽሽ ገዳሜ ሆኖአል ። ያለ ምክንያት አይደለም እንዲህ ሊሆን የሚችለው ። የሰው ልጆች በኑሮ ልምዳቸው ባለፈው ላይ ወይም ገና ባልተደረሰበት ወደፊት ላይ እንጂ ባለበት ጊዜ አይኖሩም ። እና እንደልምዱ የእብደት ዓይነት ደስታ የሚ



t.me/OLDBOOKSPDF

በራይበት የፌሽታ ወቅት እየተቃረበ በመምጣቱ ድግሱ የነበረውን ሀዘን ሁሉ ማዘናጋት ጀመረ ። የኔፕልስ ነዋሪ በዚህ አስረሽ ምችው የደስታ በዓል ለመሳተፍ የከት ልብ ሱን ማነሳሳት ጀመረ ። እኔን ግን ስለ በዓሉ እንዳስብ ያደ ረገኝ በሆቴል ኑሮዬ ትሁትና የቅርብ ደጋፊዬ የሆነው ቪን ቼንዞ ነው ። ሲፈራ ሲቸር በፌስታው እንዲሳተፍ እን ድፈቅድለት ጠየቀኝና፣

«የሚጥምህን ደስታ መምረጥ የራስህ ጉዳይ ነው ። በእብደት ደስታ ተወጥረህ ራስህን መሳቂያ ብታደርግ ግን እኔ የለሁበትም ። በኔ በኩል ቅሬታ የለም ። ደስታውን በሚ ያሻህ መጠን መሰብሰብ ትችላለህ ። በደስታው ምክንያት ለሚፈጸመው ድርጊት ጠያቂ የሌለብህ መሆንህን እመሰ ክራለሁ ።»

ቪንቼንዞ ቁርሴን እያዘጋጀ ሳለ «በነገራችን ላይ መቼ ነው ፌስታው? ›› አልኩት ።

«የገና በዓል ሰልስት ነው ጌታዬ መች አጡትና ነው የሚጠይቁኝ ።»

«አዎን አዎን አውቀዋለሁ ። ምን እኮ እርጅናውስ እየመጣ አይደል ። ቀኑን እዘነጋዋለሁ ።»

ይህን እየተነጋገርን ቪንቼንዞ አንድ አነስተኛ የደብዳ ቤዎች ማጠራቀሚያ አምጥቶ አቀረበልኝ ። አብዛኛውን ደብዳቤ ገና ሳልከፍተው ምን እንዳለበት አውቀዋለሁ ። ሊተዋወቁኝ የሚፈልጉ ሴቶች ፣ የንግድ ቤታቸውን እንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

መርቅላቸው የሚፈልጉ ነጋዴዎች እና እንዲሁ ከወንዱም ከሴቱም በሀብቴ ተማርከው የሚጽፉልኝን እያገላበጥኩ በየተራ ሳነሳ ዙሪያውን በጥቁር መስመር የተከበበ ደብዳቤ ላይ ዐይኔ ወደቀ ። የፖስታው ማኅተም ሮማ ይላል ።

«በመጨረሻው ተገኘሽ» ብዬ ትንፋሼ ደረቴ ላይ ተጠራቅሞ ከቆሽቴ ንዳድ ጋር በረጅሙ ተነፈስኩ።ቪንቼንዞ ገበታዬን አደራጅቶ ስለጨረሰ ግንባሬን አይቶ በትህትና በሩን ከፍቶ ሹልክ ብሎ ወጣ ። ዝግ ብዬ የደብዳቤውን እንቦልክ ከፍቼ ሳይ የጉዶ ፌራሪ ሆኖ አገኘሁት ። በራሱ ሕይወት ላይ ፍርድ ሰጥቶ የፈረመበት ደብዳቤ መስሎ ታየኝ ።

«በጣም ውድ ለሆኑ ጓደኛዬ» ብሎ ይጀምራል ። «በእንቦልኩ ዙሪያ ባለው ጥቁር መስመር የአጐቴን መሞት ይረዳሉ ። እግዜር ይመስገን በመጨረሻው አጐቴ ሞቶአል ። የጠቅላላ ሀብቱ ወራሽ ሆኘአለሁ ። ሕጉ የሚጠይቀውን ሁሉ ካሟላሁ በኋላ ፈጥኜ ኔፕልስ እመለሳለሁ ። ለሁሉም ቴሌግራም አደርግሎታለሁ ። ለእመቤትኗና ስለጉዳዩ ባይነግሯት እመርጣለሁ ። መቸም ደሂኔ ብቸኝነቱ ገድሏታል ። ስመለስ የዘንድሮው የካርኒቫል ክብረበዓል ለኔና ለኗና ከመቸውም የደመቀ መስሎ ነው የሚታየኝ ። እስከ አሁን የምትጽፍልኝ ደብዳቤዎች ሁሉ በፍጹም ናፍቆትና ፍቅር የተሞሉ ናቸው ። አሁን፣ምናልባት ኪሶቼ


t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህ በድንገት በገንዘብ ስለተሞሉ ከእርስዎ ጋር እፍነት ይሰማኛል ። በተጨማሪም እጅግ በጣም ከባድ የሆነብኝን እርስዎም ያበደሩኝን ውለታ ከነወለዱ ለመክፈል ተዘጋጅቻለሁ ።»

የእርስዎ ታዛዥ
ጉዶ ፌራሪ ።

ደብዳቤውን መላልሼ አነበብኩት ። እያንዳንዱ መስመር በውስጤ እንደ ረመጥ እሳት ተቃጥሎ አቃጠለኝ ። «እስከአሁን የምትጽፍልኝ ደብዳቤዎች ሁሉ በፍጹም ናፍቆትና ፍቅር የተሞሉ ናቸው ።» እኔን ጂል እንዳለ እርሱም ጂል ሆነ ። እርስዋ ግን ጥንድ ይሁዳ ናት ። አንድም ዓይነት ጥርጣሬ ወይም ቅናት እንዲያድርበት ከማር የጣፈጠ የፍቅር ቃላት ስታጉርሰው ሰንብታለች ። ከሁሉም የሚገርመው እኔን ባል ለማድረግ ከወሰነች በኋላ የፍቅር መሀላና ቃልኪዳን ማደሻ ደብዳቤዎች ታጉርፍለት የነበረው ነው ። ደብዳቤውን ይገኑ ጥቂት እንደተቀመጥኩ የሚከተለውን መልስ ማስፈር ጀመርኩ ።

«ውድ ጓደኛዬ ሆይ!

ስለ ደስታህ መስማቱ አስደስቶኛል ። የመምጫህን ቀን በናፍቆት እየጠበቅን ነን ። እመቤትኒናን በደስታ ለማስደንገጥ ያቀድከውን እድንቁአለሁ ። ነገር ግን እኔ ደግሞ በበኩሌ የምጠይቅህ አለኝ ። አንተ ከሄድህ ጀምሮ እምብዛም


t.me/OLDBOOKSPDF

ደስ የሚል ጊዜ አጋጥሞን ከወዳጅ ጋር የተጫወትን ስላልሆነ የገናን በዓል ሌሊት በደህና ስለ መመለስህ ለራት ግብዣ የኔፕልስን መኳንንት እንድትጋብዝ ስለፈለግሁ የመመለሻህ እለት የዚሁ በዓል ማለዳ እንዲሆንና በቅድሚያ እኔ ዘንድ መጥተህ የመጀመሪያው ተቀባይህ የመሆን እድል እንድትሰጠኝ በእንጋፋነት እለምናለሁ ። ጥያቄዩን ለመቀበልህ እምንታህን በቴሌግራም ብታረጋግጥልኝ ሰረገላዬ ባልከው ሰዓት ባቡር ጣቢያ እንዲጠብቅህ አደርጋለሁ ። የግብዣው ጊዜ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ቢጀምር ምን ይመስልሃል? ከግብዣው በኋላ ያለው ሰዓት ግን ያንተው ነው ፤ በናፍቆት የምትጠብቅህን ፍቅረኛህን ለማስደሰት ወደ ሮማኒ ጊቢ መሄድ ትችላለህ ። መቸም የሽማግሌ ጓደኛህን ልመና እንደምታሟላ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ ።

ያንተው ለጊዜው ፤
ሲዛር አሊቫ ።»

ደብዳቤውን አጥፌ ወዲያው ወደ ፖስታ ቤት ላኩት ። የመምጫው ዕለት ድረስ ያለውን ቀን በጣቴ ቆጠርኩ ፤ በመሀል ያለው አራት ቀን ብቻ ነው ። ወዲያው ሚሽቴን ወይም እሙኛዩን ለማነጋገር ወሰንኩ ። መቸም ካጨኋት ወዲህ ስሜትዋ በፍቅር ረመጥ መጋየትን አሳይቶኛል ። ፍቅርዋ አለመጠን አይሎ ሲወጣ ብቻ ቀዝቀዝ እያደረግሁ



t.me/OLDBOOKSPDF

አሳልፌዋለሁ ። አንዳንዴ አዝንላታለሁ ፤ አንዳንዴ ደግሞ የመሞቻዋን ቀን በናፍቆት እጠብቃለሁ ። የእርስዋ እጅ ግን ያው ነው ። የቀረበላትን ከማንም ይሁን ከማን ልብዋን ከፍታ ስትቀበል ስሜትዋ ይፈነድቃል ። የካርሜሎ ኔሪን ሳጥን እየከፈትኩ የሚሸቱን የስጦታ መቀበል ፍትወት በደንብ አረካሁ ። ሀብቱን የምፈልገው የበቀል ሥራዬን እንዲያቀና ብርሌን ስለሆነ እንደልቤ ቸርኩበት ። ባለቤቴ ግን በየቀኑ ትንሽ እየሆነችብኝ ሄደች ። በመጨረሻው እንደምን ተሆና ይህችን መናኛ መጀመሪያውን እንዳገባሁ ደነቀኝ ። በውበት ግን በእውነት ውብ ናት ። ውበት ታዲያ በገንዘብ ኃይል የሚሸጥ የአደባባይ ርካሽ እቃ መሆኑን ተረዳሁ ። ነገር ግን ሴትን መልአክ የሚያደርጋት ታማኝ ልብ ፤ ሀቀኝነት ፤ ሰብአዊ እውቀት መሆናቸውን እየተማረርኩ ተማርኩ ። ውበት ብቻውን የወንዶች ወጥመድና የልብ ፀር ነው ። እኛ ወንዶች ለውብ ሴት ፈገግታ ወይም ከንፈር ስንል ነፍሳችንን እንሸጣለን ። የመጀመሪያውን አዳም ሴት እንዳሳሳተች የእኛ ወንዶች መጥፊያ ሴት ናት ። በእኛ ብርታት ውስጥ ድክመት ተደብቆ አለ ። ይህን ደካማ ጐን ደካማ ሴት ታገኘዋለች ። ለቅንጣት ፈገግታ ወይም ከንፈር ሕይወታችንን ለስጦታ እንዘረጋለን ።

ያን ዕለት እንዳሰብኩት በቀጥታ ሮማኒ ግቢ ሄድኩ ። በሰረገላዬ የተለመደውን «የፍቅር» ስጦታዬን እቅፍ ነጭ አበባ ይዤላት ሄድኩ ። ይገርማል ፤ የዚያ ነጭ አበባ ሽታ ልጇ ስቴላ የተወለደችበትን ቀን አስታወሰኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚሽቴ ወይም አዲስዋ እጮኛዬ ወተት ነጭ የካሽ ሚር ሀር መሬት ለመሬት እየጐተተች የማለዳ ልብስዋን እንደለበሰች ያ ተወዳዳሪ የማላገኝለት ዘንፋላ ፀጉርዋ ትከ ሻዋ ላይ የሀር ነዶ መስሎ ወርዶአል ። ስገባ ከፋይ የመዝ ናኛ ወንበር ላይ ተቀምጣ ፊት ለፊትዋ የእንጨት እሳት እየነደደ ታነብ ነበር ። መምጣቴን ገና ስትሰማ ከመቅጽ በት ብድግ ብላ በተለመደው ሕያው ፈገግታዋ ንግሥት ንጉሥን እንደምትቀበል ዓይነት አቀባበል አደረገችልኝና ያመጣሁላትን እበባ እስታቀፍኳት ። ብቻዋን ላናግራት ስለፈለግሁ በሩ ተዘጋ ። ከሲኞር ፈራሪ ደብዳቤ እንደደረ ሰኝና ጉዶ በሁለትና ሶስት ቀኖች ውስጥ እንደሚመጣ ነገ ርኳት ።

«የመምጣቱ ነገር የአንቺን ከእኔ ጋር መጋባት የሚ ያውክ መስሎ ቢታይሽ ለጥቂት ቀናት ከዚህ ከተማ ወጣ ብለሽ ብትሰነብቺ ፣ እስከዚያ እርሱም ቀዝቅዞ ይቆይሻል ። ምን ትያለሽ?» አልኳት ።

ጥቂት ካመነታች በኋላ «ጌታዬ እንዳልከው አደርጋ ለሁ ። ችኩልና ደመ መራር ስለሆነ የሚያደርገው አይታ ወቅም ። እንዳልከው ብሂድ ይበጃል ። አንተን ግን ያሳስ ብሀል ፣ ነገሩን ሲሰማ ለስድብና ድንፋታ አይመለስም» አለችኝ ።

«እኔ ራሴን መጠበቅ አያቅተኝም ። እንዳንቺ ያለችውን የገነት ተክል ለዘለዓለም ይዞ ለመኖር ጥቂት ትእግስት



t.me/OLDBOOKSPDF

ያስፈልጋል ።» ጥቂት አረሳስቼ «ከአንቺም ዘንድ የፍቅር ደብዳቤዎች እንደደረሱት ጻፈልኝ» አልኳት ።

እንደ አዘቦት ነገር ጥያቄዩ በዋዛ ከአፏ ሲወጣ መጀ መሪያ ስሜትዋ ተዋከበ ። የሁኔታዩን መቀዝቀዝ ስትረዳ «አዎን ፣ አንድ ሁለት ደብዳቤዎች ስለ ሕግ ባሌ ንብረት ጉዳይ ጽፌለት ነበር ። ባለቤቴ ከመሞቱ በፊት ለሀብቱ እንደወኪል ካደረጋቸው አንዱ እርሱ ስለነበር ላማከረው ሕጋዊ ግዴታ አለብኝ ።»

ነገሩን ናቅ አድርጌ «ስለመሄዱስ ምን ወሰንሽ» አል ኳት ። አጠገቤ መጥታ በርከክ ብላ «ብሔድ ይሻላል ። እተ ማሪኩበት ገዳም ለአንድ ሳምንት ልሂድ ። ወዲያውም ሁለ ተኛ ባል አግብቼ ሕይወትን ከመጀመሬ በፊት ጥቂት ጸሎት ባደርግ እኔንም አምላክ ይታረቀኛል ። መነኳኩሰቱም በጣም ይወዱኝ ስለነበር መንፈሴን በምክራቸው ያጽናኑ ታል ።» እጆችዋን በጣም ጫን አድርጌ ከተንበረከከችበት አነሳኋት ።

«ጥሩ ነው ወደ ገዳም መሄዱ ይመረጣል ።ምን ዓ ነት ሕይወት እንደሚጠብቀን ስለማይታወቅ አስቀድሞ ከፈጣሪ ጋር መመካከር ይበጃል ። የጉዶ እልህ ሰከና በእ ሺታ ፀጥ ሲል እኔ መጥቼ እወስድሻለሁ ። ስትጸልይ ግን ለቀድሞ ባለቤትሽ ነፍስና ለኔም ጭምር ፀልይ ። በነኝሁ ውብ ከንፈሮችሽ መሀል የሚወጡት ልመናዎች ቀጥታ ወደ ገነት ከንፈው ይሄዳሉ ። ጥሩ ሀሳብ አምጥተሻል ። እንዳል


t.me/OLDBOOKSPDF

ሽው ፈጥነሽ ገዳም መግባት ይበጃል ። የጉዱ ነገር ግን የቅ ንጣት ያህል እንዳያሳስብሽ ። እርሱን ለኔ ተይው እኔ አስ ከነዋለሁ ።» አልኳት ።

«ገዳም መቼ እንድገባ ትመከረኛለህ ሲዛር?»

«መሄድ የሚቻልበትን ቀን አንቺ መርጠሽ ብትሄጂ ደስታው የጋራችን ነው ።»

«እንግዲያስ ዛሬውኑ እሄዳለሁ ።»

«እንዲህ ካሰብሽ የመዘጋጃ ጊዜ ስለሚያስፈልግሽ እኔ ልሂድ ። ገዳም እንደደረስሽ ለገዳም ኃላፊዋ እሮኛሽ መሆኔን ብትነግሪልኝ እንደልቤ እየመጣሁ ልጠይቅሽ እች ላለሁ ። ለኔም ፀልይልኝ ፣ በቅዱሳን ደናግል መሀል ሆነሽ ስትፀልይ ከሁላችንም ለመላእክት የቀረብሽ አንቺ ነሽ ። በፀሎትሽ አትርሺኝ እባክሽ ።»

«እፀልይልሀለሁ»

«አመሰግንሻለሁ ፣ በጣም አመሰግንሻለሁ ። በይ እን ግዲህ አዲዮስ» ብዬ ልወጣ ስል ፤

ኋእንዴ አትስመኝም እንዴ ታዲያ?» ከንፈርዋ በጣም ቀላብኝ ። ዐይኖችዋ አለመጠን እንፀባረቁብኝ ፣ ሁለመናዋ ቀለጠብኝ ። በዚያች አፍታ ያደረግሁትን አላስታውስም ። ብቻ በአራዊት ዓይነት ረሀብ የተዋጥሁ መሰለኝ ። እንዴት እንደያዝኳት አላውቅም ። ሞቅታ ባለው የፍቅር ስሜት ፣ ከንፈርዋ ከቦታው እስኪነቀል ሳምኳት ። አንገትዋንና ሽፋ ሽፍቷን ጭምር ሳምኳት ። እቅፌ ውስጥ ያመቅሁት ትኩ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳት ሲፈጀኝ ነቃሁና ጠቅላላ ማንነትዋ ትዝ አለኝ ። አሸ
ቀንጥሬ ፣ ባላመነታ ወረወርኳት ። ተንገዳግዳ ወንበሩን ይዛ
ከመውደቅ ዳነች ። በመደንገጥ አየችኝ ። ፊትዋ ላይ ግን ቅ
ሬታ አይነበብም ።

«ይቅር በይኝ ። አባክሽ ይቅርታሽን አድርጊልኝ።»

ፈገግታ ከንፈሮችዋን ግራና ቀኝ እየሳበው «ምንም
ጥፋት የለብህም» አለችኝ ።

ጥቂት ቆይታ ከትከት ብላ ሳቀች ። ከጉዶ ጋር ስትዳራ
ያየኋት ምሽት ዓይነት ሳቅ አመለጣት ። ድምጹ ራሱ ትዝ
ታዬን እሸብር ጤና ነስቶ በአውራ ጣቴ አስቆመኝ ። በአ
ስተያየቴ ብቻ ሳቅዋን ቀጥ አደረገችው ። በዐይንዋ ሙሉ
ሁኔታዬን በፍርሀት መከታተል ጀመረች ።

«እቴዴህ አትሳቂ ሁለተኛ ፣ የደምስሮቼን ያውካቸ
ዋል ። ልጅ ሆኜ አንዲት ሴት አፍቅሬ ነበር ። እንዳንቺ
ዓይነት አልነበረችም ። ውሽታም ነበረች ። እንቺን በም
ንም አትመስልም ። ታዲያ ትስቅብኝ ነበር ። በአንድ ሰሞን
ልበ ሰባራ አደረገችኝ ። አሁን አሳሳቅሽ እሷን ነው ያስታ
ወሰኝ ፣ አልወዳትም ፣ የልጅነት ታሪኬን በሰበቡ ስለአወ
ራሁልሽ ይቅርታ አድርጊልኝ ። በይ እንግዲህ ለመንገድሽ
እንቺም ተዘጋጂ ። ከንጹህ ሀሊና የሚመነጭ ሰላም ይስ
ጥሽ ።» እጄን እራስዋ ላይ ጫን አድርጌ እንደነፍስ አባት
ሰይዛት ምርቃን የምሰጣት ባይመስላት አልቀረም ። ግን
ያሰብኩትን ግን በነገራት ። እርግማን ቢደርስ ኖሮ በዚያን
አፍታ የመርገምት እሳት በተጫናት ነበር ። ግን አንዲት



t.me/OLDBOOKSPDF

ቃል ሳልተነፍስ ከቤቱ እየተቻኮልኩ ወጣሁ ። ባወጣጢ ብትደነግጥም ስሜቴን በዚያ ደረጃ ለማነቃነቅ በመቻ ልዋ የብቃት ስሜት ሳያድርባት አይቀርም ። እኔ ግን ልትሸ ኘኝ የቆመችበትን ቦታ እንኳ ለማየት ዞር ማለት አቅቶኝ ግቢውን ጥዬ ወጣሁ ። በፍቅርና ጥላቻ መሀል የተዘነጣጠለ ስሜት ውስጤን አቆሰለው ። ፍቅር ቢሉ ከፍቅር የተወለደ ሳይሆን ከሸቀጥ ሀብት የተፀነሰ ፣ ጥላቻ ቢሉ ማርከሻው የማይገኝለት መርዛም መፈጠርን የሚያስረግም ጥላቻ ። እና ከዚያ ያፍዝ አደንግዝ ውብትዋ ስበት መራቄን ሳረጋግጥ ራሴም መንፈሴም የኔው ሆነ ። ስረገላዬ ወጥቼ ትኩሳቴን በዚያ ቀዝቃዛ አየር እያበረድኩ ወደ ሆቴሌ ገሰገስሁ ። እን ዴት ደስ የሚል ቀን ነበር ። ከሩቅ የባሕሩ ቀለም ወደነጭ አረንጓዴ ተለውጦ ንፋስ ላይ የተንጣለለ ይመስላል ። በመ ንገዱ ግራና ቀኝ ደማቅ ልብስ የለበሱ ሴቶች በተሸከሙት ፍራፍሬ የአየሩን መአዛ ለውጠውት ያልፋሉ ። የተበሜ ጨቀ ጥቡቆ የለበሱ ሕጻናት እየቁራረጡ ያን ቦሊቃቃ ዐይ ናቸውን እያንቦገቦጉ እንደ ጆንበር የሚሞቅ ፈገግታቸውን በነጻ ይፈነጥቃሉ ።

ከሆቴል ክፍሌ እንደደረስኩ ድካም ተሰማኝ ። ስለም ሳ ፍላጐቴ ለክፍል ጠባቂዬ ፊንቼንዞ ትእዛዝ ሰስጥ አንድ ሀሳብ ትዝ አለኝና አንድ የሚስጢር እቃ የማስቀምጥበትን መሳቢያ መክፈት ፈለግሁ ። ሠራተኛዬ ቁልፉን ፈቶ እን ዲከፍት አዘዝኩትና በብር የተንቆጠቆጡ ሽጉጦች አውጥቼ ለሠራተኛዬ ሰጠሁት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«ለምንትን እፈልገው ይሆናልና ፊትተህ የጕደለውን ለመሙ
እይ» አልኩት ። ካለ አንዳች ማመንታት ፈቃዴን ለመሙ
እይ» አልኩት ። ካለ አንዳች ማመንታት ፈቃዴን ተቀብሎ አገላ
ላት በተለመደው ደግነትና ትህትና ሸጉጡን ተቀብሎ አገላ
ብሎ ካየ በኋላ «መወልወልና ቅባት ይፈልጋል» ብሎኝ
ይዞ ሊወጣ ሲል ፣ «ታማኝነትህን የምፈትንበት ወቅት የተ
ቃረበ ይመስለኛል» አልኩት ።

በሙሉ ልብ ከለመጠራጠር አይቶኝ ፣ «ጌታዩ የሚያ
ስፈልግዎትን ማዘዝ ብቻ ነው ። እኔ ወታደር ስለነባርኩ
ግዴታዬን መወጣት አውቃለሁ ። ለጌታዩስ ታላቅ ሰው
ነት ሕይወቴንም ቢያስፈልግ እሰጣለሁ ።»

እጄን በጓዳዊ ስሜት ዘርግቼ ጨበጥኩት ። እጄን ስም
እምነቱን አረጋግጦልኝ ሄደ ። ብቻዬን ስሆን ይህን ያህል
እምነትና መውደድን እንዴት ለመገንባት እንደቻልኩ ገረ
መኝ ። ለምንድነው ከሞትኩ በኋላ እንኳ ሽማግሌው የአ
ባቴ ሠራተኛ የሚወደኝ ፤ ውሻዬስ ለምንድነው እስከአሁን
የሚወደኝ? የቅርብ አከላቴ የምላት ሚሸቴና ጓደኛዬ ደግሞ
ለምንድነው በጥላቻ ሊከዱኝ እንደዚያ የተጣደፉት? የተ
ማረና የተመራመረን ሰው መርጦ ይሆን ጭካኔ ፈጥኖ ልባ
ችንን የሚያደድበው? ሥልጣኔ የጭካኔ ምንጭ ትሆን?
አልኩ ብቻዬን ።

ሀሳብ አዳከመኝ ። ማውጣት ማውረድ ታከተኝ ። ከመ
ስኮቴ አጠገብ ከተዘረጋው የመዝናኛ ወንበር ላይ አረፍ
ብዬ በባህሩ ላይ ወዲያ ወዲህ የሚንሳፈፉትን ጀልባዎች
እያየሁ እፎይታን ለማግኘት ሞከርኩ ። ባሕሩ አጠገብ ያቺ


t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙ ጊዜ ያየኋት ምስኪን ልጅ እየዘመረች ትደንሳለች ። ውብትዋና ዳንስዋ ዐይኔን ማረከው ። ታሪክዋ ትዝ አለኝ ። የወርቅና ብር ጌጣጌጥ ሠሪ እሙኛ ነበራት ። እሙኛዋ ለብዙ ዘመን በወርቅ ማንጠሪያ እሳት ዐይኑ ስለተጐዳ ድንገት ዐይነ ስውር ሆነ ። ከሥራ ሲያስወጡት እሙኛውን መልካም እድል እንዲገጥማት ለቀቃት ። ሞቴም ሕይወቴም አንተው ነህ ብላ ፣ በየአደባባዩ የዜማና የዳንስ ችሎታዋን እያሳየች ገቢ ታመጣለት ጀመር ። ፍጹም ጥገኝነት እንዳይሰማው መሶብ መሥራት አስተምራው ፣ የሠራውን በውድ ዋ ጋ እየሸጠች ችግር የሌለው ኑሮ መኖር ጀመሩ ። ስለ ትልቅነትዋና ለፍቅር መስዋእት በመሆንዋ መንገደኞች ሁሉ የፍቅር ጀግና ይሏታል ። ዐይነስውር ባልዋን በፍጹም ፍቅር ጠብቃ እየመራችው ስትሄድ ከሊቅ እስክ ደቂቅ በአ ክብሮትና ትህትና ነው የሚያናግሯት ። እንዲህ ያለ ፍቅር ከየት ይገኛል ። እውነተኛ ፍቅር የምትገኘው ጐንበስ ብለው ከሚገቡባት ደሳሳ ጐጆ መሆንዋ ግልጽ ነው ።

ከመስኮቱ ሥር ሳልነሳ መሽቶ ከፍሌ ውስጥ እሳት ነደደ ። ሠራተኛዬ ቪንቼንዞ ደብዳቤ ከወደደጅ ይዞልኝ መጣ ። ከፍቼ ሳየው እንዲህ ይላል ።

«ወዳጄ ሲዛር፣»

ገዳም በደህና ደርሻለሁ ። የተወደዱት መነኲኩሴት በናፍቆት ተቀበሉኝ ። ባሻህ ቀንና ሰዓት እንድትጠይቀኝ ተፈቅዶልሀል ። ዛሬ ጠዋት ከመለያየታችን በፊት ባሳየ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኸኝ ፍቅር እንዴት ያለ ደስታ ተሰማኝ መሰለህ ፣ ሁልጊዜ ፍቅረኛህን ለምን እንዲህ አታስፈነድቀኝም? ታማኝህ ።

ያንተው ኒና

በንዴት ወረቀቱን ጨባብጬ ከተቀጣጠለው እሳት ውስጥ ከተትኩት ። ታከተኝ ። ሁሉ ነገር ሰለቸኝ ። የቂም በቀሉ መዝጊያው ጊዜ ረዘመብኝ ። በጊዜ ተኛሁ አል ልም ፣ ተደፋሁ ። የሚቀጥለው ቀን ረጅም የሰዓት ጉ [illegible] ፍትሀት ሆነብኝ ። ቀኑ እንደዋዛ ሲመሻሽ የማታ ማ ታ ቴሌግራም መጣልኝ ።

«ለጌታ ሲዛር አሊቫ ፣ ኔፕልስ ።

የገና በዓል ዕለት እመጣለሁ ። ባቡሩ በ12.30 ኔፕልስ ይገባል ። ጌታዬ ቤት በመጀመሪያ እደርሳለሁ ።

ጉዶ ፌራሪ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራሁለት

ዕለቱ የገና በዓል ነው ። ሳያቋርጥ የሚዘንበው ዝናብ ከሚሸነቁጠው ብርድ ጋር ቀኑን ጭፍግግ ያለው አድርጎታል ። ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ገደማ ግን ዳመናው ገለጥ ብሎ አየሩ ሞቅ አለ ። ከዳር እስከዳር ከድን ያለው ዳመና ለቀቅ አድርጎት የፀሐይን ዐይን ሰረቅ አድርጐ ለማሳየት ሰማዩ በመጠኑ ገለጥ አለ ። በበዓሉ ምክንያት አበባ ይዘው የሚዘምሩት ልጃገረዶች ኔፕልስን የመዝሙርና የመዓዛ ከተማ አድርገዋታል ። አበባ የመሰሉ ደናግል ሁሉን አይነት አበባ እያሸተቱ ከተማዋን አሰሱዋት ። መስኮቶች ሁሉ በብርሀን ቀለማት አጊጠው በየቤቱ የሚበላና የሚጠጣ በሰፊው ተዘጋጅቷል ። እኔም በምኖርበት ሆቴል ውስጥ ለጉዶ ፌራሪ መቀበያ ወይም መሸኚያ ያሰብኩት ድግስ ተጀምሮአል ። የምኖርበት ሆቴል ድግሴን የድግሶች ቁንጮ ለማድረግ የሆቴሉ ዋና አዛዥ ራሱ የሥራውን ዝርዝር በጥንቃቄ መከታተል ቀጥሏል ። ያዘዝኩትን እራት በትክክል ለማዘጋጀት ያለውን የመፍጠር ችሎታ ሁሉ በማስተባበር አንድ የፈረንሳይ እውቅ ወጥቤት አቆመ ። የሆቴሉ ጌታ ራሱ ያዘዝኩትን አይነት ምርጥ የወይን ጠጅ ስም ሰምቶ ስለማያውቅ እንደሕጻን ተደነቀ ። ጥቃቅን ትእዛዛቴ ሁሉ እንዲፈጸሙ ሠራተኞች ላይና ታች



t.me/OLDBOOKSPDF

ይራራጡ ጀመር ። ገበታ በማዘጋጀት ብቻ ከፍተኛ ችሎታ ያለው ባለሙያ የኔ ፍላጐት እስኪሟላ ከረዳቶቹ ጋር ሌላውን ሥራ በሙሉ እርግፍ አድርጐ ተወ ። በሆቴሉ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ድግስ እየተዘጋጀ መሆኑ በውጪም እየታወቀ ሄደ ።

ልክ አሥራ ሁለት ሲሆን ሰረገላዬን ባቡር ጣቢያ ላኩ ። ከግብር ቤቱ ትይዩ ላዘጋጀሁት ትርኢት የሚሆን በብርሀን የተንቦገቦገ መድረክ እንዲዘጋጅ አደረግሁ ። ግብዣው የመኝታ ክፍሌን እንዳያመሳቅልብኝ ለሰርግና ታላላቅ ግብዣ ሁልጊዜ የሚያዘውን የምድር ቤቱን የግብር ቤት መረጥኩና ተዘጋጀልኝ ። ለአሥራ አምስት ተጋባዦች የተዘጋጀው ገበታ በልዩ ልዩ አንጸባራቂ ጌጣጌጥ አጌረ ። የሆቴል ቤቱ አዛዥ ራሱ ዝግጅቱን እየተከታተለ አጠናቀቀ ። ሁሉም ነገር መጠናቀቁን ካረጋገጥኩ በኋላ ተጣጥቤ ለትልቁ በዓል በተለይ ያዘጋጀሁትን ልብስ መለባበስ እንደጨረስኩ ሺንቼንዞ ኮቴን ሲያቀብለኝ ፤

«ሺንቼንዞ» አልኩት ።

«ጌታዬ» አለኝ ።

«ዛሬ ራት ላይ ከኋላዬ ትቆማለህ ። አንድ የምትጠነቀቅበት ነገር አለ ። ከጐኔ በስተቀኝ ሲኞር ፌራሪ ስለሚቀመጥ የእርሱ ዋንጫ እንዳይጐድል በጥንቃቄ ትሞላለህ ።»

«ታዛዥ ነኝ ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ምንም ዓይነት አስተያየት ቢሰነዘር የውስጥ ስሜት ህን ለመቆጣጠር ሞክር ። ቦታህ ግን ከእኔ ኋላ ነው!»

«ታዛዥህ ነኝ ።»

ለባብሼ ከጨረስኩ በኋላ ፣ «ሽጉጦቹስ» አልኩት ።

«ተመልውለው ተዘጋጅተዋል ።»

የሠረገላ ድምጽ ሰማሁ ። ሠራተኛዬ ወጣ አለ ። ልቢ ካለመጠን መምታት ጀመረ ። ስሜቴን እያረጋጋሁ ከመ ልበሻ ክፍሌ ወጣሁ ። እንግዳ መቀበያ ክፍሌ ገባ ስል ሲኞር ፌራራ በሩን ከፍቶ ሁለት እጁን ለሰላምታ ዘርግቶ ብቅ ሲል ከወትሮው በጣም አምሮበት ግንባሩ፤ደስታውን ከሩቅ ያስተጋባል ።

«እንደምን አሉልኝ ክቡር »ብሎ እጄን በሁለት እጁ ጨምዶ« ጌታ አሊቫ እንደእርስዎ ያለ ደግ ምድርን ቢዞሩ አይገኝም ። እንደምንድንዎት ። በጣም አምሮቦታል።»

«ደልቅ አንተ በጣም አምሮብሀል» ስለው ዘና ባለ መን ፈስ ሳቀ ። የእጅ ጓንቲውንና ካፖርቱን አውልቆ ተደላ ድሎ ተቀመጠ ።

«ገንዘብ ለካ የሰውን ችሎታ ሁሉ ይለውጣል ። ራሴን ታዘብኩት እኮ ጌታዬ» ብሎ መለሰልኝ ። ጥቂት ቆየት ብሎ የጌታዬ አለባበስ እንከን የለሽ ስለሆነ እኔም ግብዣውን የሚመጥን ደህና ልብስ መልበስ ያስፈልገኛል» ብሎ ብድግ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲል ፣ ብርጭቆ አንስቼ «አንዲት ብርጭቆ ወይን ጠጅ ጠጣና ነው ። ራት በሁለት ስለሆነ ብዙ ጊዜ አለን» ወይኑን ቀዳሁለትና «መልካም እድል ገጥሞህ ኔፕልስ ስለገባህ የልብ ደስታዬን እገልጽልሃለሁ» ብዬ ዋንጫዬን አነሳ ሁለት ።

«ቃሌን ለመጠበቅ እርሶ ዘንድ መጣሁ እንጂ እንደ ራሴ ፍላጐት ቢሆን በዐይኔ ላይ የሄደችዋን ውቢቱን ኗናን ማየት ነበር ረሀቤ ።»

«ሴቶች እንደጨረቃ በማታ ሲታዩ ይበልጥ ያምራሉ ፤ እንደ ከዋክብት በጨለማ ውበታቸው ይበልጥ ይደምቃል» ያለው ባይሮን አይደል? ከወትሮው አምራና ደምቃ ትቆይ ሀለች ። ደግሞ አትጠራጠር በደንብ ነው የተጠበቀችልህ ። ከኔፕልስ ወንዶች ለእኔ ብቻ ነበር ግቢዋ እንድገባ የተፈ ቀደልኝ ።

«እግዚአብሔርን ለዚህ አመሰግንዋለሁ» እያለ ወይ ኑን ጎንጨት አደረገ። «እንግዲያስ ዛሬ ማታ የሚመጡት እንግዶች እነማን እንደሆኑ ማወቅ እፈልጋለሁ ጌታዬ ፤ ከፍትወት ተግባር ይልቅ ጥሩ የራት ግብዣ ነው አሁንስ ያጓጓኝ » አለ ።

አባባሉ አስገርሞኝ ከት ብዬ ሳቅሁኝ[። «ትክክል እኮ ነው ። ከጥሩ ሴት ጥሩ ምግብ ይመረጣል ። የተጋበዙትንማ እንግዶች ግብዣው ላይ ስታገኛቸው አድናቆትህን መመ


t.me/OLDBOOKSPDF

ጠን ያቅትሀል ። ለምድር ለሰማዩ የከበዱ የምታውቃቸውና ስመጥር ናቸው የተጠሩት ። የጦር አለቆች ፣ ከበርቴ ነጋዴዎች ፣ የጥበብ ሰዎች ፣ የውጭ ሀገር አምባሳደሮች ፣ ባለቅኔ ሙዚቀኞች ሁሉ ተጠርተዋል ።

«ይህን ሁሉ ውድ ግብዣ ያዘጋጁት በእውነት እኔን ለመቀበል ነው?»

«እንዴታ! ከሚያደንቁህ ብዙ ሰዎች አንዱ እኔ ነኝ ። ራስህን አታውቅም እንጂ በዓለም ደረጃ ተወዳጅና ክቡር የሚያደርግ የሰው መውደድ አለህ ። ፋቢዮ ሮማኒ ከምሽቱ ቀጥሎ ይወደኝ ነበር ትለኝ አልነበረም እንዴ ?»

«ፋቢዮ ሮማኒ አሉኝ ። ይኸ ስም ሰሞኑን ካለመጠን ይከታተለኛል ። እርሱ ያመነኝና የወደደኝ እኮ ጂል በመሆኑ ነው ብዬዎታለሁ ።»

«ለመሆኑ ሮም እንዴት ነበርክ?»

«ሮም የሞትን መጥፎነት ነው ያስተማረችኝ ። አጎቴ በጣም ሽምግሎ ቢደክምም ነፍሱ በዋዛ ልትወጣ አልፈለገችም ። ለያንዳንድዋ እስትንፋስ እንዴት ነበር መስሎት የሚፈራገጠው ። ይህን ካየሁ በኋላ ወጣቱ ጉበዙና ብርቱው ፋቢዮ እንደምን ያለ ጭንቀትና የመከራ ጊዜ እንዳሳለፈ ታይቶኝ ሀሳቡ ራሱ አስጨነቀኝ ። እንጃ ሞት የቀለለ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልገናል ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

«እንግዲህ ስለሞት አስከፊነት አታስብ ፣ ይሏቱ
ለራት ግብዣ ለባብሰው ብዬ ደወል ደውዬ ቮንቼንዞ ብቅ
ሲል ሲኞር ፌራሪን እንዲረዳው ጠየቅሁት ። ጉዶ ፈገግ
ብሎ ከእንግዳ መቀበያ ክፍሉ ወጣ ሲል ባልተለመደ የሀዘን
ስሜት ተመለከትኩት ። ከሀዲነቱን ከተገነዘብኩበት ቀን
እንስቶ ተሰምቶኝ በማያውቅ ርሀራሄ አዘንኩለት ። ተማ
ሪዎች ሆነን ጣፋጩን የልጅነት ጊዜ በአንድነት ያሳለፍ
ነው ብርቅ ጊዜ ፣ እንደ ሁለት የአንድ ትምህርት ቤት
ምስጢረኛ ልጃገረዶች እንገት ሳንገት ተያይዘን ያደግነው
ትዝታውን ሳላስበው ከፊቴ ድቅን እያለ ሀዘን አመጣብኝ ።
በእውነት ውብና ድንቅ የልጅነት ጊዜ በአንድ ላይ አሳ
ልፈናል ። ደስ ብሎን ዓለማችንን በነጻነት ቀጭተናል ።
እርስዋ መጥታ እንደገነት መግቢያ የጠነከረውን መተማ
መናችንን ሳታፈርሰው በዋሾው ውበትዋ ዐይኖቼን ሳታ
ሳውረው እርሱንም ወደ እብደትና ውሸታም ከሀዲነት
ሳትለዋውጠው ሁሉነገር ሰብአዊና መልካም ነበር ።
ስለዚህ ይህ ሁሉ መከራና ሲቃይ በእርስዋ ስህተት ነው ።
የሕይወታችን ጉድፍ እርስዋ ነበረች ። የመጨረሻው ከቶ
ቅጣት በእርስዋ ላይ መፈጸም አለበት ። ደግሞም ቅጣቶ
ዋን ትቀበላለች ። ሁለት ጓደኞችን አቆራራጭ የሆነ
ውም ስለታም ውበትዋ ቅጣቱን ይቀበላል ። ቁጭቱ ሁሉ
አሁን ያለቦታው ነው ። የተንኮል ወጥመድ እንደማይ
ፈታ ተደርጎ ተዘጋጅቷል ። የበቀል ተንኮል እንደማይ
ፈታ መተት ተቀምሟል ። ለማመንታት ከእንግዲህ ጊዜ
የለኝም ። እያንዳንዱዋ ደቂቃ ወደ አቀድኳት የኮሶ ምሬት
መደምደሚያ ታመራለች ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለት ሰዓት ገደማ እንግዶች ተከታትለው መጡ ።
አሥራ ሁለታችን ገብተን የተቀሩትን ሁለቱን ስንጠባበቅ
ጉዶ የክት ልብሱን ለብሶ እንዳማረበት ለራሱም እየተሰ
ማው ሲገባ እንግዶቹ በሙሉ ልብ የሞቀ አቀባበል አደ
ረጉለት ።

አብዛኞዎቹ እንግዶች የእርሱው የቅርብ ጓደኞች ስለ
ነበሩ ልባዊ ሰላምታ እያቀረቡ ልባዊ ፍቅራቸውን ገለጹ
ለት ። በዚህ አፍታ አንዲት ማስታወሻ ደርሳኝ ማንበብ
ጀመርኩ ። ማስታወሻዋ ከተጋባዦቻችን እስከአሁን ያል
ጡት ሁለት ወንድማማቾች በሥራ ብዛት ግብዣችን
ላይ ሊገኙ ባለመቻላቸው ይቅርታ የሚጠይቅ መልእክት
ይዛለች ። ወዲያው ምልክት ሰጥቼ ሁለቱ ጓደቻችን በአ
ክል ምክንያት በመሀላችን ሊገኙ ያለመቻላቸውን ለተጋ
ባዥ ገልጬ ሁለቱ ወንድማማች በሁሉ ደረጃ ፍላጐታ
ቸው መቆራኘቱን ሰው እየቀለደም እያደነቀም እንግዶቼን
ወደግብር ቤት መርቻቸው መግባት ጀመርን ።

ለአሥራ አምስት ሰው አምሮ የተጌጠው ገበታ ከሩቁ
አይንን በሚማርኩ አበቦች ዙሪያውን ተጊጧል ። በየወ
ንበሩ ግንባር የተደረደረው የብርጭቆ አይነት ብቻ ታይቶ
የማይጠገብ ነው ። ወለሉ የተነጠፈበት ሲጋጃ እንደ
ፍራሽ ሲረግጡት ትሙክ ትሙክ ይላል ። የግብር ቤቱ
መዓዛ ከሩቅ ይጣራል ። የእንግዶቼ መቀመጫ ራሱ ምቾ
ትን አደላድሎ የሚጠብቅ ብርቅ ሥራ ሲሆን ቢደገፉት
ወደኋላ የሚለጠጥ ነው ። ጠቅላላው ዝግጅት የሩቅ ምሥ
ራቅ ነገሥታት የሚደግሱትን ዓይነት ሌልኛ ሆኖአል ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ለአሥራ አምስት ሰው የተዘጋጀው መቀመጫ በአሥራ ሦስት ሰው ብቻ የመሞላቱ ሚስጢር ሲታወቅ ምን ዓይነት የፍርሀት ስሜት እንደሚፈጥር በሀሳቤ ተመላለሰ ። አሥራ ሦስት ሆኖ ገበታ ላይ መቀመጥ ለአውሮፓውያን እንደ መጥፎ እድል ስለሚቆጠር የእንግዶቼን ስሜት መመዘን ጀመርኩ ። ጉዶ ቀደም ሲል እንደገለጸው መቼም ከአጐቱ ሞት ወዲህ ፍርሀት ካላደረበት በስተቀር አለኝ በሚለው ንግር ምክንያት በአሥራ ሦስት ቁጥር የሚሸበር መስሎ አልታየኝም ።

እንግዶቼ እየተጨዋወቱ ተከተሉኝ ። ሁሉም በደስታ መንፈስ ይቀላለዳል ። ገበታ ቤት ስንደርስ በሩ በሰፊው ተከፍቶ ለስላሳ ሙዚቃ ተቀበለን ። እንግዶቼ የአዳራሹን ጌጥ ሲያዩ አድናቆታቸውን መቆጣጠር አቅቷቸው በቃላት ይገልጹ ጀመር ። አስተያየታቸውን እንዳልሰማሁ ሆኜ ዋናውን የክብር መቀመጫ ያዝኩ ። የማሪናው መስፍን በግራዬ ጉዶ ፌራሪ በቀኜ ተቀመጡ ። ሁሉም የተመደበለትን መቀመጫውን ከያዘ በኋላ ለስላሳው ሙዚቃ ሞቅ ደመቅ ብሎ መሰማት ጀመረ ። ሙዚቃው ድግሱን አሟሟቀው ። እንኳን ደህና መጣችሁ የሚለው ታዋቂ ዜማ በለዘለሰ ድምጽ አዳራሹን የሞቅታ ፈገግታ ጨመረለት ።

«ቀዩን ወይን ቅዱት ዋንጫችሁ ይሞላ
ጤና ለጎበዞች ጠላት አፈር ይብላ ፤
ደስታን ተደሰቱ ፋሲካን ፈስኩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጎብስቱን ቁረሱ መስዋእቱን ባርኩ ፤
ቀይ ወይን ይቀዳ ዋንጫችሁን አንሱ
የተኛው ይቀስቀስ ጥግትንም እርሱ
ደስታን ተደስቱ ፋሲካው ይሳካ
ጓደኝነት ይዳብር አበባችሁ ይፍካ ፤
ቀዩ ጠጅ ይንቆርቆር ድካማችሁ ይቅለጥ
ሞት እንኳ ቢመጣ በደስታችሁ ይዋጥ ።»

ዘፈኑ እንዳለቀ ፊቱን ሳያሳይ መጋረጃ ውስጥ ሆኖ ለሚያዜመው ዘፋኝ ተጨበጨበለት ።

ጉዶ ፈራሪ ድምጹን ከፍ አድርጐ «እረ በሊቀመላ እኩ! ይህ ግብዣ ለኔ መቀበያ ከሆነ ስህተት ተፈጽሞአል ። ለኔ የሚገባኝ አይደለም ። ይህ ለንጉሥ መቀበያነት የሚበቃ ነው ።» አለ ።

«አንድ ሀቀኛና ታማኝ ሰው ከንጉሥ የሚያንስበት ጉልህ ምክንያት ለኔ አይታየኝም ። እኛ እዚህ የተሰበሰብ ነው ደግሞ እያንዳንዳችን ሀቀኞችና ታማኞች ነን ብዬ ስለማምን ይህ ግብዣ አይበዛብንም» አልኩ ።

የማሪናው መስፍን ስለገበታው ጌጥ አድናቆታቸውን ካዳመጠ በኋላ «ብቻ በምሥራቅ ጉዞዎ ያዩትን ሁሉ በዚህ ግብዣ ላይ እንዲንጸባረቅ ሳያደርጉ አልቀሩም ።» አለኝ «ቫቲካ የሚባል መለኮታዊ ኃይል ባለው የግሪክ አምላክ፤ ስለተደገሰ ግብዣ አንብቤ የዛሬው ግብዣ እርሱን አስ


t.me/OLDBOOKSPDF

ታውሶኛል ። ስለዚህ ጌታ ሲዛር እንደሻቴክ ሊቆጠሩ ይገባል እላለሁ» አለ ጉዶ ።

ፈገግ ብዬ «ሕይወት ልትሰጠኝ የምትችለውን ደስታ ሁሉ ለኔም ስለማትነፍገኝ የመለኮታዊ ኃይል ግፊት አያስፈልገኝም» አልኩት ።

ሰዓሊው አንቶኒዮ በሰጠሁት አስተያየት ተደስቶ «እውነታቸውን ነው የተፈጥሮ ውበትና ሰብአዊነት ከሁሉ በላይ የተሟላ ደስታን ይሰጣል ። ከሕይወት በኋላ እንኳ ሞት መኖሩ ለእኛ ሕይወት ውበትን የሚሰጥ ነው» አለ ።

ለመናገር እንዲመቸው ሾርባውን ቸኩሎ የጨረሰው ማራኬ አፉን እያባበሰ «ስሜቱ ሚዛናዊ የሆነ የጥበብ ሰው መስለህ ነው የምትናገረው ። የኔ አስተሳሰብ ግን ትንሽ ለየት ያለ ነው ። እኔን አንድም የሚያረካኝ ነገር የለም ። ረክቼ በቃኝ ያልኩበት አጋጣሚ የለኝም ። ይኸ ነው የኔ ተፈጥሮ ። ቆንጆ አበባ ሳይ ምነው በርከት ብሎ ባየው እላለሁ ፣ የማታ ጸሐይ እንኳ ደስ ካለችኝ ያን የመሰለውን በርከት ብሎ ማየት ይርበኛል ። የምትፈቀር ቆንጆ ሴትማ ሳይ............»

«የማያልፍ ፣ የማያልቅ የሴት ፍቅር ትፈልጋለህ ማለት ነዋ» አለ የፈረንሳዩ ካፒቴን

«እንዴታ ምነው አልፈልግ» ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የክብር ሚዳሊያ ደረቱ ላይ የደረደረው ሼቫሌ ማንሲኒ አንድ ሁለት ወይን ጠጅ መለስለስ ካደረገ በኋላ ሳቅ አበዛ ። ዓይኑ ግንባር ቀዶ የሚገባ ይመስላል ። ፊቱ ጠር ጣራ ፤ ሰውነቱ ቀጭን ነው ። ድምጹን ከሁሉ በላይ አክርሮ በጋብቻ ላይ ቀልዱን ያበዛል ። «እውነት ነው ለኔም ይኸ በሕግ የምናሸሞነሙነው ጋብቻ ትልቁ ስህተታችን መስሎ ነው የሚታየኝ ።»

«እና ለዚህ ነው አንተ ምክረኛው የማታውቀው» ብሎ ጉዶ ጠየቀው ፤

«እኔ አንዲት ሴት ብቻ እንድስም የሚያስገድደኝን ሕግ አልቀበልም ። እንደእውነቱ ከሆነ ከፈለኩ ሁሉዋ ንም የማልስመው ለምንድነው ?»

የገበታውን ቤት ሳቅ አናወጠው ። ጉዶ ጥያቄውን ሳይጨርስ ማዕዱ እስኪረግድ ሁሉም ተንከትክቶ ሳቅ በሳቅ ሆነ ። ሳቂ ጋብ እንዳለ «ሁሉንም እስማለሁ ስትል ካገቡት በስተቀር ማለትህ አይደል ?»

«ሁሉንም ስል ያገቡትንም ይጨምራል ። የመቸው ምኝ ነህ? ያገቡት በተለይ ያሳዝኑኛል ። ምስኪን ናቸው ። ባሎቻቸው ከሜጉላ ቤት በኋላ የሚዘነጉዋቸው ብዙ እገል ግሎት ያስፈልጋቸዋል ።»

እኔ ራሴ ሳቅ በሳቅ ሆንኩና ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

«ትክክል እኮ ነው ያልከው ። ባሎች ቀዝቃዛ ባይ ሆኑም በመታመን ቅባት ዓይናቸው እንዳያይ ታሽቶ ሚሽቶቻቸውን መስረቅ ያስፈልጋል ። በተለይ ጉዱ ፈራሪ በዚህ እምነት እንዳለህ ብዙ ጊዜ አጫውቶኛል ።» ስል ነገሩን እንዳልወደደው ፊቱ ላይ በግልጽ ታየ ።

ሁኔታውን ሌላው እንዳያጤነው ልብን የሚመስጥ ሙዚቃ እንዲዘፈን ጠቀስኩ ። ጉዱ ግን በአንድ ጊዜ ተለዋወጠ ። የእንግዶቼ የምግብ ፍላጐት እንደገና እየተከፈተ ፤ በልዩ ጥንቃቄ የተዘጋጀው ምግብ በሰፊው መመላለስ ቀጠለ ። ምርጥ የወይን ጠጅ ያለገደብ ተቀዳ ።

ቪንቼንዞ በትእዛዙ መሠረት ከኋላዬ ቆሞ የጉዱን ዋንጫ እየሞላ ይጠብቀኛል።አልፎ አልፎ የመስፍኑንም ዋንጫ ይሞላል ። የማሪናው መስፍን እንደጥንቱ ጣሊያኖች ወይንጠጅ መቀላቀል ስለማይወዱ ስካር ቀርቶ ሞቅታም አልተጫናቸው ። ዐይናቸው ቁልጭ ብሎ የመናገር ፍላጐታቸው ከወትሮው ሞቅ ደመቅ ብሎአል ። የምግቡ ዓይነት እየተለዋወጠ ሲመላለስ የተጋባዡ የደስታ ድምጽ እንደንብ እየተመመ አልፎ አልፎ የብርጭቆ የቢላዋና ሹካ ቅጭልጭልታ ግብር ቤቱን አሟሙቆታል ። እኔም እንደሌሎቹ ተጋባዦች አቅራቢያዬ ከተቀመጡት በተለይ ከጉዱና ከማሪናው መስፍን ጋር አወጋሁ ።

አሁን ግብዣው አቅጣጫውን መለወጥ ጀመረ ። ሙዚቀኞቹ የጀመሩትን ቅኝት ሲጨርሱ ቀልድና ሁካታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ው ያቋም እንደተባለ ነገር ፀጥ አለ ። ግብዣ ቤቱን ባ ልተጠበቀ ዓይነት ድብት አድርጎ የሚይዝ ፀጥታ ዋጠው ና ያሳላፊዎቹ የእግር ድምፅ ብቻ ይቆጥር ጀመር ።

የዝምታው መነሻ ተጋባዡ አሥራ ሶስት ሆኖ ገበታ ላይ የመቀመጡ ዜና ከአንዱ ጆሮ ወደ ሌላው መዳረሱ ነው ። ዝምታውን በጫወታ ለመለወጥ ሞከርኩ ፣ አልሆ ነልኝም ። ሁሉም ወደቀን ቅዝቱ ስተት ብሎ ገብቷል ። ግማሹ በእጁ የዳቦ ቁራሽ ያፍተለትላል ፤ ግማሹ ብርጭቆ ይነቀንቃል ፤ ግማሹ ጠረጴዛ ልብሱ ላይ ያፈጣል ፤ አን ዳንዴ ሁሉም በሰፊው በተከፈተው መስኮት ጨረቃዋን ያያሉ። በመጨረሻው ቪንቼንዞ ሻምፓኝ ሲከፍት ሆን ብሎ አስጮኸው ። ሁላችንም ጆሮአችን ላይ የተተኮሰብን መስሎን በአንዴ በሳቅ ፈነዳን ። በዚህ መሀል ተጋባዡ ገበታ ላይ አስራ ሶስት ሆኖ መቀመጡን ይፋ አድርጌ ለተጋ ባዦቹ መናገር የሚያስፈልግ መሰለኝ ፤ ግን አመነታሁ ።የሀ ገሪቱ ምርጥ ሰዎች በጥንቆላ የማያምኑ ሲሆኑ ስለሚችሉ ከነቱ አምልኮቱን ከመጤፍ አይቆጥሩትም ብዩ አሰብኩ ። እየመ ጉዶ ፌራሪ ግን ጠባዩ በይፋ በፍርሀት ተለወጠ ። እየመ ላለሰ ብርጭቆውን ከገለበጠ በኋላ እጁ በፍርሀት እየተንቀ ጠቀጠ የበላበትን ሳህን አሽቀንጥሮ ወረወረ ። በዚህ ጊዜ እኔ ለመናገር ብድግ አልኩና ፤

«የተከበራችሁ ውድ ጓደኞቼ ፤ ይህ ከጆሮ ጆሮ የዘመተው የአሥራ ሶስት ሆኖ ገበታ መቀመጥ ጉዳይ ለኔ ከተከሰተ ጥቂት ጊዜ ሆኖአል ። ከአሥራ አምስት



t.me/OLDBOOKSPDF

ተጋባዥች መሀል ሁለቱ ወንድማማቾች ስለቀሩ ቁጥራችን እሥራሶስት ሊሆን ቻለ ። ይሁንና የሁላችንም የአእምሮ ደረጃ ለጥንቆላና ከንቱ እምነት ቦታ ስለሌለው ችላ ብየው ነበር ። ይህ የአሥራ ሶስት ቁጥር ነገር የጀመረው ክርስቶስ የመጨረሻውን ራት ባበላ ዕለት ከመሀል አንዱ ከሀዲ መሆኑ በታወቀ ጊዜ ነው ። ከመሀከላችን ግን ክርስቶስም ሆነ ይሁዳ ስለሌለ ሊያሳስበን አይገባም ። በተለይም ዛሬ የልደት በዓል ምሽት ስለሆነ ለጥንቆላ ቦታ የለውም» አልኩ ። ንግግሬን የደስታ ጭብጨባ አጀበው ።

ከፊትለፊቴ የተቀመጠው የጦር መኮንን «እባካችሁ ይህን አጉል ነገር ተውን ። ይኸ የፈሪ አሮጊቶች ግብዣ አይደለም ። ይልቅስ ዋንጫችን ይሞላ ይሁዳም ቢሆን የኛን ዓይነት ግብዣ ተጋብዞ ቢሞት ማንም አያዝንለትም ነበር ።» ሶስት ጊዜ ዋንጫውን አንስቶ መሞላቱን እያሳዩ ሲገለብጥ ሌላው ሁሉ በርሱ ዓይነት እያነሳ የተቀዳለትን ገለበጠ ። እያደር ደስታ ሲደምቅ የከንቱ እምነቱ ፍራቻ ተረሳ ። ጉዶ ፈራሪ ብቻ ፍርሀት የገባው መሆኑ እስታወቀበት ። ወይንጠጁን ከልክ በላይ ሲመላልስ ግን ሁሉን ረስቶ እንደገና ተጫዋች ሆነ ።

በመጨረሻው ጣፋጭ ቀረበ ። ለዋናው የመጠጥ ጊዜ እንዲቀመጥ ያዘዝኩት ብርቅና ድንቅ የወይን ጠጅ መከፈት መቀዳትና መጠጣት ጀመረ ። ገበታው ትርኢት በዛበት ። የደስታ ድምጽ ጣሪያውን ቀዶ ወጣ ። የሻምላ ባለሙያተኞች ሰልታቸውን በወሬ ከሸከሹት ፣ ሰዓሊውም


t.me/OLDBOOKSPDF

በወሬ ቀለሙን ይቀባ ጀመር ፤ ባለቅኔውም ቅኔውን ለመ ቀኘት ፤ ሁሉም የየዝንባሌውን ለማውራት ተቻኮለ ። ሻምፓኝ መላልሶ በዞረ ቍጥር ተጋባዡ ስካሩን አልቻለው አለ ። እኔና መስፍኑ ብቻ ራሳችንን መቆጣጠር ቻልን ። እኔ ሆንብዬ ወይኑም ሻምፓኙም እንዲያልፈኝ አደረግሁ ።

ሁሉም ሲጫወት ጀርዬ ወደ ጉዶ ፌራሪ ወሬ አዘነ በለ ። ስለሚሽቴ ውበት ጐኑ ላለ ሰው ያወጋል ። ቅዱስ ስሙ እንደተነካበት ሰው ደሜ ያለመጠን ተቆጣ ። ልቤ እንደዚያ ግሎ እጅና እግሬ ግን እንደድንጋይ ቀዘቀዘብኝ ። በዚህ ቁጡ ስሜት ድንገት ብድግ ብዬ ቆምኩና ፀጥታ ለመ ጠየቅ ገበታውን መታ መታ አደረግሁ ። በብዙ ጉትጐታ ተጋባዡ ፀጥ ብሎ ያዳምጠኝ ጀመር ።

«ጓደኞቼ ፤ በዛሬው ዕለት ጓደኛዬን ጉዶ ፌራሪን እን ኳን ደህና መጣህ እንድትሉልኝ እለምናለሁ ።» ንግግሬን በጭብጨባ ሲቀበሉ ጉዶ እያጉመተመተ ሲጃራውን ለኰሰ። «ይህ ጓደኛችን ለጥቂት ቀናት ተለይቶን ቅር ተሰኝተን ነበር ። አሁን ግን ተመልሶልናል ። አመጣጡም ሲወጣ እንደነበረው ሳይሆን በሀብት ተንቆጥቁጦ ነው የተመለሰ ው። ስለዚህ ክብሩ ሊሰጠው የሚችለውን ግብዣ እዘጋጅተ ንለታል።» አሁንም ተጨበጨበ ። ዋንጫ ተነስቶ ለጉዶ ጤንነት ተጨለጠ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ጉዶ እንዴም ምስጋናውን አልተቀበለውም ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዶን ዞር ብዬ ሳየው የተሞላ ሻምፓኝ ፊትለፊቱ ተቀምጧል ፤ በከንፈሩ መሀል የተለኮሰ ሲጋራ ይዟል ። መልከ መልካም ፊቱ በመጠኑ ጠመም ብሎ በይኑም በድካም ዓይነት ቆርዝዟል ። ረጅሙን መስኮት አልፎ የገባውን የጨረቃ ብርሀን ያስተውላል ።

«ጓደኞቼ እንድትደሰቱልኝ ካስጠራኝ ምክንያት አንዱ የሲኖር ጉዶ ፌራሪ መመለስ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ልዘረዝርላችሁ የተነሳሁበት የራሴ ደስታ ነው ። ይኸውም በሽማግሌ እድሜዬ ፣ በግማሽ ዓይነስውር ሁኔታዬ ሊታገባኝ የወሰነች ቆንጆ አጋጥማኛለች ። ስለዚህ ይህ ግብዣ የጌሠርግ ጭምር ነው ።» ጉዶ ከመቀመጫው እንደመነሳት እንደመናገር ብሎ እንደገና ተቀመጠ ። ፊቱ በድንጋጤሙት መስሎአል ።

«በቃ እንግዲህ ጌታ ኣሊቫ የሴት ቀሚስ መከተል ከጀመረ ከእንግዲህ ለእንዲህ ያለው ግብዣ ቦታ ስለሌለ ደስታን ደህና ሰንብች ብለው ይሰናበቱ» ብሎ ሼቫሌ ቀለደ ።

«እኔም ይኸን ከእርሶ አልጠብቅም ነበር» አለ ጉልድሮ «እንዴት ነጻነትዎ ሀያ ሴት ሲፈቅድሎ በአንዲት ሴት መብትዎን ሁሉ ይነጠቃሉ?» ሌላው ተጋባዥ ከወደጥግ ድምጹን እንደጸሎተኛ አለሳልሶ «ብጽኢት ፣ ከአልማዝና ከእንቁ የምታስንቅ ከተገኘችስ አንዲት ብትሆን ትመረጣለች እንጂ ከብዙ ሴት ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

« ጊዜ የማያመጣው ጉድ የለም ። አሁን አንተም ሳሉስ ስትሪ እንዷት ትበልጣለች ትል ጀመር ? አንተም የኔኛልስ ሴቶች ውሽማ? እርግጠኛ ነኝ የወይን ጠጁ እንጂ አንተ አይደለህም የምትናገረው ።»

እጄን ገበታው ላይ ያ.ገፍ አድርጌ ልናገር የምፈልገ ውን እስከወጋ ቆምኩ ። ሌላው ተጋባዥ እንደገና እንኳን ደስ ያለህ ብሎ እስተጋባልኝ ። ከጉዶ በስተቀር ሌላው ሁሉ በደስታ ፈነደቀልኝ ።

«ጓደኛችን ሮመልካሙ ጉልድሮ ያለው ትክክል ነው ። ሴቶችን በመራቅ የታወቀ ስም እንዳለኝ የሰማችሁት ነው ። ነገር ግን በውበትዋ ተወዳዳሪ የሌላት ቤት አጥምዳ ያዘች ኝ ። እንደምታፈቅረኝም በልዩ ልዩ ምልክቶች አረጋገጠች ልኝ ። ለጋብቻ ወዳ ሕይወትዋን አስረከበችኝ ። ይህን ሁሉ በረከት ረግጦ ማለፍ ሰብአዊ ክብሬን የሚነካ ስለሆነብኝ ጋብቻውን መቀበል ግድ ሆኖብኛል ። ከገነት የተላከልኝን ፍሬ ሳለመቀበል መሞከር ከሰዎች ተራ የሚያወጣኝ ስለ መሰለኝ እድሌ የሰጠኝን ተቀብያለሁ ። ስለዚህ ሁላችሁም ለኔ ሙሽራ ክብር ብላችሁ ዋንጫችሁን አስሞልታችሁ እንድታነሱልኝ እለምናለሁ ።» ስል ሁሉም ዋንጫቸውን እያስሞሉ ብድግ አሉ ። ጉዶም ጠምዘዝ እንዳለ ብድግ አለ ። ብርጭቆው ግን በእጁ ውስጥ አልረጋ ብሎ ይንቀጠ ቀጣል ። በአንድ ጊዜ ተጋባዦቹ በሙሉ ተነስተው ብርጭቆአቸውን አስሞልተው «የሙሽራዋ ስም ይገለጽል ንና ዋንጫችንን እናንሳላችሁ» አሉ የማሪናው መስፍን ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎን ስምዋ ይገለጽልን ። ምናልባትም የታወቀች ላትሆን ትችላለች» አለ ጉዶ ።

«ስምዋን አንተ በተለይ በደንብ ታውቀዋለህ ።» ዋንጫዬን ብድግ አድርጌ ባጭሩ «ለእመቤት ሮማኒ ዋንጫችንን እናንሳ!» አልኩ ።

«ውሸታም! ቀጣፊ!» ብሎ ጉዶ በአንድ ጊዜ ስድቡን አለበሰኝ ። የተሞላውን ሻምፓኝ ፊቴ ላይ ረጨብኝና ብርጭቆው እግሬ ስር ወርዶ አመድ ሆነ ። ተጋባዡ መቀመጫውን በአንድ ጊዜ ጥሎ በዙሪያችን ቆመ ።

ጉዶ የሚጨብጠውን አጥቶ «አንተ ደንቆሮ ፤ ስጋህን ነው በጣጥሼ ለንፋስ የምሰጠው» ብሎ አንገቴ ላይ ጉብ ለማለት ተጋበዘ ። እኔ የፈሰሰብኝን ሻምፓኝ በመሃረብ ስጠራርግ የጋበዝኩት የጦር አለቃ የጉዶን እጅ ይዞ «አበድክ ወይስ ሰከርክ? የሠራኸውን ሥራ ታውቃለህ?» ብሎ ጠየቀው ። ጉዶ ደምስሩ ተግተረተረ ። ትንፋሹ ዳገት እንደሚወጣ ሯጭ አቀብ አቀብ እየተነፈሰ ፡ «አንተ ሌባ ፤ አንተ ቀጣፊ ፡ በሕይወትህ ትከፍላታለህ ለሠራሀት ወንጀል» ብሎ ዘለፋውን አልጨረሰው ሲል የማሾፍ ሳቅ እየሳቅሁ «በደስታ በሕይወቴ እከፍላለሁ» ስል ተጋባዡ የየራሱን ፍርድ ለመስጠት ይመለከተናል ። «እኔ ግን የበደልኩህ ነገር የለም ። ቆንጆዋ እመቤት ባንተ ላይ ያላትን ጥላቻ አረጋግጣ ፤ እኔን ማፍቀርዋንም ገልጻ ነው


t.me/OLDBOOKSPDF

ያጨኋት ። የሚያጠራጥር አቋም ቢኖራት እኔም በዚህ እድሜዩ ባላጨኋት ነበር ።» አልኩ ።

ጉልድርሮ የተባለው ተጋባዥ እየጮኸ «በሁለመናህ የምታሳፍርና የምታስቀይምስ አንተው ፈራሪ ስለሆንክ ድንፋታህን ያዝ አድርግ» አለው ።

እያንዳንዱ ፍርድ ይሰጥ ጀመር ። «ጌታ ሲዛር ጥፋት የለባቸውም» የሚለውን አስተያየት እያንዳንዱ ተጋባዥ ወዲያው ሰነዘረ ።

«ፈራሪ ካሳ መስጠት አለበት» የሚል አስተያየትም ተሰነዘረ ። የፈራሪ ፊት የሞተ ሰው ፊት መሰለ ። ጥርሱ ገጦ ዓይኑ ፈጠጠ ፤ በመጨረሻው እየተንደረደረ ወደኔ መጥቶ «እኔኑ በበደልከኝ መልኬ እኔው ልካስህ አንተ ፈሪ ወራዳ ሌባ ፤ ለካሣህ የሚገባህ ይኸ ነው» ብሎ በቃሪያ ጥፊ ይቀመሰልህ ቢለኝ ጣቱ ላይ ያጠለቀው የራሴው የአል ማዝ ቀለበት ጉንጬን ቧጭሮ አደማኝ ። ወደጦር አለቃው ዘወር ብዬ «እንግዲህ ወዳጆቼ የፈሪ ሞት ከመሞት በይፋ ፍልሚያ ይዘጋጅና የክብር ሞት ልሙት» ብዬ ጠየቅሁ ።

የጦር አለቃው ፍልሚያ እናዘጋጅለን ብሎ ወዲያው ወሰነልኝ ። ጉዶ ፈራሪ እንደተበዳይ ሆኖ በቅርብ የሚያ ውቀውን ካፒቴን ለፍልሚያው እንዲቆምለት ቢጠይቅ ፤ መንስኤው በደለኛነት ስላለው ኀሊናዩ እሺ ብሎ ሳንተ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲቆም አይፈቅድልኝም አለው ። ጉዶ እየዞረ የሚቆም ለትን ጠያየቀ ። ሁሉም እምቢ ሲለው ለፍልሚያ የሚቆ ምለት ፍለጋ የገበታ ቤቱን ለቆ እየተቆናጠረ ወጣ ። ቪን ቼንዞን ጠቀስ አድርጌ ከኋላ ኋላ እንዲከተለው ሰደድ ኩት ። የማሪናው መስፍን «ጌታ አሊቫ የዚህን መናኛ ሰው ዘለፋ በትዕግሥት መቻላቸው እንደተአምር የሚቆጠር ነው» አሉ ።

የጦር አለቃው ተፋላሚም የሚቆምለትን ተጠሪ ፍለጋ ሂዶ እስኪመለስ የፍልሚያውን ዓይነት እንጠያየቅ አለኝ ።

አሥራ አንዱም ተጋባዦች ከኔ ጐን የሚቆሙ መሆ ናቸውን አረጋገጡልኝ ። የጦር አለቃው «አሁን እኩለ ሌሊት ሆኖአል ፤ ስለዚህ ፍልሚያው ጠዋት በአሥራ ሁለት ሰዓት መሆን አለበት»አለ ።

«ተበዳይ ደግሞ እርስዎ ስለሆኑ የመሣሪያውን አይነት መምረጥ ይችላሉ ።» አሉ መስፍኑ ።

«በሽጉጥ ይሁንልኝ» አልኩ ።

«የሽጉጥ ፍልሚያ ከሆነ ከቪላ ሮማኒ ፊትለፊት ካ ለው ጉብታ ጀርባ ሜዳው ላይ ብናደርገውስ?»

ይሁን ብዬ እጅ ነሣሁ ። ቦታው ከሰው መኖሪያ አካ ባቢ የራቀና ብቸኛ ስለሆነ እቅዱን የሚያሰናክል አይ መጣም ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«ይሁን እንግዲህ መሣሪያው ሽጉጥ ፤ ሰዓቱ ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ፤ በተፋላሚዎች መሀል የሚኖረው ርቀት የበዳይ ወገን ሲገኙ ይወሰናል» አለ የጦር አለቃው ።

ሁሉንም በፈገግታ አየት አድርጌ ካዳረስኩ በኋላ «እንግዲህ አመሰግናለሁ ፤ ለሆነውም ችግር ይቅርታችሁን እጠይቃለሁ ። በኔ ላይ ላሳችሁ ከፍተኛ ግምት ባለውለታችሁ ነኝ ። ደግነታችሁን በሕይወት ካለሁ በደስታ እከፍላለሁ ፤ ከሞትኩም ትዝታችሁን ይገፍ ገነት እቆያችኋለሁ ። የነገውን ፍልሚያ ከተረፍኩ በሠርጌ ቀን የደስታዬ ተካፋይ አደርጋችኋለሁ ። ለጊዜው ግን በደህና እደሩ» ። እየጨበጡኝ በሞራል አብረውኝ መቆማቸውን እየገለጹልኝ በየተራ መውጣት ጀመሩ ። እኔም ተሰነባብቼ ሹልክ ብዬ ወጥቼ ወደክፍሌ ሄድኩ ። ከሁካታው አምልጬ ፀጥታ የሰፈነበት ክፍሌ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ያህል ፀጥ ብዬ ተቀመጥኩ። ቪንቼንዞን ከላኩበት እስኪመለስ ተቻኮልኩ። የሆቴሉ ሠራተኞች የታላቁን ግብግር መሰናዶ እያነሳሱ ላይና ታች ሲመላለሱ የሚያወሩት አልፎ አልፎ ይሰማኛል ። ከተጋባገሮቼ ጋር ግን ሞትም ተጋብዞ በመካከላችን ተቀምጦ እንደነበር ከኔ በስተቀር ማንም የሚያውቅ አልነበረም ። ከመካከላቸው አንዱ ከሀዲ ስለ ሆነ መሞት አለበት ። ቀትኛው እንደሚሞት ደግሞ እኔ ጠንቅቄ አውቃለሁ ። የሞት ዕጣ የኔ እንዳልሆነች እርግጠኛ ነኝ ። የኔ መሞቻ ጊዜ አሁን አይደለም ። ያለ የሌለ የተፈጥሮ ኃይላት ሁሉ የበቀል ተግባሬን እስካከናውን ሕይወቴን ይጠብቁዋታል ። ለወጉ ያህል ብዕርና ወረቀት አውጥቼ


t.me/OLDBOOKSPDF

ኑዛዜዬን እስፍሬ ለማሪናው መስፍን እንዲደርስ አድራሻ ጻፍኩበት ።

እኩለሌሊት ካለፈ ቆየ ። ቪንቼንዞ አሁንም አልተመለሰም ። ጊዜ ለመግደል መስኮቱን በሰፊው ከፍቼ በጨረቃ ብርሀን የተወለወለ ብር መስሎ የሚያብረቀርቀውን ባሕር ቆሜ ተመለከትኩ ። ንጋት ላይ ፍዝዝ ብዬ እንደተቀመጥኩ ቪንቼንዞ አጠገቤ እንደጅብራ ተገትሮ አየሁት ።

«በስመአብ! መጣህ እንዴ አንተ እህ እንዴት ሆነ?» ብዬ ጠየቅሁት ።

«ሁሉም ነገር እንደሀሳብዎ ተሳክቷል ፤ ሲኞር ፌራሪ ስቱዲዮው ገብቷል »።

«እዚያ ነው ትተኸው የመጣኸው?»

«አዎን ከግብር ቤቱ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ በተሳፈረው ጋሪ ከኋላ ተንጠላጥዬ ተከተልኩት ፤ ቪላ ሮማኒ ሲደርስ በሩን እንደእብድ ብዙ ጊዜ ከደበደበ በኋላ ሽማግሌው ጂያኮሞ መጥቶ ትልቁን በር ከፈተለት ። ዛፍ ስር ቆሜ ጊቢውን ሳስተውል ቅጽረግቢውን ጭለማ ውጦት ጂያኮሞ እየተንቀጠቀጠ የያዘው ፋኖስ ብቻ እጁ ላይ ይታያል ።

«እመቤቲቱን ማግኘት አለብኝ» ብሎ ሲኞር ፌራሪ ጂያኮሞ ላይ ቢያንባርቅበት ሽማግሌው ሰይጣን ያናገረው ይመስል ዐይኑን እንደጉጉት አፍጦና ድርቅ ብሎ «እመቤቱ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሉም ሄደዋል» ሲለው ዘሎ ሽማግሌው ላይ ተወርውሮ እን ደስልቻ እህል ወዲያና ወዲህ አወዛወዘው ።

«አዎን እመቤቱ የሉም ወደገዳም ከሄዱ ዛሬ ሁለት ቀን ሆናቸው ፤ ገዳሙ ከዚህ የአሥራ ስድስት ኪሎ ሜትር መንገድ አለው ።» እያለ እንደእብድ ጮኸ ።

«የት ነው የሄደችው?» እያለ አሥሩን ካስለፈለፈው በኋላ ከነፋኖሱ ጂያኮሞን አሽቀንጥሮ ቢወረውረው እስ ፋልቱ ላይ ወድቆ ፋኖሱም እንክሽክሽ አለ፣ ሽማግሌውም ተሰብሮ ወዲያው ማቃሰት ጀመረ ። ከዚያ ወዲያ ሲኞር ፌራሪ እንደእብድ እየጮኸ ፣ «ሂደህ ተኛ፣ ሞት እስኪመ ጣልህ ተኛ ። እመቤትህ ስትመጣ ደግሞ ልገድላት መጥቼ እንደነበር ንገራት ። ይህ ቤትና በውስጡ የሚኖሩ ሁሉ የተ ረገሙ ናቸው» አለ ።እርግማኑን ሲጨርስ ባለ በሌለ ጉል በቱ እየሮጠ ግቢውን ጥሎ ወጣ ። ርቆም አልሄደ ። ግቢ ውን ትንሽ ወጣ እንዳለ በድንገት መሬት ላይ ድፍት አለ ።

ማንነቴን እንዳያውቅ ፊቴን በባርኔጣዬ ሸፍኜ አንድ ባልዲ ወስጄ ውሀ ደፋሁበትና ነፍስ ዘራ ። ቀና ሲል መን ገደኛ መስዬው መሳልኦ ካመሰገነኝ በኋላ አጠገቡ ከነበ ረው ቧንቧ ውሀ ብዙ ጠጥቶ ወደ ቤቱ መንገዱን ቀጠለ ።

«እህ ከዚያስ ተከተልከው ?»

«አዎን ተከተልኩት እንጂ ጌታዬ ፣ አንድ ከመንገድ ወጣ ካለ መጠጥ ቤት ገባ ብሎ ሁለት ሰዎች አጅበውት ተመለሱ ። ሲኞር ፌራሪ ለጥቂት ጊዜ ሰዎቹን ሲያናግራ


t.me/OLDBOOKSPDF

ቹው ደስ ያለው ይመስላል ። ምን እንደተባባሉ ባይሰማኝም ሁለቱ ሰዎች ለሲኞር ፌራሪ በፍልሚያው ላይ ሊቆሙለት የተስማሙና ወዲያውኑ ወደዚህ ሆቴል ለመምጣት የወሰኑ ይመስላል ። ባሉትም መሠረት እዚህ ሆቴል ደርሰዋል ። ምክንያቱም አሁን ስገባ በጨረፍታ የጦር አለቃውን ሲያነጋግሩ አይቻቸዋለሁ ።

«ሲኞር ፌራሪ ከሁለት ጓደኞቹ ከተለየ በኋላ ወዴት ደረሰ?»

«ወደስቱዲዮው ቀጥታ አሻቀበ ። ሁኔታውን ስከታተል እንደዘጠና ዓመት ሽማግሌ አንገቱን ወደመሬት ደፍቶ ነበር የሚሄደው ። አንድ ጊዜ ቆም ብሎ ቡጢ ጨብጦ አንድ ነገር ላይ እንደመፎከር እጁን ወደሰማይ ሰበቀና ወዲያው እቤቱ ጥልቅ አለ ። መሪር ለቅሶ ግን ርቄ እስክሄድ ይሰማኝ ነበር ።»

«ይኸው ነው መጨረሻው? ቪንቼንዞ ?»
«ይኸው ነው ጌታዬ ።»

ልቤ ርህራሔ በሌለው ውሳኔ ረግቶ ተቀመጠ ። ፀጥ ብዬ ጥቂት ከተቀመጥኩ በኋላ «ቪንቼንዞ ፣ የሠራኸው ሁሉ አርክቶኛል ። ይኸ ወጣት እንዴት እንደሰደበኝና እንዳዋረደኝ አይተሀል ፣ በደሉ ሊታጠብ የሚችለው በአንድ መንገድ ብቻ ነው ። ስለዚህ እነዚያን ያዘጋጀሀቸውን ሽጉጦች አውጣ ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

በሙሉ ፈቃደኝነት ሽጉጦቹን ከተቀመጡበት አውጥቶ አዘጋጀ ።

«ግን ዛሬ የገና በዓል መሆኑን ጌታዬ ያስታውሳሉን»

«አዎን አውቃለሁ» አልኩት ስሜቴ እንደቀዘቀዘ ።

ፎአሁን ስመጣ በዚሁ ሆቴል ሁለት ለግድያ የሚፈላለጉ ወንድማማቾች በአንድነት እየጠጡ ቢንቼንዞ ፍላማ ዕለቱ የክርስቶስ ልደት ስለሆነ በመሀከላችን ያለው ጥላቻ ሁሉ እንደሰም ቀልጧል አሉኝ ።»

«እና የሁለቱ ወንድማማቾች ጉዳይ ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለው?» አልኩት ።

ሠራተኛዬ አየት አደረገኝና ፊቴ ላይ ምንም የርህራሔ ስሜት ያለመኖሩን ሲገነዘብ ብቻ ጌታዬን መላእክት ከጉዳት ሁሉ ይጠብቆት» አለኝ ።

ትካዜ በተሞላበት ፈገግታ «አመሰግናለሁ ወዳጄ» አልኩት ። «የምትለኝ ይገባኛል ። ግን ፍርሀት አይደርብህ ስለኔ ። እስቲ አሁን ጥቂት ልተኛ ። አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን ትኩስ ቡና አምጣልኝ። እስከዚያ ግን አንተም እረፍ።

ወዲያው መኝታ ክፍሌ ገብቼ እንደለበስኩ አልጋዬ ላይ ጋደም አልኩ ። እንቅልፍ እንዲወስደኝ አልሞከርኩም ። አእምሮዬ በልዩ ልዩ ጉድ ተጭኖአል ። የጉዶም ሀዘን ተሰማኝ ፣ በአሁኑ ወቅት እርሱ የሚልማው እኔን



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደተሰማኝ ትገዝ አለኝ ። ሞቶ አልተቀበረም ፣ ከመቃብሩ ለመውጣት ሳጥኑን አልሰበረም እንጂ ሴላውን የኔን መከራ ተቀብሎአል ። ስለዚህ ከዚህ መከራው የሚገላግለው ሞት ብቻ ነው ። ተኩሴ ይስተው እንደሁ ለማየት እጇን አው ጥቼ ለኢላማ በጨብጥ ይንቀጠቀጥ እንደሁ ስሞክረው እንደድንጋይ ድርቅ ብሎ እጇ ለማለም ይችላል ። ልቡ ላይ አልተኩስም ። ከልቡ በላይ መትቼው ከመሞቱ በፊት ማንነቴን እንዲያስታውስ ማድረግ አለብኝ ። የመጨረ ሻው የእባብ መርዜ ይኸ መሆን አለበት ። ጨክና እንድ ጨክን ያደረገኝ እርሱው ስለሆነ ፣ መሳልሶ በሴንጢው ወግቶ ያቆሰለኝ እርሱው ስለሆነ ፣ የምወዳትን ልጇን በጥ ላቻ ዓይን ያያት ስለሆነ በስሜ ላይ ያላገጠ ስለሆነ ፣ አእ ምሮዬ ውስጥ እየተደበቀ ብልጭ የሚለው ርህራሄ ቦታ ሊኖረው አይገባም ። አብረን ያሳለፍናቸው የልጅነት ጊዜ ዎችም ቢሆኑ በእርሱ ልብ ሙት ሆነው እንዳስጨከኑት ሁሉ በኔም ልብ ቦታ ሊኖራቸው አይገባም ። በዚህ የመ አት ሀሳብ መሀል ጥፍጥ ያላት እንቅልፍ ወሰደኝ ።

የፍልሚያው ሰዓት ሲደርስ ቪንቼንዞ ጢሱ የሚቡለ ቀለቅ ትኩስ ቡና አመጣልኝና ተነሳሁ ። ልብሴን እየለበ ስኩ አንድ ነገር አሰብኩ ።

ፍልሚያው ቦታ የሚገኙት ዳኞቹም ሆኑ ሀኪሙ ፋቢዮ ሮማኒን ሆኜ የሚያውቁኝ ስላልሆኑ ለመምታት ዞር ስል ለጉዶ ያሀል መነፅሬን ለማውለቅ መቻሌን አሰ ብኩ ። ምንም እንኳን የጸጉሬ ንጣትና ሪዜ የፊት ገጼን

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢለዋውጡትም ዓይኗ ብዙ ያውቀኝ ለነበር ሰው በትክክል
ማንነቴን ስለሚናገር ጥቁር መነጽሬን ማውለቁን መረጥኩ።
ልብሴን ለብሼ ሳልጨርስ ቪንቼንዞ ካፖርቴን ይዞ ገብቶ
የጦር መኮንኑ መምጣቱንና ከሆቴሉ ጓሮ ሰረገላ እየጠበ
ቀኝ መሆኑን ነገረኝ ።

ሽጉጦቹ የተቀመጡበት ሳጥን ተይዞ ወጣሁ ። የጦር
መኮንኑን ታማኝ ሠራተኛዬ ቪንቼንዞ አብሮኝ መቆም ስለ
ሚፈልግ አብሮን ቢሄድ የሚታመን መሆኑን አስረድቼ
ፍልሚያው ቦታ ጉዞ ጀመርን ። ከጦር መኮንኑ ጋር እስከ
አሁን ስለተደረጉት የፈሪና የደፋር ተፋላሚዎች ፍልሚያ
እየተነጋገርን ብዙ ተጓዝን ። ከተማውን ወደታች ጥለን
በኔው በጌታ ሮማኒ ግቢ ማለፍ ጀመርን ። ፍልሚያው
ቦታ ልንደርስ ስንል የምወደውን ሰው ለመግደል መወሰኔ
አንቀጠቀጠኝ ። መድረስ አይቀርምና ቦታው ደርሰን ስን
ወርድ ሀኪሙ ቀድሞን ደርሶ አገኘነው ። ፈረንሳይ ይሁን
ጣሊያን ባለየለት ቋንቋ ሰላምታ ሰጠን ። ከዚያ ወዲያው
በተፋላሚዎቹ መካከል የሚኖረው ርቀት ሀያ ሜትር
እንዲሆን ተወስኖ ተለካ ።

ዝግጅቱ በሚደረግበት አፍታ ቀስ ብዬ የፀሐይ መነ
ፅሬን አውልቄ ኪሴ ከተትኩና ባርኔጣዬን ወደግንባሬ
ደፋ አደረግሁ ። አሁን ጸሐይዋ በደንብ አልወጣችም እንጂ
ነግቷል። የቀስቃሽ ወፎች ዝማሬ በደንብ ይሰማል ። ብርዱ
ሳይሆን የመግደል እርግጠኛነቱ ሆዴ ገብቶ ያንጠረጥረ
ኝል ። የርህራሔ ነገር ለቅንጣት በሰውነቴ የለም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዶ እንደደከመው ፊቱ ላይ ይነበባል ። ካፖርቱን አውልቆ ሲወረውር ገና የሌሊት ልብሱን እንደለበሰ ነው ። ሽጉጡን ሲያስጨብጡት እንደልጅ ተቀበላቸው ። በቀል እንደተጠማ ሰው ሽጉጡን አገላብጦ ቃኘ ።

የጦር አለቃው ወደኔ መጥቶ አየና «ከእድሜዎ ጋር የማይመጣጠን ልጅነት ሰውነትዎ ላይ ይታያል» አለኝ ።

ወዲያው የቁርጥዋ ሰዓት መጣችና ጀርባ ለጀርባ ቆመን ሽጉጦቻችን መጉረሳቸው ተረጋገጠ ። የጦር መኮንኑ ፤ «ተዘጋጅታችኋል» ብሎ ጮኸ ።

«ዝግጁ» ብለን መለስን ።

ፊት ለፊት ፤ ዓይን ለዓይን ተገጣጥመን ቆምን ። ፈራራ ዓይኔን ሲያይ «በስመአብ» ብሎ ጮኸ ፤ ከንፈሩ ተንቀጠቀጠ ።

ቆጣሪው «አንድ» አለ ።

ሽጉጣችንን አነሳን ።
«ሁለት»

ማለም ስንጀምር ጉዶ እጁ በኃይል ተንቀጠቀጠ ። እኔ ግን በኩራት አለምኩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሶስት» ተኮስን ። የፌራሪ ጥይት ታካኝ እያፋጨች ሳትነካኝ አለፈች ። የጥይቱ ጪስ ገለል ሲል ፌራሪ ተዘርሮአል ። ሀኪሙ ወደርሱ ሮጠ ። ደረቱ ደም አፈታ ።

ቆጣሪው «ጥሩ ምት ነው» ብሎ አስተያየት ሰነዘረ ። «ጥሩ ምት ነው ። በአሥር ደቂቃ ውስጥ ይሞታል» ። ፌራሪ ራሱን ሲያውቅ ቀና ብሎ ሁላችንንም አየን ። ሀኪሙ አረቄ አስጉንጩውና የአፍታ ጉልበት አግኝቶ ራሱን ቀና አደረገ ።

በእጁ እየጠራኝ «ልናገር ፥ ብቻውን ላናግረው» አለ ። ሌሎቹ ገለል ሲሉ ፥

«ስለ እግዚር ብለህ አንተሰው ማነህ?»

«መቼ አጣኸኝ ፥ ልብህ እየነገረህ ፥ የድሮ ጓደኛህ ፋቢዮ ሮማኒ ፥ የበደልከኝ ሚሽቴን የቀማኸኝ ፥ የሰደብከኝ ፥ ያዋረድከኝ ጓደኛህ ነኝ ።»

«ፋቢዮ? ፋቢዮ?» ብሎ ጮኸ« እርሱማ ሳጥን ገብቶ ሲቀበር አይቻለሁ» አለ ። በጣም ተጠግቼ« ነፍሴ ሳይወጣ ነው ተገንዝቤ መቃብር ቤት የገባሁት ። አምልጬ ወጣሁ ። ቤቴ ብሄድ ስታላግጥብኝ ሚሽቴን ስታማግጥ ደረስኩብህ ። ምልክቶች ልንገርህ እንዴ ፥ ከግቢው በስተጀርባ ብቻዬን ከምናፈስበት አጸድ ውስጥ በሞትኩ ማግስት ከእርስዋ ጋር ስትዳራ አየሁህ ።

«ለመሆኑ እርሷ...... አውቃለች?»

«ገና አላወቀችም ፥ በቅርብ እንድታውቀኝ አደርጋለሁ ፥ ከሠርጋችን በኋላ አሳውቃታለሁ ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

አንጀቴ ተላወሰ ። እንደሴት እንባዬ አነቀኝ ። የልጅነት ደጉ ጊዜ መጥቶ አናወዘኝ ።

«አበቃ! ተፈጸመ!» እንደሕጻን እየተኮላተፈ ደጋገመ «ፋብዮ...... ይቅር በለኝ......»

እንደአውሬ አጓራ ። ዓይኑ እንደሳት ወደእኔ እየተንቀለቀለ መሬቱን በእጁ ይደበድብ ጀመር ። በሀዘን እጁን ይዤ አጽናናሁት ።

«አበቃ እንግዲህ ፤ ኀሊናህን አትቅጣ ። በቀሌን የደገስኩት ለዚህ ነው ። ሁለታችንንም ጉድ ያደረገችን እርስዋ ናት ። አንተን እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ ።»

«ሁሉም አለፈ አልከኝ? ፋቢዮ ይቅርታ አደረክልኝ፤ እንደመለበቅ እንደመፈራገጥ አለውና ሞተ ። እጁ በእጄ ውስጥ ወዲያው ትኩሳቱንና ንዝረቱን አጣ ። የቤተሰቤን አልማዝ ቀለበት አውልቄ እጁን እንደጥንት ፍቅራችን ስሜ እጄን አጣምሬ ቆሜ በሀዘን አየሁት ። ቆጣሪው ፊቴን አይቶ ሀዘን ገባው ።

«ጌታዬ ፊትዎ የዓመት ሀዘን የደረሰበት ይመስላል ። አሁን በቀጥታ ሄደው እረፍት ያድርጉ፤ለጥቂት ሳምንታት እንዲያውም ይህን ከተማ ጥለው ወደውጭ እረፍት ቢያደርጉ ይሻላል ። ወደገጠር ቢሄዱ ሁሉን ነገር ረስተው ለጥቂት ቀናት የሚነፍሰውም ወሬው ተረስቶ አዲስ ሆነው ይመለሳሉ» አለኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራሶስት

ከፍልሚያው መልስ ብቻዬን ቪላ ሮማኒ መታጠፊያ
አለፍ ብዬ ከሰረገላው ወረድኩና ፣ ቪንቼንዞ ሆቴል እንደደ
ረሰ የራሴን ሰረገላ የሮማኒ ግቢ በራፍ ድረስ እንዲልክልኝ ፣
ያንዕለቱን ወደ አቬሊኖ ስለምንጓዝ እርሱ ሻንጣዬን እንዲ
ያደራጅ አዘዝኩት ። ጸጥታ በነገሰበት ተራራማዋ አቬሊኖ
ጭንቀቴን ሁሉ በጥቂት ቀናት እረፍት ለመወጣት እንደ
ምችል እርግጠኛ ነበርኩ ። ጉዞዬንም ከያንዕለት ማምሻ
ላለማሳለፍ በመፈለጌ የሰጠሁት ትእዛዝ ድርቅ ያለ ስለነበር
ቪንቼንዞ አንገቱን እንደመድፋት።አድርጎ ፤

«ከጌታዬ ጋር እኔም ለመጓዝ እችላለሁ?»አለኝ ።
የግዴታ ፈገግታ ባንዴ አሳይቶኝ ፤

«ለምን? አስፈላጊ አይደለም ። ሁኔታዬን አታይም
እንዴ ? ልቤ በሀዘን ከብዳለች ወንድ ልጅ ሲያዝን ብቻውን
ነው መተከዝ ያለበት ። ከዚህ ሌላ ደግሞ የካርኒቫል በዓል
ስለደረሰ አንተ እንዳቀድከው መደሰት ስለሚያስፈልግህ
ካለብህ ግዴታ ሁሉ ነጻ መሆን ይገባሃል ። ለኔ አታስብ
ቪንቼንዞ ፣ እዚህ ቀርተህ ጊዜህን በደስታ አሳልፍ» አል
ኩት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

እንደለመደው በትሕትና እሺ አለኝ ። ፊቱ ላይ ግን እምቢታ በግልጽ ይነበባል ።

«ጌታዬ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ እፈልጋለሁ ። ዛሬ ያየሁት ሞት ለካርኒቫል በዓል የነበረኝን የጋለ ስሜት ገሎታል ። ጌታዬም በሀዘን ልብዎ የተሰበረ ስለሆነ ልለዮት አልፈልግም» አለኝ ።

ሁኔታው የሚመለስ ስላልሆነ ሀሳቡን መቀበል ግድ ሆነብኝ ። «እንደአሳብህ እንግዲህ» አልኩት ። «የሁለታችንንም የጉዞ ሻንጣ አዘጋጅ ። ነገሩን ለማንም እንዳትነግር ። ሰረገላዬን ግን ሮማኒ ግቢ በራፍ ስለምጠብቅ አሁኑኑ ላክልኝ» ብዬ ቪንቼንዞ ነጂው ጐን ተቀምጦ ሰረገላው ከዓይኔ ሲሰወር እኔ ጌታ አልባ ፣ ክብር አልባ ወደሆነው ቤቴ ማዝገም ጀመርኩ ። ግቢው ጭጭ እርጭ ብሎአል ። ሕይወት ለመሀላ ዝር የማይልበት ሆኖአል ። እመቤቲቱ በጊቢው ባለመኖርዋ መስኮቶቹ በሙሉ ተዘግተዋል ። እቤቱ ውስጥ እሬሳ የተኛም ይመስላል ። ለመሆኑ ማነው የሞተው? የሚል ጥያቄ መጣብኝ ። የሞትኩት እኔው ነኝ ፣ ባልሞት ያን የልጅነት ጓደኛዬን እገድላለሁ? እርስዋ ግን ሁለታችንንም ገድላ ፣ በሕይወት ትኖራለች።ይህ ስሀተት ነው ፣ አሁን ደግሞ እርስዋ መሞት አለባት ። የዚህ ሁሉ ሞት ምክንያት የሆነች ነፍስዋ በገሀነም እሳት መንጫረር ፣ መኮማተር አለበት ። የሞት ሞት መሞት አለባት ። አሁን ግን ብቻዬን ቆሜ የእርስዋን ሞት አላቀናብርም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጓደኛዬም በእርስዋ ስህተት ስለተቀሰፈ ቅጣትዋን ከእኔ ጐን ቆሞ ያስፈጽማል ።

እየተዘዋወርኩ የግቢዩን ናፍቆት ተወጣሁ ። የምወደውን ቦታ ሁሉ ረገጥኩ ። ባጠገቤ የሆነ ጥላ ውልብ ሲል ዞር አልኩ ። የሞት ማህተም አፉን የዘጋው ሰው መሬቱ ላይ ተዘርግቶ ከተመታው ልቡ በላይ ደሙ ሲያፈታ አየሁ ። ትርኢቱ ዘግንኖኝ ከጭንቀቱ ለመገላገል ስሞክር ሁሉም ነገር ለካ አእምሮዬ የሚፈጥረው እንጂ በአካል አልነበረም። ጉዱን በእንዲህ ሁኔታ በሕልሜም ሆነ በውኔ አየው ይሆን የሚል የስጋት ሀሳብ አናወዘኝ ።

ወዲያው ደግሞ በተፈጥሮ ግርማ ሞገስ ቅርንጫፎቻቸውን በሰፊው ያንዠረገጉት ዛፎች ቅጠሎቻቸው እየታመሱ ፀጥታውን ገለል አደረጉልኝ ። ደወል የደስታ ደወል እየሩን በጥኡመ ዜማው የሚያስፈነድቅ በአራቱም የንፋስ አቅጣጫ ተናኘ ።

ሰላም ለሰው ልጆች ሁሉ በምድር ! ሰላም ለሰው ልጆች ሁሉ በምድር ! የሚል ድምጽ ከገደል ገደል አስተጋባ ። ሰላም ለኔ ቦታ የለውም ። እኔ ከሰው ልጆች ሁሉ የተነጠልኩ ፍቅር ወንድማማችነት ለኔ ትርጉም የላቸውም በዚህ የማያቋርጥ የሀሳብ ማዕበል ውስጥ እንዳለሁ ሰረገላዬ ጐዳናውን እያተረማመሰ ሲመጣ ሰማሁና ተጠጋሁት ። ወዲያው ተሳፍሬ የሰረገላውን ነጂ ወደ አኦንዚዮ ገዳም አፍጥኖ እንዲያደርሰኝ ነግሬው መንገዝ ጀመርን ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ለሁለት ሰዓት በሰረገላዬ ተጉዤ ከዓለም ሁሉ ተለይቶ ብቻውን ከቆመው ግዳም ስደርስ ደወሉን ደወልኩና ጥቂት ከጠበቅሁ በኋላ በሩ ተከፈተልኝ ። ማንነቴን አስረድቼ እን ድገባ ከተፈቀደልኝ በኋላ አንዲት መነኩሲት ከፊት ለፊቴ እየሄዱ ሚሽቴ ወዳለችበት ክፍል አመራን ። እለቱ የክርስቶስ ልደት በመሆኑ ባለቤቴ ከመነኳኳስቱ ጋር ቅዳሴ ገብታለች ተባልኩና መነኩሲቷን እየተከተልኩ ስለሚሽቴ መጠያየቅ ጀመርኩ ።

«እመቤት ኒና የእናንተ ተማሪ ነበረች ፤ በተለይ እር ስዎ ከሁሉም የተመረጠች አድርገው የሚመለከትዋት ነበረች ብዬ እገምታለሁ ፡ ለመሆኑ አያያዝዋ እንዴት ነበር ?» ብዬ ጀመርኩ ።

«ከሁሉ አብልጬ የምወዳት ተማሪ የለችኝም ። እዚህ የሚማሩትን ተማሪዎች ሁሉ በእኩል ዓይን ነው የማያቸው» አሉኝ ።

«አጥብቄ በመጠየቄ ይቅርታ እለምናለሁ ፤ ሆኖም የወደፊት ባልዋ ስለሆንኩ እባክዎ ስለጠባዩዋ ዘርዝረው ቢነግሩኝ ። »

መነኩሲቷ በመንፈሳዊ ዐይናቸው ከእግር እስከራሴ ቃኝተውኝ በጭንቀት ተነፈሱና ፤

«ኒና ሮማኒ የዓለም ሴት ናት ፤ የዓለምን መንገድ ብቻ መከተል ትወዳለች ። ጌታ ሮማኒን ስታገባ በጣም አዋቂና



t.me/OLDBOOKSPDF

ምስጉን ሰው ስላገባች ሕይወትዋን ይለውጥላታል ብለን ደስ ብሎን ነበር ። እርሱም ሞተ ፤ ነፍሱ በሰላም ትረፍ ። ሁለተኛ ባል ግን ታገባለች ብዬ አልጠበቅሁም ነበር ። ብቻ የጊርስዋን ሁለተኛ ባል ማግባት ጎሲናዩ አይደግፈጡም ። በግልጽ አስተያየቴ ይቅርታ ።»

መነኩሲቷን ካመሰገንኩ በኋላ «ሁለተኛ ባል ለኔና በጣም አስፈላጊዋ ነው ። ምንም የሚያስከብራት ሰው የላትም ፤ በዚህ ላይ ቆንጆ ናት ፡ ወጣት ናት ።»

«እንዲህ ያለው ቁንጅና እርግማን ነው ። ብርቱ እርግማን ነው ። ይቅርታ ፡ አስተያየቴ የተገራ አለመሆኑን አውቃለሁ ። ሕመሜ ግልጽነት ነው ። ቢሆንም ለሁለታችሁም መልካም ምኞት እመኝላችኋለሁ ። »

መነኩሲቷ አንድ የቤተ መጽሐፍ ክፍል አስገብተውኝ «እዚህ ትመጣልሀለች ፤» ካሉኝ በኋላ ትኩር ብለው ተመልከተውኝ ያመመህ ወይም የደከመህ ትመስላለህ ። ወይን ጠጅ ልላክልህ » አሉኝ ።

«ደህና ነኝ» ብዬ ምዬ ተገዝቼ ግብዣውን አስቀረሁ ።

«ስለኒና ቸኩዬ አስተያየት በመስጠቴ አዝናለሁ ፤ ይቅርታ» ብለው ዝም አሉ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«ከልብ የወጣ ግልጽ አስተያየት የሚጎዳ ነገር የለ ውም ። ሕይወታችንን የሚጎዳው ከአንጀት ያልሆኑ አስተ ያየቶች መንገዱን ሲያዛቡት ነው» አልኳቸው ። ትተውኝ ሄዱ ። ጥቂት እንደጠበቅሁ ከቅዳሴ ቤቱ ሰው ወጥቶ መሄድ ሲጀምር ያለሁበት ክፍል በር ተከፍቶ ሚሽቴ ኒና ብቅ አለች ።

በተለመደው የሴትነት ግርማዋ ቀረብ ብላ «መምጣ ትህን ስሰማ እንዴት መሰለህ ደስ ያለኝ» አለችኝ ። በሁኔታዬ መቅዝቀዝ ተደናግጣ !

«ምንችግር ተፈጠረ?» ብላ በቷዳከመ ድምጽ ጠየቀ ችኝ ።

«ቁጭ በይ ፤ ጥሩ ዜና ይዤ አልመጣሁም» አልኳት ። ተቀመጠች ። በፍርሀት ተንቀጠቀጠች ። የፊት ቀለምዋ ሁሉ ተለዋወጠ ። ለመናገር አፍዋን አርጥባ «ምንድነው መጥፎው ዜና ፤ ጉዱን ምን አገኘው ፤ አየኸው እንዴ አንተ?»

«አየሁት ፤ ትቼው መጣሁ ። ይህን ቀለበት ልኮል ሻል ።» ብዬ የአልማዙን ቀለበት ሰጠኋት ።

ቁንጅናዋ ሁሉ በአንድ አፍታ ጠወለገ ፤ ፈዘዘች ደነዘዘች ። ቀለበቱን ከተቀበለች በኋላ ሁሉን ነገር ያወ ቅሁ መስሏት ድንጋጤዋ አስታወቀባት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ይህን የሰጠሁት ጓደኛውን እንዲያስታውስ ነበር ፣ ለምንድነው የሚመልስልኝ? አይገባኝም» ብላ እንባዋ ዐይንዋን ሞላ ። «ግን ለምን እንዲህ ቀዘቀዝክ አንተ ፣ ምን ነካህ? ሳመኝ የሆነውንም ንገረኝ ሳለመሳም ወሰንኩ ።

«ገባኝ ፡ አትወደኝም ። የሚያፈቅር ሰው ድንጋይ ሆኖ አይቆምም ። እኔ እኮ ብርቱውን ችግር ታቀለዋለህ እል ነበር ። አንተ ግን መናገርም አትችል ።»

«አንቺን ከሚያስቸግር ጉዶን ለኔ ተይው እኔ ፀጥ አደርግልሻለሁ ብዬሽ አልነበር? በቃሌ መሠረት ፀጥ አደረግሁት ።»

ደነገጠች «ጸጥ ! እንዴት ነው ጸጥ? ሞተ ነው የምት ለኝ ። ሞተ? አይደረግም! እና አንተው ገደልከው?»

በሀዘን ራሴን ደፍቼ «አዎን ገደልኩት ። በግልጽ ፍልሚያ በምስክር ፊት ተጋጥመን ገደልኩት ። አጥንት የሚነካ ስድብ ስለሰደበኝ ዛሬ ጠዋት ተጋጥመን ገደልኩት። ነፍሱ ከመውጣቷዋ አስቀድሞ ግን ይቅር ለእግዚአብሔር ተባባልን ።»

«እንዴት ብሎ ሰደበህ?»
አስረዳኋት ። ደምዋ በመጠኑ ተመለሰ ።
«ከመሞቱ በፊት ስሜን ጠራ?»

«ከጠቡ በፊት ምንም አላል።ሌሊቱን ግን ሊገድልሽ ገቢያችሁ መጥቶ ነበር ። ቢያጣሽ ረግሞሽ ወጣ ። »የእፎ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይታ ትንፋሽ ዋጠች ። ከእንግዲህ ሰላም ያለ መስሎአት ከንፈርዋን አረጠበች ፤ ተደላድላም ተቀመጠች ።

«ለምን ይረግመኛል? እኔ ለርሱ ደግ ሆኘ ነው የኖርኩት ፤ ከፉ ሆኘበት አላውቅም»

«ግን ምነው አላዘንሽለትም ?»

«ለምንድነው የማዝንለት ። ባሌ ከመሞቱ በፊት ጥሩ ሰው ነበር ። ከሞተ በኋላ ግን ሁኔታውን ሁሉ የማልችለው ሆነ»

ዘለህ እነቃት እነቃት የሚል ሰይጣን ከጀርባዬ ገፋፋኝ ። እንደምንም አብርጄ ሸሸት ብዬ ቆምኩ ።

«እንግዲያውስ ተሳስቻለሁ ። እኔ በጣም የምታዝኝ መስሎኝ ነበር ።»

ዘላ በእጆችዋ ትከሻዬን ይዛ «አንተ ጉብዝ ጀግና ነህ ሰደበህ ቀጣኸው ፤ ክብርህን በጀግንነት አስመለስክ ። ለዚህም አፈቅርሀለሁ» ። ከጉዶ ጣት አውልቂ አምጥቼ የሰጠኋትን የአልማዝ ቀለበት አንስታ «ይህ ቀለበት የፋቢዮ አባት ቀለበት ነበር ። በኋላም የፋቢዮ ሆነ ። ለጉዶ የሰጠሁት ጓደኛውን እንዲያስታውስበት ነበር ። መልሶ ከላከው ለኔ ብለህ እባክህ አንተ አድርገው ብላ ጣቴ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ሻጠችው ። የራሴን ቀለበት መልሼ አጠለቅሁትና ሳቄ መጥቶ ጉንበስ ብዬ አሳለፍኩት ።

«ለመሆኑ እስከመቼ ነው በዚህ ገዳም ተደብቀሽ የም ትቆይው? ከእንግዲህ ኔፕልስ ከመመለስ የሚያዳግትሽ አንድም ነገር እኮ የለም ።»

«ኃላፊዋን የጠየቅኋቸው ለአንድ ሳምንት እድሜ ነው ጊዜው እስኪያልቅ መጠበቅ አለብኝ ። ከዚህም በላይ ልቆይ አልችልም ። የጉዶም ሞት ፈጥኖ ከተማ እንድገባ ያስገድደኛል» ።

«ለምን እንደሚያስገድድሽ መጠየቅ እችላለሁ?»

«በኑዛዜው መሠረት ሀብቱን ፈጥኖ መረካከብ አለ ብኝ ። ሮም ከመሄዱ በፊት የጠቅላላ ሀብቱ ወራሽ አድር ጎኝ ፈርሞ ኑዛዜውን በወረቀት ሰጥቶኛል ።»

«ይህን ወረቀት ማየት እችላለሁ?»

«እየው ፣ እንዲያውም እዚህ ይገኛውዋለሁ ።» ወረቀቱን ከአርሳዋ ለማወጣት ሄደች ። ይህችን ምንም ዓይነት ፍቅር ሊሰጣት የማይገባትን መናኛ ሴት ልክ እንደ ኔው ጓደኛዬ አፍቅሮ ሀብቱን አውርሶአት ይሆናል ። ወረ ቀቱን አውጥታ አንቦልኩን ከፍታ ሰጠችኝ ። ሕጋዊ የው ርስ ኑዛዜ ነው ። በሙሉ ፈርማው ፣ እማኞችና የድርጅት


t.me/OLDBOOKSPDF

ማኅተም በደንብ አለበት ። «ያለኝን ሀብት ንብረት በሙሉ» ብሎ ያረጋግጣል ።

«መቼም ይኸ ሰው ከአንጀቱ ሳያፈቅርሽ አልቀረም?»

በረጅሙ ተነፈሰች ። «በእርግጥ ይመስለኛል ። ግን ብዙ ሰዎች ናቸው የሚያፈቅሩኝ ። አዲስ ነገር አይደለም ለኔ ። መፈቀርን ለምጄዋለሁ ።»

ሰዓቴን እየት አደረግሁ ። «ካንቺ ጋር ስሆን አላው ቅም ሰዓቱ ክንፍ አውጥቶ ይበራል ። አሁን መሄድ አለ ብኝ ። ብስጭቴንና ያየሁትን አሰቃቂ ትርኢት ሁሉ አቬ ሊኖ ሄጄ መርሳት አለብኝ ።»

«አቬሊኖ?» ብላ ብዙ ካወጣችና ካወረደች በኋላ ፣ «ይገባሀል ሂድ ። ሬሳ ማየት በጣም ያሰቅቃል ። ግን አትቆይ ። ሳጣህ ጭንቅ ይለኛል ።»

«አይዞሽ ። መለያየት ፍቅር ያደረጃል ይባላል ። ለኛም ይሠራ ይሆናል ። ደህና ሁኚልኝ ፣ ጸልይልኝ» ብዬ አቅፌ ራስዋን ደባበስኳት ። ለጉዶ ፌራሪም ጸልይለት ። አፍቅሮሽ ባንቺ ምክንያት እኔን ባለውለታውንና ጓደኛ ውን አስቀይሞኝ ሞተ ። ለባልሽም ጸልይ ። ምናልባት የሁለቱ ጓደኛሞች መንፈስ ሙታን ተገናኝተው እንዳይወ ቅሱሽ ለሁለቱም ጸልይ ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

ሀ

እጅ እግርዋ በፍርሀት ቀዘቀዘ ። መልስ ለመተንፈስ ብዙ ታግላ «እሺ እጸልይላቸዋለሁ» አለች ።

ነገሩን በማንሳቴ ደስ አለኝ ። የስጋ ሞትዋ ቀላል ነው ። እኔ የኅሊና ሞትዋን ነው የፈለግሁት ። ለመጸለይ ባሰበች ቁጥር ነፍስዋ ሱባኤ ይገባና ጥፋተኛ መሆንዋን ትረዳለች ። የእጅ ጓንቲዬን አጥልቄ ፡ ካፖርቱን ደርቤ ለመሄድ ተዘጋጀሁ ።

ድንገት የፊትዋ ቀለም ልውጥውጥ አለ። «መሄድህ ነው በቃ?» አለችኝ ።

«አዎን ምነው ፊትሽ ለወጥ አለብኝ ፍቅሬ?»
«እስቲ እጅህን ልየው» ድምጽዋ ሻከረብኝ ።
ጓንቲውን ውልቅልቅ አድርጌ አሳየኋት ።

የአልማዙን ቀለበት ያጠለቅሁበትን እጄን አገላብጣ ስታይ ሰውነትዋ በሙሉ እንደመንቀጥቀጥ አለ ።

«ምን ዓይነት ትንግርት ነው! አሁን ደግሞ ምን ስሜት አደረብሽ?» አልኳት ። በቀልድ መንፈስ ።

«እጅህ ከዚህ ቀለበት ጋር ይገርማል ልክ የፋቢዮን እጅ ቁርጥ ነው ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

ምንም ነገር ለመተንፈስ በማልችልበት ቅጽበት ምርር ብላ እንደህጻን አለቀሰች ። ወዲያው ራስዋን ዘንግታ እጄ ላይ ተዝለፈለፈችብኝና ሰዎች እንዲረዱኝ የመጥሪያ ደወሉን ስደውል መነኳከስቱ መጡልኝ። ተሯሩጠው ውሀ አምጥተው አጠጡዋት ። ጠበል አምጥተው ቀባብዋትና ነቃች ። በረጅሙ ከተነፈሰች በኋላ ፣

«አሁን ሻል አለሽ?» አልኳት ።
«አዎን ተሽሎኛል» አለች ።

ከመነኳኩስቱ አንደኛዋ በአዛኝ ዓይነት ወደእኔ ዞር ብለው «ለመሆኑ በአንድ ጊዜ እንዲህ ያደረጋት ምንድነው» ብለው ጠየቁኝ ።

«ምኑን አውቄ እነግሮታለሁ እማሆይ ። የአንድ ወዳጅዋን ድንገተኛ ሞት አርድቻት ነበር ፡ እመቤቲቱ ይኸን እንኳን ችላው ነበር ። ጤንነትዋን በአንድ ጊዜ ከቁጥጥርዋ ውጭ ያደረገው እርስዋ እንደምትለው የኔና የሞተው ባለቤትዋ እጅ መመሳሰል ነው ። ይኸ ለኔ እንደተአምር የሚቆጠር ትንግርት ነው ።...... ብቻ የሴትን ተለዋዋጭ ስሜት መገመት እኮ አይቻልም ። ለሁሉም ይቅርታ አድርጊልኝ ። በጣም አዝናለሁ ፥ የባልሽን አይነት እጅ እግዜር ስለሰጠኝ አዝናለሁ ።»

«ክፍሌ ልሂድና ልረፍ ። ደህና ሁን ሲዛር ከአቬሲኖ ጻፍልኝ ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

እጅ ነስቼ የዘረጋችውን እጅዋን ስሜ ተለያየን ። በር ከደረሰች በኋላ ዘላ መጥታ ተጠመጠመችብኝና በናፍቆት ዓይነት ሳመችኝ ። ጤናዋን ሊመልሱ የመጡት መነኳኩሴት እኛ ስንሳሳም ዓይተው ጉንጮቻቸው ቀሉ ። ከንፈሮቻቸው በጸሎት ዓይነት ተንቀጠቀጡ ።

እጅዋን አወዛውዛ ስትወጣ ሁኔታዋ ግራ አጋባኝ ። በጋለ ስጋዊ ፍላጐት የሳመችኝ መነኩሲቷ ሊያገኙት የማይችሉትን ነገር አሳይቶ ስሜታቸውን ለመፈታተን መ ሆኑ ከነከነኝ ።

እርስዋ በሩን ዘግታ ከሄደች በኋላ ለምድር ለሰማዩ የከበዱት መነኩሲት ዐይናቸው እኔ ላይ እንደመሰቀል እለና እንባ አቀረረ ። ከድንጋጤዬ የተነሳ የምናገረውን አጥቼ «እማሆይ እኔ መቼም......»

«ምንም ነገር መናገር አያስፈልጐትም ጌታዬ፣ አስፈላጊ አይደለም ። አልማውያን ቤቶች በሀይማኖት የታሰርነውን መፈታተናቸው የተለመደ ነው ። ግን ጭካኔ ነው ። እንደ እመቤት ሮማኒ ያሉት እኛ የክርስቶስን ግማደ መስቀል በደ ረታችን የተሸከምነው የማይገባን አድርገው ይገምቱናል ።» መነኩሲትዋ በስሜት ግለው ደረታቸውን እየደበደቡ «እኔ እኔ እራሴ እንኳ» ካሉ በኋላ ላለመናገር ወዲያው በረድ አሉ መሰለኝ፣«የገዳማችን ደንብ ማንኛውም ጐብኚ ከአንድ ሰዓት በላይ እንዳይቆይ ነው፣ከገቡ አንድ ሰዓት ስላለፈዎት በሩን የምታሳይዎ ሰው ትላክልዎታለች ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

«እሰኞቹ አንዳንዴ የምትሠራውን አታውቅም፤ በኔ ፍቅር ምክንያት ከኔ ጋር በፈታችሁ ባሳየችው ድንገተኛ ትኩስ ስሜት በጣም አዝኛለሁ ።»

«በርስዎ ፍቅር ምክንያት ብቻ ነው ብለው እንዴት ያስባሉ ጌታ? ነገሩማ ይመስላል፣ ብቻ የእርስዎን አስተያየት እንዳላሳስት እፈራለሁ ።»

ጥቂት አመንትተው ዝም ካሉ በኋላ ደግሞ «ቀጥተኛ ሰው ይመስሉኛል እርስዎ ። ምናልባት ኒናን ከጥፋት የሚያድኑ ይሆኑ ይሆናል ። ዝምታን የሚያህል የለም እንጂ ብዙ ልነግሮት እችላለሁ ። የሚያፈቅርዋት ከሆነ አያሞካሽዋት ። በባዶ ጭንቅላት መኮፈስ ነው የእርስዋ መጥፎ ። ወዲያ ወዲህ የማያወላልት ብልህ አመራር፣ምናልባት ማን ያውቃል ? ይገዛት ይሆናል ። እንደመጠራጠር ብለው «ደህና ይሁኑ ጌታ» ብለውኝ ሲወጡ እጅ ነስቼ ተሰናበትኋቸው ።

ጥቂት እንደቆምኩ አንዲት በእድሜ አንጋፋ የሆኑ መነኩሲት ከግቢው መርተው ሊሸኙኝ መጡ ። በክፍልና ክፍል መሀል መነኩሴዋን ተከትዬ ስወጣ ከአንድ ገርበብ ብሎ ከተዘጋ ክፍል ሁለት ወጣት መልከመልካም ሴቶች አሾልከው ሲመለከቱኝ አየሁ ። መነኩሲቷ በንዴት በሩን ባይዘጉት ልጃገረዶቹ ስለኔ የሚሰጡትን አስተያየት በትክክል መስማት እችል ነበር ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ማዝ ጥያቄ ነው ። እና እኛ ወንዶች ራሳችን እስኪመለጥ ፣ ጸጉራችን እስኪነጣ ሰርተን ለፍተን ጀርባችን እስኪጐብጥ ግረን የመኖርና የመደሰት ፍላጐት ከውስጣችን ተሟጦ እስኪጠነፈፍ ደክመን የመጨረሻው ወሮታችን ምንድነው ታዲያ? ደስታ? አልፎ አልፎ ነው ፡ ለባል አለመታመን ፣ ዘወትር የሴቶች መቀለጃ መሆን? መቀለጃ በመሆን መታለፍ ብቻም ከሆነ እድል ነው ። አጠራጣሪነቱ ሳይታለም የተፈታ ነው ። ሀቁ መደለል በራስ ቤት ሁለተኛ ዜጋ መሆን ነው ። እርግጠኛ ነኝ በዚህ ገጽ ይህን ጽሑፍ የምታነቢ ሴት ፣ ይህ ሊሆን አይችልም አይደረግም ትዩ ይሆናል ። እኔ ግን እውነቱን ልንገርሽ አንቺ የጥቂቶቹ ጥቂት ስለሆንሽ የአክብሮት ሰላምታዬ ይድረስሽ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራአራት

አቬሊኖ ጸጥታ የሰፈነባት የሕልም ስዕል የመሰለች የውበት ረሀብተኛ ቱሪስቶች ያልወረረዋት ትንሽ መንደር ናት ። ከጥንታዊ ቤተክርስቲያኑ በስተቀር የሚታይም ነገር የላትም ። የአቬሊኖ ውበትዋ ተፈጥሮአዊ መልኳ ላይ ነው ። እዚህ የተፈጥሮ ጥላ ከለላ ከነገሰባት ተራራማ ወረዳ ኮረብታውን እያደነቅሁ በረጅም መተንፈስ ጀመርኩ ። ከበቀል ሥራዬ ፋታ አግኝቼ ጫንቃዬን የሰበረኝን ሸክሜን ለጥቂት ጊዜ አሳርፌ ለአንድ ሰሞን ሰው ሆንኩ ። ዙሪያዬን የከበበው ተራ ነገር ነው ። የበቀል ፍትወት ባቃጠለው ስሜቴ ላይ ግን እንደቅቤ የሚያርስ ተሀድሶ ሰጠኝ ። አቬሊኖ የተፈጥሮ ውበት እንጂ ሆቴል የላትም ። ስለዚህ ቪንቼንዞን ይገፍ አንዲት ቤት ቤት ክፍል ተከራይቼ ገባሁ ። በኔፕልስ ያሳለፍኩት ኧመንኧ ሕይወት ስልችቶኝ ተራ ኑሮ መኖር ደሀ ሰው መሆን ጣመኝ ። ሶስት ቀን ሙሉ ከራሴ ጋር እየተወያየሁ ሰውን ሳላናግር ውዬ አደርኩ ። ቪንቼንዞ የሚያስፈልገኝን ሁሉ እያዘጋጀ በጥንቃቄ ከብስጭቴ አስታመመኝ ። እያደር የመንፈስ ሰላም ከጸጥታዬም ትርጉም አገኘሁ ። የተጠለልኩበትን ጎስቋላ ቤት እያየሁ ተፈጥሮን ብቻ እንዳጤን አደረገኝ ። እልፍ እልፍ ድህነት የሚያስገኘውን ሰላም ለመጀመሪያ ጊዜ ተገነዘብኩ ። የተ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠጋኳት ሴት ድሀ ናት ። ፍራፍሬ ለቅማ ሸጣ የምትረዳት ሴት ልጅ አለቻት ።

አንድ ቀን ቪንቼንዞ ምሳ አብልቶኝ ገበታውን ሲያነሳሳ ፊቴን አይቶ ስሜቱን መዝኖ ፤«ጌታዬ ሊላ ምንቲን አይታዋታል?» ብሎ ጠየቀኝ ።

አስደነቀኝና ትኩር ብዬ አየሁት ። ድህነት ልጅነቱን አገርጅፎታል እንጂ ገና ጐረምሳ ወጣት ነው ።

«የማነች ሊላ ምንቲ?»
«የባለቤትዋ ልጅ»
«እኔ አላየኋትም ። ምነው ጠየቅኸኝ?»

ግንባሩ ፈካ አለ ። ዓይኖቹ የብርሀን ጸዳል አፈለቁ ። «ይቅርታ ያድርጉልኝ ጌታዬ ። ሊላ ውብ ልጅ ናት። በሀገራችን አንድ አነጋገር አለ ። ልቡ እንደ ድንጋይ ቢከብድ የሴትን ልጅ ውብ ፊት ሲያይ ሀዘኑ የማይከፈልለት የለም ።»

እጁን በመሰልቸት አወናጨፍኩና «ቪንቼንዞ፣ውበት የዓለም እርግማን ነው ። ታሪክን አንብ፣ታላላቅ ድል አድራጊዎችና ብልሆች እጃቸው ታስሮ ወደ ውድቀት ያመሩት በውበት ወጥመድ እየታያዙ ነው ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

«ቢሆንም ጽጌረዳ ስትፈነዳ ማየት ደስ የማይለው የለም ። የሌት ከዋክብት ሲፈኩ ዐይኑን ከፍቶ ማየትን የሚጠላ የለም ። ሊላ ሞንቴንም ማየት ደስታ ነው ።»

ልቤ በሀዘን ቢቆስልም ከት ብዬ በሁኔታው ሳቅሁ ። «ፍቅር ያዘህ መሰለኝ ቪንቼንዞ ፤ እንዲሁ በቀላሉ አጣድፎ ያዘህን ፡ በሶስት ቀን? ታሳዝነኛለህ ።»

«ጌታዬ ተሳስተዋል» ብሎ አቋረጠኝ ። እርስዋ ከዚህ ሁሉ የነጻች ናት ። አፈቅርሻለሁ ብዬ ለመናገር ድፍረት ያንሰኛል ። ገና ጉጆዋን እንደተወች ለጋ የወፍ ጫጩት ናት ። የፍቅር ቃል ሊያስፈራራት ይችላል ።»

እውነትም መሳሳቴ ገባኝ ። የራሴ የፍቅር ታሪክ ጉልዳፋ ስለሆነ የሌላውንም ማስደንገጥ የለብኝም ። የኔ እጅ የፍቅር አመድ አፋሽ ቢሆን የሌላውን እድላም መዳፍ ማስደንበር የለብኝም ። ስለዚህ ስሜቱ እንዳስደሰተኝ ሰው ሆኜ ቀረብኩ ። ከልቤ መልካም እድል ተመኘሁለት ።

«ጌታዬ እኔስ መጀመሪያ ለእርስዎ ነበር ያየኋት ። ነጭ ጸጉር አበቀሉ እንጂ እርስዎም ገና ጉረምሳ ነዎት ። ይህንንም ያረጋገጥኩት የፍልሚያው ዕለት ዓይኖን አይቼ ነው ፤ ገና ጉብዝ ነዎት ።»

መንፅሬን አውልቄ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩ ። «ከአቪሊኖ እስክወጣ ዐይኔን ማየት ትችላለህ ። ይህን


t.me/OLDBOOKSPDF

መነጻር የማደርገው ለተለየ ጉዳይ ነው ። አቬሲኖ እስካለሁ ድረስ መነፅሩ አስፈላጊነት የለውም ። መቸም እስከአሁን እንድተማመንብህ አድርገኸኛል ። እና ይህን ታማኝነት ትህን ደግሞ እንዳታጓድልብኝ ተጠንቀቅ ።»

ይህን ስለው ወዲያው ትክዝ ብሎ ጐኑን የወጉት ያህል ፊቱ በልቡ ምሬት ተጐሳቆለ ። ብድግ ብዬ ትከሻውን በእጄ ዳስሼ ፤

«አሁን ተሳስቻለሁ ፤ ይቅርታህን አንተ ታማኝ ሰው ነህ ። ሀገርህን በጀግንነት ለማገልገል ግዴታህን የተወጣህ ነህ ። እኔን ግን ገና ልጅነህ ስትል ተሳስተሀል ። እኔ ልጅነት ጠፍቶብኛል ። ትልቅ ሀዘን ልጅነቴን በልቤ ውስጥ እንዳለ ገድሎብኛል ። የጡንቻ መፈርጠም ፤ የዓይን ትኩረት ፤ ውጫዊ ኃይሎች ናቸው ። እድሜን የሚጥለው የልብና የነፍስ ስቃይ ብዛት ነው ። ስለዚህ እኔ የቀኑ መርዘም የሚሰለቸኝ ሽማግሌ ሰው ነኝ ። ግን ላስፈራራህ አልፈልግም ሊላ የፍቅርህ እጣ ክፍልህ ስለሆነች ከማፍቀር አትቦዝን» አልኩት ። ሰሞኑን ሁሉ እንደጥንቱ ነጻነቴ ያለመነፅር ዳገት ቁልቁለቱን ማየቱ ደስታ ሰጠኝ ።

የምኖርባት ቤት ጐስቆል ብላ የተሠራች ደሳሳ መኖቢያ ብትሆንም አስፈላጊውን ሰላም ስለሰጠችኝ ተስማምታኛለች ። የቤትዋ ባለቤት ደግሞ ራሱን የቻለ ሊነገር የሚገባው ታሪክ ስላላት ኩሩ ናት ። ባልዋ በአንድ የእብነ በረድ ካባ ይሠራ ነበር ። የገዛ ጓደኛው ድንጋይ ሆን ብሎ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥሎበት ተጨናፍልቆ ሞተ ። ይህ ከተፈጸመ በኋላ የባልዋ ገዳይ እጅዋን ሊጋብቻ ጠየቃትና በነፍስ ገዳይነት ከሰሰ ችው ። አፉን ለእብለት ሲያሞጠሙጥ በጥፊ መታ እርግ ማንዋን እስኪሞት ድረስ እስታቀፈችው ። ታሪክዋን ስታ ወጋኝ ቤትዋ ፊት ለፊት ያለማችው የፖም ሁዳድ ይታየ ኛል ። ኑሮዋን በዚህ ፍሬ ላይ መስርታ ከሴት ልጅዋ ጋር ትኖራለች ። ወተት የመሰሉ ጥርሶችዋን ገለጥ እያደረገች እንደ እስሊ ሮማውያን እጆችዋን እያወናጨፈች ፤ «ቤቴን ለ ማንም ተራ ሰው አልከፍትም ። ለበቁ የኪነት ሰዎች ፤ ባለ ቅኔዎችና የመሳሰሉ እረፍት የሚፈልጉ የእእምሮ ሰዎች ብቻ ቤቴ ያርፋሉ ። ይህን የማደርገው ለኑራት ሳይሆን የልጃገ ገረድ እናት በመሆኔ ነው ።»

«እና ሴት ልጅ አለችሽ?»

«አንዲት ሊላ አለችኝ ። በረከቴ እሳታለሁ ። እለኝ ታዬ ናት ። በእርስዋ ብርታት ነው እነኝህ የፖም ዛፎች በመንደረኛው የማይመረቱ ፍሬዎችን የሚያፈሩት ። ፍሬውን ገበያ ይዛ ስትቀመጥ ደግሞ የፊትዋ ፈገግታ ራሱ ገብያውን የሚፈጥር ይመስለኛል ።» ይህን ነግራኝ ብዙ ቀን ሳንተያይ ሰነበትን ።

አንድ ቀን ሊላን አየኋት ። ከተቀመጥንበት ቤት በላይ ባለው ጉብታ ቅርንጫፎቻቸውን በሰፊው እንጣለው ከዘ ረጉት ዋርካዎች ስር እየተናፈስኩ ቦታው የሚሰጠ ውን ደስታ እያደነቅሁ ስዝናና አንዲት ሴት ልጅ በእጠ


t.me/OLDBOOKSPDF

ገቤ ውልብ አለች ። የሚያስጎመዥ የክረምት ፍሬ በቅ ርጫት አንግባለች ። ሰላምን የማይተነኩስ ዐይን የሚማርክ አረማመድዋ ሳበኝና በዐይኔ እከተላት ጀመር ። ልብስዋ የገበሬ ልጅ ልብስ ነው ። አጠር ያለ ሰማያዊ ጉርድ ላይ ጠቆር ያለ ወፍራም ሸሚዝ ለብሳ ከበላዩ ፈገግ ያለ የአንገት መሀረብ ጣል አድርጋበታለች ። ረጅም ፀጉርዋ እንደሀር ነዶ በአጭሩ ተጎንጉኗል ።

ጀርባዋን ብቻ ስላየሁ ፊትዋን ማየት አለብኝ የሚል ፍላጎት አደረብኝ ። ወዲያው ከፊት ለፊቴ መምጣት ጀመ ረች ። እንቡጥ ገጽዋ ከፊት ለፊቴ መጣብኝ ። ያን ሰበር ያለ ዐይንዋን ሳይ ከልብ በመነጨ አክብሮት አንገቴን ለሰላምታ ዝቅ እንዳደርግ ያደረገኝን ስሜት አላውቅም ። ምን እንደሁ በፍጹም አላውቅም ። በውበትዋም አይደለም ፣ ምክንያቱም ከእርስዋ ይበልጥ የተዋቡ አይቻለሁ ። ብቻ በቃል ሊገለጽ የማይቻል ልዩና ውድ ምክንያት አለው ።

ለሰላምታዬ አጸፋውን ስትመልስ ጉንጮችዋ በመ ጠኑ ቀሉ ። ጥቂት ካመነታች በኋላ አንገትዋን በዓይናፋር ነት ደፋ አድርጋ «ጌቶች ጥቂት ኮረብታውን ወጣ ቢሉ ተራሮቹን ከዚህ በበለጠ በሰፊው ማየት ይችላሉ» አለችኝ።

የፊትዋ ገጽ የእናትዋን ስለያዘ ሳያት የማውቃት መሰለኝ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ፈገግ ብዬ «እሀ ሊላ ምንቲ ነሽ?» አልኳት ። እንደገና አፈር ብላ «አዎን ሊላ ነኝ ጌቶች» አለች ። ሀዘን በተቀላቀለበት አትኩሮት ተመለከትኳት ፡

ቪንቼንዞ እንዳለው ውብ ልጅ ናት። ትህትና የከበበው ሙሆ የማያሳጣ ድብቅ ውበች አላት ። የዘማዊት ሴት ውበት ሳይሆን ተፈጥሮ የሚሰጠውን ትኩስነትና የሚያስከብር ሰብአዊ ውበት አላት ። ከተማ ካየኋቸው ብዙ ውብ ሴቶች ሁሉ ያችን የገጠር ቆንጆ የሚስተካከል አሰቤ ላገኝ አልቻልኩም ። አስተያየቴ አላስደነገጣትም ። ብቻ እንዳል ተለመደ ትርኢት ቆም ብላ አየችኝና «የት ነው የምትሄ ጂው?» ብዬ ጠየቅኋት ።

«እናቴ ራት እንድ ናዘጋጅሎት ለሥራ ትጠብቀኛለች።»
«እንደዚህ እጅሽ እስኪሻክር ብዙ ትሰሪያለሽ እንዴ?»

«እረ እንዲያውም ልሠራ የሚገባኝን ያህል አልሠራም። ሥራን አፈቅራለሁ ። ትክሣታችንን የሚያስተካክልልን ሥራ ነው ። እጅ ተጣጥፎ ሲቀመጥ ነው ሰው የሚኮረፈው። ሐመሙም የሚያጠቃው ሥራ ፈቱን ነው ። እውነት መሆኑን ደግሞ አረጋግጫለሁ።የኛ ጐረቤት ጴጥሮስ ጥቅልል ብሎ የሚያቃስተው የሚጠግነው ጫማ ሲያጣ ነው ። ገንዘብ አጥቶ አይደለም ፤ ግን እጁ ሥራ ሲፈታ ቁስ ጠርታ ችሁ ኑዛዜዬን ላፍስ ይላል ። አንድ ቀን እናቴ ታዲያ አሮጌ ጫማችንን ሰብስባ ብትወስድለት አልጋ ውስጥ ተቀምጦ ሲጠግን ዋለ ። አሁን እንደርሱ ጤነኛ ሰው የለም ። እረ


t.me/OLDBOOKSPDF

ልሂድ ። የመልካም ሴት ምልክትዋ ሥራ መውደድዋ ነው ትላለች እናቴ ።»

«ቪንቼንዞ ቡና ማፍላት እንኳን አይረዳሽም እንዴ?»

ስሙ ድንገት በመጠራቱ ጉንጭዋ ላመል እንደማፈር አለ ። ዐይንዋን ሰበር አድርጋ ፤

«ጉበዝ ሠራተኛ ነው።ቪንቼንዞ እኔ ያፈላሁትን ቡና መጠጣት በጣም ይወዳል ። ሁልጊዜ አንቺው ብቻ አፍሊ ይለኛል።እርስዎ ግን የቪንቼንዞን ቡና ይወዱ ይሆናል ።»

ነገሬ ስላልገባት ሳቂ መጣ ። የዋህነትዋ ፡ በተወሰኑት የዕለት ተዕለት ተግባሮችዋ ብቻ መወሰንዋና የሕጻንነት ሁኔታዋ አስገረመኝ ።

«የለም እኔ በነኝህ እጆችሽ የምትሠሪያቸውን ሁሉ እወዳለሁ። ቪንቼንዞን ግን እንዲህ ካንቀባረርሽውና የሚጠጣውን ቡና ሁሉ ካፈላሽለት ሊኩራራ ይችላል ።»

ደንገጥ አለች ። ነገሩ አልገባትም ቪቼንዞ ለእስዋ እንደማንኛውም ከእርስዋ ያልተለየ ጥሩ ሰው አድርጋ ነው የምታየው።የጾታው ልዩነት ጨርሶ አልተከሰተላትም።ለእርሱ የምታደርገው መስተንግዶም ለሴት ጓደኞችዋ ከምታደርገው ባልተለየ ሁኔታ እንደሚሆን ገመትኩ ። የእንጋገሬን ሚስጢር አስብ ያደረገች መሰለችና መልሳ ተወት አደረገችው ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«እንግዲህ የአሥር ደቂቃ መንገድ ወጣ ቢሉ ጌቶች ቅድም ያልኳዎትን ተራራ ያያሉ ። ተራራው ሲያብብ ቅዱስ መልአክ እዚያ ላይ ቆሞ ነው አሉ ሀገሩን የሚመር ቀው ። ስለዚህ ውብ ነው ይመልከቱት ።»

አበቦች ውበታቸውን ለከበባቸው ንፋስ መደበቅ እን ደማይችሉ ዓይነት ፈገግ ብላ በትህትና ትታኝ ሂደች ። እንደመሮጥም እንደመደነስም እያለች ቁልቁለቱን በልጅ እግርዋ ተንደረደረች ። ስትሮጥ ትዘምራለች የፍስህ ልሳንዋን ከፍታ እየሩን እልል ታሰኛለች ። እንደመኸር ወፍ ደስታ የሚፈነጥቀው ድምጽዋ እቆምኩበት ድረስ እየ መጣ ከዐይኔ ርቃ እስክትሄድ አተኩሬ እንዳያት አደረገኝ ። ጥላ በበረደው የቀትር ኋላ የፀሐይ ብርሀን የጸጉርዋን ጉንጉን እንደወርቅ እያፍለቀለቀው በሥራ የቀነበረው ሰውነትዋ የውበት ግርማ ለብሶ ከዐይኔ ተሰወረች ።

እንዲህ ያለችዋን እኔ አግኝቼ ሳላጭ በመቅረቴ በእ ድሌ አዘንኩ ። ያኔ ነጻ በነበርኩበት ጊዜ ባያት እንኳ ጥቅ ምዋን ልረዳ መቻሌን እጠራጠራለሁ ። እኛ የገንዘብ ድሎት ያለን ወንዶች የገጠር ሴት ጥቅምና ውበት ሊገባን አይች ልም ። የተማሩ የተመራመሩትን በዓለም ጥበብ የረከሱትን ወይዛዝርት ነው እኛ የምናጨው ።

ተራራው እናት ያለሀሳብ ተደላድዬ እንደተቀመጥኩ ግምኛውን ተቀብዬ እኪሴ ያስቀመጥኩት አንድ የፖስታ ጥቅል ትዝ አለኝ ። ማክስ የተባለው ፍልሚያውን ያስተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ናበረው ወዳጄ ነው እንድ የራሱን ደብዳቤ ጨምሮ የላክልኝ ። ማክስ በደብዳቤው ፈራሪ ሀይማኖታዊ የቀብር ተግባር ሁሉ ሳይጓደልበት መቀበሩን መቃብሩም የፋቢዮ ሮማኒ የሲጋ ወንድምም ባይሆን ባለው የቀረበ ጓደኝነት በሮማኒ ቤተሰብ መቃብር ቤት አቅራቢያ መሆኑን ከደብዳቤው ተረዳሁ ። የእርሱን ደብዳቤ አስቀምጬ የፖስታው ጥቅል የታሰረበትን ሲባጐ በጥሼ ወረቀቶቹን ገለጥለጥ ሳደርግ አጥንቴ ድረስ የሚያንገሸግሸኝ የሽቶ ጠረን ሸተተኝ ። አገላብጬ ሳይ ከጉዶ ኪስ የተገኙ የኗና ደብዳቤዎች ናቸው ። አንድ በአንድ ደብዳቤዎቹን ሁሉ በየተራ አነበብኩ ። ጉዶ ሮም በነበረበት ጊዜ በፍቅር ሞቅታ የኗዋ ጉድ የጻፈችለት ነው ። የተጻፈበትን ቀን ሳገናዝብ አንደኛው ሚሽቴ እኔን አዲሱ ባልዋ ለመሆን ፈቃድዋን የገለጸችልኝ ቀን ፣ ሌላኛው የፍቅር ሚስጢር የተለዋወጥንበት ዕለት ሆኖ አግኘሁት ። ደብዳቤዎቹ በሙሉ በጋለ የፍቅር ስሜት ጋልበው የሚያስጋልቡ በመጨረሻው ጣፋጭ ቃላት ስሜትን እያነሳሱ የሚገንዙ ፣ ዓላማቸው ጉዶ ከተጠመደበት የፍቅር ሕልም እንዳይነቃ አስረው የሚገንዙ ናቸው ።

ከነኝህ በቃላት ውበት ታሽተው ከተጻፉት መስመሮች መሀል «ለምንድነው ይህን ያህል ደጋግመህ ስለጋብቻ የምትጽፍልኝ ጉዶ ፍቅሬ ? ዓለም ድብቅ ፍቅራችንን ገና ሲረዳ መነፋፈቃችን ሁሉ እንደጢስ በኖ የሚጠፋ ይመስለኛል ። አንተ ገና ባሌ መሆንክን ስታውቀው በእርግጥ ፍቅረኛዬ መሆንክን ታቆማለህ ። ይኸ ደግሞ ያሳዝነኛል ። ስለዚህ ፍቅሬን የምጠይቅህ የሁልጊዜ ፍቅረኛዬ እንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ትሆን ነው ። ልክ ፋብዮ በነበረ ጊዜ እንደሆንከው አሁ
ንም ተራ የሆነውን የጋብቻ ሀሳብ ጥለህ ተወዳዳሪ የሌ
ለው ፍቅረኛዬ ሁን ።»

ቃላቱን ሳጤናቸው ሀሳብዋን በትክክል ተረዳሁት ። ከሞተው ሰው ጋር የነበራትን ግንኙነት እየቀጠለች እኔን ደግሞ ለማግባት ነው ሀሳብዋ ። የረቀቀው የእቅድዋ መንገድ ይህ ነበር ። መቸም ግሩም ደብዳቤ ጸሐፊ ናት ። ልክ ለሞተው ውሽማዋ ትልክ የነበረውን ዓይነት በቃላት የተንቆጠቆጡ ደብዳቤዎችን ለኔ ደግሞ እቬሊኖ ድረስ ትል ክልኛለች ። አሁን ያለችው ኔፕልስ ግቢዋ ነው ። የመ መለሻ ቀኔን በናፍቆት እየጠበቀች ናት ። ቋዘኛ ሌባ አይ ደለችም ። የሌባ ዐይነደረቅ ናት ። ሌቦችን ፣ ወንጀለኞችን ግን የሚከታተል ሕግ ነው ። ሕጉ እንዲህ ያለችዋን ሴት ፍታት ይላል ። ፍታት! ይህን የሚመርጡና የሚከ ተሉ ይፍቱ ። እኔ ግን ፍትህን የማይበት ሌላ መንገድ አለኝ ።

ደብዳቤዎቹን አጣጥፌ ታስረው በመጡበት ሲባጐ አብ ቼ ኪሴ ስመልስ የላከልኝን የወዳጄን የማከስን ምክር አስታ ወስኩ።«ዐይንህ እያየ ገደል ውስጥ ራስህን ከመወርወር በፊ ት አስተውል» ይላል።«ጠላት ያዘጋጀው ገደል ከሩቁ ገደልነ ቱ ከታወቀ ቀስ ብሎ እንዳላወቀ አይቶ ተጠግቶ ጠላትን ገደል መክተት ይበጃል» የሚለው ልቤ ገባ ።

ተነስቼ ተራራውን ዝግ እያልኩ ወረድኩ ። እንደፍ ራሽ የሚትምከምከውን ሳር እየተረገጥኩ ያረፍኩበትን


t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት መንገድ ይገዬ አቆልቆልኩ ። በአትክልት ተንቆጣ ቁጣ ያማረችውን የሲኞራ ሞንቴን ቤት እንደተጠጋሁ የወንድና ሴት ደስተኛ ድምጽ ፣ ሳቅና ጭብጨባ ሰማሁ ። ድምፅ የመጣበትን አቅጣጫ አቆልቁዬ ሳይ ቪንቼንዞ የሸ ሚዙን እጀታ ጠቅሎ ግንዲላ እያገላበጠ በመጥረቢያ ሲተ ረከክ አየሁና ቆም ብዬ እመለከት ጀመር ። ሲላ አጠገቡ ቆማ በልበል እያለች እያጨበጨበች ታበረታታዋለች ። ልክስክስ ሥራ የለመደ የከተማ ሰው ሲሠራው በማይችለው ደረጃ ቪንቼንዞ እንጨቱን እያወራረደ ሲበታትነው እኔ ራሴ ተደንቄ አየሁት ። በዚህ እፍታ አንድ ሀሳብ ብልጭ አለ ልኝ ። እነኝህ ሁለት የፍቅር ተክሎች በደንብ እንዲያብቡ ቢደረግ ቪንቼንዞ ከጌታው በላይ ደስተኛ ሰው ሊሆን ይች ላል ። የዛቢያ አያያዙ የገጠር ኑሮን መቅመሱን ይጠቁማል። አሁንም ቢሆን ይህን ተራራማ ፣ ሳር ቅጠል የሞላበት የፍራፍሬ ሀገር ልቡ ወዶአል ። በየሙሽሩ በአበባ ሽታ ታድሶ በየዛፉ በሚንጠለጠለው ብስል ቀይ ፍሬ ከሲላ ጋር ሆኖ ቢያመርት የጊዜ ወረት የማይሽረው ደስታ ይሸም ታል ። ከዚህስ በላይ ምን ምኞት አለ ። ሰውነትን በጤን ነት አእምሮን በሰላም ለመጠበቅ ከዚህ ዓይነት ኑሮ ወዲያ እርግጠኛ ነገር ምን ይገኛል ። ለዚህ ደስታው ተፈጻሚ ነት እኔ የምረዳው ነገር የለም? ብዬ ራሴን ጠየቅሁ ። ይህን ብፈጽም አእምሮዬ ከጭንቀቱ በመጠኑ ይገላገላል ። በተለይም ጉዶን ከገደልኩ ወዲህ ከደሙ ጋር አዳዲስ ልብ አብጋኝ ብስጭቶችን አምጥቶብኛል ። መንታ ጫፍ ያለው ጅራፍ አእምሮዬን ይወነጭፈኛል ። አንድ ደግ ነገር ብሠራ ታዲያ ይህን እንደ ክረምት ሌሊት የጨለመ


t.me/OLDBOOKSPDF

የቆጣ ማዕበል መንፈሴን የሚያፈካ የንጋት ኮከብ አላገኝ ይሆን? ልክ ይኸን ሳስብ ሊላ ተንከትክታ ሳቀች ። የታዳጊ ልጅ የሳቅ ድምጽ ምን ያህል ደስ ይላል ። አሁን ምን የሚያስደስት ነገር አገኘች ። አየት ሳደርግ መጥረቢያውን ከእጁ ተቀብላ እንደርሱው አድርጋ ለመፍለጥ በዚያች ትንሽ እጅዋ መጥረቢያውን እያነሳች ስትፍጨረጨር እርሱ ደግሞ በተራው ዳርቆሞ በኩራት እያየ ይስቃል ። በመጨረሻው እንጨት ፈለጣ እንደማይሆንላት አይታ ሽርጥዋን እያረጋገፈች የእናትዋ ጥሪ ወደቤት ብር ብላ እንድትገባ አደረጋት ። ወደርሱ ስጠጋ በሙሉ ጉልበቱ ያገላብጥ የነበረውን ፈለጣ ተወት አድርጎ አፈር ብሎ አየኝ ።

«ይህን ዓይነት ሥራ ትወዳለህ ለካ ቪንቼንዞ?»

«የጥንት ትዝታ ነው ። ወታደር ከመሆኔ በፊት ገጠር ከእናቴ ጋር ሕይወት ትጥመኝ ነበር ። »

«ምን አለ ታዲያ አሁንም ገጠር ደስ ካለህ ማን ይከለክለሀል ።

«ከጌታዬ መለየት አልፈልግም ፡»

«ሊላ ምንቲን ብታገባ የግድ ትለየኛለህ» ስለው ፊቱ በደስታ ጥርት ብሎ ራሱን ግን በአሉታ ነቀነቀ ።

«አትሰማኝም ፡ በጣም ልጅ ናት አይሆንም ።»

«አሁን ታድጋለች ። ጥቂት ወራት አብረሀት ስት



t.me/OLDBOOKSPDF

ክርም ሁሉን ታውቃለች ። ብዙ ጊዜ አለህ ። እንዳልከው ውብ ናት ። ከዚህ በላይ ግን ምንም የማታውቅ አዲስ ፍጡር ስለሆነች ዋናው ይኸ ነው ። በሴት ሕይወት ንጽህና ብርቅ ነገር ነው ። ንጽህና እንደአምላክ የሚከበር ቅድስና ነው።»

«ቢሆንም ስሜትዋን በአፈቅርሻለሁ ከማሳዘን ምንም ነገር ቢቀርብኝ ይሻላል» አለኝ ።

ይህ ፍቅር ስር ሰዶ እስኪለመልም ከእቅዴ በላይ አቬሊኖ ለመሰንበት ወሰንኩ ። ቪንቼንዞ በትህትና ስላገለገለኝ ሽልማት ልሰጠው ወሰንኩ ። ጥረቴ በዋዛ አልቀረም ። እያደር ልጅቱ ቪንቼንዞን ታፍረው ጀመር ።

አንድ ቀን ሲኞራ ምንቲን ከፍሌ ጠራሁ ። ደንግጣ አገልግሎቷ ተጓድሎ እንደሁ ጠየቀችኝ ። ሁሉ ነገር ያስደሰተኝ መሆኑን ካረጋገጥኩ በኋላ ፤ «ጥያቄዬ ስለሴት ልጅሽ ሊላ ነው» አልኳት ። ዐይንዋ በእንባ ተጋረደ ።

«የሊላን ጋብቻ እንደሚያስፈራ ሞት ከአእምሮዬ ስከላከል ነው የኖርኩት ። ብቸኛ ስለሆንኩ እንድትለየኝ አልፈልግም» አለች ።

«ሳትለይሽ ብታገባስ ። ለምሳሌ ቪንቼንዞን?»

«ቪንቼንዞንስ እወደዋለሁ ። ጥሩ ልጅ ነው ። ታዲያ እርሱ ጌታውን ማገልገል ብቻ ነው ደስታው»

«ይኸን አውቃለሁ ። አንቺ ጥሩ እናት ስለሆንሽ ሁለቱንም ተመልከቻቸው ። ምናልባት ስሜትዋን ላለማሳዘን ብሎ ይሆናል ። ግን ምልክቱን ታገኝዋለሽ ። ይኸን


t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቅል ውስጂና ሊላን ጐጆ ለማውጫ ይረዳኛል ። አራት ሺ ፍራንክ ነው ። ሊላ የፈለገችውን ብታገባ ተጠቃሚ በት ። ቪንቼንዞ ግን ባልዋ እንደሚሆን አልጠራጠርም ። ገንዘብ ለኔ ምኔም አይደለም ፤ ለሁሉም ይሁን ጥሎሽ ልጅቱ እስክታገባ ሚስጢር አድርጊው ።»

ልከለክላት በማልችለው ቅጽበት የሊላ እናት እጄን ጐትታ ሳመችኝ ። በልጅዋ እድል ተደሰተች ። ደረትዋን በኩራት አቅንታ «አመሰግናለሁ ጌታዬ ። ስለሊላ ብዬ አመሰግናለሁ ። እጄ እስኪሞረድ ብጥር የልጄን እድል የሚያቀና ጥሪት ላቀያት አልቻልኩም ። አማልክት እርስ ዎን ልከው እድልዋን አቃኑልኝ ። ጌታዬ ይቅርታ ያድር ጉልኝ ። ዐይንዎን ሳይ መንፈሴ ፈጥኖ መከራና ሀዘን እንደ ደረሰበት ይነገረኛል ። በጐ ድርጊት ስቃይን ያቃልላል ። ደስታዎ እንዲመለስ እንጸልይሎታለን ። ሊላና እኔ ሆነን እስከመጨረሻዋ እስትንፋሳችን እንጸልይሎታለን ። ይመ ኑኝ ጌታዬ የሊጋሳችንን ስም ለቅዱሳን እንዲቀርብ ሌትና ቀን እንማጸናለን ። ማን ያውቃል ኤሎሂአችን ይሰማና ደህና ውጤት ይገኝ ይሆናል ።»

«በጐ ነገርስ መገኘቱ አይቀርም ። እኔ ግን ለጸሎታ ችሁ የምበቃ አይመስለኝም ። ይልቅስ ለሞቱት ጸልዩ፤ ከህጥያታቸው እንዲገላገሉ ጸልዩላቸው ።»

ደገኛዋ ሴት በሀዘን አይታኝ እንደገና ከንፈርዋን በጸሎት እያንቃነቀች ትታኝ ወጣች ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቪንቼንዞ ገባ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ፈገግ ብዬ ሰላምታ ሰጠሁትና «በላ ቪቼንዞ መለያየት ፍቅርን ስለሚፈትን ለጉዞአችን እቃችንን በሙሉ ጠቅል ። ተነገ ወዲያ ከአቬሊኖ እንነሳለን ።

ባሰብነው ቀንና ሰዓት ተነሣን ። ሊላ አንገትዋን በቅሬታ ደፋች ። ቪንቼንዞ ግን ሀሳቡ የተሰበሰበ ይመስላል ። የሊላ እናት አስተያየት ደግሞ ሁሉ ነገር ትክክል መሆኑን ይጠቁማል ። ያንን ተራራማ ወረዳና ሕዝብ ደግሜ የማላየው መሆኔን ስለማውቅ ልቤን ሀዘን ተሰማው ። የሊላን ጉንጭ ነካ አድርጌ ያቺን ቆንጆ ፊትዋን ለመጨረሻ ጊዜ አየሁ ። በሠራሁት ትንሽ ደግ ሥራ ግን ልቤ ተስፋ አለመለመ ። ኅሊናዬም የብቃት ደስታ ተጐናጸፈ ።

በአዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ወር መጨረሻ ኔፕልስ ስገባ የቅርብ ወዳጆቼ የጋለ አቀባበል አደረጉልኝ ። ፍልሚያውን ያካሄደው የጦር አለቃ ከዚህ በፊት እንደነገረኝ የፍልሚያው ወሬ በአንድ ሰሞን ተረስቶ ጠበቀኝ ። ከወር መለያየት በኋላ ኔፕልስ ለካርኒቫል ስትደገስ ደረስኩ ። የከተማይቱ ቀለምዋ ፤ ድምጿና ጠቅላላ መልኳ ሁሉ ለካርኒቫሉ ወይም ለዓመታዊው የእብደት አይነት ክብረበዓል ተዘጋጅቷል ። ሙዚቃው ይቀልጣል ይዘፈናል ይደነሳል ፤ እንዲያውም ሙሽራ የሌለው ሰርግና ምላሽ ሆኖአል ። እኔ ግን ከዚህ ርቄ የራሴን ለማሳካት የቅድሚያ ዝግጅቶችን ማቀናጀት ላይ አተኮርኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራአምስት

አሁን እንኘ‍ያን ከሰርጌ ቀን ቀደም ብለው ያለፉትን ትንግርተኛ ቀኖች ወደኋላ መለስ ብዬ ሳስተውል እንደ ሚሞት ሰው ሕልም ትዝታቸው ይጭበረበርብኛል ። በሚለዋወጡ ቀለማት እንዴ ብርሀን እንዴ ጭለማ እንዴ ደግሞ በድንቅ ሥራ የተዋቡ ቅንጅቶች ሺ ጊዜ ሺ ግዙፍና ረቂቅ ነገሮች ቋሚ ያልሆነ መጠናቸውን እየለዋወጡ ሕይወቴን አመሰቃቅለውታል፣ ትክክለኛና አስተማማኝ አእምሮ እንዳለኝ ባውቅም አንዳንዴ ማበዴ ይሆን እያልኩ በውል ያጠነጠንኩት የበቀል እቅዴ ሁሉ ተስፋ ይቆርጣል። የተቃወሰ አእምሮ ቅዠት ይሆን? ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ ። በተቃራኒው ግን የእያንዳንድዋ ቅምር ሂደት ፍጥነቱ እንኳ ያላሰለሰ ፣ ቅንጅቱ ያልተፋለሰ ቅንብር ያለ ሥራ ነበር የምሠራው ። እንደባንክ ሠራተኛ ሂሣብ የምሠራው ሁሉ በየደረጃው የተሳለና የተመዛዘነ ነበር ።

ከአቬሊኖ በተመለስኩ በሳምንቱ ከእመቤት ሮማኒ ጋር የመጋባት እቅዴ በይፋ ተሰማ ። ይህ ዜና በከተማው በይፋ በተወራ በሁለተኛው ቀን የፍልሚያው እለት ከቆ መልኝ ወዳጂ ከማክስ ጋር ትልቁ ጉዳና ተያየንና እርሱ ተጥረብርቦ በትህትና ሰላምታ ቢሰጠኝም እኔ እፍረቴን መደበቅ አቃተኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«እና ጋብቻችሁ በተሳካ ሁኔታ ያለቀለት ነገር ሆኖአላ?»

እንደምንም ፈገግ አልኩና «እንዴታ ትጠራጠራለህ እንዴ ? »

ጥርት ያለ ፊቱ በአንድ ጊዜ ዳመና አንጃበበበትና ሁኔታው እንደመረበሽ አለ ።

«የለም እኔ እንኳ ተቃራኒውን አስቤ ነበር ።»

«የምታስበው ምን ላይ እንደሆነ ይገባኛል ወዳጄ ። ነገር ግን እኛ የዓለም ወንዶች ምርጫችን የሚስተካከለው ሴት ልጅ ከጋብቻ ቀንዋ በፊት የፈጸመችውን የፍቅር ሥራዋን ሳያተኩሩ ከጋብቻው በኋላ እንዳታታልለን ብቻ መጠንቀቅ ላይ ነው ። የላክልኝ ደብዳቤዎች ምንም አይሉም ። እመቤት ሮማኒን በጋብቻ መያዝ ማለት ከአውሮፓ የመጨረሻዋን ቆንጆ መያዝ ነው ።» አሁንም እንደገና በማስመሰል ሳቅሁ ።

ማክስ ግራ የተጋባ ቢመስልም የተመሰቃቀሉ ነገሮችን ማስከን ስለሚያውቅበት ፤

«ይኸማ ከሆነ እሰየ ነው ። በሙሉ ልቤ መልካም እድል እመኛለሁ ። የራስዎን ደስታ መርጠው መዳኘት የሚችሉት ራስዎ ነዎት ። እኔ ለግሌ አሁንም ነጻ መሆን ለዘለዓለም ትኑር እላለሁ ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

ከማክስ አፎንኮርት ጋር በዚሁ ተሰነባብተን ተለያየን። ከእርሱ በስተቀር መጪውን ጋብቻዬን በጥርጣሬ የተጠያየቀ የለም ። እኔም ዝግጅቱን ተአምር እስኪባል አጣደፍኩት ። የሠርግ ዝግጅቱ ዓመታዊውን የካርኒቫል በዓል ለማሟሟቅ የቀረበ አድርገው የሚያወኑ ሁሉ ነበሩ ። በሠርጋችን ቶሎ ቶሎ የይድረስ ድረስ ምርጥ ድግስ ጥድፊያ ሚሽቱም ልክ ጉዶ ዕለተ ሞቱን ለማቅረብ እንደ ተቻኮለው እርስዋም ለማፋጠን ፈቃደኛ ነበረች ። ሠርጉ እንዲፋጠን የምትፈልግበትም ምክንያት ለሀብት ባላት የማይረካ ጥማት ነው ። ከተገናኘን ጊዜ አንስቶ ፡ ተዋውቀን ጌታ አሲቫ ብላ እስክታጨኝ ድረስ ዋናው ዓላማዋ ሀብቴን ለመያዝ ነው ።

የሠርጋችን ዜና በኔፕልስ ገና እንደተሰማ በሚሽቴ እድል እፋሽ አጉንባሽዋ ይቀኑባት ጀመር ። ይኸ ደግሞ ለእርስዋ እርካታን ሰጣት ። የእርስዋ አይነት ሴቶች ዓላማ ከእርስዋ በሀብት አነስ ያሉትን ሴቶች ማሳዘንና ማበሳጨት ነው ። ስለዚህ ኗና የምትወደው ደሀ ሴቶችን ማሲቃየት ነው ። በጥቃቅን የኪስ ገንዘብ ኀሊናቸውን ታቆስላለች ። የሚብረቀረቅ ሀር ቀሚስ የከበረ ከፋይ መጉናጸፊያ እውነተኛ የአልማዝ ፈርጥ የተጠለፈበት ልብስ ለባብሳ በሀገር በማይገኝ ሽቱ ታውዳ ለእለታዊ መታጠቢያ ሳሙና የሌላቸውን ምስኪን ልጃገረዶች እያስጐመጀች መፈጠርን ታስጠላቸዋለች ። ምስኪን ደሀ ሴቶች የሚያደርጉትን ቢያውቁ በእርስዋ ብልጭልጭ ልባቸውን ማሳረር አልነበረባቸውም። ሴቶች ሲባሉ የደስታን መጠን የሚለኩት በሚኖራቸው


t.me/OLDBOOKSPDF

ቀሚስ ልክ ነው ። በደረሰባት ድርብርብ ሀዘን ምክንያት ሆን ብለን ሠርጉን ሰው እንዳይበዛበት ከወሰን በኋላ ቦታው የተጋባንበት ካቴድራል እንዲሆን አደረግን ። ዱሮ ሳውቃት ዐይንአፋር ለመምሰል እንገትዋን ሰበር ታደርግ ነበር ። ሰሞኑን ባየኋት ቁጥር ዐይንዋ ተጕልጕሎ ፍጥጥ ብላ ስታ ተኩረኝ ዐይን ላይን ግጥም እንላለን ። ፋቢዮን ይመስላል በሚለው ሀሳብ ሰውነትዋ ሲገዘገዝ ማየቱ፡ ለኔ ደስታን ጨ መረልኝ እንጂ አልከፋኝም ።

ሮማኒ ጊቢ እንደልቤ ተመላለስኩበት ። ጥቁር መነ ጽሬን አድርጌ አንድም የሚጠረጥረኝ የለም ። ጂያኮሞ የተባለው አንጋፋው የአባቴን ሠራተኛ ጉዶ እንገላቶ ከጣ ለው ወዲህ የአሊጋ ቁራኛ ስለሆነ አተኩሮ የሚከታተለኝ የለም ። አሮጊትዋ ሞግዚት ጂያኮምን ታስታምመዋለች እንጂ ሚሽቴ ጨክናባታለች ። እንዲያውም ዘመዶቹ ከሎምባርዲያ መጥተው እንዲወስዱት ሚሽቴ ደብዳቤ ልካለች ብለው ነግረውኛል ። እኔው ራሴ «ክእንግ ዲህ እርሱን እዚህ ማስቀመጡ ምን ጥቅም አለው» ስ ትል በጆሮዬ ሰምቻታለሁ ። ጂያኮሞ ጉልበቱ ተሟጧል ። ዐይኑ ታውሮአል ። የርስዋን ውሽማ ሲታገል ወገቡ ተሰብሮአል ። ከብዙ ዓመት ትሁት አገልግሎቱ በኋላ ወደ ውጪ መወርወር አለበት! የሚያየው ጠፍቶት ፥ ተ ርቦ በሽታ ጠንቶበት ቢሞት ለእርስዋ ምን አለበት? ቀን አልፎበታል ። እንደእቃ አገልግሎቱን ፈጽሞአል ። ስለዚህ ወደዚያ ማስወገድ ነው ። ለምን ለርሱ እከራከ ራለሁ? የራሴን እንክብካቤ ግን በግሌ አዘጋጅቼለታለሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለጊዜው አንጋፋዋ ምግዚት እሱን እንደሕጻን እያገላበጠች ትንከባከባዋለች ። በርሱ ብቻ አይደለም ልቤ የተሰበረው ። አንድ ማለዳ ጊቢውን ሳቋርጥ ጥቁር ነገር ወድቆ አየሁ ። ተጠግቼ ስመለከት የኔው ውሻ ሞቶ ተኝቷል ። ታማኝ ዐይኑ ፈጦ ጭንቅላቱ ተበርቅሶ አገኘሁት ። ብሽቀትና ንዴት አእምሮዬን አዞረውና አትክልተኛውን ጠርቼ ፤

«ማነው ይህን የሠራው?» አልኩት ።

«እሜቴን ትናንትና ስለነከሣቸው ግደሉ ብለው ስላዘዙን በጥፋቱ ገደልነው ።»

አጕንብሼ ጸጕሩን ስደባብስ እንባዬ መንጽሬ ውስጥ ተንጠባጠበ ። አምስት ፍራንክ አውጥቼ ለሰውዬው ሰጠሁና «ለድካምህ ይኸውልህ ፤ ይህ ውሻ ስላሳዘነኝ እዚያ ዛፍ ሥር በደንብ ቅበረው» አልኩት ። እጅ ነስቶ ትእዛዜን ተቀበለኝ ።

የውሻዬ ውለታ ከበደኝ ። ከሚሽቴ በተቃራኒ ታማኝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጠላቶቼን ለይቶ በየተራ ጥላቻውን ገልጾላቸዋል ። በመጨረሻ አታላይ ሲጋዋን በጣጥሶ ለመጣል ተጣጥሮአል ። የታማኝነት ተግባሩን ፈጽሞ ወደቀ ።

በታወቅሁበትና በተከበርኩበት ፤ በሀብት ከብሬቴ በቅናት በታየሁበት ከተማ እያደር ብቸኛ እየሆንኩ አደባባይ መዞር አዘወተርኩ ። አልፎ አልፎ መቃብር ቦታ እሄዳለሁ ። የአባቶቼን መቃብር ቤት የሚስጢር መግቢያ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይቼ እመለሳለሁ ። አንድ ቀን ሮማኒ ጊቢ ራሴው ቤተመ ጽሐፍት ክፍል ሳነብ ብዙ ቁልፍ የሚቀመጥበትን መሣ ቢያ ከፍቼ ቁልፎች የሚጠራቀሙበትን ጣሳ ገልብጬ ከወደሥር አንድ የዛገ ትልቅ ቁልፍ አገኘሁ ። መቃብር ቤት ይላል ። ሰሞኑን ስለሚያስፈልገኝ ኪሴ ከተትኩ ። ጥላ ሲበርድ እግር ጠብቄ መቃብር ቤቱን መክፈት ይችል እንደሁ ለማረጋገጥ ሄድኩ ። እግረመንገዴን የመቃብር ስፍራው ደርሼ የሮማኒ ቤተሰብ መቃብር ቤት ብረት በር መግቢያ የጥቂት ሜማ ርቀት ላይ እብነበረድ የለበሰውን አዲሱን የጉዶ ፌራሪን መቃብር ቆሜ አየሁ ።

ከመቃብር ቤቱ ስመለስ እግረ መንገዴን መርከበኞች ወደሚዝናኑበት ዳንስ ጉ ራ ብዬ እመለከት ጀመር ። ጊታር እየመቱ ታምቡር እየደለቁ የዳንሱን አዙሪት ከወጣት ሴቶች ጋር ያስነኩታል ። ፊቶቻቸው ከንፈሮቻቸው በደ ስታ የጋሙ ሳቅና ፈገግታ የማይለዩዋቸው ባማሩ ልብሶች የተዋቡ አሳጥማጆችና መርከበኞች የሕይወትን ደስተኛ ስዕል ዐይን ላይ ይስላሉ ። የልብሶቻቸው ቀለም ድምቀት ፤ ሴቶቹ አንገቶቻቸው ላይ ያጌጧቸው ዐይን የሚስቡ ጨሌ ዎች ያን የየካቲት ሰማይ አፍክተውታል ። እንደሞኝ በግማሽ ልብ ዳንሱን አየሁ ። አንዴ እየጮኸ ፤ አንዴ ደግሞ እያንሾካሾከ የሚዘምረውንም ልጅ እስኪጨርስ ጠብቄ ሰማሁት ። የዘማሪውን ግጥም ሳጤን

እንደመሞት ምን አለ ውበት
በተለይ ድንገት
ሞቶ ከሚወድዋት ደጅ መገኘት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደመናደድም እንደመገረምም ብዬ እንደምንም የልቡን እንደልቡ ዘፍኖ እንዲጨርስ ጠበቅሁት ። ዘፍኖ ሲጨርስ ምነው ግጥሙን ሞቶ ከሚወድዋት ደጅ መገኘት ከሚል ገድሎ ከሚወድዋት ደጅ መገኘት ቢለው እያልኩ ተቆጨሁ ። በዚህ ጨዋታ መሀል እያጨበጨቡ ዘፈኑን ከሚያዳንቁት ጉን ያን የማውቀውን መርከበኛ ወዳጄን አንድሪያ ሉዚያኑን አገኘሁት ። በልቤ የሚመላለሰውን ችግሬን ገና ሳገኘው የፈታልኝ መሰሎኝ ደስታ ተሰማኝ ። ፓሌርሞ የወሰደኝን ጉበዝ ጠጋ ብዬ ትክሻውን መታ አደረኩት።ዞር አየ። ግን አላወቀኝም ። አይፈረድበትም ። መጀመሪያ ሲያየኝ ጺምና መነጽር አልነበረኝም፣ ልብሴም የዓሣ አጥማጅ ነበር ። ስሜን ስጠራለት ጌታዬ ብሎ በሁለት እጁ እየነቀነቀ ሰላም አለኝ ።

«ግን ጌታዬ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ እለምናለሁ ። መጀመሪያ ላይ አላወቅሆትም ነበር ፤ ግን ብዙ ጊዜ ስለ እርስዎ አስብ ነበር ። ስምዎንም ብዙ ጊዜ ስምቻለሁ ። ምን ዓይነት ዝነኛ ስም ነው ያለዎት ፤ ባለጸጋ ነዎት ፤ ታላቅና ለጋስ ስም ነው ያለዎት ። ምን ዓይነት የተደሰተች ነፍስ ናት ያለችዎት ። ደግሞ ለጋብቻ እየተቃረቡ ነዎት ። ፍቅር የችግር ሁሉ ደምሳሽ ናት» ሲጋራውን በአንድ ጊዜ አብንኖ ባርኔጣውን አውልቆ ፣

«ለጌታዬ ፍጹም ደስታ እመኛለሁ» ካለ በኋላ በጥያቄ አይን ትኩር ብሎ ሲመለከተኝ አየሁት ። ለምኑ ካመሰገንኩት በኋላ ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

«በሁኔታዬ ሳልለወጥ የቀረሁብህ አይመስለኝም ወዳጄ» አልኩት ።
እንደማፈር አለና «ሁላችንም በጥቂቱ መለወጥ አለብን ፤ ቀኑ ያልፋል ። እያንዳንዷ ቀን ደግሞ ከልጅነታችን በመጠኑ እየቆረሰ ያልፋል ። እና ሁላችንም ሳናስበው እናረጃለን ።» ሳቅ አልኩና «ስለዚህ ባለፈው ጊዜ ካየሽኝ ወዲህ አርጅቻለሁ ማለት ነው?»

«ትንሽ በመጠኑ»

«ብርቱ ሕመም ደርሶብኝ ነበር ።» ረጋ ብዬ ማስረዳት ጀመርኩ ። «ዐይኖቼ አሁንም ድካም አለባቸው ፤ ግን እያደር እየጠነከርኩ ነኝ ። ይልቅ እስቲ አንዴ ለበረታ ጉዳይ ስለምፈልግህ ላናግርህ» ብዬ ከአጀቡ መሀል ይዤው ወጣሁ ።

ራቅ ብለን ብቻችንን ከሆን በኋላ «ጀልባህ ደህና ናት ፤ አይደል ?»

«ለመቤታችን ምስጋና ይግባት ደህና ናት ፤ እንዲያውም ታድሳለች ። አሁን በሜዲትራኒያን ባሕር ላይ ከሚንቀሳቀሱት ትበልጥ እንደሁ እንጂ በምንም አታንስም ።»

«እስቲ እንግዲያውስ ላስቸግርህ የፈለኩበትን ጉዳይ ልንገርህ» በማለት ቀረብ ብዬ ድምፄን መለስ አድርጌ «አንድ ጓደኛዬ የሆነ ሰው በጣም ተቸግሮ ከኔፕልስ በሚስጢር ሹልክ ብሎ መውጣት ይፈልጋል ። በሕግ የሚፈለግ አይደለም ። አድሎ ፍርድ እንዳይበየንበት ሸሽቶ የሚሄድ ነው ። አንድ ጊዜ በመርከብህ አሰበበት ቦታ


t.me/OLDBOOKSPDF

እንድትሸኘው እፈልጋለሁ ። ለዚህ ውለታህ እጥፍ ድርብ ዋጋ እከፍላለሁ ።»

«እንዲህ ከሆነማ እኔ ለመተባበር ዝግጁ ነኝ ። ግን የት ነው ሰውየው የሚሄደው ?»

«ቺቪታ ቪኪያ ወደብ ነው የሚሄደው ፤ ከዚያ በኋላ በሌላ መርከብ ተሳፍሮ ወደ ሩቅ ቦታ ይዘልቃል ።»

«ቺቪታ ቪኪያ እሩቅ ነው ። በጣም እሩቅ ነው ። ወራቱም መጥፎ ነው ። ተጋፊ ንፋስና ማዕበል ይበዛ ዋል ። እኔ መቼም ፍላጎትዎን ለማሟላት ወስኜ ነበር ። ነገር ግን ሁኔታውን ሳየው ከአቅሜ ጋር የሚመጥን አይደለም ። ትንሽዋ መርከቤ አደጋውን አትችልም ፤ ሌላ ዘዴ ግን አላጣም ። እንዲያውም የፊታችን እርብ ቺቪታ ቪኪያ የምታመራ የጓደኛዬ መርከብ አለች ። ለጓደኛዎ ይስማማ አይስማማ አላውቅም እንጂ ነገሩ ይሳካል ። ጓደኛዬ ገንዘብ ይወዳል ። በተለይ የገንዘቡን መጠን ጠቀም ቢያደርጉለት እኔ እሺ አስኘዋለሁ ።»

አንድ የሆነ ከባድ ግምት ያለው ገንዘብ ጠቀስኩ ለት ። አንድሪያ ዐይኑ ቋምጦ ተቅበዘበዘ ።

«ይኸማ የእድሜ ልክ ችሮታ ነው ። እኔ ሀያ ጊዜ ተመላልሼ አላገኘውም ። በቃ በቃ ፤ እንደተፈጸመ ይቁ ጠሩት ።»

«ጥሩ እንግዲህ ፣ ሚስጢርነቱን አስጠንቅቀው ። የሚጓዘውን ሰው ጥያቄ እንኳ እንዲጠይቀው አያስፈል


t.me/OLDBOOKSPDF

ግም ። ቅድም እንዳልኩህ ቦታው ካደረሰው በኋላ እርሱ በራሱ መንገዱን ፈልጎ ይቀጥላል ።»

ይህቺ ለጊዜው ለችግርህ ትሁንህ ብዬ ሁለት ባለ ሃያ ፍራንክ ሳንቲሞች በሥራ የጠቆረ እጁ ውስጥ ጠብ አደረኩለት ።

«እና እንደምታውቀው እኔ ለገንዘብ ግድ ስለሌለኝ ይህን ጉዳይ እንደምንም ተሯሩጠህ አሳካልኝ ። ድካም ህን የምዘነጋ እንዳታደርገኝ ። ሁሉንገር ከተሳካ በኋላ በዚህ አድራሻዬ ነገ ወይም ተነገወዲያ ሆቴሌ እንገናኝ ።» አድራሻዬን ካርዴ ላይ ጻፍ ጻፍ አድርጌ ሰጠሁት ። «አደራ ዱ ግን ጓደኛህ ምስጢርነቱን እንዲያውቅ አስጠንቅቀው ። ከዚያ ወዲያም ነገሩን ፍጹም እንዲዘነጋው ያስፈልጋል ።»

«በቃ ተግባብተናል ጓደኛዬ፣በእድሜም የገፉ ስለሆነ ለሁሉም የማስታወስ ኃይሉ የተዳከመ ነው ። በኔ ይሁንብ ዎት አይስጉ ።» ደህና ሁን ተባብለን ተለያየን ።

ይህ በሆነ ማግስት ከቀትር በኋላ እግሬ ወደ ማል ወደው አጸያፊ ጉዳና ወሰደኝ ። መንገዱን አውቀዋለሁ ። ከመቃብር ካመለጥኩ ወዲህ መሄድ ቀርቶ ማሰቡ ራሱ ስለሚቀፈኝ በዚያ መንገድ ላለመሄድ ተከላከያለሁ ። መንገዱን ገባ እንዳልሁ በሩቅ ከመቃብር ስወጣ አሮጌ ልብስ የገዛሁበትን የሸማግሌውን መደብር እየሁና እየተ ጠጋሁ ሳስተውል ወሰከ የጠጡ አሮጌ ልብሶች ተመሳቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለውና ተከምረው በራፍ ላይ አንድ የይሁዲ ባርኔጣ ያደረገ ወጣት ፒፓ በአፉ ሰክቶ ተቀምጦ አየሁ ። ጠጋ ብዬ «የመደብሩ ባለቤት አንተ ነህ ?» ስለው

«አዎን እኔ ነኝ ጌታዬ» አለ ።
«የቀድሞው ባለቤት ወዴት ደረሰ ?»

ከት ብሎ ከሳቀ በኋላ «ራሱን በጠበቢ ዘክዝኮ በሺ ፍ ፍራንክ የገዛውን ከፋይ የአልጋ ልብሱን በደም ለውሶ ሞተ።»

«ምስኪን ፣ ልቡን እንደመንሳት አደረገው እንዴ?» አልኩና ቆሜ ተከዝኩ ።
«ዱሮስ ምን ጤና ነበረው ጌታዬ ?»

ለሰጠኝ አዲስ ዜና አጉርሼ ደህና ሁን ብዬ መንገ ዴን ቀጠልኩ ። ሽማግሌው ካሰመጠን አሳዘነኝ ፣ የበቀል ጥሙን ሁሉ ጠጥቶ ረክቶ በመጨረሻው በራሱ ላይ ዘ መተ ። የኔም መጨረሻ ይኸው ነው ። እንግዲህ እንደአበደ ጅብ የራሴን ሥጋ ቆራርጬ መሞት የመጨረሻ እጣዬ ነው። ይህን ሀሳብ በሆዴ እያመላለስኩ ሳዘግም ከአንድ ፎቅ ስገነት አገዷት የማውቃት ሴት ጽጌረዳ አበባ ወርውራ እግሬ ላይ አረፈ ። ለትህትናው ያህል አበባውን አንስቼ ባርኔጣዬን ከራሴ ላይ ብድግ አድርጌ አመሰግኜ ከዐይንዋ ዞር ስል መንገድ ላይ ለሚጫወት ብላቴና አበባውን ወርወር አ ደረግሁለት ። አበባ ምን ቢቆንጅ ሽታ መዓዛው ምን ቢያ


t.me/OLDBOOKSPDF

ውድ ለኔ ፋይዳ የለውም ። የጽጌረዳ ውበት ንጹህ ነው ። ሽታው የደስታን ቀን ያስታውሳል ። የደስታን ቀን ደግሞ እኔ ባስታውስ ራሴን መጉዳት እንጂ ጥቅም የለኝም፤ እኔ ከጽጌረዳ ጋር አልወዳጅም ።

የኔዋ ሚሽት ሁልጊዜ ስለምታጌጥበት መጀመሪያ ከጉዶ ጋር ተቃቅፈው ያየኋቸው ማታ እንኳ ጡትዋ ላይ ቀይ ጽጌረዳ አድርጋ በድሪያው መሀል ተፈረፈረ ። ይጠ ስገን ነው ፤ አሁን ከምኖርበት ሰማይ ጠቀስ ደን የጽጌ ረዳ አበባ የለም ። የጽጌረዳ አበባ መልክና መዓዛ እስከ መጨረሻው በውስጤ ጉምዝዞ ሞቷል ።

ያን ምሽት ከሚሽቴ ወይም ከእጮኛዬ ጋር ቲአትሩ አምሽቼ ተመለስኩ ። ቴአትሩ ላይ እምብዛም ደስተኛ እለመሆኔ ያስታውቃል ። በመጨረሻው ሸኝቻት ክፍሌ ገ ባሁ ። ደክሞኝ ስለነበር የሞት ያህል እንቅልፍ ወሰደኝ ።

ናፖሊዮን በትእግስት መጠበቅ ለሚችል ሰው ዓለሙ ሁሉ ወደርሱ ይጓዛል ይላል ። እኔም በትእግሥት መጠበቅ ስለቻልኩ የምፈልገው የተበቃዮች ዓለም በመጨረሻው እየፈለገኝ መጣ ።

ቀኑ እንደአዙሪት እየተሽከረከረ የሡርጌን እለት ዋዜማ እፊቴ አምጥቶ እንደገና የምሠረግበት ቀን ዝግጅቱ ሁሉ ተጠናቆ የጉድ ዓይኑን አፍጦ መጣ ። ለክብር ሞገሱ የሚገ ባው ዝግጅት በሙሉ ተጠናቀቀ ። የቁርስ ግብዣው እጅግ በጣም ለተወሰኑ የቅርብ ጓደኞቻችን ብቻ የተዘጋጀ ሲሆን



t.me/OLDBOOKSPDF

ትልቁና ዋናው ግብዣ ማታ ሙሉ ራትና ዳንስ ያለው ም ሽት ተዘጋጀ ። የመጀመሪያውና የመጨረሻውም ድንቅ እንዲሆን ብዙውን ገንዘብ አወጣሁበት ። የጌታ ሲዛር አሊሻ መጋረጃ ተከፍቶ ለመጨረሻው ጊዜ የሚዘጋበት ታላቅ ግብዣ በሆቴሌ ተደገሰ ።

አንድ መቶ ሀምሣ ሰው ተጋብዞ ሁሉም ለመምጣት መልስ ሰጠ። ሠርጉ እንደ ነገ ጠዋት ከሰዓት በኋላውን ውቢቱ ሚሽቴ ዘንድ ሄጄ እንደባልና ሚሽት ስለጠቅላላው ዝግጅት እንነጋገር ጀመርን ። ኒና በእውነት ተውባለች ። ዓይንዋን እየጠበቅሁ ጠቅላላ ሁኔታዋን ትኩር ብዬ አያታለሁ ። ዓይኔ በመነጽር፤መሸፈኑ በጆ እንጂ ያጉረጠረጠውን ዓይኤን ብታጤን ዘሎ ለማነቅ ያደባ ነብር ነበር የሚመስለው ።

«በሕጻናት የልብወለድ ታሪክ ውስጥ የሚነበበውን ልዑል ነው እኮ የምትመስለው ሲዛር፤» አለችኝ እንደኩራት እየሞከራት ፥ «የምትሠራው ነገር ሁሉ በመጨረሻውና ከፍተኛ ወግ የተቀናጀ ነው ። ባለጸጋ መሆን እንደ ምን ደስ ይላል ። ከመከበር ወዲያ በዓለም ምን ጥሩ ነገር አለ?» ብትል ፤

«ከፍቅር በላይ ሊሆን አይችልም» አልኳትና ልት ከራከር አልሞከረችም ።


t.me/OLDBOOKSPDF

«ትክክል ነው ፤ ፍቅር የመጨረሻው ጥሩና ተፈላጊ ነው ። ግን አንድ ሰው ፍቅርም ሀብትም ካለው ሕይወቱ ምን ያህል የገነት ኑሮ ይሆን? ።»

«ትልቅ ገነት ሆነለት ማለት ነው ። እንዲህ ያለው ገነት ከተገኘ ገነት መግባት በጣም አስፈላጊ ነው እንዴ? እባክሽ ፣ ይና ዓለምን ገነት ታደርጊልኛለሽ? ወይስ ባልሽን የወደድሽውን ያህል ትንሽ ወይም ትልቅ ታፈቅሪኛለሽ?»

ትከሻዋን እንደማንቀጥቀጥ ካደረገች በኋላ «ግን ለምንድነው ስለሟቹ ባሌ ብዙ ጊዜ ማውራት የምትወደው? እኔ ስሙን መስማት ራሱ ታክቶኛል ። ስለሞተ ሰው ማስ ታወስ እኮ አስፈላጊ አይደለም ። በሚያስቀጥጥ ዓይነት አሟሟት የሞተ ስለሆነ ሳስታውሰው ትዝታው ያሸብረ ኛል ። ብዙ ጊዜ ለርሱ ፍቅር እንዳልነበረኝ ደግሞ ነግሬሀ ለሁ ። ትንሽ ነበር የምወደው ። መሞቱን ያረዳኝን ያን መጻ ጉዕ የመሰለ መነኩሴ ያየሁ ዕለት አሞኝ አደረ ። ደህና እኮ ከጉጁ ጋር ምሳ ስንበላ ነው በቁስያት መነኩሴው መጥቶ ያስደነገጠኝ ። ሁለታችንም ካለመጠን ደነገጥን ። ልቤን ግን አልሰወረውም ። አሁን አንተን ነው የማፈቅረው ። በእው ነት እወድሃለሁ ።»

ሶፋው ላይ ጋለል ብላ እንደተቀመጠች ጠጋ ብዬ እጇን ማል አደረግሁባት ።

«በእውነት ትወጅኛለሽ? እርግጠኛ ነሽ?»

ጭንቅላትዋን በክንዴ ላይ አሳርፋ ሳቅ አለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«በጣም እርግጠኛ ነኝ ። ስንት ጊዜ ነው ይህን ጥምዝ ጥያቄህን የምታቀርብልኝ? እንደምታምነኝ ምን ልበልህ? ምን ላድርግልህ ሲዛር?»

«ምንም አልፈልግ ። ግን እኔን ነው ወይስ ሀብቴን ነው የምታፈቅሪ ?»
ራስዋን በኩራት ቀና አደረገች ።

«አንተን ነው የማፈቅረው ። ሀብት ስሜቴን የሚለው ጠው ይመስልሀል ? ተሳስተሀል ሲዛር ። እኔ የማፈቅርህ ስለራስህ ነው ።»

የምሬት ፈገግታዬን አላየችም ። እንደ አባይ የሚፈስ ውን ሀር ጸጉርዋን ዳበስኩት ።

«የሕጻናት ልብወለድ ውስጥ የሚነበበውን ልዑል ትመስላለህ አልሽኝ ። ለዚህ አነጋገርሽ ሽልማት ይገባ ሻል ። መጀመሪያ የላኩልሽን የአልማዝ ስጦታ ታስታው ሺዋለሽ?»

«እንዴት አላስታውስም ። እርሱ ለአንዲት ንግሥት የሚገባ አልማዝ እኮ ነው ።»

«የኔ የውበት ንግሥት ደግሞ አንቺ ነሽ ። ያ ስጦታዬ ግን ያለኝንና ልሰጥሽ ያዘጋጀሁትን በፍጹም ሊወዳደር አይችልም ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

ዐይንዋ ከተደበቀበት ወጥቶ ተቅበዘበዘ ።

«እባክህ ልያቸው ። ካለኝ አልማዝ ፀላይ የሚያምሩ ከሆን በእውነት የሚያስደንቁ ናቸው ። ግን ሁሉንም ለኔው ነው የምትሰጠው ወይስ ?»

«ሁሉንምላንቺ ነው የምሰጠው» ወደኔ ጠጋ እያደረግ ኋት ፣ «ሁሉንም ለሙሽራዬ ነው የምሰጠው ። የፈርጥና እንቁ ሀብቴን ላንቺ ብቻ ነው የምሰጠው ። እንደደም የቀሉ እንቁዎች፣ የተንቀለቀሉ ብርቅ አልማዞች፣ የተጣጠፉ ፈርጦች ፣ በወቅት እንደሚለዋወጥ የሴት ፍቅር የሚንቦገ ቦጉ ሉሎች ሁሉ ።» በድንጋጤ ሰውነትዋ ፈዘዘ ፣

«እኔ ባለቅኔ እንዳይደለሁ ታውቂያሽ ፣ ቃላት አፌ እንደገባ እንጂ መርጬ አልናገርም ።»

የሆነ የሀሳብ ሰመመን ይዟት እያየሁ ንግግሬን አዲስ ባስለመድኩት ሻካራው ድምፄ ቀጠልኩ ። ከሀሳብዋ ስት ነቃ ስግብግብ የሀብት መዝረፍ ፍትወትዋ ትውስ አላት ፣

«ታዲያስ ዛሬ ያን ያልከኝን አልማዝ ታሳየኛለህ?»

«ዛሬ አይደለም ኒናዬ።ሌሊት ከሠርጋችን በኋላ ነው ። ሌላም ነገር ቃል የገባሁልሽን አሳይሻለሁ ። ረሳሽ እንዴ ፣ መንፀሬን አውልቄ ዓይኔን አሳይሻለሁ ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እዎን አንተን ራስህን እንተነትህን ማየት እፈልጋ ለሁ ።»

«አልማዙን ግን የማሳይሽ ነገ ሌሊት ከኔ ጋር ለመ ሄድ የፈቀድሽ እንደሆነ ነው ። » በመገረም ሳቀች ።

«ስግብግብ ነህ እንዴ ሲዛር ። ውድ ሀብትህን የምትድ በቅበት ልዩ ቦታ አለህ ማለት ነው ?»

«ባንክ እንኳን የሚጠረጠርበት ጊዜ አለ ። እንዲህ ያለው ሀብት በገንዘብ አይተመንም ። ልሰጥሽ ያሰብኩትን አልማዝ ለሰው አስቀምጥ ብሎ መስጠቱ እምነቱን መፈ ተን ነው ። ስለዚህ እኔ ብቻ የምደርስበት ድብቅ ቦታ አለኝ። ታዘብሽኝ እንዴ?»

በእጅዋ የአንገቴን ዙሪያ አቅፋ ሳመችኝ ፣ ከንፈሬን በሳመችኝ ቁጥር ነፍሴ በስቃይ ትጨነቃለች ።

«አልታዘብህም ጌታዩ ። ለምን እታዘብሀለሁ? ደግ ነህ ፣ ደፋር ጀግና ነህ ፣ አባመስጠት ነህ ፣ የወንዶች ኩሩ ነህ ፣ ብቻ አንዳንዴ ......» ሀሳብ ይዞአት እልም አለ ።

«ብቻ አንዳንዴ ምን?»

«አንዳንዴ አንዳንድ ሁኔታህ ፋቢዮን እየመሰለኝ እደነግጣለሁ ።»


t.me/OLDBOOKSPDF

«እኔ አሁንስ ሰግቼ መሞቴ ነው ። ምንድነው ይኸ እኔን ስታይ ባልሽን የምትሰይው ? ገዳም ሳይሽ ብመጣ እጅህ እርሱን መሰለኝ ብለሽ ያን ያህል ታመምሽ ፣ ምን ድነው ነገሩ ወይስ የዱሮው ባልሽ ሆኜ የመጣሁ መሰለሽ?»

ከተናገርኩ በኋላ በሳቅ ፈነዳሁ ። እርስዋ ግን በመ ጠኑ ሰውነትዋን መቆጣጠር አቅቷት ተወራጨች ። መለስ አድርጋ ደግሞ እንደኔው ከት ብላ ሳቀች ።

«ግራ የሆነ ነገር እንደማስብበስ ይገባኛል ። ምናልባት ትክክል አይደለሁም ። ብዙ ነገር ተለዋወጠብኝ እኮ ሲዛር። ነገ ግን አልማዞቹን ለማየት እንሄዳለን አልከኝ ።»

«አዎን ነገ ማታ እንደ ሰርገኞቻችን እየተጫወቱ ትተን ሔደን ወዲያው እንመለሳለን ። »

«ብቻ ጊዜ ማጥፋት የለብንም። ደንገጡሬ ልብሴን ማዘ ራጀት አለባት ። የአልማዝ ጌጣጌጤ ጥብቅ ቦታ መግባት አለበት ። ሌሊቱን ሆቴል አድረን ፣ ሲነጋ ሮም ፣ ከሮም ፓሪስ ነው የምንጓዘው ፣ እንዲህ አይደል እንዴ ፕሮግ ራሙ ።»

«ይኸው ነው ፣ እንዲሁ ነው የተዘጋጀው ።»

«ግን አልማዙን ለምን አንተው ሂደህ አታመጣና አትሰጠኝም?»


t.me/OLDBOOKSPDF

«ብዙ ዓይነት ነው ። አስመርጨሽ የምትፈልጊውን ሁሉ ትወስጃለሽ ። ምርጫሽን አንቺው ስትወስኚ ነው እኔ ንም ደስ የሚለኝ ። »

«ባልመርጥስ ፣ ሁሉንም ብወስድስ ምን ትላለህ ሲዛር?»
«ደስታዬ ነው»
«እውነትም በጣም ደግ ነህ ። ግን አሞላቀከኝ ።»

«ለመሆኑ አንቺን ማሞላቀቅ ይቻላል?» በማሾፍ መልክ ጠየኳት ። «መልካም ቤቶች እንደጥሩ ፈርጦች ናቸው ። ይበልጥ በተጠነቀቁላቸው መጠን ይበልጥ ያን ጸባርቃሉ ።» በቀልድ ዓይነት እጄን መታ አደረገችኝ ።

«እንዳንተ በተናገረ ቁጥር ከአፉ ማር ጠብ በሚል አይነት ምርጥ ቃሉን ያሰማኝ ሰው እስካሁን የለም ።»

«ጉዶ ፌራሪ እንኳ?» ስል በምጸት ዓይነት ጠየኳት ።

ምርር ባለ ጥላቻ ዓይነት ሰውነትዋን ሰብስባ ፊትዋን ኮስተር አደረገችና ፤

«ኤዲያ! ጉዶ ፌራሪም ሰው ሆኖ ። እረ እንዲህ በዋዛ የሚያናግረኝ ሰው አልነበርኩም ። እርሱ ጠብ እርግፍ ብሎ ተንቀጥቅጦ የንግሥት ያህል ይፈራኝ ነበር ። ባለቤቴ በርሱ ላይ በነበረው እምነት ምክንያት ሊቀርበኝና መጥፎያውን


t.me/OLDBOOKSPDF

ሲከስትበት እኔን ለመድፈር ተቀናጣና ተገቢ ቅጣቱንም ለመቀበል በቃ ።»

ከመቀመጫዬ ብድግ ብዬ ነገ ድረስ ላንተያይ ነው፤ እንግዲህ ታላቁ ቀን እጁን ዘርግቶ ባልና ሚስት ሊለን ይጠብቃል፤ እስከዚያ ግን ደህና እደሪ ።»

ኮሊታዬ ላይ ያለውን አበባ እያገላበጠች ደረቴ ላይ ጥቂት ልጥፍ አለች ።

«የቀድሞውን የጋብቻ ቀለበትሽን አሁንም እንዳደረግሽ ነሽ እንዴ?»

ከአራት ዓመት በፊት ያጠለቅሁላትን ቀለበት አወለቅሁ። «ነገ ከዚህ የበለጠ የደስታ ምልክት የሆነውን አጠልቅልሻለሁ ።» ብዬ ጥላቻዬን አጥንቴ ውስጥ ቀብሬአፍዋን ግጥም አድርጌ ሳምኳት ። በእቅፌ እንዳለች ጨምድጄ ነፍስዋን ከስጋዋ ለመለየት ፈቃዴ ነበር ። ቀና ብላ ስታየኝ የውስጤን ያነበበች መስሎኝ ደነገጥኩ ። ያየችው ገቢው የተትረፈረፈ ባለጸጋ ፤ ሴቶች ሁሉ የሚቀኑባት በሀገር ሁሉ የታወቀች ሴት ሊያደርጋት የተዘጋጀ አንጋፋ ከበርቴ አድርጋ ነው ። የቀድሞ ባልዋን መምሰሌን የምታስበውም በአጋጣሚ አንድ ሰው ሌሎች ሁለት ምስያዎች በዓለም ይኖሩታል በሚለው አስተያየት እንጂ የምሩን ፋቢዮ መሆኔን ጠርጥራ አይደለም ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ቤቱ ስደርስ መርከበኛው ወዳጄ እንድሪያን በቀጠር ኩት ቀንና ሰዓት አገኘሁት ። እርሱን ሳይ እቅዴ ሁሉ መፈ ጸሙ ተረጋገጠልኝና በደስታ ተመሰጥኩ ። «እንድሪያ ሉዚያኒ» ብዬ ሙሉ ስሙን ስጠራው «ክቡር ጌታዬ» ብሎ ተቀበለኝ ።

ክፍሌ አስገባሁት ። ወርቅ ቅብ ወንበር ላይ አስቀ መጥኩት ።

«መቼም እናንተ መርከበኞች የዚህ ዓለም አዱኛ ስሜት አይሰጣችሁም ። ሰማዩን ሙሉ ይዛችሁ ትዞራላ ችሁ ፤ የባሕር ወርቃማ ስጋጃ ምንጣፍ ላይ እየተንሳፈፋ ችሁ ሕይወት ሳይሰለቻችሁ ትኖራላችሁ» አልኩት ።

«አዎን ጌታዬ ፤ የባሕር ኑሮ እንደ ኩተለመደ እር ሱን የሚያስንቅ ነገር የለም ።»

ምርጥ ወይን ጠጅ ከፍቼ ቀዳሁለትና አንድ ጊዜ ከተጉ ነጨ በኋላ ፤ ውድነቱን በጣዕም አውቆ እያጣጣመ «ለክቡር ጌታዬ ጤንነት» ብሎ ዋንጫውን አነሳልኝ ።

ለመልካም ምኞቱ አመሰገንኩት ። «እና ጓደኛዬ እንድሪያን ፤ መቼ ማግባት ታስባለህ ?»

«ብዙዎች ወዳጆቼ ባገኙን ቁጥር አያ እንድሪያ አን ተም ታገባና ፣ ቤት ልጆችና ሚሽት የምትልበት ቀን


t.me/OLDBOOKSPDF

ይመጣና ይህን የባሕር ዓለም የሚያስንቅብህ ታገኛለህ» ይሉኛል።» አዬ ጌታዬ የማገባት ሴት ባሕሩንና ማዕበሉን የምታፈቅር መሆን አለባት ። የፊጣሪን ቁጠኛ ሞገድ ማየት የሚችል ዓይን እንዲኖራት እፈልጋለሁ ። ልጆቼም የባሕሩ ጨው በደማቸው ውስጥ ከሌለ አልፈልጋቸውም ፤ ልጆቼም አይደሉም ።»

የሚጠጣውን ተጉንጭቶ በመደነቅ ዐይኑን አንከባለለ ። ስሜቱን በደስታ አስዋኝቶ «አንዲት እናቴ የምትወዳት ቆንጆ አለች ። የካርሜሎ ኔሪን ቴሬሣ ትመስላለች ። እንደማለዳ ሊሊ የተዋበች ናት ። መንፈስዋ እንደባሕር ሞገድ ነው ። የባሕሩን ማዕበል እንደርስዋ የሚወድ የለም ። እና ምናልባት እመቤታችን ከፈቀደች የአደይ አበቦች ሲፈነዱ ማን ያውቃል እኔም በተግባር የፍቅር ዘፈን እዘፍን ይሆናል ።»

ታዋቂውን የሲሲሊያን የፍቅር ዜማ እንጉርጉሮ ወይንጠጁን ለመልካም ዕድል አንስቶ ጨለጠው ። የቁጣ መንፈስ ስሜቱን ዘረፍ አደረገውና ዞሮ ዞሮ ታሪኩ ሁሉ ያው አንድ ርእስ ነው አልኩ ። ያው እያንን ስለሚያጠምደው ፍቅር ፤ የጥፋት ምንጭ ፡ ስለሆነው ፍቅር ፤ ርጉም ስለሆነው ፍቅር ነው ። ከዚህ የሰውን ልጅ ነፍስ አጥምዶ ከሚጨርስ ወጥመድ መገላገል አይቻልም ማለት ነው?

ወዲያው እንድሪያ ስለፍቅር ማለሙን አቆመና መቀመጫውን ወደ እኔ ጠጋ አድርጎ ፤


t.me/OLDBOOKSPDF

«እና ችግር ስላገኛቸው ጓደኛዎ......» ነገሩን ሳይጨርስ የእኔን አስተያየት በዐይኑ ይጠብቅ ጀመር ።

«ቀጥል ያዘጋጀኸውን ንገረኝ እባክህ» አልኩት ። «ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል ።» አነጋገሩ ፍጹም ልበ ሙሉ ሆኖአል ።

«አርብ ዕለት ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት መርከብዋ ኔፕልስን ለቃ ትሄዳለች ። የመርከብዋ ካፒቴን አንቶኒዮ ባርዲ ከአስር እስከ አሥራ አምስት ደቂቃ ይጠብቃል ።»

«ብቻ እንዳይዘገይ ነው ዋናው ነገር።ለመሆኑ በገንዘቡ ተስማማ?»

«መስማማት ነው? ለዚህ የማይስማማ ምን ሰው ይባላል ። ምንም እንኳ በሽማግሌ ዕድሜው ሁሉን ስላየ ሕይወት የሚሰለቸውና የማይደሰት ቢሆንም የቀረበለት ገንዘብ የማይገፋ ነው ። ሽማግሌው በደስታ ነው አሁንስ የተስማማው ። ጓደኛዎን ደግሞ እንዳያናግር ስላስጠነቀቅኩት ጓደኛዎ ሽማግሌውን መርከበኛ ዲዳ ነው ሳይል አይቀርም።»

«በጣም አመሰግናለሁ ፤ ልክ ይኸን ነው የፈለኩት የመጨረሻው ጥያቄዬ ደግሞ »

«ጌታዬ ምንም ነገር ቢጠይቁኝ የማልፈጽምበት ምክንያት የለም ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

«አንዲት የጓደኛዬን ትንሽ ሻንጣ አሁኑኑ ለመርከቡ ካፒቴን በአደራ እንድታስረክብልኝ እስክመጣልህ ድረስ እዚሁ ብትጠብቀኝ ።»

ለአንድ ሁለት ደቂቃ ትቼው መኝታ ክፍሌ ገባሁ ። ሁልጊዜ ቆልፌ የማስቀምጠውን ሳጥን ከፍቼ ቪንቼንዞ ሳያየኝ ያደራጀሁትን ጥቂት አገልግሎት ላይ ያልዋሉ ባለሺ ፍራንክ ኖታዎች ከነቆዳ ሻንጣው አንስቼ እንግዳ ክፍል ገብቼ ለአንድሪያ ሰጠሁትና ሻንጣዋን ጠልጠል አድርጐ ብድግ አለና ፤«ጓደኛዎ ያላቸው እቃ ይኸ ብቻ ከሆነ ሀብታም ሰው አይደሉም ።»

ልክ ነው በእውነት ድሀ ሰው ነው ፣ ድሀ የሆነበትም ምክንያት ውለታ የዋለላቸው ሰዎች ስላታለሉትና ስለከዱት ነው ። ድሀም በመሆኑ ነው የመጓጓዣውን ዋጋ የከፈልኩለትና በተቻለኝ መጠን ልረዳው የሞከርኩት ።

«ሀ ደገኛ ልብ ነው ያለዎት ጌታዬ ።» ቀስ ብሎ እያጉመተመተ «ምነው እንደርስዎ ብዙ በነበር ፣ አዱኛ ብዙውን ሰው ገሽሽ አድርጋው ስታልፍ ዘመድ ወዳጅ የተባለው ሁሉ ገሽሽ አድርጐት ያልፋል እንጂ የሚጠቅመው አይገኝም ። ከዕለታት አንድ ቀን ባለጸጋ የነበረው በችግር ድፍት ብሎ ይቀራል ፣ ለመሆኑ ይኸ ጓደኛዎ ልጅ እግር ነውን?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎን በጣም ልጅ እግር ነው ፣ ገና ሰላሳ አልሞላ ውም ።»

«ልክ እንደ አባት እኮነው የሚንከባከቡለት ፣ ብቻ ውለታዎን እንዳይዘነጋ ።»

«ተስፋ አደርጋለሁ ።» ሳቄ መጣና ፈገግ ብዬ መለስ ኩለት ። «እና ይኸን ደግሞ ለራስህ አድርገው» ብዬ አንድ እንቦልክ ገፋ አደረኩለት ። «እቤት እስክትደርስ አትክፈተው ፤ በምትወዳቸው እናትህና በዚያች ፍቅረኛህ ፊት ክፈተው ። መጠኑ እንደሚያስደስትህ ተስፋ አለኝ ፣ የቤተሰቦችህ ደስታ የኔም ደስታ ነው ።»

ዓይኑ ላይ የልቡ ደስታ እየተፍለቀለቀ ሻንጣውን መሬት አስቀምጦ እጁን እየፈራ ሲጨብጠኝ ዘረጋና ሞቅ አድርጌ ጨብጬ አሰናበትኩት ። የተሳሰረ የመርከበኛ ግንባሩ ሲፍታታ ታየኝ ።

«መቼም ጌታዬ ዳግመኛ ስንገናኝ ነው የልቤን መናገር የምችለው ፣ አሁን አፌም በደስታ ተሳስሮአል ።»

«አዎን ዳግም ስንገናኝ ታመሰግነኛለህ ፣ ምስጋና ግን የሚያስፈልገኝ አይደለሁም ።»

እስከወዲያኛው ላንገናኝ ተለያየን ፣ እርሱ ንፋስና ባሕር ሞገድና ማእበል የሚሰጠውን ደስታ ለማፈስ ወደ ድድር ሕይወት እኔ ደግሞ..... ወዴት ነው? የምሄድበትን


t.me/OLDBOOKSPDF

እስቲ ቸኩዬ አልገምት ፣ ደረጃ በደረጃ ውስብስብ ያለውን በእንባና ደም የራሰውን ደረቅ መሬት ሁሉ ካዘገምኩ በኋላ እንደጊን ስለታም ሱፋጭ አልፌ መጨረሻው ምሬት እስኪ ሆንብኝ መተከገር የሌለውን ማስፈያ ሁሉ እንዳልዘነጋ ፤ እስቲ ላስብ

ያንኑ ምሽት ሠራተኛዬ ቪንቼንዞን አናገርኩት ። ቪን ንቼንዞ ለሠርግ ጉዞዬ እንደማይከተለኝ ስለነገርኩት ስሜቱ ሁሉ ውድቅድቅ ብሎአል ። በሠርግ ጉዞዬ ሊከተለኝ ያለ መቻሉ ቅን አገልግሎቱን በመስጠት በደስታዬ መደሰት ስላልቻለ ከፍቶታል ። ቢከተለኝ በተለይም ስለሠርጌ የሚ ጠረጥራቸውን ነገሮች ሁሉ መልስ ሊያገኝባቸው ስለሚ ችል በመቅረቱ ይበልጥ ጠርጣሪ አድርጎታል ። ዓይኑን በምንጣፉ ላይ ሰክቶ እንደቆመ ፤ «ወዳጄ ቪንቼንዞ» አልኩት ፣ «እንግዲህ ለእኔ እንኳ የደስታ ቀን መምጣቱ ነው ። በቁንጅናዋና በሀብቷ በመላው ኔፕልስ የተደነቀች ዋን እመቤት ሮማኒን በነገው ቀን ላገባ ነው ።»

«አውቃለሁ ጌታዬ» ይህን ሲል ዐይኑን ከምንጣፉ ላይ አልነቀለም ።

«በደስታዬ አትደሰትም ማለት ነው እንዴ?»

ፈጥኖ ወደላይ ቀና ብሎ አየኝና እንደገና ግንባሩን ደፍቶ «በእርግጥ የሚደሰቱ ከሆነ ለምን አልደሰትም »

«እርግጠኛ አይደለህም እንዴ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«በጭራሽ ጌታዬ ደስተኛ አይደሉም ። የሕመምም የሀ ዘንም ስሜት ይታይቦታል ።»

«ተሳስተሀል እኔ ደስተኛ ነኝ ። እኔ ደሀና ነኝ ፤ ደስተ ኛም ነኝ ። ስለጤንነቱና ደስታዬ ደግሞ እኔን እንኳ አያሳ ስበኝም ። አንተንም እንዲሁ መሆን አለብሀ ። ይልቅ አንድ የምትሠራልኝ ነገር አለ።ነገ ማታ ወደ አቬሊኖ ትሄ ድልኛለሀ »

«ወደ አቬሊኖ?» እያጉመተመተ ያንኑ ቃል ደገ።።

«አዎን አቬሊኖ ፤ ምን የሚያስደንቅ ነገር አለበት ። ለሲኞራ ሞንቲ ደብዳቤ ይዘሀልኝ ትሄዳለሀ ። አየሀ ቪንቼ ንዞ እስከአሁን ታማኝነትን አሳይተሽኛል ፤ አሁንም ለትእ ዛዜ መታመንን እፈልግብሀለሁ ። በትክክል እንድትረዳ ልኝ የምፈልገው ነገ ከሰርጉ በኋላ እዚህ አትፈለግም ። በሶስት ሰዓቱ ባቡር መነሳት አለብሀ ። እዚያ ሆነሀ ደብዳቤ እጽፍልሀለሁ ። ብዙ አላስጠብቅሀም ፤ በምታገኘው ጊዜ ግን ከሊላ ጋር የፍቅር ጊዜ አሳልፍ ፤ አትፍራ ፤ እንደም ምታፈቅራትም ንገራት ።»

ተጨነቀ ። «ግን ችግር እንዳለ አውቀዋል ? እርስዎ አ ርብ የሚነሱ ከሆነ እቃዎን እንኳ የሚያደራጅ የለም ። እንዴት ታዲያ ባቡር ድረስ እንኳ አልሸኞትም?»

ሳቅሁበት ።

«አንተን ደስ ካለሀ እቃውን ማምሻሀን አደራጀው ። ግን የእመቤቲቱ አገልግሎት ይበቃኛል ፤ ከእንግዲሀ



t.me/OLDBOOKSPDF

አንተ ማሰብ የለብህም ። የአቬሊኖ ጉዞህ ከዚህ ሁሉ በላይ ለኔ ብልጫ ያለው ነው ። ደግሞ የምታደርስልኝ መልእክት አለ ።»

እንዲት ትንሽ የተቆለፈች የብረት ሳጥን አዘጋጅቼ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጬ አሳየሁት ።

«ይህን ይዘህ እንድትሄድ ።»

የውስጥ ስሜቱን መቋቋም እንዳቃተው ይታየኛል ። ሥራዬን ሁሉ ፈርቷል ። ደስተኛ እንዳልሆንኩ አውቋል ። እኔም ትእግስት እያጣሁበት ሄድኩ ። በመጨረሻው ፡ «የምትነግረኝ ካለ ንገረኝ» አልኩትና ። እጄን በፍርሃት ተጭኖ ፤

«ይቅርታ ያድርጉልኝ ። ባላዩኝ ሰዓት ሁሉ እኔ አዮት ነበር ። በውስጥዎ ሀዘን አለ ፤ ደሙ ወርዶ የማያባራ ቁስል በልቦ ውስጥ አለ ። እንዲህ ያለው ሀዘን ሞትን እንደሚ ያስከትል የታወቀ ነው ። እባክዎ አብሬዎት ልቆይ ፤ ጌታዬ ይፍቀዱልኝ ። ፊትዎን ለምጄዋለሁ ። ለኚህ ትልቅ ሴት ወይዘሮም ያለዎት ፍቅር ለልቦ ደስታን አልሰጠውም ። ሰርጉን በተጠጉ ቁጥር ሀዘኖ እየከበደ ነው የሄደው ። ዛሬ ዛሬ ደግሞ ሌቱን ሙሉ ይጽፋሉ ። በመኝታ ሰዓትዎ ሁሉ ይጽፋሉ ። እና እንዲህ ልቦ በሀዘን መሰባበሩን እያየሁ ፤ እንዲህ ብቸኛ መሆንዎን እያወቅሁ እንዴት እኔ ከሊላ ጋር መደሰት እችላለሁ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደጅረት ውሀ እየተከታተለ የሚወርደውን ቃሉን ለማቆም እጄን ጨብጠው የያዙኝን እጆቹን እያላቀቅሁ» የተቆጣሁ እንዳይመስልህ» በእርጋታ መንፈስ አልኩት «ነገር ግን ከመጠን በላይ ስላሳሰብኩህ አዝናለሁ ። ለእኔ አታስብ ። ነገ የለፋሁበትን ሁሉ አገኛለሁ ። የመጨረሻው ደስታዬም ይኸው ነው ። ስለዚህ አትጠራጠር ፤ ራስህን አታስጨንቅ ። የተለመደ ቅንነትህን አትንፈገኝ ። ባልኩህ ሰዓት ሹልክ ብለህ ሲኞራ ሞንቲ ዘንድ ድረስልኝ» ብዬ ትከሻውን መታመታ አደረኩት ። «በል ይልቅ ስለሰርጌ ቀን ብለህ ፊትህ ፈገግ ይበል ። ያለዚያ ሲላን አታገኝም» አልኩት ።

«ሌላው ከአንተ የምፈልገው ደግሞ ፤ በፍጹም እንዳትከታተለኝ ነው ። መታመንና ቅንነት አስፈላጊ ናቸው ። ግን እኔ ደግሞ ከአንተ ዛሬ የምፈልገው መታዘዝን ነው ። ፍጹም ታዛዥነትህ ያስፈልገኛል ። ተኝቼ ወይም ነቅቼ ሳለሁ በግሌ መሆን አለብኝ ። አንተም የራስህን እኔም ያሻኝን መሥራት አለብኝ ። ገባህ ቪንቼንዞ?»

«አዎን ገባኝ ጌታዬ» ሲል በልቡ ውስጥ ነገር እንደተምታታ በፊቱ ላይ ፈገግታ መጣ ። «ስለድፍረቴ ይቅርታ ያድርጉልኝ» አለኝ ።

«ለምኑ ነው ይቅርታው? ከልብህ ስለወደድከኝ፤ እንደምትወደኝ አውቃለሁ።አሁን ግን እኔ ከአንተ የምፈልገው ትእዛዜን እንድትፈጽም ነው ። ትእዛዜን ደግሞ ብትበቀ


t.me/OLDBOOKSPDF

ለኝ የዘለዓለም ጓደኞሞች ነን ። ከመጠን በላይ መውደድ ደግሞ ይቅርታ የሚያስጠይቅ አይደለም ።»

«ትእዛዞን እፈጽማለሁ ።»

«ይህን የብረት ሳጥን ነው ለሲኞራ ሞንቲ የምሰጥ ?»
«አዎን በእጅዋ እንድትሰጣት ። እስከመጣ እርስዋ ዘንድ ይቀመጥ።» ፊቱ በአንድ ጊዜ ፈካ ።

«ወዲያው ሊላን አይቼ አጠግባታለሁ ።» እንደማፈር ብሎ እቃዬን ሊያደራጅ ገባ ። ራት ላይ ተቀምጩ ጠራሁ ትና የጣሊያን ምርጥ ወይን ጠጅ በሁለት ብርጭቆ ቀድቼ በአንደኛው ውስጥ እንቅልፍ የሚያመጣ ፈሳሽ ጠብ አድ ርጌ ቪንቼንዞን እንዲጠጣ ጋበዝኩት ።

እኩል እንስተን ግጥም አድርገን ጠጣን ። ራት የቀረ በበትን ገበታ እንሳስቶ ፊት ለፊት እያዛጋ እንዲጠርግ የሰ ጠሁትን ካፖርቴን ይዞ መኝታው ክፍል እንደገባ ቀረ ። የማነብ መስዬ መጽሐፍ ገልጩ ለእኩል ሰዓት ጠብቄ ክፍሉ ብገባ እንቅልፍ ይዞት ሔዶአል ። የእንቅልፍ መ ጠጡ ጭልጥ አድርጐ ወስዶታል ። ሊከተለኝ በማይችል በት አይነት በእንቅልፍ አስሬ ያን ሌሊት መፈጸም ያለበ ትን ጉዳይ ለማከናወን ማንነቴን እንዳይታወቅ ተጠማጥሜ በጭለማ ወጣሁ ። በሙታን መንደር የማዘጋጀው ስላለ አንድም ፍጡር ሳያየኝ ገሰገስኩ ። ቪንቼንዞን ያጠጣሁት ለአራት ሰዓት ያህል በተኛበት እንደሚይዘው ስለማውቅ


t.me/OLDBOOKSPDF

ድብቅ የሙታን መንደር ሥራዬን እንደጻዕረ ሞት ያለስ ጋት አከናውንኩ ። በእርግጥ ብዙ ሰዓት ፈጀብኝ ። ሥራ ዬን ስጨርስ የሙታን አጽም አጥንቴ መቅኖ ውስጥ የተ ሰካ ያህል ተሰማኝ ። በረደኝ ፤ ጥርሴን እስኪነዝረኝ አንቀ ጠቀጠኝ ። ያሰብኩት እንደምንም ተጠናቆ ተፈጸመ ። ለመጨረሻው ትራጄዲ ወይም ኮሚዲ መድረኩ ሁሉ ተዘ ጋጀ ።

ሥራዬን ጨርሼ ዝናብና ጉርፍ አልፌ ቤቴ ስገባ ቪንቼንዞ አሁንም እንደተኛ ነው ። ነቅቶ ጠብቆኝ ፊቴንና መንፈሴን ቢያይ ኖሮ በጣም ይደነግጥ ነበር ። ፊቴን እኔው ራሴ በመስታወት ብመለከተው ሰቀጠጠኝ ። አንድ ሽበቱ የተመሰቃቀለ ዓይኑ የጉድ ተከታታይ የመሰለ ጨካኝ መጻጉዕ እመስላለሁ ። ልብሴ በዝናብ ሾቅአል ፤ እጅና ጥፍሬ መቃብር ብቻውን ሲጎደፍር አድሮ የነጋበት ይመስላል ። ጫማዎቼ በጭቃ ከብደዋል ። ጠቅላላ ሁኔ ታዬ አንድ አሰቃቂ ተግባር ፈጽሜ የመጣሁ ይመስላል ።

ንጋት እየተጠጋ የሡርጌ ማለዳ እየመጣ ነው ። የተለመደ ቦታዬ ተቀምጬ ሳነብ ቪንቼንዞ እየተጨናበሰ ወጣና «እስከአሁን ድረስ ምን ጉድንድ ዋጠህ ቪንቼንዞ?» ብዬ ቀለድኩበት ።

«እኔ እኮ ወይንጠጅ አለመድኩም ፤ አልኮሉ ነው መሰለኝ እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ አለ ጌታዬ» አለ ።

ማንም ሳያየኝ ባዘጋጀሁት የድብቅ ሥራ እየተኩራ ራሁ ጥቂት እንቅላፋሁ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራስድስት

የሠርጌ ቀን ሰማይ የተነደፈ የጥጥ ባዘቶውን ደመና እያንከባለለ አረፈደ ። ሌሊቱን ሙሉ ይነፍስ የነበረው ኃይለኛ ንፋስ ግን አሁንም በውድድር እንደሚቀዝፉ መርከቦች ዳመናውን በጠራው ሰማይ ላይ ነዳው ። ከተማው በዓመት በዓል ካርኒቫል ደስተኞች ተሟሙቋል ። በዓል አክባሪው የካቴድራሉን መንገድ ይዞ ጥቂት በጥቂት እየበረከተ ጥሩውን ቦታ ተሻምቶ ሠርጌን ለመታዘብ ይቻኮላል ።በሰፊው የሚወጋለት የከበርቴ ሠርገኛ የሚዋብበትን ብርቅና ድንቅ የፋሽን ልብስ ፣ ለሠርጉ የሚመጡት እውቅ ሠርገኞች የሚመስሉትን ለማየት የጓጓው መንገደኛ የካቴድራሉን አካባቢ አጅቦታል ። የሠርጉ መፈጸሚያ አምስት ሰዓት ስለሆነ ለአራት ሩብ ጉዳይ የማሪናውን መስፍን ሚዜዬ አድርጌ ሰረገላዬ ውስጥ ገባሁና ጉዞ ጀመርን ። ለዚሁ ትልቅ ቀን ተብሎ የለበስኩት አምሮብኛል ። በብዙ ጥንቃቄ በእውቅ ሰፊ የተዋጣለትን ልብሴን ለብሻለሁ ። የጸጉርና የጺም አበጣጠሬ እዚህ ጐደለው አያሰኝም ።

ታዲያ አንዳንዴ የደስታ ስሜት በውስጤ እየጋመ የሙሽራነት ገጽታ የሚመስለውን ገፈህ ጣልና የውስጥ ማንነትክን አውጣው ይለኛል ። አንድ የሆነ ስሜት ከውስጤ እየገነፈለ እንደ ሰከረ እብድ አስካክተሀ ሳቅ ፣ አም

ባርቅ ፡ ዝፈን ፣ ሽልል ፣ እያንጉራጉርክ አቅራራ ይለኛል ። በውስጤ ይኸ ሁሉ እንዳለ ውጫዊ አፌ ደግሞ ያለማቋረጥ ያስለፈልፈኛል ። ነገሬ ሁሉ ሰም ለበስ ምጸትና አሽሙር ስለሚበዛበት ከአንድ ሁለቴ መስፍኑ ሳይቀሩ በመገረምና በመጠርጠር ዘወር ብለው አይተውኛል ። ዓሀመት በዓሉን በሳቅ በድሪያ በዘፈንና በዳንስ አለከልካይና ታዛቢ በጨዋታ ለማሳለፍ በየአደባባዩ በብዛት የወጣውን ሕዝብ እንደምንም እየተጋፋን ሰረገላዩ ካቴድራል ሲደርስ የተለያየ በርካታ ሕዝብ መምጣቴን ሲጠባበቅ በማየቴ ደነቀኝ ።

ቤትእዛዜ መሠረት በጣም ልዩ የሆነ ቀይ ምንጣፍ ከሰረገላዩ መቆሚያ ካቴድራሉ ዋና በር ድረስ ተነጥፎ አል ። መስፍኑን ከጉኔ አድርጌ ከሰረገላ ወርጄ መቅደሱ እስክገባ የተመልካቹ ዓይን እንደትንግርት ይመለከተኝና የሚሰጠው አስተያየት አልፎ አልፎ ይሰማኛል ። በተለይ እንዲት የጠፉ መልከዋን ጉልላት የመሰለው ዐይንዋ የሚመሰክርላት ዞብዞቤ አሮጊት እኔን በደንብ ለማየት ግፊያውን ዋሳ ከወጣች በኋላ «ይችን የተነገረለት ሀብታም እዩት ! ሀብቱን ያጠራቀመው እንዲት ገንዘብ እንደመኮሮኒ የሚውጥ ደማም አፍ ያላትን፤ያውም በድሆች ጭንቀት የምትሰቀዋን ክፉ ሴት ሚሽት ለማድረግ ነው ። ለጉድ ነው ! ክብረቱ ሁሉ የአንዲት ሴት አፍ ለመሙላት! ይኸ መጥፎ ነው አለች ።»

መስፍኑ እነኝህን ቃላት ሲሰሙ ወደእኔ ዞር ብለው ሲመለከቱኝ እኔ እንዳልሰማ ሰው ጸጥ አልኩአቸው ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

መቅደስ ውስጥ ብዙ እንግዶች ቢኖሩም እኔ የጠራኋቸው ከሀያ ወይም ከሰላሳ አይበልጡም ። ለአብዛኞቹ ሰላምታዬን ስለሰጠኋቸው እነርሱም «እንኳን ደስ ያለህ» ብለውኛል ። በዙሪያዬ ያሉት አስደናቂ ሰዎች የሚደነቅ ሕይወት ያላቸው መስለው ታዩኝ ፤ አብዛኛዎቹ ፤

«እና እቅድህን በተግባር ለመተርጐም ቆርጠሀል ማለት ነዋ! በቃ ምንም የምህረት ስሜት የለህም ማለት ነዋ» የሚሉኝ ይመስለኛል ።

አልፈራኋቸውም ። በፈለጋችሁት እሳት ጥበሱኝ እንጂ አሁን በሕይወቴ እያለሁ በቀሌን መወጣት አለብኝ የሚል እልህ አደረብኝ ።

በችንካሩ ላይ የሚደማውን የክርስቶስ ስዕል አይቼ «አላፊ ፍላጐትህን የምትከተል አንተ ስህተተኛ ሰው ያንተን መጨረሻ የሚደመድመው ማነው?» የሚል ጥያቄ ያቀረበልኝ መሰለኝ ።

«ማንም ይሁን ማን ፣ ሰማይ ቢሰነጠቅ ፣ ምድር ቢከፈት ስህተተኛዋን ሴት ሳልቀጣ ፣ ፍርድ ሳላርም አላልፍም ።» ብዬ መለስኩለት ።

የሀሳብ ውድቀት መንፈሴን ይዞ አደበተው ። የፀሃይዋ ጨረር በልዩ ልዩ ቀለም ያማረውን የመስኮት መስታወት ሲመታው ሰማያዊ ፣ ወርቅማ ሀምራዊ ወይን ጠጅማ


t.me/OLDBOOKSPDF

ብሩህ ቀለማት ሁሉ ቅርጽና ማማርን እየጨመሩ የጸሎት ቤቱ
ን አደመቁት ። ከዚያ ዝግ ያለ ግርማ ሞገስ ያለው የሙዚቃ
ድምጽ እንደፏፏቴ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የእጣን ጪስ
ያጀበውን አየር ስርጎ ቀሰቀሰው ።

ያለፈው ሰርጌ ትዝ አለኝ ። ጉዶ ፈራሪ ከጐኔ ቁሞ ፥
በዚሁ ቦታና ሥፍራ ልቤ በተስፋ አድጎ ፍቅርና ደሲታ
አስከሮኝ ትዝ አለኝ ። ጓደኛዬ በሚሸቴ ውበት የመጀመሪ
ያውን የመርዝ ዋንጫ ሲጨልጥ ታየኝ ። እኔ ተላላው ግን
እነኝያ ሁለት ወዳጆቼ እንደዚህ ይከዱኛል የሚል ህልምም
አልነበረኝ ። የጋብቻውን ቀለበት ከኪሴ አውጥቼ አየት አደ
ረግሁት ፤ አዲስ መስሎ ተብረቅርቋል ። በወርቅ ሥራ ጥበብ
ተቀባባ እንጂ ያው የዱሮው አሮጌው ነው ።

አምስት ሰዓት ሆኖ ደወሉ ሲያምም በሮቹ በሰፊው
ተከፈቱና ዞርብዬ ሳይ የሚጉተት ቫዋል የለበሰችው ንግ
ሥት መሳይ ሙሽራዋ ባለቤቴ በክብር ታጅባ ስትገባ
አየሁ ። ሠርጌን ለመመስከር ወይም ለማስተዋል የመጣው
ሁሉ አድናቆቱን በይፋ ሲያንሾካሹክ ሰማሁት ። የለበሰ
ችው ቀሚስ ነጭ ከፋይ ሲሆን ፤ ከራስ ጸጉር እስከ እግር
ጥፍርም ፣ምርጥ ዓይነርግብ ተላብሳለች ። የሰጠኋት አልማዝ
በላይዋ ላይ እየተፍለቀለቀ የልዩ ልዩ ቀለመ ብርሀን ምንጭ
አስመስሏታል ። ጸጉርዋ ውስጥ አልማዝ ፥ ወገብዋ ላይ
አልማዝ ፤ ጡትዋና ያልተሸፈኑ ክንድዋ አልማዝ በአልማዝ
ሆናአል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከልቧም ባይሆን ባል የሞተባት በመሆንዋ አጃቢ ሚዜዎች የሉዋትም ። ተገሎታች ሻልዋን ቁንን ብሎ የሚ ጐትተው አንድ ወንድ ልጅ ነው ። ሁለት የአምስትና የስ ድስት ዓመት ሕጻናት ፊት ፊትዋ እየሄዱ የንግሥት አጃ ቢዎች መስለው የነጭ ጽጌረዳ ፍርፍር ይነሰንሳሉ ። የሕጻናቱ ውበት ከሕልም አለም አምልጠው የወጡ ሕፃን መላእክት ይመስላሉ ። ሻዋል ደጋፊው ሥራዎቻቸውን ያለስህተት በትክክል ስለሚፈጽሙ ነገሩን ሁሉ ሆን ተብለው በሙሽሪትዋ መሰልጠናቸው ያስታውቃል ።

የጋብቻው ሥርዓት ተጀመረ ። ለጸሎት ተንበረከክን ። ቀለበቱ መጽሐፉ ላይ ተደረገ ። ሙሽሪትን ዞር ብዬ ሳይ በአልማዝ የቀበጠ ራስዋ ወደፊት ተዘንብሎ በጸሎት የተ ጠመደች ትመስላለች ። ቄሱ ጠበሉን ረጩት ። ቀለበቱን አንስቼ ለሁለተኛ ጊዜ ጣትዋ ላይ አጠለቅሁላትና እዱሮ ቦታው ተውኩት ። አሮጌው ቀለበትዋ መሆኑን አስታው ሳው ይሆን? ያስታወሰችው አትመስልም ። እንዲያውም ይበልጥ ቀለበቱ ሲደረግላት ረከታለች ። በውበት ላይ ውበት ጨምራለች ። በዚሁ የጋብቻው ዋናው ሥነ ሥርዓት ተፈጸመና ቀጥሎ ቅዱስ ቁርባን ተሰጠን ። ሚሽቴ መልአክ መስላ ያለጥርጣሬ ተቀበለች ። አፍዋን ስትከፍት ከውበትዋ የተነሳ የሚያቀብለው ቄስ ራሱ ሳይማረክላት አልቀረም ።

ይህን ሰዎች የሚያከብሩትን ቅዱስ ቁርባን በማዋረዳ ችን ምንድነው ቅጣታችን ብዬ ራሴን ጠየቅሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«እኔ ብነድ ብቃጠል ፣ እርስዋ ደግሞ የኔን ሶስት እጥፍ መንደድ መቃጠል ይገባታል ። ሁለታችንንም በደንብ አራርቆ ሊይዝ የሚችል ገሀነም መኖር አለበት ።»

እና በዚህ ዓይነት ሕሊናዬን ስጠጋግን ዓይኔ በግደግዳው ላይ ተደርድረው በሀዘን በምሬትና በሕመም የሚመለከቱንን ሥዕሎች አይቼ ትኩረታቸው ሁሉ ወደ እድናቆት የተለወጠ መሰለኝና እየገረመኝ እኔን የመሰለ ሰው እርስዋን የመሰለች ሴት በግንባራችን ተደፍተን መሞት ሲገባን ፈጣሪ ፊት ቀርበን በጥፋታችን ከመቅጽበት አለመቀሰፋችን ይገርመኛል ።

ቅዱሳን ሰማእታት በኛ ተግባር ልትደነቁ ይገባችኋል ። እናንት በኛ ሰዓት ብትኖሩ ኖሮ በዘመናችሁ ከገጠማችሁ እፈላ ዘይት ገብቶ መጠበስ ሺ ጊዜ የባሰ እሟሟት ትሞቱ ነበር ። በናንተ የደረሰው ሲጋን ብቻ የሚቆራርጥ የአጭር ጊዜ ስቃይ ሲሆን ነፍሳችሁ ከነኃይሉ ከነፍቅርና እምነቱ ፣ ከነተስፋና ደግነቱ ጋር እንደተከበረላችሁ ነበር ። ዛሬ ነገሩን ሁሉ የተገላቢጦሽ አድርገነዋል ። አዲስ ዓይነት ትምህርት ተምረናል ። ሲጋችንን በልብስ በምግብና ምቾት ጠብቀናል ፣ ነፍሳችንን ግን ለእሳት ፣ ለስቃይ ፣ ለጥፋትና መከራ ዳርገናል ።

እኔ በልዩ ልዩ የውስጥ እሳቱ ስነድ ስቃጠል ፣ ስለግን ስንጨረጨር ለካ የጋብቻው ሥነ ሥርዓት አልቆ ኖሮአል ። በሚሸቱ ድብቅ ጉሽሚያ ተቀስቅሼ ስነቃ ሁሉ ነገር ተፈ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጽሞ ሚሽቴ የራሴው ሆናለች ። በጥንድ ሠርግና ሙሽርና የግሌ ሆነች ። ሞት እስኪለየን የሚለው እነጋገር ልቤን ነካው ። ከናዴን ለሚሽቴ አቅንቼ እቅፍ ድግፍ አድርጌ መውጣት ጀመርን ። ሞት እስኪለየን ጊዜው በጣም ረዘመብኝ ። ስለዚህ በሕይወታችንና በሞታችን መካከል ያለውን ጊዜ በሰዓት እየለካሁ መቁጠር ጀመርኩ ። ሰዓትና ደቂቃውን በመልክ በመልኩ እየለየሁ ሸለግሁት ። ይህን ሁሉ የአሳብ ስሌት ስሸልግ አፌ እየተጉመተመተ አንዳንዱ ቃል እያመለጠኝ ለሌሎች በደንብ ይሰማል ። በግራና ቀኝ እኛን ለማድነቅ የተሰለፈው ሕዝብ ውቢቱን ሙሽራዬን ደግፌ ስወጣ ፈገግታዬን ማየት ስላለበት አጀቡን እስካልፍ ጥንቃቄ አደረግሁ ። የካቴድራሉን ዋና በር ስናልፍ ብዙ ልጃገረዶች በቅርጫት ፍርፍር አበባ በተኑልን ። ሰረገላ ስንቃረብ አንዲት ቤት ልጅ ቀይ የጽጌረዳ አበባ መንገዳችን ላይ ወረወረችልንና ሰይጣኔን አመጣችው ። የሰማይ የምድር ቁጣ የተጫነኝ ይመስል ያንን ቀይ ጽጌረዳ ሆን ብዬ በእግሬ እየደመጠጥኩ ሚሽቴ ሽምቅቅ ብላ ቀናብላ እስክታየኝ እንዳልነበር አደረኩት ። ዙሪያችን ያለው ተመልካች በድንጋጤ ተጓሸመ ። አበባውን የወረወረችው ልጅ ሁኔታዬ ዘግንኖአት ራስዋን አማትባ ቦታውን ጥላ ወደኋላ ፈረጠጠች ። መሳሳቱ ገባኝ ። የውስጥ ብሽቀቴን መቆጣጠር አቅቶኝ ደካማነቴን ሰው እንዲታዘብ በማድረጌ አዘንኩ ። የኒናን ድንጋጤ ለማስከን ፤

«ምንም አይደለም፣ የግል ጥላቻ ስሜት አለብኝ ። ቀይ ጽጌረዳ አልወድም በአበባ መልክ የቀረበ የሰው ደም


t.me/OLDBOOKSPDF

መስሎ ይታየኛል ።»ሰደቻ መታት ።

«ምን ዓይነት አሸባሪ ሀሳብ ነው ፣ እንዴት እንዲህ የለውን ነገር ታስባለህ» ?

ጭጭ ብዬ በጥንቃቄና አክብሮት ሰረገላ አስገባኋት ። ከዚያ እኔም ገባሁና ወደ ሆቴላችን ተጉዘን ለቁርስ ግብዣ ተዘጋጀን ።

እዚህ ላይ ደስ አለኝ ። ከእንግዲህ እንኳን ደስ ያላችሁ እንባላለን ። የኔፕልስ ታዋቂ ሰዎች በግብዣችን ተገኝ ተዋል ። ግብዣው ግን እምብዛም የተሟሟቀ አይደለም ። ሴቶቹ የሚሽቴን ጌጣጌጥ አይተው ያኮረፉም ይመስላል ። ይህን ሁሉ ሀብት ይዞ ጌታ አሊሻ ወንድላጤ ሆኖ ቢቀር ምንኛ ባማረበት የሚሉም ይመስላል ።

የቁርስ ግብዣውም አብቅቶ ከክብር ቦታችን ስን ነሳ የቀረኝ አንድ ጣጣ የዳንስ ምሽት ግብዣው ብቻ ነው ። ሚሽቴን ማረፊያ ክፍልዋ ድረስ ሸኝቼ ለማታው ግብዣና ለምንጓዝበት ለማግስቱ ጉዞ እንድትዘጋጅ ጊዜዋን ሁሉ ሰጥቼ ልተዋት ተቃረብሁ ።

ከእንግዲህ የምንገናኘው ከማታው ሶስት ሰዓት በሚ ደረገው የዳንስ ምሽት ነው ። የበዓሉም ዋናው እፍታ የሚ ቀመስበትና ለሙሽሮቹ የመልካም ምኞት መግለጫ የሚደ ረግበት ምሽት ይኸው ነው። ጊዜውም ፍጹም የደስታ የሙዚ ቃና ንጉሣዊ ኧመንኧ የሚካሄድበት ይሆናል ። እና በታላቅ ሥነ ሥርዓት ባለቤቴን በተለይ ለእርስዋ ወደ ተዘጋጀው



t.me/OLDBOOKSPDF

ክፍል መራኋት ። በምታገኘው ጥቂት የፋታ ጊዜ ብዙ የምትሠራው እንዳለ አስቀድማ ነግራኛለች ። ይኸን የተደራረበ ከባድ የሥርግ ልብስ አውልቃ እረፍት ማድረግም አለባት ። ለማታው የዳንስ ምሽት የምትፈልጋቸውን ሁሉ አስቀድማ ማዘጋጀት አለባት ። ለፓሪስና ለሮም የሚጉላ ጉዞ የሚያስፈልጋትንም ከደንገጡርዋ ጋር ሻንጣ ማደራጀት አለባት ። ለዚህ ሁሉ በታላቅ አክብሮት እጅዋን ስሜ እንድታርፍና እንድትዝናና ተለየኋት ። የዳንሱ ማግስት የሚሉት ነገር ገርሞኝ አሳቀኝ ። በፓሪስ ጉዞዋ እንዴት እንደምትደሰት ታየኝ ። እና እንደማንኛውም የኔ መደብና ደረጃ ወንዶች ሁለት ጊዜ ላገባኋት ሚሽቴ ነጻ ጊዜዋንና ነጻነትዋን ሰጠኋት ። በሕይወትዋ ወርቅና የምትደሰትበትን የመጨረሻ ነጻ ግላዊ ጊዜዋን ሰጥቼ ተውኳት ። የማታ ልብስዋን ፣ ጌጥዋን ጌጣጌጥዋን ፣ ሌሎችን ሴቶች የምታስቀናበትን ፣ ብዙ ሴቶች ሰላምና ክብራቸውን፣እምነትና መብታቸውን፣ነፍሳቸውን ሳይቀር የሚለውጡበትን ጌጣጌጥ እንድታዘጋጅ ተውኳት ።

እኔም ረጋ ብዬ እየተዝናናሁ በሆቴሉ ሰፊ ሳሎን ፒፓዬን አቀጣጥዬ ከተማዋን በረጅሙ ማየት ጀመርኩ ። ሕዝቡ አሁንም ጭፈራውን በሰፊው ተያይዞታል ። በቀላሉ ደስታን ገብይቶ መኖር የሚያቅበት የሀገሬ ሰው ልማድ ገረመኝ ። ሰንደቅ ዓላማው ይውለበለባል ፣ ጥሩምባው ይነፋል ፣ አታሞው ይደለቃል ፣ ሁሉም የሚያስጮኸው እንዲሰማለት ፣ የሚያደርገው እንዲታይለት መሬት ለቆ ይወሰጣል ። ግማሹ እየተከራከረ እጁ እስኪነድ እየተጨ



t.me/OLDBOOKSPDF

በጨብ ይወራረዳል ። አበባ ሻጮች ፣ ለስላሳ መጠጥ ሻጮች አለ አበባ አለ ለስላሳ እያሉ አየሩን በጩኸታቸው ያዋክቡታል ። ጐረምሶች በሚያማምሩ አበቦች እያባበሉ ጉች ጉች ያለ ጡት ያላቸውን የገጠር ቆቶች ያሽኮረምሟሉ ። አውቆ አበዱ ሳይቀር ይደንሳል ፣ ውሻው ይጮሀል ፣ ከሩቅ የቤተ ክርስቲያን ደወል ይሰማል ። በዚሁ ሁሉ መሀል ደግሞ ሶልዲ እያንቃጨሉ ፣ መከራ እያፏጩ ደባደቦአቸውን ዘርግተው ደረታቸውን ገልጥጠው ይለምናሉ ።

ትእይንቱ ሰልችቶኝ ወደክፍሌ ለመሄድ ዞር ስል ሁካታው ባንዴ ጋብ ብሎ ሬሳ ታጅቦ ሲሄድ አየሁ ። ያን እንቶፈንቶ ዓለማዊ ቁቁታ ሬሳው መሀል ለመሀል እየከፈለ ሲያልፍ በአንድ ጊዜ ጸጥ ለማድረግ መቻሉ ግርም አለኝ ። የሬሳው እግር ከመሀል ሾልኮ ሲያልፍ ደግሞ ያው ዓለማዊ ሁካታ እንደገና ነፍስ ሲዘራ እንደሞኝ ቆሜ የምቱት ፈጥ ነው መረሳታቸው ገረመኝ ። የማያቋርጥ የሀሳብ ሰንሰለት በአእምሮዬ ውስጥ እየተቅጨለጨለ በመጨረሻው ወደ ክፍሌ ገባሁ ። ቪንቼንዞ አሁን ወደ አቬሊኖ ለመሄድ ፍላጐቱም ስለገፋፋው ይዞት የሚገዘውን ለማስረከብ ጠራሁት ። በወርቅና በኖታ አሥራ ሁለት ሺ ፍራንክ የሚገመት ሀብት የያዘውን የብረት ሳጥን አስረከብኩት ። በመጨረሻው በጐ ሥራዬ ልቤ ሳይደሰት አልቀረም ። ይህ ገንዘብ ቪንቼንዞን በአቬሊኖ ጥሩ ገበሬ አድርጐ ሊያቋቁመው ይችላል ። አንድ የታሸገ ደብዳቤ ደግሞ ለሲኞራ ሞንቲ እንዲያደርስልኝ ሰጠሁትና ደብዳቤው ከደረሳት ጊዜ ጀምሮ አንድ ሳምንት ድረስ እንዳትከፍተው እንዲነግርልኝ አጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብቄ አስጠነቀኩት ። በደብዳቤው ላይ የተጻፈው በብረቱ ሳጥን ውስጥ ስላለው ገንዘብ ዝርዝር መግለጫ ሲሆን በተጨማሪም ደገኛዋ ሲኖራ ሞንቲ የጌታ ሮማኒ ግቢ ካለ ችው ከአንጋፋዋ ሞግዚት ጋር በመገናኘት የአልጋ ቁራኛ የሆነው ጂያኮሞ ረጅም ሕይወት ስለሌለው ነፍሱ እስኪወ ጣ ድረስ እሱን እንድታስታምመው እንድትተባበራት የሚጠይቅ ነው ።

እና ከአሁኑ የሁኔታዎችን መድረሻ ባሰብ ልቤ በደ ሲታ ረካ ። ያቺ ውብ ተራራማ የንሞንቲ መንደር ቪንቼን ዞና ሊላ ትዳር በሰላምና ፍስሀን ተጐናጽፋ ሲኖራ ሞንቲና እሱንታ ደግሞ ተገናኝተው በመደጋገፍ ያለፈ ሕይወታ ቸውን እያሰቡ የነሊሳን ልጆች እየሳሙ ሲኖሩ ታየኝ ። ለጥቂት ጊዜ የኔን መሰወር በሀዘን እያሰሉ ግራ ይጋቡ ይሆናል ። ቀስበቀስ ግን እኔው ራሴ መዘንጋትን እንደምፈ ልግ ሁሉ እኝርሱም እርግፍ አድርገው ይዘነጉኛል ።

አዎን እኔም በበኩሌ በጉ ለዋሉልኝ የተቻለኝን ያህል በጉ ሥራ ሠርቼላችዋለሁ ። ቪንቼንዞ የዋለልኝን የትህትናና የታዛዥነት ውለታ ለመክፈል ሞክሬአለሁ፡፡ ሌላው ዕዳው ገብስ ነው ። ከእንግዲህ የቀረኝ ያው ነው ። የበቀል ጥሪዬ ይጮሀል ፣ ቀን ከሌት ከወር እስከወር ለብዙ ወሮች ደረጃ በደረጃ አስፈሪ ጣቱን እንደጻዕረሞት ቀስር መከራ!መስሎ ሲጠቅሰኝ ሰንብቷል ። አሁን ግን ጋብ ብሎአል ። ከፊት ለፊቴ ተጋርጦ በነፍሴ ላይ የበቀለኛ ደም የለበሰ ዐይኑን በኔ ላይ ተክሎ ውጋ! ምታ! ግደል ይለኛል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራሰባት

የማታ ማታ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የዳንስ ምሽት ምንሽንሽ ብሎ ተጀመረ ። እንደቤተ መንግሥት ግብር ቤት በሺ ሻማ የግብዣው ክፍሎች አምረው ደምቀዋል ። በመላው ኢጣሊያ የታወቁ መኮንኖች ደረታቸውን በኒሻን አንቆጥቁጠው ተደርድረዋል ። በልዩ ልዩ ጌጥ ያሸበረቁ ውብ ወይዛዝርት በሕልም ውስጥ እንደሚታይ የውበት ሀገር ጌጥ በዚያ እንደመስታወት በሚያንጸባርቅ ወለል ላይ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ታይተው የሚጠገቡ አይመስሉም ።

የቆንጆች ቆንጆ የኮከቦች ሁሉ ኮከብ ሆና ያመሸችው የኔዋ ምሽት ናት ። እንከን በሌለው ውበት ፣ ተወዳዳሪ በሌለው ማራኪነት አልማዝ ለብሳ ፣ አልማዝ መስላ ስት ታይ እኔ ራሴ ስሜቴን መቋቋም አቅቶኝ በውበትዋ ጥሪ ልቤ በኃይል መታ ፤ ለዐይን እንደሚያጥበረብር ብርሃን ፈገግታዋ ንና የውበትዋን ግርማ አይቼ አስተውሎ መጥገብ እቃተው እንደማለዳው ጤዛ ጠብታ ፣ እንደ ልጆች ተረት የውበት ንግ ሥት ሚሽቴ እንደዛሬ ተውባ አታውቅም እስከል ድረስ በቁ ንጅናዋ ተማረኩ ። ቀሚስዋ ላይ የሚንቦገቦገው የአልማዝና የእንቁ ፈርጥ አንገትዋ ላይ ያሰረችው ውድ ጌጥ በጆሮዎችዋ ላይ የሚንተገተጉት እንጥልጥሎች በሙሉ የነፍስ ገዳዩ ሀብት ናችው ። ጸጉርዋ ላይ ያሰረችው የአልማዝ ጌጥግን እናቴ በሕ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይወት ዘመን ታጊጥበት የነበረው የቤተሰቡ ማስታወሻ
ነው ። ይህን ሁሉ አልማዝና እንቁ የሚፈነጥቀውን የብርሀን
ጸዳል የሚያስንቀው ግን ከግንባርዋ በታች የሚፍለቀለ
ቀው የዐይንዋ ግርማ ነው ። ስለተጠሩት ወይዛዝርት አለባ
በስ የሚገርመው ደረጃችንን ለመመጠን አብዛኞቹ ከአ
ንገታቸው ጀምሮ ቀሚሳቸው ሁሉ በተውሶ አልማዝ ተጠ
ልፎ የተጊጠ ነበር።ስለዚህ ዙሪያዬ ያለው ሁሉ እንደ እሳት
ያበራል።ብርና ወርቅ ይንቦገቦጋል ፣ የከበረ እንቁ ከብርሀኑ
ጋር ይንቀለቀላል ፣ ፍጹም ጣፋጭ መዓዛ ያለው ሽቶ በየበ
ኩሉ ይጣራል ። ከሕይወት ዘመኔ ሁሉ በደረጃው እጅግ
በጣም ከፍተኛ የሆነው የዚያን ዕለት ምሽት ትግዘታ በአን
ጉሌ ተጠራቅሞ ዛሬ የሚሰጠኝ ውጤት የተደበላለቀ ነው ።
አዎን ፣እስከሞት ድረስ ያ ሌሊት ሆደባሻ ያደርገኛል ፣ ከ
ሞቴ በኋላ ደግሞ ማን ያውቃል ፣ መጨረሻ በሌለው ብቀላ
ነፍሴን የማጥፋት ዘመቻዬን ለመበቀል ይሟገተኝ ይሆናል ።
ሚሽቴ በለሰለሰ እንደበትዋ «ጌታዬ መደነስ አለብህ እኮ ፣
ሥራህን እየዘነጋህ ነው ፣ የዳንሱን ምሽት መክፈት አለ
ብህ» ስትለኝ ከው ብዬ የደነገጥኩት ድንጋጤ እስከ
አሁን ያንቀጠቅጠኛል ።

የማስነሻ ቁልፉ እንደተነካ መኪና ብድግ አልኩ ።

«የምን ዳንስ ነው ደግሞ?» ብዬ እንደመቀለድ
ሳቅሁና» እኔ እኮ ጥሩ ዳንሰኛ ጓደኛ የምሆንሽ አይመስለ
ኝም ።» አልኳት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ዋ! አደራ ሀን እንዳታሳፍረኝ ብቻ» አለችኝ ። «ይህን የመጀመሪያውን ዳንስ ብቻ ያለስህተት መደነስ አለብህ ፣ እዚህ ላይ ስህተት ከቃዋ አጉል ነው ።» ሙዚቃው ጀመረ የወገብዋን ዙሪያ በእጄ ይገፎ ተዘጋጀሁ ። በፍቅር ዋና በጥላቻዋ መሀል መገዝገዙ ብዙ ስላሰቃየኝ በተቻለኝ መጠን ፊትዋን ላለማየት ሙከራ አደረግሁ ። እክብሮት የሌለው ርኩስ ዓይነት ፍቅር በልቤ አድሮ ጭፍን የሆነ የቁጣ ስሜት አስከተለብኝ ። ተነስተህ ከዚያ ሁሉ ጓደኛና አድናቂ ሕዝብ መሀል ጉድዋን ለፍልፍና አጋልጠህ በውርደት አመድና ትቢያ አልብሳት የሚል ግፊት መጣ ብኝ ። ያን ብፈጽም ግን በዚያ እውቅ ምርጥ መኳንንትና ወ ይዛዝርት መሀል እኔ እብድ እርስዋ ጤነኛና ትክክለኛ የሚል ግምት እንደሚሰጠን አወቅሁ ።

እንደለስላሳ የባሕር ነፋስ በሀንጋሪ ቫልስ ሙዚቃ ስልት ወገብዋን ይገፎ በአዳራሹ ተናኘሁ ። አረግመዴ ከኒና ጋር ሰምና ወርቅ ሆና በደስታ ረክታ ሚሽቴ በምስ ጋና ዓይነት ቀና ብላ እስክታየኝ ድረስ የዳንስ ችሎታዬን አስመሰከርኩ ። አዳራሹን ሁለትና ሶስት ጊዜ ዞረን እስክ ንመለስ ድረስ ተጋባዥ ዐይኑን ከእኛ ላይ መንቀል አትቶት በተመስጦ ይመለከተን ነበር ።

ከዚያ በኋላ የኛን ጅምር በመከተል ወለሉ በሰው ጢም እስኪል ድረስ ሁሉም በጡድን በጡድን የጓር አበባ መስሉ በዳንስ ሙዚቃው ስልት ይወዛወዝ ጀመር ። የሚ ሽቴ ትንፋሽ እየሞቀኝ ትኩሳትዋ ትኩሳቴን እያጋለው ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

የሥራ አከላቴ በልዩ ንዝረት ሲንቀሳቀስ ሚሽቴን ወደ ደረቴ ልጥፍ አድርጌ ትንፋሼንም አሳቤንም መቆጣጠር አቃተኝ ።

እነኝያን ለተንኮል የተፈጠሩ ከንፈሮችዋን ገለጥ አድ ርጋ ፤
«በመጨረሻው አፈቀርከኝ አይደል?» አለችኝ ።

«በመጨረሻው እንዴት አልሽኝ ? ከመጀመሪያው ጀምሬ ባልወድሽ ኖሮ የዛሬው መጨረሻ እንዲህ ያምር ነበር?» አልኳት ። ትንሽ ሳቅ አለችና «ቀዝቀዝ ለማለትስ ሞክረህ ነበር ፤ እኔ ግን እንድታፈቅረኝ እንደማደርግህ አውቅ ነበር ። ከእንግዲህ ለፍቅሬ እንደምትሞትል ኝ እርግጠኛ ነኝ» አለችኝ ።

እጅግ በጣም ተጠጋኋትና «አሁንም ሞቼልሻለሁ ፥ አሮጌውን እኔነቴን ላንቺ ስል ገድዬዋለሁ» ።አልኳት

የድምጽዋን ልስላሴ በዓለም ተወዳዳሪ እንደሌለው አጣፍጣ «ፍቅሬ እባክህ የአሁኑ አነጋገርህ ሚስጢሩ ምን ድነው?» አለችኝ ።

«ለውጠሽኛል ፥ አድሰሽኛል ማለቴ ነው ፍቅሬ» አልኳት ። በጆሮዋ እያንሾካሾኩ «ሽማግሌ መስዬ ነበር ፣ ዛሬ ሌሊት ላንቺ ስል ወጣት እሆናለሁ ። የቀዘቀዘው ደሜ ዛሬ ላንቺ ሲል እንደእሳተገሞራ ግንፋይ ይግላል ። ያለፈው



t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣትነቴ እንደገና ይተኩሳል ። ማንም ሴት ፍቅረኛ ጥሞ አት በማያውቅ ዓይነት ዛሬ ሴሲት በፍቅሬ ትረኪያለሽ ።»

ነገሬን አድምጣ ተጠመጠመችብኝ ። ቃሎቼ አረኩዋት ። ከሀብት ቀጥላ የምትወደው የወንዶችን ስሜት መቀስቀስ ስለሆነ ጥምዋን አረካች ። መጀመሪያ ወጥመድዋ ውስጥ ታስገባለች ፤ ቀጥላ በምርኮዋ ደስታን ሽምታ በመጨረሻው በፍቅር ትነክሰዋለች ። ንክሸዋ ግን በሞት ይቀሰፋል ። በዚህ ሥራ እርስዋ የተለየ ችሎታ አላት ።

ሙዚቃው እንደመቀዝቀዝ ሲል ሚሽቴን እየመራሁ ከአንድ የሮማ ልውል ጋር አቆራኝቼ እኔ ቪንቼንዞ መሄዱን ለማየት ከአዳራሹ ሹልከ ብዬ ወጣሁ። ቪንቼንዞ ሄዶአል። አንድ የሆቴሉ ሠራተኛ የሆነ ጓደኛው በባቡር አሳፍሮት ተመልሶአል ። ከኗና ጋር ለመደነስ ስዘገጃጅ በመስኮት አይቶኝ በዐይኑ ሙሉ እንባው እየፈሰሰ ለመሰነባበት እንኳ ድፍረት አጥቶ መሳፈሩን የሸኘው ሠራተኛ ነገረኝ ። ለነገሩ ቀዝቅዝኔ በጥሞና አዳመጥኩ ፤ በውስጤ ግን የሚያንቀጠቅጥ ዓይነት ብቸኝነት ተሰማኝ ። ታማኝና ትሁት ሠራተኛዬ አጠገቤ እስካለ ድረስ የጓደኝነት ከለላ ይሰማኝ ነበር ። አሁን ግን የተጋረጠኝ ብቸኝነት እንደድንጋይ ከበደኝ ። ከሰው ልጅ ሁሉ ተነጥዬ መቆሜ ተሰማኝ ። እርስዋ እኔ እና አምላክ ብቻ በዚህ ዓለም ያለን መሰለኝ። በነኝህ ሶስቱ መሀል ፍርድ መጧላት አለበ ት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ግንባሬን ደፍቼ ወደዳንሱ አዳራሽ ስመለስ እበሩ ላይ አንዲት ወጣት ልጅ አጋጠመችኝ ። ወተት የመሰለ ነጭ ለብሳ የጸጉርዋን ጌጥ ራስዋ ላይ ፈንጥቃ ፊትዋ በፈገግታ ግሞ ጉንጭዋ ላይ ስርጎጥ እንጥቦ እየኋት ። በጥቢ ወራት ጥቅምት ላይ የምትፈነዳውን የመስከ አበባ ትመስላለች ። በዓይናፋር ዓይን በሕጻን ልጅ ንጹህ ሀቅ ፤ «እንዴት ነው ደስ የሚለው ? በሕልም ዓለም ያለሁ ነው የሚመስለኝ ። ለኔ ይህ የመጀመሪያዬ የዳንስ ምሽት መሆኑን ያውቃሉ» አለችኝ ።

ፈገግታ እያሳየሁ ፤ «እውነትሽን ነው ? ተደስተሻላ ?»

«ደስታ ብቻ ነው ፤ ፈንጥዣለሁ እንጂ ። ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ እስከዛሬ ማታ ድረስ ቆንጆ መሆኔን አላውቅም ነበር ።»

ፊቴ ኮስተር ብሎ ትኩር ብዬ እያየሁ «እና የሆነ ሰው ዛሬ ነገረሽ ማለት ነዋ?»

እንደማፈር አለችና ፤

«ትልቋ የማጃናው ልዑል ውሸት በማይናገር ደረጃው እያቆላመጠኝ እጅግ የተዋብኩ መሆኔን ነገረኝ ።» አለች ።

ደረትዋን ያጌጠችበትን አበባ ነካ አድርጌ «እነኝህ አበቦችሽ እንዴት በአዳራሹ ሙቀት መጠውለግ እንደ ጀመሩ አየሽ ? እነበሩበት የአበባ ተክል ተመልሰው እየተ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወዛወዙ ንጹሁን አየር ቢቀምሱ እንደሚደሰቱ ገምቺ። ትልቅ ልዑል የምትይው እነኝህን አበቦች ውብ ናችሁ ቢላ ቸው እንደገና የሚለመልሙ ይመስልሻል ? እና ያንቺንም ሕይወት መግሣና ውዳሴ እንደነኝህ አበቦች ያጠወልጋችኋል እንጂ አያለመልማቸውም።በውበት ከሆነ ከአንቺና ከእርስዎ ማንኛችሁ ትዋባላችሁ?» አልኳት ወደሚሽቴ በጨረፍታ እየጠቆምኩ ።

ትኩር ብላ በቅናት ዓይነት ካየቻት በኋላ ፣

«አይ ብቻ እርስዎ የለበሰችውን ዓይነት ልብስ ብለብስ፣ በአልማዝ ጌጥዋ ባጌጥ እንደርስዎው መዋብ አያቅተኝም ።»

በምሬትና በመሰልቸት ተስፋ መቁረጥ ተሰማኝ ። ይችም አዲስ አበባ ገና ብቅ ሳትል በመርዙ መለከፍዋ ገባኝ ። «አንቺ እቤትሽ ግቢና እንደርስዋ እንዳትሆኚ ተንበርክከሽ ለፈጣሪሽ አልቅሺ ። » አልኳት።ፍጥጥ ብላ ስታየኝ አይኔም ሆነ ፊቴን ከአይንዋ ሳልነቅል ፣ አንቺ ወጣት ነሽ የእናት የአባትሽ አምላክ ገና ስላልተለየሽ የነ ጥብ ያህል እንኳን እርስዋን እንዳትመስይ በእርስዋ የሚደ ርሰው መጨረሻ የሌለው መከራ እንዳይደርስብሽ ተማ ጸኝ ።» መኳኩባት ።

የልጅትዋ ዐይን በፍርሀት ስለተቅበዘበዘ ተሙት አደረ ግኋትና ትኩር ብዬ እያየኋት ፤


t.me/OLDBOOKSPDF

«ያቺ ሴት የኔ ሚሽት መሆንዋን አልነገርኩሽም ። የነገርኩሽ ታሪክ ግን የሌላ ሴት ነው ። ሥራ ሲበዛ እእምሮዬ የማስበውንና የምጠቁመውን እያተረማመሰ ያሳስታል ። በድንገተኛ አስተያየቴ ሳትረበሺ ጫወታሽን ቀጥይ ልጀ ። የማጀናው ልዑል የሚናገረውን ሁሉ ግን አትመኚ» ብያት ዳንሱ አዳራሽ ሁካታ ውስጥ ጥልቅ አልኩ ። ይኸን ስጨብጥ ያን ሰላም ስል እየጐሸምኩና እየዳበስኩ እንግዶቼን እያናገርኩ ፤ የምሥራች እየተቀበልኩ አላልፍ ብሎ ያስቸገረኝን ረጅም ደቂቃ እየቆጠርኩ አዳራሹን ሳቋርጥ ባለቅኔውን ሉዚያኖን አገኘሁት ።

በደነዘዘ ፈገግታ ሰላምታ ሰጠኝና በዚያ ራሱ በጥበቡ አሳምሮ በቀመመው ሙዚቃ መሣይ ድምጹ ፤

«ጊዜ አጥቼ ነው እንኳን ደስ ያልዎት ያላልኩዎ ጌታ ፤ ያገቧት ቆንጆ ግን ለውበታቸው አምሳያ የማይገኝላቸው ውብ ናቸው» አለኝ ።

በዝምታ አንገቴን ዝቅ አድርጌ አመሰገንኩ ።

«የኔ ጠባይ መቼም ከሰው አይገጥም ። ይኸውሎት በዚህ ደስታና ፍሥሀ መሀል እኔ አጥንቴ ድረስ ሀዘን ይሰማኛል ። አሁኑኑ ወደቤቴ ሄጄ የለቅሶ ዜማ ብደርስ ይሻለኛል ።»

«ምን አለበት ታዲያ ያሰቡትን ይፈጽሙ እንጂ ፤ ሠርግቤት ሄጄ የሀዘን ቤት ፤ ሀዘን ቤት ሄጄ የሠርግ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት ስሜት ይመጣብኛል የሚሉ እርሶ ብቻ አይደሉም ሌሎችም አሉ።»

ሉዚያኖ ፊቱን ክስክስ አድርጎ ፤

«ሰሞኑን የሲኞር ፈራሪን አሟሟት እያሰብኩ ምስኪንነቱ በይበልጥ እየተሰማኝ ነው ። በቡና ወይም በኮኛክ ሊያልፍ የሚችለው ነገር በሰው ሕይወት አለፈ። እኔ መቸም ሰውን በጥይት ከመምታት በቃላት ጥይት መምታትን እመርጣለሁ ። ምናልባት የእውነተኛውን ጠብ ምክንያት እንደቃኤልና አቤል ታሪክ አልተነገረኝ ይሆን?»

«ኢባክህን ፈራሪን ተወው ፤ ለሴት ሲል የሞተ እርሱ ብቻ የመጀመሪያው እንዳልሆነ ሁሉ የመጨረሻም አይሆንም ።»

ይህን እየተጫወትን ባለቅኔውን ከሌሎች እንግዶች ጋር እንዲጨዋወት መሀል አስገብቼ ተውኩት ። ራት እኩለ ሌሊት እንዲቀርብ ስለታቀደ ሰዓቴን እየት ሳደርግ ለአምስት ሩብ ጉዳይ ሆኖአል ። ልቤ በኃይል ወዲያው መምታት ጀመረ ። ደሜ በጅሮ ግንዴ እያማጠ እስኪሰማ ድረስ ነዘረኝ ። በጉጉት የጠበቅሁት የመጨረሻው ሰዓት መድረሱ ታወቀኝ ። ልክ በመጨረሻው!



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራስምንት

እያመነታሁ ፣ በቀሰስተኛ እርምጃ ወደባለቤቴ ጠጋ አልሁ ። ከፋይ ወንበር ላይ ዘና ብላ ተቀምጣ በዳንስ የደ ከመ ሰውነትዋን አሳርፋ ያቺን እንቡጥ ቆንጆ እያምካሽ መንፈስዋን ከለወጠው የጣጃናው ልዑል ጋር ታወጋለች ። ዶትርታ ጠይቄ እምቢ በማያሰኝ ቃና «የኔ ትፍስሂት ፣ ቃል የገባሁልሽን ላስታውስሽ ነው የመጣሁት» አልኳት ።

«እኔም በጉጉት እየጠበቅሁህ ነኝ ፤ መቼና እንዴት እንደምንሄድ ንገረኝ ።»

«የሆቴሉን ጓሮ በር ታውቂው የለ ፤ ከሀያ ደቂቃ በኋላ እዚያ እንገናኝ ። ብቻ ማንም እንዳያየን ተጠንቀቂ» ልብስዋን አየት አደረግሁና «ሞቅ ያለ ነገር ደግሞ ብትደርቢ አይሻልም?» አልኳት ።

«ለእሱስ የብርድ ልባብሽ መጎናጸፊያ አለኝ ፣ ግን አንዳንቶይ ያስፈልጋል ።»

«ለራት እንደርሳለን ።»

«ለመሆኑ ሙሉ ጨረቃ አለች ? በጨረቃ ካንተ ጋር መሞብ ምንኛ ደስ ይላል።»

«ጨረቃ ባትኖር አትቀርም ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እንግዲህ ከሀያ ደቂቃ በኋላ እዚያው እንገናኝ ። ለ ጊዜው ለዳንስ የለመነኝ አለ» ብላ አዲስ ሙዚቃ ሲጀምር ብድግ አለችና ከማርኬ ጋር ተያይዘው ይወዛወዙ ጀመር ።

ከመቅጽበት እግሬ እንደእንዝርት እየፈጠነ የዳንስ አዳራሹን ጥዬ ወደ ግል መኝታ ክፍሌ አመራሁ ። እኔነቴን ጋርዶ የቆመውን መጋረጃ ሁሉ ገፍትሬ መጣል ነበረብኝ ።

በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ወደጥንቱ ሰውነቴ ተመልሼ መስታወት ፊት ቆምኩ ። በእርግጥ የጸጉሬን ንጣት መቀየር አልቻልኩም የሪዜ መላጨት ግን የእድሜዬን ወጣትነት መመስከር ጀምሮአል ። የዓይኔን ጥቁር መነፅር አንስቼ ወረወርኩ ። የኮከብ ያህል ውብትና ስለት ያላቸው ዓይኖቼ ፋቢዮ ሮማኒ መሆኔን በይፋ መመስከር ጀምረዋል ። ሰውነቴን እንጠራርቼ ሽማግሌ በመምሰል የተሳሰረውን ጡንቻዬን ሳፍታታው እንደብረት ጠንክሮ አገኘሁት ። በሙሉ ጉልበት ከት ብዬ ጮኬ ሳቅሁ ። ያ አሮጌ ልብስ ሻጭ ይሁዲ በአንድ አፍታ መግደል ትችላለህ ያለው ትዝ አለኝና ያለጥርጥር መግደል መቻሌ ተሰማኝ ። ጩቤ ከስገባው አውጥቼ ስለቱን ከጫፍ እስከጫፍ በአውራጣቴ እየዳሰስኩ ያለስለት መግደል እችላለሁ ? ለመሆኑ ይህን ጩቤ መውሰድ ያስፈልገኛል ? ተጠራጠርኩ ። አዎን ! ድንገት ያስፈልግ ይሆናል ብዬ ልብሴ ውስጥ ድብቅ አደረግሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የኔንቴን ምስክሮችስ ማስተማመኛዬን መያዝ አለብኝ ። በአንድ ቦታ ሰብስቤ ያስቀመጥኩት ስለሆነ ስቀበር የነበ ሩኝን የሚሸቱና የልጇ ፎቶ ያለበት የአንገት የወርቅ ድሪ ፣ ኒና ራስዋ የሰጠችኝ የካርድ ማስቀመጫና መነኩሴው በአስከሬኔ ላይ የጣሉልኝን መስቀል ሰብስቤ ያዝኩ ። በመጨረሻው ማርኬ የላከልኝ የደብዳቤ ስብስብ ትዝ አለኝ ። ኒና ጉዶን እያሞካሸች የጻፈችውን የፍቅር ደብዳቤ ኪሴ ከተትኩ ። ሌላው ምስክሬ እዚያው መቃብር ቤት ነው ። በነፍስ አውጪኝ ጭንቀት የበረቃቀስኩት የሬሣ ሣጥን መኖሩ ብቻዬን እንከትክቶ አሳቀኝ ።

የመኝታ ቤቴ ምንም አይነት የውሳኔዬን ፍንጭ እንዳ ይሰጥ አስተካክዬ ከራስ ጸጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ የሚ ሸፍን በርኖስ ዓይነት ካባ ለበስኩ ። ያለዚህ ደህና ልብስ ለብሼ ብወጣ ጌታ ፋቢዮ ሮማኒኒቴን ማንም ሊያውቅ ስለሚችል ተጠንቅቄ አገጩ ድረስ ተሸፋፍኖ ዐይኔ ድረስ የሚወርድ ባርኔጣ አደረግሁ ። ለወቅቱ ብርድ እንዲህ አድርጎ መልበስ የተለመደ ስለሆነ ብዙ እንደማ ያስጠረጥር ተማመንኩ ። የተቃጠርንበት አትክልት መውጫ ጨለምለም ያለ ስለሆነ ኒና እምብዛም እንደማታ የኝ ገመትኩና ሩጫዬን ቀጠልኩ ። አዳራሹን በመስኮት ላይ ወጥታለች ። አቀጠሮው ቦታ ወጥቼ መጠበቅ ጀመ ርኩ ። እያንዳንድዋ ደቂቃ እንደሰዓት ረዘመችብኝ ። የሆ ቴሉ ሠራተኞች ራት በማዘጋጀት ፣ ሌሎቹ የዳንስ ግብዣ ውን በማድነቅ ተጠምደው ስለነበር ጥላ መስዬ እቆምኩ በት ቦታ እንድም ሰው አላየኝም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን ባትመጣስ ? ብታመልጥስ? የሚል ጥያቄ መጣ ብኝና ድንጋጤ ወረረኝ ። እንደምንም ከሀሳቤ ተገላግዬ ወዲያና ወዲህ ስሄድ ረጅም የብርድ መጐናጸፊያ ከላይ አስከታች ለብሳ ሽቶዋ አፍንጫዬን ፈልጐ አመደኝና ዞር ስል አጠገቤ ቆማ በአካል አየኋት ። አባትዋን እንዳገኘች ሕጻን ዘላ ደረቴ ላይ ውድቅ አለች ።

«ብዙ አቆምኩህ ፍቅሬ ? መጨረሻ ላይ የተሰማው ሙዚቃ ልቀቁኝ የማያሰኝ ነበር ፣ እንዴት አድርጌ አቋ ርጨ ልውጣ ፣ ብቻ ከአንተ ጋር በዚያ ሙዚቃ ባለመደነሴ አዘንኩ ።»

«አስቆጨሽኝ ፣ ግን እንዴት አዳራሹን አቋርጠሽ ለመውጣት ቻልሽ ?» እያልኩ ወገቡዋን በግራ እጄ ጥም ጥም አድርጌ መንገዳችንን አስጀመርኳት ።

«በቀላሉ ነዋ! ሙዚቃውእንዳለቀ አብሮኝ ይደንስ የነበረውን ይቅርታ ጠይቄ ወደ ክፍሌ ወጣሁና የብርድ መጎናፈፀያዬን ደርቤ መጣኋ!»

መንፈስዋ እንደጋለ ስለሆነ ትሲቃለች ።
«የኔን ደስታ ለማሟላት ስለመጣሽ አመሰግናለሁ ፣ ደንገጡርሽ ምን አለች ስትመጪ ?»
«ደንገጡሬ ስመጣ ጨርሳ አላየችኝም። እርስዋም ከሆቴሉ ወንዶች ጋር ትዳራለች መሰለኝ ። ምስኪን ነገር ስለሆነች ትደሰት» ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙ ዘልቀን ብቻችንን ሄድን ። ማንም ሰው በሳላዋ ነጻነት ተሰማኝ ። የሆቴሉን እንግዶች ከሚያመላልሱት ጋሪዎች አንደኛውን ጠጋ ብዬ የቀብር ቦታውን ሳልጠራ በአቅራቢያው ያለውን የሰው ቤት ስም ጠርቼ ተሳፈርን ።

«ቅርብ ነው አላልከኝም ነበር እንዴ ?»

«ስራት በቶሎ እንድንመለስ ብዬ ነው እንጂ ቦታውስ ቅርብ ነው ።»

ጋሪ ውስጥ ተቃቅፈን በግማሽ ብርሀን መጓዝ ጀመርን «በመጨረሻው የኔ የብቻዬ ሆንሽ አይደል?» አልኳት።

ከንፈር ለከንፈር ተገናኘን ። በጋለ ስሜት የበላባ ዘመን ትኩሳቴን አበረድኩባት ። እንደልብዋ እንድታቅፈኝ ለቀቅኋት ። ደስ ብሎአት ፈነደቀች ። ከተማው ጠርዝ ስንደርስ ጋሪው አቁሞ ወረድን ። ባለጋሪው ሂሣቡን ተቀብሎ ወደኋላ ሸመጠጠ ። ስለማንነታችን የሚያውቀው አንድም ነገር የለም ። ለእርሱ ሲጋዊ ፍላጐታችንን ያለከልካይ ለመወጣት ከተማውን የሸሸን ነው የሚመስለው ።

«ለምን እስክንመለስ ጠብቆ እንዲወስደን አታቆየውም ነበር ?» አለችኝ ።

«ስንመለስ በአቋራጭ እንደርሳለን»። ወገቡዋን በእጄ ደግፌ መሄድ ጀመርን ። እንደ ፍርሀትም እንደመብረድም አንቀጠቀጣት ። እየተገመተመተች ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሲዛር ከዚህ በላይ ርቀን መሄድ አለብን እንዴ?»

«የሶስት ደቂቃ መንገድ ቢሆን ነው ። ከዚህ አይበል ጥም በረደሽ እንዴ ?» በጣም እየተጠጋችኝ

«ትንሽ በርዶኛል አሁንም ብዙ እንሄዳለን?» አለችኝ ።

«ትንሽ ነው» ስላት ልብስዋን ከፍ ከፍ አድርጋ ጥግት አለችኝ ። ጨረቃዋ ድንገት ሙሉ ለሙሉ ብቅ ብላ በውድቅት የጨለመውን ሰማይ ወገግ አደረገችና በብርሀንዋ መሄድ እንጂ መመለስን ወደማያውቁት የወጣቶች የሽ ማግሌዎችና የሕጻናት የመኝታ ክፍል ወለል አድርጋ አሳየች ።ይህንየመቃብርክፍልምዕቴ ገና ስታይ በጥርጣሬ በረገገች ።

«ምን ዓይነት ስፍራ ነው ይኽ?» ሕይወትዋን ሙሉ የመቃብር ቦታ አይታ ስለማታውቅ የሞት ያህል የቀብ ር ቦታ ትፈራለች ።

«ሀብቴን ሁሉ የማስቀምጠው እዚህ ነው ። ይህን ስላት የገዛ ድምጼ ለራሴ እንኳ ሻከረኝ ። ወገብዋን ጠበቅ አድርጌ ይገፑ አይዞሽ ከኔ ጋር ሆነሽ ምንም ነገር ሊያስ ፈራሽ አይገባም ፣ ነይ አይዞሽ» አልኳት ።

እየደገፍኩም እየገፋሁም ፣ መቆምም መናገርም አቅቷት ጽሑፍ የሌለባቸውን መረማመጃ የሆኑትን መቃ ብር እያለፍን የወላጆቼን መቃብር ቤት ተጠጋን።የአስር ሰይጣን ጉልበት ያህል አውጥቼ እየነዳኋት መቃብር ቤቱ በራፍ ነክተን ተገቢ ስፍራዋ አደረስኳት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ጨረቃዋ ተመልሳ ወፍራም የዳመና መጋረጃ ውስጥ ገባች፡፡የመቃብር ቤቱን ቁልፍ ገና መክፈት ስትጀምር ስረገ ላው ለቀቀና በሩ ወደኋላ ተገፍትሮ ወለል አለ ፡፡ ሙሽራዬ እምልጣኝ ለመሸሽ ወደኋላ ተቁነጠነጠች ፡፡ በብረት እልህ ወገብዋን ጠምጥሜ ያዝኳት ፡፡

ድክም ባለ የፍርሀት ልሣን «ወዴት ነው የምትዬ ደው እ...... እኔ ፈራሁ» አለችኝ ፡፡

«ምን የሚያስፈራ ነገር ተገኘ? ጨለማው ነው ያስ ፈራሽ ? በእርግጥ ጭለማ ነው ፣ ለዚህ ደግሞ መብራት እናበራለን ፡፡ «አንቺን አንቺን» አንድ ጊዜ አቀበት ላይ ተጠራቅሞ መውጫ እንዳገኘ ጐርፍ ባቄን ለቀቅሁት ፡፡ «አንቺን አንድም የሚያስፈራሽ ነገር የለም፡፡ይልቅ ነይልኝ እናናዩ» ብዬ ተሸከሚ ደረጃውን አወረድኳትና በሩን ከውስጥ ቆለፍኩት ፡፡ በመጨረሻም አስገብቼ የመቃብር ቤቱን በር ስለቆለፍኩት ፈጣሪዬን አመሰገንኩት ፡፡ በዚህ ደስታ ያ ልክላከለው የማልችለው ሳቅ አንድ ጊዜ ደግሞ እንከትክቶ አሣቀኝ፡፡በስቅ የመቃብር ቤቱ የገደል ማሚቶው ደጋገመው ፡፡ በዚህ ጊዜ ኗና ባቄን የሰይጣን ሳቅ አስመሰሉ ተጠመጠመችብኝና ፣ «ለም ፈርታ በፍጹም ተስፋ መቁረጥ እንዲህ የምትስቀው ? በጣም ያስፈራል» አለች ንድ ነው በጭንቀት ድምጽ ፡፡

«የምስቀው ጨረቃዋ ደስ ብላኝ ነው ፡፡» ብዬ ምንቱ ጥሪቴን ሳምኳት ፡፡ ቀስብዬ በጀርዋ «ደረጃው ለትናገኝሽ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሙብ እግሮችሽ ስለማይመች አሁን ፍቅሬን እቅፍ አድርጌ በደረቴ ላይ ልጥፍ አድርጌ አወርድሻለሁ ፣ እምን የአልጋ ዝና እንቁ ማስቀመጫዬ ድረስ ወስጄሽ ለፍቅሬ ላንቺ ለባለቤቴ ያለኝን ውድና ብርቅ ሀብት ሁሉ እሰጥሻለሁ ።»

እንደትንግሽ ሕጻን ታቅፌ ደረጃውን አወረድኳት ። ከእቅፌ ለማምለጥ ትሞክር አትሞክር አሁን አላስታውስም ። ብቻ የበቀል ጥሜን የምረካበት ሰዓት ስለረዘመ በ ደሜ ንዝረት ምክንያት አብደት ወይም ሞት ይከተለ ኛል ብዬ እፈራ ነበር ። እኔ እንደዚያ ግዬ እርስዋ ደግሞ እንደበረደ ቀዝቃዛ አንገቴን አጥብቃ የያዘችበት እጅዋ እንደብረት ይወጋኝ ነበር ። በመጨረሻው ደረጃውን ሁሉ ወርጄ ጨረስኩና ውድ ሸክሜን መሬት አሳረፍኩኝ ። ለአንድ አፍታ የምሠራውን ዘንግቼ ፈዝዤ በጭለማ አፈጥ ጀመር ።

«የት ነው ይኸ ቦታ? ያልከውስ መብራት የት አለ ?» ብላ ጠየቀችኝ ።

ምንም ሳልመልስላት ከኪሴ ክብሪት አውጥቼ ስድ ስቱን ትላልቅ ሻማዎች አያያዝኳቸው ። የቆመችበትን ቦታ ምንነት ልታውቅ አልቻለችም ። ትክ ብዬ አያት ጀመር ። ፊቴን እንዲያሳስት የደፋሁትን መከለያ ሳላወርድ ፍጥጥ ብዬ አየኋት ።

ድንገት ያለችበትን አወቀችው መሰለኝ የሚሰቀጥጥ ፍርሀት ያዛት ። በድንጋይ የተሰሩ የመቃብር ኪሶችን የመ



t.me/OLDBOOKSPDF

ታን ስሞችን ፡ በምስጥ የተበሉ የሬሣ ሣጥኖችን እይታ በፍርሀትና መረበሽ እሪ እያለች መጥታ ተጠመጠመችብኝ። «ውሰደኝ ከዚህ! ፡ አውጣኝ!» ሬትዋን ልብሴ ውስጥ ደብቃ «የመቃብር ቦታ ነው! የሙታን ሰፍራ ነው! በጣ ሬየም ብለህ አውጣኝ! አውጣኝ! ቶሎ ብለህ አየር የማገ ኝበት ቦታ አውጣኝ ቤታችን እንሂድ! ወደቤታችን!» በእጅዋ ጨብጣ እንዳዳምጣት ጕነጠችኝ ። በእንባ ዓይ ንዋ ፍጥጥ ብላ አየችኝ ።

«ሲዛር ምንድነው ዝም የሚያሰኝህ ? ለምንድነው እዚህ ያመጣኸኝ ። ያዘኝ ሳመኝ ተናገር ፡ የሆነ ነገር ተናገር ዝም አትበል!»

በፍርሀት ስቅቅ ብላ አለቀሰች ። እጅዋን ከላዬ አንስቼ ተውኳት ።

«እባክሽ ዝም በይ ፡ ይኸ እንደልብ አፍ የሚከፍቱ በት አይደለም ። የቀልድ ቦታ አይደለም! ይግባሽ የኔ እመቤት! ይኸ ቁርጠኛ ቦታ ነው ። ባልሣሣት የነሮማኒ መቃብር ቤት ነው ።»

ልክ ይኸን ስትነፍስ መንሰቅሰቅዋን ቀጥ አድርጋ ቆመች ። ድርቅ ብላ ቃል ሳትተነፍስ ትኩር ብላ አየችኝ ።

«የባልሽ አያቶች ሁሉ የተኙት እዚህ ነው ፡ ያንቺም ቅንጅና መጨረሻው እዚሁ ነው ።»ድምጼ እየወፈረና



t.me/OLDBOOKSPDF

ትእዛዝ ሰጪ እየመሰለ «ከስድስት ወር በፊት ባለቤትሽ ፋቢዮ ሮማኒ እዚህ ተቀበረ ።»

አሁንም ምንም አልተናገረች በአንድ ምትሀት ወደ ድንጋይነት እንደተለወጠች ውብ ፍጡር በሙት ዓይነት ዝምታ አስተዋለችኝ ። ይህን ከተናገርኩ በኋላ ደግሞ ውጤቱን ለማየት ዝም አልኩ ። ነፍስዋን ከመሰረቱ ቀስቅሼ ለማሰቃየት ስለምፈልግ ጭጭ አልኩ ። በመጨረሻው በማይሰማ የቅዠት ልሣን ፣ «አንተ አብደሀል መሰለኝ» አለችኝ ። እጇን ጨብጣ በማዘዝና በመጕትጐት «ተነስ እንሂድ እባክህ ። ይኸን ቦታ ጥለን እንሂድ፣ይኸን አሰቃቂ ስፍራ ትተን እንሂድ» ትለኝ ጀመር ። «አልማዝና እንቁውንም ቢሆን አልፈልገውም ። እዚሁ ሊቀመጥ ይችላል ።»

ንግግርዋን አቋርጬ ጨለም ወዳለ ቦታ ጐተትኳት ። ወደጥግ ጭለማ ለብሶ ወደተቀመጠው የራሴው የሬሣ ሣጥን እያስጠጋሁ ፤

«ተመልከቺ» ድምጼን ዝቅ አድርጌ እያንሾካሾኩ «ይኸ ምን ይመስልሻል ? ተመልከቺው እስቲ ፣ በርካሽ እንጨት በይድረስ ይድረስ የተሠራ ሳጥን ነው ። የኮሌራ ሳጥን ነው ። አትደንግጪ ፣ የባልሽ ስም ተጽፎበታል ፣ በዚህ ውስጥ ነበር የተቀበረው ። እና ታዲያ እንዴት ሊከፈት ቻለ ? ወዴት ደረሰ ?»

እንደያዝኳት ነፍሱ እንደመታው ዛፍ ተወዛወዘች ። አዲስ የፍርሀት ብርድ ሆድዋ ገብቶ ያንጠረጥራት ጀመር ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ጉልበትዋ ሁሉ እንደቄጤማ ተውረገረገና ይዟት ሊቆም ስላልቻለ ቁርጭምጭሚትዋ ላይ ቁጭ አለች ።

«ወዴት ሄደ ታዲያ? ወዴት ሄደ ፋቢዮ ሮማኒ?» ድም ጼን ከመቃብር ቤቱ በላይ አጉልቼ ፤

«ወዴት ሄደ ? የት ነው ያለው ፣ ያ ምስኪን የዋህ ፣ ያ ሁሉን የሚያምን ሞኝ ፣ በገዛ ጣሪያው ስር ሚሽቱ የገዛ ጓደኛውን የምትወሽምበት ድንፋፍ ፤ እንደዚያ እየወደ ዳት ፣ የእውር ጭፍን እንከን በሌለው እምነት እየተንከባ ከባት ፣ እና የት አለ? እዚሁ ነው »ብዬ ከተንበረከከችበት ስፍራ ጎትቼ አነሳኋትና« ዛሬ ማታ እኔነቴን ያለመጋረጃ አሳይሻለሁ ብዬ ቃል ገብቼልሽ አልነበረም ? በዛሬው ምሽት ወጣት እሆንልሻለሁ ብዬሽ አልነበረም ? ይኸው አሁን ቃሌን ለመፈጸም ቀርቤአለሁ ። እይኝ ኒና ! እንቺ ሁለት ጊዜ ያገባሁሽ ሚሽቴ ! እይኝ ! ባልሽን አታውቂም እንዴ ?»

በርኖስ መሳይ ግርዶቬን አወላልቄ ጣልኩና ፊት ለፊቷ በገሀድ ቆሜ ታየኋት ። በድንገት ውበትዋ እልም አለና ጣረሞት መሰለች ። ከንፈርዋ ሰማያዊ ሆነ ። ዐይንዋ ውበ ቱን ጥሎ ጉድጓዱ ውስጥ እንደተቀበረ አጉርጣ አየ ችኝ ። እጆችዋን እንደመጻጉ እያወናጨፈች በልመና አርገ በገበች ። እያቃሰተች ወለሉን የሙጥኝ ብላ ዓይኔን ሸሸች ።

«አይሆንም ! በጭራሽ ፋቢዮን ሊሆን አይችልም ፤ ሊሆን አይችልም ፋቢዮ ሞቷል ፣ ሞቷል አንተ ግን እብድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነህ ይህ አንተ የፈጠርከው ጨካኝ ቀልድ እንጂ እውነት አይደለም ። ማታለያህ ነው! እኔን ለማስፈራራት የፈጠ ርከው ተንኮል ነው ።»

ሺባ ሆና እጥፍጥፍ ካለችበት ለመነሳት ስትሞክር ጠጋ ብዬ በመሰሪ ትህትና ልደግፋት እጄን ዘረጋሁ ። ነካ ሳደርጋት በንኪኪቴ ብቻ ሰውነትዋን በሙሉ ሰደቻ መታት ። እንደምንም በእግርዋ ከቆመች በኋላ ታስተው ለኝ ጀመር ። አጥንቴ ድረስ በሚያነብ ትኩረት አጉርጣ ከእግር እስከራሴ መጀመሪያ በመጠራጠር ፣ ቀጥሎ በፍር ሀት ፣ በመጨረሻው ተስፋ በሌለው እርግጠኝነት አስተ ዋለችኝና በእጅዋ ዐይንዋን ሸፍና ሊታይ እንደማይቻል የጉድ አዋጅ ተከላከለችኝ ። እንደ ቀስት ተወርውሮ እንደ ውጋት ዓይነት ወይም በሽታው እንዳልታወቀለት እንስሳ በረጅሙ ታቃስት ጀመር ። ሳቄ አመለጠኝና ጥርሴን እንደነከስኩ ሙኪ ሳቅሁ ።

«እህ ፡ በመጨረሻው ማንነቴን አወቅሽ? እርግጥ ነው! በሙጠኑ ተለውጫለሁ ። ይህን ጽጉሬን ታስታውሺ እንደሁ ከሰል የመሰለ ጥቁር ነበር ፣ አሁን እንደበረዶ ነጥቷል ። የሕመም ደረጃውን ልትገምቺ በማትችይው የጸእር ስቃይ ጽጉሬ መልኩን ለወጠ ። ከዚህ በስተቀር ልታስታውሺኝ ትችያለሽ ።»

በእዩዩዋ መሀል «እረ አይሆንም አይሆንም ፣ በጭ ራሽ አይደረግም ፣ ውሸት መሆን አለበት ። ሀሰት ነው ጭካኔ ነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ብዙ የምነግርሽ ስላለ አድምጪኝ ። የሞትን ሰን ሰለት በጥሼ እቤት ስመጣ ፣ የአባወራነት ቦታዬ በሌላ ወንድ ተይዞ ደረስኩ ። በገዛ መናፈሻዬ አንቺ እና ጉዶ ኮከብ ተዋናይ ሆናችሁ የፍቅር ተአምር ስትፈጥሩ ደረስኩ ።»

ራስዋን ቀና አድርጋ በፍርሀት የሆነ ነገር እነበነበች ። በጣም ተጠጋኋትና ፤

«ትሰሚኛለሽ ? ሙሉ ጨረቃ ነበረች የምሽት ወፎች ይዘምራሉ ፣ የመድረክ ቅንብሩ ተስተካክሏል ። የኮሚዲውን እድገት እኔ በምን ዓይነት ስሜት እከታተል እንደነበር ይገባሻል ። ብዙ ለኔ አዲስ የሆኑ ነገሮችን ተማርኩ ። የአንቺን ዓይነት ትልቅ ልብ ላላት ወይ ዘር አንድ ባል በቂ ያለመሆኑን ተገነዘብኩ ።» እጇን ትከ ሻዋ ላይ ጭኜ ዐይንዋን እያየሁ ሳወራ እርስዋም አፍጣ እያየች ፣ ታዳምጠኛለች ። «እና በሶስት ወር የጋብቻ እ ድሜ ውስጥ ራስሽን ለሌላ ወንድ አቀረብሽ ። ለመካድ እንዳትከጂይ ። ጉዶ ፈራሪ በስም እንጂ በሌላው ሁሉ ባልሽ ነበር ። ስለዚህ ለሁኔታው መዘጋጀት ነበረብኝ ። ለኮሚዲው ኮሜዲ ለማጭበርበሩ ማጭበርበር ፣ ሌላውን ታውቂዋለሽ ። እንደጌታ አሊቫነት የተጫወትኩት ሁሉ እንደተዋጣልኝ አልክድም ። ለሁለተኛ ጊዜ ከአንቺ ጋር ተ ዳርቼ ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ላገባሽ ቻልኩ ። አሁን አንቺ በፍ ጹም የኔ መሆንሽን የሚጠረጥር አለ ? ሞት እስኪለየን ማ ለቴ ነው»።



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን እንባዋ ከዐይንዋ ደረቀ ። እንደቆሰለ እባብ ሸሸችኝ ። ፊትዋ እንደ ሬሣ ሰም ለበሰ ። ዓይንዋ ብቻ ጭለማ ውስጥ ይወዛወዛል ። ከእርስዋ ዞር ብዬ በአንዱ የሬሣ ሳጥን ላይ ተቀመጥኩ ። ሳስተውላት አንድ ሀሳብ በአእምሮዋ መጸነሱ ገባኝ ። የተደገፈችበትን ግድግዳ ሸሸት ብላ በፍርሀት መንፈስ ቆማ ትጠብቀኝ ጀመር ።

ቀስ በቀስ ዓይኔን በዓይንዋ እየጠበቀች ደረጃውን አልፋ ወጣችና ቸር ብላ የላይኛው የመውጫ ደረጃ ደረሰች ። ሳቂ መጣብኝ ። በዚያች ጉልበትዋ የመቃብር ቤቱን በር የቻለችውን ያህል ወዲያና ወዲህ ሞከረችው ። እሪ ብላ ለእርዳታ ስትጮኽ የመቃብር ቤቱ የገደል ማሚቶ ብቻ ሰምቶ መልስ ሰጣት ። የሙታን ሰፈር የዛፎች ፉጨት ብቻ ጥሪዋን ተቀበላት። በመጨረሻው እንደ አውሬ ድምፅ ታጓራ ጀመር ። በቀሚስዋ ደረጃውን እየጠረገች ወርዳ እንደነብር ዘላ ልትቋቋመኝ ጉብ አለችብኝ ። ደምዋ መሞቅ ስለጀመረ የቀድሞ ውበትዋ እንደመመለስ ብሎአል ።

«ያንን በር ክፈት እኔ የምልህን ብትሰማ ይሻላል» ብላ በእግርዋ መሬቱን እየደበደበች ጮኸችብኝ ። «ይህን በር ክፈትልኝ ነው የምልህ አንተ ነፍሰ ገዳይ ከሀዲ ! አልወድህም ምንጊዜም እንደጠላሁህ ነበር ፣ አሁንም አልወድህም ይቁረጥልህ፣እኔን ለመግደል ምንም መብት የለህ ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደአጉል ነገር አየኋትና አስተያየቴ ወደኋላ መለሳት ። እያላገጥኩ ፣ «መብት የለህም አልሽኝ ። ተሳስተሻል አንድ ጊዜ ሚሽቱን ያገባ ወንድ የሆነ መብት በሚሽቱ ላይ አለው ፣ ሁለት ጊዜ ያቺኑ ምሽቱን ያገባው ግን እጥፍ መብትና ሥልጣን አለው ። አንቺም ስለነፍስ ማጥፋት ትናገሪያለሽ? ለመሆኑ ለዚህ አፍ አለሽ አንቺ ሁለት ወንዶች የገደልሽ? ደማቸው ራስሽ ላይ ነው ። እኔ ምንም ዛሬ ቆሜ ብታይኝ የትናንቱ ሰው ሬሣ ነኝ ፣ ተስፋ ፤ እምነት ፣ ደስታ ፣ ሰላም ትላልቅና ደጋግ ቁምነገሮች ሁሉ ከውስጤ ባንቺ ምክንያት ስለሞቱ ሞቼአለሁ ።» ስለጉዶ ብዬ ለመናገር ስጀምር በኃይል እያለቀሰች አቋረጠችኝ ።

«ጉዶ ያፈቅረኝ ነበር ። አዎ ያፈቅረኝ ነበር ።»

«አዎን ያፈቅርሽ ነበር።አንቺ በሴት ቅርጽ ያለሽ የሰይጣን ቁራጭ ። አፈቀረሽ ነይ ላሳይሽ» ብዬ ጉትቼ መቃብር ቤቱ ጥግ አቆሜ« ልክ በዚህ ትክክል ከቆምን በት በስተግራ የውሽማሽ ጠንካራ አስከሬን ተኝቷል ። ቀስ በቀስ እድሜ ለአንቺ እየበሰበሰ ነው ። ያን መልከ መልካም ገላውን ምስጥ እየተንሸራሸረበት ፣ ረቂቅ ነፍሳት ያን ዘንፋላ ጸጉሩን እያበጠሩለት ነው ። ደረቱ ላይ ያለው ቁስሉ እያገዘ ነው ።»

«አንተ ነህ የገደልከው ፣ አንተ ነህ የምትወቀሰው ።»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እኔ አልገደልኩትም ። በጭራሽ ! አንቺ እንጂ እኔ አልገደልኩትም ። የሞተው በአንቺ ውሸታምነት ነው ። ቃልሽን ስጥተሽው ሌላ እንግዳ ከበርቴ ለማግባት መዘጋጀትሽን ሲረዳ ነው በፍልሚያ እጁን ሰጥቶ በአንቺ ውሸት በኔ ሽጉጥ ሰላምን ያገኘው ። አንቺ እኮ የእርሱንም ሞት ስትሰሚ ተደስተሽ እንጂ አላዘንሽም ። ደግሞ ስለ ነፍስ ማጥፋት ትናገሪያለሽ ። አየሽ እኔ አንቺን ከሴቶች ሁሉ የረከስሽውን ሴት ሀያ ጊዜ እየቀሰቀስኩ ብገድልሽ ሀጥያትሽን ሊከፍል አይችልም ሞትሽ ።» ከላዩ ላይ አሽቀንጥሬ ወረወርኳት ። በዚህን ጊዜ የንግግሬ ሚስጢር ገብቷት አወራጫት ። ሙሉ ጌጥዋ በላይዋ ላይ የሻማውን ብርሀን እየፈነጠቀ ብርክ ይዟት ሰውነትዋ ተሸማቀቀ ።

«እኔን እኮ ለምን እንደምትወቅሰኝ አላውቅም ። እኔ ከሌሎች ሴቶች የባሰ በደል አልፈጸምኩም ።»

«ከሌሎች ሴቶች የባሰ በደል! አንቺ እፍረተ ቢስ ። በዚህ ዓይነት ነው የጾታ ወገኖችሽን የምታዋርጂው ። ያነበብሻቸው መጻሕፍት አለመታመን ወንጀል አይደለም ከሆነም በፍቺ የሚስተካከል እንስቶኛ ማኅበራዊ ስህተት ነው ብለው ነግረውሽ ይሆናል ። እኔ ግን ትክክለኛውን ልንገርሽ ፣ በአራዊት ሕግም ቢሆን ፣ ለዓይን የሚቀፍ ነገር በግልፅም ቢገኝ ለታማኝ ወንድ እምነት አጉዳይ ሴትን የመሰለ አስከፊ ነገር የለም ። እበር ስር ተወትፎ ሰውን ከኋላ ከሚወጋ ፈሪ ነፍሰገዳይ ወንጀለኛ የባሰች በባል



t.me/OLDBOOKSPDF

ሽፋን በባል ጥሩ ስምና ክብር ሽርሙጥና የምታካሂድ ቤት የረከሰች ናት ።»

እንዴ ደግሞ የእምቢተኝነት ስሜት በውስጥዋ ሲዛመት ታየኝ ።

«እኮ ምን በደልኩ ? የተዋብኩ እንደሆን የኔ ስህተት ነው እንዴ ? ወንዶች ጂል የሆኑልኝ እንደሆነ እኔ ምን ላድርግ ? አንተም አፈቀርከኝ ፤ ጉዶም አፈቀረኝ ፣ እንዳ ታፈቅሩኝ መከላከል ነበረብኝ ? ላንተም ሆነ ለእርሱ የተለየ ስሜት አልነበረኝም»

«አውቃለሁ ። ማፍቀር ከተፈጥሮሽ ጋር አልተወለደም ። የኛ ሕይወት ላንቺ የብርጭቆ ወይንጠጅ ነበር ። እንዴ ጣፍጦሽ ጠጣሽ አበቃ ። አሁን ግን እንደምትፈል ጊው አልሆነም ።»

ራቅ ብላኝ በአንድ እጅዋ ደረትዋን ደግፋ ድንጋይ ላይ ተቀምጣ አንገትዋን ወደ መሬት ደፋች ።

«አንቺ ኀሊናም ፣ ተጸጸች ልብም ፣ ማስተዋልም የለሽም እንዴ ?» እየጮሁኩ አልኳት ። ጨካኟ ፈጣሪዬ ! ምንገር ያለህ፤ እንዴት እንዲህ ያለችዋን ሴት አልዋት ? የመጨረሻው ጨካኝ አውሬ እንኳ ለአምሳያው ከዚህ የተሻለ ሀዘኔታ አለው ። ስሚ አንቺ ጉዶ ከመሞቱ በፊት



t.me/OLDBOOKSPDF

አውቆኝ ነው የሞተው ። ልጇ በቸልተኝነትነትሽ ከመቀ ትዋ በፊት አውቃኝ ነው ያረፈችው ። »

ተመልከቺ ብዬ ቀጠልኩ ፣ «ለታሪኬ ትክክለኛነት ማረጋገጫ አለኝ ። እነኝህ ነገሮች አብረውኝ ተቀብረው አገኘሁ ።» ፊት ለፊቴ እንደተቀመጠች የአንገቴን ሀብል የካርድ ማስቀመጫዬን ፣ ጭንዋ ላይ ወረወርኩላት ። «እርግጠኛ ነኝ ታስታውሻቸዋለሽ ፤ ይኸ» የመነኩሴውን መስቀል እያሳየሁ ፣ «ከእኔ ጋር ሳጥን ውስጥ ተቀብሮ አገ ኘሁት ። ሳንቺ ይጠቅምሽ ይሆናል ፣ ዛሬ ጸልይበት»።

በእጅዋ አቋረጠችኝ ፣ በሕልም እንደሚቃዥ ሰው መናገር ጀመረች ።

«ከዚህ መቃብር ቤት አመለጥኩ አልከ ፣ እንዴት እንዳመለጥክ አስረዳኝ» አለችኝ ።
ሀሳብዋ ስለገባኝ ሳቄ አመለጠኝ ።

«አስፈላጊ አይደለም ። የወጣሁበት ቀዳዳ አሁን በሲሚንቶ ተደፍኗል ። ከእንግዲህ እዚህ ቤት የተዘጋበት ፍጡር ሊያመልጥ የሚችልበት መንገድ የለም ።»

እግሬ ላይ ዘላ ወደቀች ። ጭንዋ ላይ የነበረው ማረጋ ገጫዬ ሁሉ መሬት ወደቀ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ፋቢዮ ፣ ፋቢዮ ! አድነኝ እዘንልኝ ፣ ወደብርሀን አውጣኝ ። ወደንጹው አየር ቀላቅለኝ ። እባክህ ልኑር ፣ ልተንፍስ ። ብትፈልግ በኔፕልስ አስጐትተኝ ! የፈለከውን ስም ስጥተህ አሳፍረኝ ፣ ግን የሕይወትን ትኩሳት ብቻ አትንሳኝ ። ያዘዝከኝን ፣ ያልከኝን ሁሉ እፈጽማለሁ ! ብቻ የመኖርን ዕድል ፍቀድልኝ ። ልጅነኝ ። እረ ውሸሞቻቸውን በእሥር እጥፍ የሚቆጥሩ አሉ ። ታዲያ እኔን ለምን ይህን ያህል የተለየሁ በደለኛ ታደርገኛለህ?»

«ለምን ! ለምን !» ሲታ ያዘኝ «ምክንያቱን ልንገርሽ? ባል ከመጀመሪያው በደል ሲፈጽምበት ፣ እርጉ ራሱ ፈራጅ ሆኖ ለፍትህ ኢሎሔ ቢል ኖሮ ፣ ከመጀመሪያ ውኑ ክብሩን ያዋረደችዋን ለመቅጣት እርምጃ ቢወስድ ኖሮ ፣ እና እንዲህ ዓይነት ወንዶች በርካታ ቢሆኑ ኖሮ እንዳንቺ አይነትዋ እንዲህ ባልበዙም ነበር ። በእስር የሚቆጠሩ ውሽሞች አሉሽ ! አንቺስ በአንድ ብቻ መች ተሳሳትሽ ? ስለአንቺ የምለው ሌላም አለኝ ። ሁለት ወንዶችን ጂል አድርገሽ መች በዚህ ብቻ ተወሰንሽ ። ሶስተኛ ስታጠምጂ አልተገኘሽ መሰለሽ ። እኔን ጌታ አሊዋ አድርገሽ ስታወጪ ለጉዶ ፈራሪ ደብዳቤ ጽፈሽ በመውደድ ቃላት ዓይኑን አፍዘሽ የፍቅር ደብዳቤ ርም ድረስ እየላክሽ ምንጊዜም ውሽማዬ እንደሆንክ እንድትቀር ነው የምፈልገው አላልሽውም ? ደብዳቤዎቹ እኝሁልሽ እኔ በደንብ ስለማውቃቸው ከእንግዲህ አልፈልጋቸውም» ብዬ ፊቴን ዞርኩላት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ደብዳቤዎቹን ከወደቁበት ቦታ አላነሳቻቸውም ። እግሬ ስር እንደወደቀች ናት ፤ የብርድ መጐናጸፊያዋ ከላይ እየተንሸራተተ በአልማዝና እንቁ የተጌጠው የሙሽራ ልብስዋ እያንጸባረቀ መሬቱን ይጠርጋል ። ጸጉርዋ ላይ ያሉትን ክብ የአልማዝ ጌጦች መንጭቄ አነሳሁና ፤

«እነኝህ የራሴ ናቸው ። ይኸም ጣቴ ላይ ያደረኩት ለጉዶ ሰጥተሽው የነበረውና ሲሞት የመለሰሽልኝ የአልማዝ ቀለበት የራሴው ነው ። እነኝህ የእናቴ አልማዝ ናቸው ። አሁን ልታጌጪባቸው አይገባም ። ሌላው የሰጠሁሽ ውድ ጌጥ የሌባ ንብረት ስለሆነ ተገቢሽ ነው ። በእርግጥም ለክብረ ንጽሕናሽ የሚመጥኑ እነኝህ የተሰረቁ ጌጦች ናቸው ። ይህን በልቅ ቸርነት የለገስኩሽ ሀብት ሁሉ በወንጀለኛነቱና በደም አፍሳሽነቱ በመላው ሲሲሊያ የታወቀው ሽፍታ የካርሜሎ ኔሪ ንብረት ነው ። ከዚህ ሀብት ልሰጥሽ ቃል ገብቼ ነበር ። እነሆ ተረከቢኝ። የካርሜሎ ኔሪን የዘረፋ ሀብት የተከማቸበትን የሬሣ ሣጥን የሚመስል ሰንዱቅ ብርግድ አድርጌ ከፈትኩላት ። ሆን ብዬ አስቀድሜ አደራጅቼው ስለነበር ገና ሲከፈት አልማዝና እንቁው ነው መጀመሪያ የሚታየው ። «የጌታ ሲዛር ኦሊቫ ሀብት ከየት እንደመጣ አሁን ገባሽ? ። ይህን ሁብት ከሞት የተነሳሁ ሌሊት እዚህ ተደብቆ አገኘሁት ። ምን እንደማደርገው በዚያን ጊዜ ግራ ገብቶኝ ነበር ። በኋላ ግን በደንብ ነው ያገለገለኝ ። አሁንም ቢሆን ሀብቱ ገና እ[illegible]ቶንካም እንዳለ ነው ። ከዛሬ ጀምሮ እንግዲህ ተራፊው ሁሉ ያን[illegible] ነው ልትገለገይበት ትችያለሽ ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ስትሰማ ቀጥ ብላ ቆመች ። የብርድ መጕናጸፊያ ዋን ከንድዋ ላይ እየጠመጠመች እመር ብላ የሽፍታው ሳጥን ላይ በደረትዋ አረፈች ። የተሰፋ ጭላንጭል ፊትዋ ላይ እያበራ ትኩር ብላ የአልማዙን ነጸብራቅ ታይ ጀመር ። የፊትዋ መሸብሸብ ከመቅጽበት ያረጀች አስመስሏታል ። ያ ሲያዩት ቢውሉ የማይሰለቸው ፊትዋ የውበት መአዛ ውን ተገፎአል ። ቆዳዋ በሙሉ በሆነ ንዳድ የተቃጠለ መሰለ ። ጸጉርዋ በወርቅ መያዣ እንደተያዘ ተንጨፍሮ ተበ ታተነ ። ዓይንዋ ብቻ ሆነ ወጣትነትዋን የሚመሰክረው ። ድንገተኛና ያልተጠበቀ የርህራሔ ስሜት እንደ ማእበል ድንገት በውስጧ ተቀሰቀሰ ።

«ዋ ሚሸሌ !» ብዬ ጮኽኩ «ዋ ባለቤቴ ! እንደዚያ ከሕይወቴ አስበልጬ ያፈቀርኩሽ ፤ ሚሸሌ ሙትልኝ ብት ይኝ ለአፍታ ሳላመነታ የምትን ጽዋ ለፍቅርሽ ብዬ የምጨ ልጥልሽ ሚሼሌ ፤ ለምን ከዳሽኝ ? ለምን መታመንን ነፈ ግሽኝ ? ለእውነት ፈጣሪ በሚያውቀው እውነቱን ልንገ ርሽ ፥ ከሞትኩ በኋላ አንዲት ቀን እንኳ አዝነሽልኝ በማ ግስቱ ጉዶን ብትመርጪ ለአንቺ የሚኖረኝ ርህራሔ ታላቅ ይሆን ነበር ። የበደልሽኝንም ይቅር እል ነበር ። ከሞት ተነ ስቼ ይህቺን ታህል ለኔ ማዘንሽን ባውቅ ድምጼን አጥፍቼ መንገዴን እቀጥል ነበር ። ግን ሀጥያትሽን አንቺው በአፍሽ መሰከርሽ ። በተጋባን በሶስተኛው ወር እንደሸጥ ሽኝ ስረዳ ፥ ፍቅሬ ፥ ስሜ ፥ ማእረጌና ክብሬ ለአንቺ ወሲባዊ ሀጥያት መጋረጃ ብቻ መሆኑን ሳውቅ ፥ ያውም ከልብ ጓደኛዬ ጋር ! አቤት እምላክ እንደምን ያለ ሙት


t.me/OLDBOOKSPDF

ቢጋ የለበሰ ሰው ይህን ጉድ ይቅር ይላል ታዲያ ? እኔ ከሌሎቹ ሰዎች የበለጥኩ አይደለሁም ፤ ነገር ግን ከሌሎች አብልጨ እኔ አንቺን የወደድኩሽን ያህል አንቺ ደግሞ እኔን በድለሽኛል ።»

አድምጣ ስታበቃ ወደኔ በጥቂቱ ጠጋ አለችና ፈገግ እንደማለት ብላ ድክም ባለ ድምጽ «ፋቢዮ ! ፋቢዮ!» አለች ።

ድምጼም የውስጥ ስሜቴም በሀዘን ፣ ስፍስፍ ባለ የምስኪንነት ስሜት ሙትት እንዳለ ፤

«ምን!? ፋቢዮ!? አንቺ ከዓዕረ ሞት ጋር ምን ጉዳይ አለሽ? ። የተጠላ ስም ምን ያደርግልሻል ? ማንም ወንድ ምሽቱን ባላፈቀረበት ደረጃ አፍቅሬሽ አንቺ ግን ማንኛዋም ሴት ባልዋን ባልጠላችበት ደረጃ ጠላሽኝ ። ለዚህ አሳዛኝ ደረጃ ያበቃሽኝ እኮ አንቺ ነሽ ።»

ልመልሰው የማልችለው እልህ መጥቶ እዬዬ ብዬ እንዳላለቅስ እንኳ ጉሮሮዬን ዘግቶ ይንጠኝ ጀመር ። ልጅነቴን ሳልጨርስ ሕይወቴ መበላሸቱ አሳዘነኝ ። ሁኔታዬን ተረድታ መጥታ አንገቴን ጥምጥም አድርጋ ያዘችኝና !

«ፋቢዮ ይቅር በለኝ እባክህ ፤ ቸኩዬ በመናገሬ ነወ እንጂ አሁንም እወድሀለሁ ። ለደረሰብህ መከራ ሁሉ እክስሀለሁ ። አፈቅርሀለሁ ፣ ከእንግዲህ እታመንልሀለሁ


t.me/OLDBOOKSPDF

እስከመጨረሻው ላንተ እሆናለሁ ። አይ ! አሁንም ሙብቴ አልተነካም ።»

ስሜትዋ ድንገት ተቀሰቀሰና ደረትዋን በደረቴ ላይ ከንፈርዋን በከንፈሬ ስር አድርጋ ዓይን ዓይኔን እያየች ስለአነጋገርዋ መልሴን ትጠብቅ ጀመር ። ፊቴን ቅጭም አድርጌ ትኩር ብዬ አየኋት ።

«ውበት ? የምስጥ ሲሳይ ነው ፤ እኔ ለውበት አልጓጓም ። በውዳቂ ነፍስ የተሞላች ቆንጆ ሰውነት ለኔ ምኔ ናት ? ይቅርታን ዘገየሽ ። እንደኔ የተበደለ ሰው ይቅር ቢልም ይቅርታው ከልብ አይደርስም ።»

አሁንም እንዳቀፈችኝ ናት ። ዓይንዋ ግን የሚፈልገው ነገር እንዳለ አይነት ይቅበዘበዛል ። ከውጪ የሚያፏጨው ኃይለኛ ንፋስ የዛፎቹን ቅርንጫፍ እየገነጣጠለ ይጥላል ። በየግድግዳው ስንጥቅና ቀዳዳ የሚገባው ንፋስ ደግሞ የመቃብሩን ቤት የብረት መዝጊያ ያናውጠዋል ።

ኃይለኛ ንፋስ መሆኑን ከማወቁ በፊት ለኔ እንዲያውም የታሰረው ሽፍታ ካርሚሎ ኔሪ ከእስር ቤት ከነሰንሰለቱ አምልጦ የሌብነት ሀብቱን ለመውሰድ በሩን የሚታገል መስሎኝ ነበር ። ይህን ሳሰላስል ድንገት ፊትዋ በሆነ የተንኮል ሀሳብ ምን እንደፈለገችና ሳላጠራጥር እንደመብረቅ ፈጥና ከልብሴ ውስጥ ወረቀቱን መዛ አወጣች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«በገየሽ አልከኝን» አለችኝ ። እንደአውሬ እያስካካች ፣ «በፍጹም አልዘገየሁም ሟችስ አንተ ነህ፤አንተ የተረገምክ» ።

ለአንድ አፍታ ልትበካብኝ ያሾለችው ጩቤ በሻማው ብርሀን እያንጸባረቀ አፈዘዘኝና ወዲያው ለጥፋት የተዘረጋውን እጅዋን ይዤ ጩቤውን ለመውሰድ እንታገል ጀመር ። የሞት ሞት ያህል ጩቤውን ጨቡዳ ጥርስዋን ነክሳ እስከመጨረሻው እስትንፋስዋ ታገለችኝ ። መቃብርን አሸንፈ የተነሳው ሴሊት የታገለኝን አስከፊ በራሪ ትዝ እስኪለኝ ተወራጭታ አወራጨችኝ ። ከሰው ሊወጣ በማይችል ዳቢሎሳዊ ኃይል ልብሴን እየቀዳደደች ጩቤውን እየሰበቀች ታግላ በመጨረሻው ጣልኳትና ጩቤውን ከእጅዋ ፈልቅቄ አወጣሁ ።

«ማንኛችን ነን እንግዲህ ስለነፍስ ማጥፋት የምንናገረው ?» ሲቃ እንደልቤ አላናግር አለኝ ። ቢሳካልሽ አሁን አርደሽኝ በደሜ እጅሽን አጥበሽ ጀብዱሽን ለዓለም እየነሰነሽ ልትመጻደቂ ነበር ። ደሜን ልብሽ ውስጥ ቀብረሽ በጸሎት አፍሽን አብሰሽ የጻድቅ አሟሟት ልትጠይቂ ነበር ። ደግሞ ይቅርታዬን ትጠይቂያለሽ ። ከዚህ ወጥተሽ የውሸትና የአብለት ትምህርትሽን እንደልብሽ ልታስፋፊ ነበር ።»

አጵረጠችኝና መናገሬን አቆምኩ ። አስፈሪ ነገር ፊትዋ ላይ ይነበባል ። በጥርጣሬ ዙሪያዋን እየቃኘች አንድ ቦታ ፍጥጥ ብላ ወደጭለማው ማተኮር ጀመረች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ኢሻ ሄምበል እሰቲ» ድምጽዋ ውስጥ ፍርሀት አለ ። «ተመልከት አሁንም ቆሞአል እኮ ፣ ምን ያህል ገርጥቷል! ። እንዳትናገር ፣ እንዳትንቀሳቀስ ጸጥ ብለህ ቁም ፣ ድምጽህን እንዳይሰማው እኔ ሂጄ እነጋግርዋለሁ ፣ ሁሉንም እነግረዋለው ።» እጆዋን በመከላከል ዓይነት ከፍታ ፤

«ጉዶ! ጉዶ!» ብላ መኸች ።

እየቀፈፈኝ አተኩሬ ሰሚትዋ የተሳበበትን ስፍራ ፍጥጥ ብዬ ማየት ጀመርኩ ።

እጄን ይዛ «ገደለው! ገደለውና አፈቅርሀለሁ» እንደ ገና ፍርሀት መጣባትና «እእእ!» ብላ ወደኋላዋ ማፈግፈግ ጀመረች ። «መጣብኝ እኮ... ተጠጋኝ እኮ! እይ! እይ! ወደኔ አይደለም ጉዶ ። እኔን ትትንካ ፣ እኔን መንካት አትችልም ። ቶቢ የሞቷል! ስለዚህ እኔ ነጻ ወጥቻለሁ ። ነጻ ነኝ!» ስመ ከላከል እጆዋን ወደላይ እንደዘረጋች የሆነ ነገር በኃይል የመታት ያህል መሬት ወርዳ ተንጠፈችና አቃሰተች ። ነጣፊው ድንጋይ ላይ አ! አሰኝቶ መታት ። «ሞተች እንዴ?» ይህን ስል የበቀል ጥም አፌ ውስጥ ስለነበር ምንም የርህራሔ ስሜት አልነበረኝም ። እንዲያውም ደስታ ተሰምቶኝ ነበር ። ጉዶን የገደልኩ ጊዜ እሱን ለመግደል ጥይት ከሽጉጡ ተፈትልካ ስትወጣ በልቤ ውስጥ የነበረኝን ያህል ቁጭት የማጣው ግማሽ አሁን የለኝም ። የፈራሁ ህጥያት ታላቅ ነበር ። ወደዚያ ህጥያት የመራችው ግን እርሱዋ ነች ። ስለዚህ የእርሷ ህጥያት ከእርሱ ህጥያት ይበልጣል ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ንጣፉ ላይ ጸጥ ብላ ወደቃ ቀረች ። አተኛኘትዋ የሞተች አስመሰላት ። ሞትም ቢሆን ግድ የለኝም ። ግን እውነት የውሽማዋ ጓእረሞት ታይታት ይሆን ? አልጠራጠርም ። እመዳይ የመሰለ ጥላውን እኔ ባይ ግን ፍንከች ብዬም አልደነገጥም ። ለሁለታችን ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆንችው እርስዋ ስለሆነች ሁለታችንም ተበቃይ ነን ።

«አንተ ጉዶ» ብዬ ተጣራሁ ። «የተደረገውን እየህ አይደል? ለበደልህ ፍርድ አገኘተሀል ። በቀልህንም ተወጥቼልሀለሁ ። ከእንግዲህ ይቅርታን አታጣም ። ያንተ ሀጥያት በስጋህ መቃጠል ነጽታለች ። ለእርስዋ ግን ገሀነም ራሱ ሲያንሳት ነው ።»

ወደ ደረጃው ማዝገም ጀመርኩ ። ትቻት የምሄድበት ሰዓት የደረሰ መስሎኝ ተራመድኩ ። «ባትሞትስ ? ባት ሞትም በጥቂት ደቂቃዎች ትሞታለች ። አመነታሁና ቆም አልኩ ። የውጪው ንፋስ እንደገና በኃይል ሲነፍስ የመቃብር ቤቱ በር ተንቅሎ የሄደ ያህል ተወዛወዘ። የዱር እንሰሳት በሙሉ አፋቸውን መሬት ተክለው የጮሁ ያህል ምድርዋ ተርገበገበች ፣ ተንቀጠቀጠች ። በእርግጥም መቃብር ቤት ውስጥ የሚሽሎከሎኩት ነፍሳት ሁሉ በፍርሀት እስኪጮሁ ቤቱ በንፋሱ ኃይል ተናጋ ። ትልቁ ደወል ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት መሆኑን ወዲያው ደወለ ። ከሆቴሉ ታላቅ ግብዣ ከጠፋን ሁለት ሰዓት ሊሞላን ነው ። ይሄኔ ጓዳ ጎድጓዳው ሳይቀር እየታሰሰ እየተፈለግን ነን ። ቢሆንም እዚህ ሊደርሱብን አይችሉም ። ወደመውጫው ራ



t.me/OLDBOOKSPDF

መድ ብዬ እንደኛውን ደረጃ እንደረገጥኩ ሚሽቴ ዝርግት ብላ ከተኛችበት ነፍስ ዘርታ መንቀሳቀስ ጀመረች ። በዓይንዋ አልፈለገችኝም ። ግን የሆነ ነገር ተናገረች ። ቀና ብላ ጸጉርዋን ማስተካከል ጀመረች ። የጸጉርዋን ቀለምና ልስላሴ እያደነቀች ድንገት መሳቅ ጀመረች ። ከእርስዋ በማይጠበቅ ዓይነት መቃብር ቤት ውስጥ ያሉትን ነፍሳት እኔንም ጭምር እንዲያውም ልትገድለኝ ከምክረችበት ሰዓት ይበልጥ አስፈራራችኝ ።

ተነስታ እንደ ማለዳ አበባ እስከነግርማዋ ቆማ እንደ ሕጻን ፈገግ ብላ በጥንቃቄ ቀሚስዋን ማስተካከል ጀመረች ። እዚያው ቆም እንዳልኩ ሳያት ወደሸፍታው የስርቆት ሀብት ተጠግታ አልማዝና እንቁውን ፣ ወርቅና ብሩን ፣ ጥንታዊ የወግ ጌጣጌጡን በጥንቃቄ እያነሳች ዋጋቸውን እንደሚገምት ነጋዴ እየመዘነች አገላብጣ ታስተውል ጀመር ። የቤቱን ጌጥ በመልክ በመልኩ እየለየች በየተራ አንገትዋና ትከሻዋን እስኪከብዳት ጌጣጌጡን አጠለቀች ። ሊገለጽ በማይቻል እንጸባራቂ ቀለማት አሸብርቃ እንደትንግርት አፌን ከፍቼ ቆሜ አየኋት ። የቆምኩበትን ደረጃ ጥዬ አጠገብዋ ለመድረስ ራመድ ከማለቴ ፣ ራቅ ብሎ መንዘር እንደጀመረ የመሬት መንቀጥቀጥ ሰማሁና ወዲያው እማም! ብሎ የሆነ ነገር የመሰንጠቅ ድምጽ ሰጠ ። በድንብ ለማዳመጥ ቆም አልኩ ። በመቃብር ቤቱ ዙሪያ ኃይለኛ ንፋስ ተነስቶ ምሱን እንዳስለቀቁት ሰይጣን አውሎ ንፋስ እያፏጨ ሻማውን ድንገት በልብ አድርጐ አጠፋው ። መልሼ አበራሁት ሚሽቴ ግን አሁንም የሽፍታውን የሌብነት



t.me/OLDBOOKSPDF

ሀብት በማገላበጥ ተጠምዳ ምንም ነገር አታይም!አትሰ ማም አትለማም ። ቆየት ብላ ድንገት እንደ እብድ ሙሀ ሳቀች ። ፍርሀትም ሀዘንም ጀመረኝና «ኒና ! ኒና !» ብዬ ጠራኋት ።

እየሳቀች ወደኔ አየት አደረገች ። የፊትዋ ለዛ ተመል ሶአል ። በደበዘዘ ብርሀን ቆሜ በአልማዝና እንቁ የብርሀን ፍንጣቂ እንደእሳት እየተንቦገቦገች ከሰው ሕይወት ውጪ ያለች ተፈጥሮ ትመስላለች ። በኩራትና በሳቅ መሀል ከአን ገትዋ ሰብር ብላ አንዲት ቃል ሳትተነፍስ ሰላምታ ሰጠ ችኝ ።

«ኒና» ብዬ እንደገና ጠራኋት ፤

ያንኑ አስፈሪ ሳቅዋን እንደገና አስካካችና ክዱር የፍቅር መዝሙሮች አንዱን የምወደውን ግጥም እየገጠ መች እየሙሸች መዝፈን ጀመረች ። ጥንታዊው ታዋቂ እንጉርጉሮ ከአፍዋ ወጥቶ በገደል ማሚቶ እየተቀባበለ በ ጆሮዬ ሲንቆረቆር በርስዋ ላይ ያለኝ ቂጣ በመጠኑ ተቀነሰ። ድንገት የርህራሔ ስሜት መንፈሴን አተራመሰው ። የአሁንዋና የኔዋ ሚሽት የተለያዩ ሆነው ታዩኝ ። የአ ሁንዋ ረዳት የሌላት አእምሮዋን የሳተች ምስኪን ሆና አ ገኘኋት ። በዚህ ሁኔታዋ አንዲት የጸጉርዋን ቅንጣት እን ኳን ለመጉዳት ሳለመፈለግ ወሰንኩ ። በቁርጠኝነት ከመ ቃብር ቤቱ አውጥቼ በነጻ ልለቃት ራመድ አልኩና ስጠ ጋ እርሷ በቁጣ ሸሸችኝ ። ወደ ኋላዬ እንድገፈተር ልት ረግጠኝ ሞከረች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ማነህ አንተ? አንተ እኮ ሞተሀል ፤ በእርግጥ ሞተሀል! ከመቃብርህ እንድትወጣ ማነው የፈቀደልህ ለመሆኑ ኸረ?» በእንቢተኝነት ፊትዋን ከስክሳ እየተከላከለች ረዳት እን ደሚጠይቅ ሰው እጅዋን አጨብጭባ ፤

«እርሱ እኮ ሞቷል ጉዶ ደስ አላለህም እንዴ ?» ጥቂት መልስ ለማግኘት ጠበቀችና «መልስ አልሰጠሽኝም እኮ ጉዶ ! ፊራህ እንዴ? ለምንድነው እንዲህ የገረጣሽው ? የተኮሳተርከውስ ? ከሮም ገና መመለስህ ነው መሰለኝ ። ስለእኔ ምን ሰማህ ? ታማኝ አይደለችም አሉህ እንዴ? ግዴለም እኔ አሁንም አፈቅርሃለሁ ። እህ ፤ ረሳሁ ፣ ለካ አንተም ሞተሀል ጉዶ ። አሁን ትዝ አለኝ ። ለካ ከእንግዲህ ወዲህ አንተም ልትጐዳኝ አትችልም ። አሁን ነጻ ነኝ ደስ ብሎኛል» ።

አሁንም ያ አስፈሪ የመንቀጥቀጥና የመስንጠቅ ድ ምጽ ከወደጣሪያው እንደገና ተሰማ ። ምን ሊሆን ይችላል? የፍርሀት ስሜት አደረብኝ ።

ኗና ያንኑ ጥንታዊ መዝሙር ሙሀ መዝፈንዋን ቀጠለች ። ደግማ ደጋግማ በሞቀ ስሜት እየዘመረች እዚ ያው የሌባውን ሀብት ሳጥን ተደግፋ ዕቃ መምረጥዋን ቀጠለች ። አንድ በወርቅ የተጌጠ አሮጌ መስታወት አውጥታ ካለመጠን እየፈነደቀች እኔ ከወጣሁበት ሳጥን ላይ ተቀምጣ ፊትዋን ማየት ጀመረች ። በሻማ ብርሀን ፊትዋን እያየች የአንገትና የእጅዋን ጌጥ እያስተካከለች


t.me/OLDBOOKSPDF

መዝሙርዋን በረጅሙ ቀጠለች ። አሁን ውበትን በናቁ ሙታን መሀል ተቀምጣ የምትሠራው ሁሉ ያስፈራል ። ሀብትና ንብረት ንቀው ባንቀላፉ ሙታን መሀል ተቀምጣ አልማዝና እንቁ ስታገባብጥ ሁኔታዋ ይዘገንናል ። አሁን የምትሠራውንና የምታደርገውን አታውቅም ። እያዘንኩ ከቁም ሁሉ ነጽቼ አየኋት ። አሁን የበቀል ጥሜ ሁሉ ረክቷል ። ከእንግዳ ነ ጦርነት አልቀጥልም ። እኔ ፍቅሬን እንደተነጠቅሁ እረቢዋ ደግሞ አእምሮዋን አጥታለች ። አሁን እኩል ሆነናል ። ለመናገር ፈልጌ ቃላት ስመርጥ ያ ደጋግሜ የሰማሁት መአተኛ የመሰንጠቅና የመናጋት ድምፅ እንደገና ሲሰማ ህብኝ የመቃብር ቤቱ የፈነዳ ያህል ደንግጬ ከቆምኩበት ደርቼ ቀረሁ ፤ የአሁኑ ድምፅ ልክ እንደተተኮሰ መድፍ ጩርሶ ጣሪያና ግድግዳው ጉድጓዱ የገባ መሰለኝ ። ምን መአት እንደወረደ ተገንዝቤ ሬሳ ሳጥኔ ላይ ተቀምጣ ፊትዋን በመስታወት እያየች ፍልቅቅ የምትለዋን ሚሽቴን ጉትቼ ለማውጣት እጄን ከመሰንዘሬ በፊት እንደ ፈራሁት የመቃብር ቤቱ ጣሪያ ተሰንጥቆ ድንጋዩ አሸዋውና ፍርክስካሹ ሲወረወር ወደ ኋላዬ ተስፈነጠርኩ ። ጉዱን ለማየት ብሞክር ዐይኔም አፌም በአዋራ ተሞልቶ ማየትና መናገር ተሳነኝ ። እንደምንም ዐይኔን ጠራርጌ ስገልጥ ሁሉም ጨልሟል ። ሁሉ ነገር ጸጥ ብሏል ። ሁሉ መናው ተዳፍኗል ። የውጪው ንፋስ ብቻ አሁንም ጥፋት ለማምጣት ሽምጥ ይጋልባል እንጂ ሌላው ሁሉ ጭጭ እርጭ ብሎአል ። በተደረመሰው የመቃብር ቤት ቀዳዳ የሚገባው ኃይለኛ ንፋስ አሠር ገሰሱን ከውጪ እየጠረገ እፊቴ ላይ እምጥቶ ከደነው ። ከንፋሱ ኃይለኛነት የተነሳ



t.me/OLDBOOKSPDF

የዛፎች ቅርንጫፎች ተጣጥፈው ይንሳጠጣሉ ። በዚያን ሰዓት የሚሰማው ድምጽ ሁሉ ያስፈራል ። በዚህ ይሉኝታ ቢስ ፍርሀት እየተርበተበትኩ ፣ ክብሪት ከኪሴ አወጣሁ ፤ ሁለቱም እጄ እየተንቀጠቀጠ የሞት ሞቴን ጫርኩ ፣ ብ ርሀን አገኘሁ ። ብርሀኑ ግን ደካማ ስለሆነ ምንም ሊያሳየ ኝ አልቻለም ።

«ሂና!» ብዬ ጮኽኩ ።

መልስ የለም ። ሻማ ከቅርቤ ዳብሼ እየተንቀጠቀጥኩ አበራሁ ። በብርሀኑ ያየሁት አስከፊ ትርኢት ሳላስበው ስቅቅ አድርጐ አስጮኸኝ ።

«አቤት አምላክ! ፍርድህ የማያወላውል ፣ በቀልህም ከኔ በቀል የበለጠ ነው» ብዬ ጮኽኩ ። ሰው ሊያንቃንቀው የማይችለው ነጣፋ ድንጋይ በአውሎ ንፋሱ መንስኤ ከጣሪያው ወርዶ ከሁለት ደቂቃ በፊት ፊትዋን በመስታ ወት እያየች ትስቅ ከነበረችው ስፍራ አርፏል ። እርስዋ ም እኔው ሳጥን ውስጥ ተደፍጥጣ ገብታለች ። ከአንድ እጅዋ በስተቀር ሌላው ሰውነትዋ በሙሉ ድንጋይ ጨፍ ልቆታል ። ብቻውን ተነጥሎ ከተረፈው እጅዋ ላይ የጋ ብቻ ቀለበትዋ በማሾፍ ዓይነት ያብረቀርቃል ። ያ እጅ አሁን ድረስ በህልሜ ይታየኛል ። በጣም ይዘገንነኛል ። ያ እጅ ኤሎሔ! የሚል ይመስለኛል የሚዝትብኝም የሚ ጠራኝና የሚጸልይም ይመስለኛል ። ስሞት ደግሞ ወደ መቃብር የሚጠቁመኝም ይመስለኛል ። የልብስዋ ጫፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይታያል ። ከወደጥግ ደምቀ እየጐረፈ ይወጣል ። እየተንቀጠቀጥኩ ፣ እንደሰከረ ሰው እየተወላገድኩ እንደምንም ጠጋ ብዬ ያንን እጅዋን ነካሁት ። ለመሳም አጐነበስኩና የሆነ ነገር ከንፈሬን እንዳላሰነካው ከለከለኝ ። ንጣፉ ላይ የመነኩሴውን መስቀል አግኝቼ እጅዋ ውስጥ አኖርኩና ገና ከነትኩማታቸው ያሉትን ጣቶችዋን አጣጥፌ ተውኳት ።

«ላደርግልሽ የምችለው ይኸው ነው ። እኔ ይቅር ባልልሽ ፈጣሪ ይቅር ይበልሽ» ብዬ ዓይኔን ጭፍን አድርጌ ትችት መብራቱን አጥፍቼ ደረጃውን መውጣት እንደጀመርኩ እንደገና ወደኋላዬ ዞር አልኩና ይህን ዘለዓለም የማየውን ትንግርት አየሁት ። ያ ድንጋይ ከወረደበት አቅጣጫ የመቃብር ቤቱ ጣሪያ ተከፍቶ ጨረቃዋ ብርሀንዋን እንደባትሪ ወለል አድርጋ አስገብታ ከሌላው ነገር ሁሉ የሚሸቱን እጅ እስከነአልማዙ ከሩቅ ታሳያለች ። እፍጥጬ እንደጉድ አየሁት ። አልማዙ ነጸብራቁን እየፈነጠቀ ዐይኔን የወጋው አሁን ድረስ ያመኛል ። በተቆለፉት ጣቶችዋ የተያዘው ነጭ መስቀል አእምሮዬን ያዋኸቀዋል ። እንደማልቀስ እየከጀለኝ የመቃብር ቤቱን አስፈሪ ትርኢት ሸሽቼ ሚሽቱ ዳግም የማትወጣበትን የመቃብር ቤት በር ከፍቼ ወጣሁና ነጻውን አየር ተነፈስኩ ። መሞቷዋን አሁንም ስለምጠራጠር በኔው ዓይነት የቁጣ ግለት የሚወራጨውን ንፉስ እየታገልኩ በሩን በጥንቃቄ መልሼ ቆለፍኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እሁን መተማመኛ አገኘሁ ከእንግዲህ እታመልጥም የሚሥጢር መግቢያውን አሽጌዋለሁ ፤ ድምጽዋንም ማንም አይሰማም ። ጥቂት ትወራጭና ትሞታለች ። ከእንግዲህ አትስቅም ፣ አትስምም ወንድን ለማጥመድ አትቀላምድም ፤ ከነሕይወትዋ ልክ እንደኔው ተቀብራለች ።

በለቅሶ ስርቅታ ዓይነት ይህን እየለፈለፍኩ አእምሮዬ ውሉን እየሳተ ፣ ጉልበቴ መቆሙን እየከዳ ፣ ሁለመናዬ ስጋ ደና ምድሩ እንደተቆጣ ውቅያኖስ ውሀ እየዋዠቀብኝ ፣ ዉረ ቃ እንደዳመናው እየተከታተለችኝ ፣ የሩቅና የቅርብ ዓለማት በሙሉ ትርጉም አልሰጥ እያሉኝ ፤ ጥያት ራቅሁ ። የሚ ጠብቁኝን የፈንታ ዕጣዬን ለመጋተር ትቻት ሄድኩ ።

ሳይነቃብኝ ተኳታታይ ሳይደረግብኝ ኔፕልስን ተሰ ናብቼ ወጣሁ ። በካባዬ ተሸፋፍኜ ማንነቴ ሳይጠረጠር የም ትጠብቀኝን መርከብ ደረስኩ ። ካለአንድ ኮሽታ በውልብታ ሂጂ ወዳጂ እንድሪያ ያዘጋጀልኝንም መርከበኛ አንቶኒዮ ባርዳ ስለማንነቴ በተሰጠው ውሰታ መሠረት ሳይጠይቀኝ ሰተት ብዬ ተሳፈርኩ ።

ግለዳው የደሰደሰ ያለው ነበር ። ገና ባልጋለች ጀንበር ባሕሩ በሞገድ እየተነሳ ንፋሱን ሰዋ ሲመለስ ፀሐይዋ ከላይ በግርማ ሞገስ ዓለሙን የምትረከብ ትመስ ላለች ። እኔ ግን ይህን ሁሉ የተፈጥሮ ትርኢት የማይበት የአእምሮ ትእግስትና የማየት ፍላጐት አልነበረኝም ። ቂም እርግዝ የበቀል እርጥብ አራስ በመሆኔ እፊቴ የቀረበውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉ ትኩሣት እያራገኝ በገገምተኛ ዓይኔ ከቅዠቴ እየ ባነንኩ አስተውላለሁ ። የብርሃን ፀዳል በሰማይ ስሎሉ እየ ጋመ መርከቡ የተወለድኩበትን ምድር ለቆ ሲሸሽ ገገምተኛው ዓይኔ ማመን አቅቶት በሕልም የማልፈው መሰለኝ ። በሕልሜም ሆነ በውኔ በዚያን ሰዓት ሁሉ ነገር ለኔ ውሸት አይነት ነበረ ። ሀሳቤ ዞሮ ዞሮ እርስዋ የተኛችበትን አስፈሪ ስፍራ አምጥቶ ትኩስ የሬሣዋን ትዝታ ያስታቅፈኛል ። አሁንስ መሞትዋ ተሰምቶኛል ። እጣ ክፍልዋ ገድሏታል ። ይቅርታን የሚጠይቅ ትህትና ባይኖራትም እስከመጨረሻው ለተንኮል ባትተኛም በመጨረሻው በገዛ ውቤዬ ልትገድለኝ ብትጥርም እኔ ላድናት እችል ነበር ።

ተፈጸመ ሲለው ድንጋዩ ወደቀ ። ማን ያውቃል...... ስለ እርስዋ ጨርሶ ላለማሰብ እየሞከርኩ ከኪሴ የመታብር ቤቱን ቁልፍ አውጥቼ እንደዋዛ ወደ ሆደ ሰፊው ባሕር ወረወርኩት ። ሁሉ ነገር አበቃ እንግዲህ ። ከእንግዲህ የኔን ወዴትና እንዴት እንደደረስኩ ምን ሆኜ ምን እንዳ ደረኩ እሚያስብም የለም ። ካለአንዳች ጥያቄ ቺሼታ ሼኪያ ደርሼ ወደ ሴግሆርን ፤ ደቡብ አሜሪካ በሚ ያመራ የንግድ መርከብ ተሳፍሬ ጉዞዬን ቀጠልኩ ። በዚህ ዓይነት ለሁለተኛ ጊዜ በሌላ ስምና ሰውነት በዓለም ሁሉ ተዘንግቼ ከነሕይወቴ ተቀበርኩ ለማለት እችላለሁ ። አሁን በዚህ ደን ውስጥ እንደሳጋ የሰው ሰንጥር ሆኜ ስለ ተቀመጥኩ የማምለጥ ፍላጎት የለኝም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደማገኘውም ልብስ አጻፋ ፣ አፈጉልጻፋ መጤ ሠራተኛ ከሰፈው ግሮአደር ጋር ተቀላቅዬ ማደር ጀመርኩ ። መውጫው መግቢያው የማይታወቀውን የሰው አገር መንገድ ስፈልግ ቢያቅሙት የማይጠግበውን የሰው አገር ሰው ስለማመጥ እንደቀልድ ውስብስብ ያለውን የስደተኛ ሕይወት ጀመርኩ ። በዚህ ሕይወት የዕለት ተዕለት ኑሮ ስመራ እንደሸረሪት ድር የተተበተበውን ማንባሬን ፤ እንደ በረዶ የነጣውን ጸጉሬን አይቶ በጣሊያ ሀገር ለአንድ ሰሞን ትንግርታዊ አጠፋፉ እንቆቅልሽ የሆነውን ከበርቴው ጌታ ሲዛር አሊሻ ነው ብሎ የሚጠቁምብኝ የለም ። ቀኑ እንዳመት በሚረዝምበት የባዕድ ሀገር ከወረዳ ወረዳ ስንከላወስ አንድ ቀን ስለጣሊያን ሀገር የሚናገር የአንድ ጋዜጣ አርእስት አነበብኩና ማተኮር ጀመርኩ ። ርእሱ ትንግርታዊ የኔፕልስ ከበርቴ አጠፋፍ ይላል ። ያገር ነገር ካገር ሲርቁ ብርቅ ነው ፣ የራስ ነገር ከራስ ሲፎቁ ያስደግጣልና ዜናውን በጥድፊያ አነበብኩት ።

«ጌታ አሊሻ የሚባል ከበርቴ እመቤት ሮማኒ የምትባል ባለጸጋ ወይዘሮ ያገባ ሌሊት ወደት እንደገባ ሳይታወቅ ከነአዲሲቱ ሚሽቱ በአስገራሚ ሁኔታ ጠፍቷል ። ይቀመጥበት የነበረው ሆቴል ጌታ እንዲሁም የቀድሞ አጃቢው ቪንቼንዞ ፍላሚ የተባለ ሠራተኛው በከተማው ፖሊስ ስለከበርቴው አድራሻ ተመርምረው ሁለቱም ግለሰቦች ስለሁለቱም አጠፋፍ የሰጡት ፍንጭ የለም ። የኔፕልስ ከተማ ፖሊስ የዚህን እንቆቅልሻዊ አጠፋፍ ሚስጢር የሚፈታለትን በደስታ የሚቀበል መሆኑን ገልጿል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በመጨረሻው እስከ አሥራ ሁለት ወራት ስለከበርቴዎቹ ምንም ዓይነት ዜና ካልተገኘ የጌታ ሮማኒ ቤተሰብ ሀብት ወራሽ እንዳጣ ተቆጥሮ ሀብት ንብረቱ በሙሉ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን መወሰኑ ተገልጿል» ይላል ።

በተራ ስሜት ካነበብኩት በኋላ ለምን የሮማኒን መቃብር ቤት አልፈተሹምን የሚል ጥያቄ መጣብኝ ። ተጨባጭ ፍንጭ ከነምርቱ እዚያ ያገኙ ነበር። ያገሬን ሰዎች ግን አውቃቸዋለሁ ። በከንቱ ውዳሴ የሚያመልኩ ተጠራጣሪዎች ናቸው ። የመቃብር ቤት ከፍተው ሙታን ከሚያስቀይሙ የቀረ ቢቀር ይመርጣሉ ። ሀብቴን መንግሥቴ ቢወርሰው ግን ልጄ እንደወረሰው ስለምቆጥረው በመገረም ደስ አለኝ እንጂ አልተከፋሁም ።

መጀመሪያ እንደነገርኳችሁ እንግዲህ እኔ የሞትኩ ሰው ነኝ ። የሕይወት ትኩሳት ፣ የማያቋርጥ የእንቅስቃሴ ስበት ያለው ዓለም የኔ አይደለም ። ሰማይ ጠቀስ ዛፎች አፈርላፈር የሚጐተት ሳርቅጠል ፣ ሌቱ ሲነጋና ሲመሽ የሚዘምሩት አእዋፍ ብቻ ናቸው የኔ ጓደኞች ። በእርግጥም እነርሱ ብቻ ናቸው የውስጥ ስሜቴን ፣ በምሬት የሚጋየውን ስቃዩን አድምጠው የሚያውቁልኝ ። የሁልጊዜ ስቃይ መከራዬን ተፈጥሮአዊ የተበቃይ ጭንቀቴ የሚመሰክሩልኝ እነርሱ ብቻ ናቸው ። ብቀላ ምንኛ ጣፋጭ ነው! ግን የኋላ ኋላ መዘግነኑን ማነው የሚቀርጸው? ቂም በቀሉ በኔው ጭንቅላት ብቻ ነው ድሩን ያደራው ። ለዚህ እንኳ ቅሬታ የለኝም ምክንያቱም የበቀል ፍርድ በቀልነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ገዳዩን የመግደል እንዴ ሎሚ ተራተራ ነው ። ለዚህ ከእርስዎ በስተቀር ማንንም አልወቅስም ። እርስ ዎን ግን ከሞቶች በኋላም ቢሆን ምሬም አልምራትም ፣ አልቻልኩም እንጂ ልምራት ሞክሬአለሁ ። ወንድ ል ጅ በእውነት ሕይወቱን ያሰናከለችበትን ሴት ይቅር ሊላት ይቻለዋል ? እጠራጠራለሁ ። ለኔ ግን መጨረሻው ገና ነው ፣ ገና ፣ ገና ፣ ገና...... ምናልባት ስጋዊ ሕይወቴ ከዓለማዊ ወህኒ ቤቴ ሲላቀቅ ያኔም ቢሆን በአንድ ጨለምለም ያለ ጥጋት የእርስዎን ተለዋዋጭ ተንኮል እየተከተልኩ ከገሀ ነም አስፈርጥጬ እያስፈራራሁ እየተከታተልኩ ለዓለም ወላለም እንዳለው እስከምንጊዜውም እከታተላታለሁ ።

ለዚህ እዘኑልኝ አልልም ። አዛኝ አንጀት አልሻም ። አያስፈልገኝምም ። እጥፉን ቀጣሁ ፣ በዚህ አድራጎቴ ከነ ርሱ ይልቅ እኔው ተቀጣሁ ። ይህ ደግሞ ምንጊዜም መሆን ያለበት ነው ። ቁጭትም ጸጸትም የለብኝም ። አንዲት ነገር ብቻ ታስጨንቀኛለች ። ትንሽ ናት ስጋ የሌላት ቅዠት አይነት ናት ፣ በሙሉ ጨረቃ ምሽት ትመጣብኛ ለች ። በተቻለ ሁሉ ከብርሀንዋ ለመደበቅ በርና መስኮቱን ዘግቼ ጭላንጭል መግቢያውን ደፍኜ የግንባሬን ዐይኖች ጨፍኜ ብቸኛ ቤቴ እደበቃለሁ ። ጥረቴ ሁሉ ግን ከንቱ ነው ። አንድ አበሳ የሚያህል የጨረቃ ብርሀን ተሰርቆ በበሩ ስር ተወርውሮ በግድግዳው ንቃቃት አምልጦ እን ደምንም እኔ ያለሁበት ክፍል ይገባል ። ይህን የሚያስ ቀር ምንም ነገር የለም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የዚህ አገር አየር እንኳ የጨረቃዋን ቀለም እምብዛም አይለውጠውም ። የሚጐበኘኝ የጨረቃ ብርሀን ቀለም ግን ለምን ትዝዝ ያለ ወደ ውሀ አረንጓዴነት እንደሚለወጥ አላውቅም ። በውስጡ ደግሞ በአረንጓዴ መስክ እንደተጠራቀመ የኩሬው ውሀ ለምን በውስጡ ደግሞ እንዲት ትንሽ ልስልስ ጤዛ መሳይ የአልማዝ ጌጥ ያረገች እጅ ለምን እንደሚታይ አላውቅም ። ያቺ እጅ ተንቀሳቅሳ ቀና ትላለች ። ጥንጥዬ ትናንሽ ጣቶችዋ ወደ እኔ ይጠቁሙና እየዛቱብኝ ይንቀጠቀጣሉ ፣ ከዚያ በኋላ ወደነርሱው እንድመጣ እያግባቡ ፣ እየጠሩ ፣ እንደዎት ዝግ ብለው በትእዛዝ ዓይነት ቆርጠው እያስገደዱኝ ወደ አንድ ብርሀን ፣ ፍቅር እማይታይበት ጥጋት ወደ አንድ የደስደስ የሌለው ቀፋፊ ዓለም ይመሩኛል ።



t.me/OLDBOOKSPDF